# አብርሆት
# ENLIGHTENMENT

ቅፅ 1 አስረኛዓመት
ነሐሴ2011ዓ.ም
Issue 1 (10th Year)
August 2019

## ‹‹ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በአፍሪካ ወይም በዓለም የሚጠራ ዩኒቨርሲቲ ለመሆን መልካም አጋጣሚ አለው›› ክብርት ዶ/ር ፍፁም አሰፋ





# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
# Debre Markos University

## Vision

Debre Markos University strives to be one of the top ten universities in Africa by 2025

## Mission

Debre Markos University has the following missions:

- Producing competent and Innovative professionals;
- Carrying out problem solving research at local and national levels;
- Providing community and consultancy service that contribute to the national development objectives


- Providing community and consultancy service that contribute to the national development objectives


## Values

Debre Markos University adheres to the following core values:

- Student centeredness
- Quality and speedy service delivery
- Good governance
- Team spirit
- Academic freedom
- Competitiveness in scholarships
- Collaboration for mutual benefits
- Recognition of merit
- Professional ethics
- Social responsiveness

# አብርሆት
# ENLIGHTENMENT

ቅፅ 1 አስረኛ ዓመት
ነሐሴ 2011ዓ.ም

Issue 1 10th year
August 2019

አብርሆት መፅሔት በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት በሁለት ቋንቋ የሚዘጋጅ ዓመታዊ መፅሔት ነው፡፡

## አዘጋጆች

### ዋና አዘጋጅ
ደሳለው ጌትነት (ዳይሬክተር)

### ሪፖርተሮች
ሁሉንአየን ጋሻው (የህዝብ ግንኙነት ባለሙያ)
ነፃነት አማረ (ሪፖርተር)
እንደሻው ያዛቸው (የህዝብ ግንኙነት ባለሙያ)
ሠለሞን ይታየው (ሪፖርተር)
ቴዎድሮስ አንዱዓለም (የህትመትና ሚዲያ ባለሙያ)

### ተጋባዥ ፀሐፊ
መ/ር ምንዋጋው ተመስገን

### ፎቶ ግራፍ
ሐብታሙ በጋሻው
እመቤት አዳሙ

### ኮምፒውተር ፅሁፍ
ሐይማኖት ድንቁ

### ዲዛይንና ሌይአውት
አሜን የቋንቋና ኮምፒውተር ስልጠና ማዕከል

### ህትመት
ቢኮሎ ማተሚያ ቤት

## ማውጫ

አርዕስት ገፅ

ርዕሰ አንቀፅ ................................................ 2
የፕሬዝዳንቱ መልዕክት ................................ 3

**እንግዳችን**

‹‹ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ... በአፍሪካ ወይም በዓለም የሚጠራ ዩኒቨርሲቲ ለመሆን መልካም አጋጣሚ አለው›› ዶ/ር ፍፁም አሰፋ...5

**አካዳሚክ**

ዓለም አቀፍ ተሞክሮን ወደ አካባቢያዊ ፋይዳ ያሸጋገረ ተቋም ..................................10
የህክምና ተማሪዎች የተግባር ትምህርት በሆስፒታሎች ..................................13
ውስንነት የማይገድበው የህክምና ትምህርት ቤት ..................................15
ምስለ ችሎት ውድድር ለመውጫ ፈተና ተማሪዎችን ብቁ ያደርጋል..................................17
ሴትነትና አመራርነት ..................................18
የመጀመሪያው የሶስተኛ ዲግሪ ፕሮግራም ..................................19
የቡሬ ካምፓስ ሁለገብ እንቅስቃሴዎች ..................................20

**ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት**

በጎ ሃሳብን ለማበልፀግ የተቋቋመው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የበጎ ሃሳብ ማዕከል ..................................22
አገራዊ ቅርፅ እየያዘ ያለው በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተጀመረው የልዩ ተሰጥኦ ማበልፀጊያ ማዕከል..................................25
ሃገር በቀል ዕውቀትን የማዘመን ፕሮጀክት ..................................28
የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ግብርና ፕሮጀክት ..................................29
አገራዊ እሴቶቻችን የተንፀባረቁበት የሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም ሰባተኛ የምርምር ጉባኤ ቅኝት ............ 31
ውጤታማ የልዕቅና ማዕከላት ..................................32
ዝክረ አድዋ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ..................................33
ብዙዎችን ነፃ ያወጣው ነፃ የህግ አገልግሎት ..................................35

**አስተዳደር**

‹‹ዩኒቨርሲቲውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ሰራተኛ በባለቤትነት ስሜት መስራት አለበት››..... 37
የፋይናንስ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ..................................38
የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ አስተዳደር ሰራተኞችን የጄኤጂ ምደባ አካሄደ .................................. 39

**ቢዝነስና ልማት**

‹‹የግንባታ ሥራ ፈታኝና ዉስብስብ ዘርፍ በመሆኑ የሁሉን አጋር አካላት ትኩረት ይሻል››..................................41
የአይሲቲ አውቶሜሽን ሥራዎች በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ..................................42

**ተማሪዎች**

‹‹ትምህርት የቅድሚያ ቅድሚያ የምሰጠው ዓላማዬ ነው›› ..................................43
ከሜዳሊያ ጀርባ... የስኬታማ ተማሪዎች ወግ ..................................46
ከራሳችን ጋር የተዋወቅንበት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የባህል ፌስቲቫል..................................47
የተማሪ ፓሊስ የግቢያችን የሠላም ዘብ ..................................49

**ማንን እናስታውስ**

ዝክረ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ..................................50
አራት ዐይና ጎሹ ካልዕ ..................................51

Top News of The Year ..................................53
ዜና ፎቶ ..................................65
Quick Facts about DMU..................................71
Academic Programmes ..................................72

ስልክ ቁጥር፡ +251581780033

ፋክስ፡ 0587711764
ፖ.ሳ.ቁ፡ 269
ኢሜል፡ prcd@dmu.edu.et
www.dmu.edu.et

# ዩኒቨርሲቲዎች ለሃገራዊ ‹ሥርዓት› ግንባታ ሞዴል ሊሆኑ ይገባል፡፡

ደሳለው ጌትነት
የህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር



ትንሿ ኢትዮጵያ እየተባሉ በሚሞካሹት ዩኒቨርሲቲዎቻችን ውስጥ አገራዊ ስብጥርን ይዘው ከአራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘናት የተሰባሰቡ ተማሪዎች ዕውቀትን በመሻት ዛሬን ብቻ ሳይሆን የተሻለ ነገን የሚገነቡበት ህልም ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህንን ህልማቸውን እውን ለማድረግም መምህራን ተማሪዎቻችውን በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት አንፀው ሊያሳድጓቸው ደፋ ቀና ይላሉ፡፡ መንግስትም ከአገሪቱ በጀት አብላጫውን በመመደብ ምግብና መኝታ ሳይጓደልባቸው ለአገራቸው መልካሙን ሊያደርጉበት የሚችሉበትን ዕውቀት እንዲገበዩ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር በርካታ ዜጎችን ከ45 በላይ በሆኑ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች እያስተማረ ይገኛል፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች መቶ በመቶ በሚባል መልኩ የተደራጁት በተማረ የሰው ሃይል ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከሠራተኛ እስከ ተማሪ ድረስ በትንሹ የትምህርት እርከኖችን ያላለፈ ሰው አይገኝም፡፡ ሆኖም ግን በእነዚህ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚታዩት ክስተቶች መማር ማለት ምን ማለት ነው? ብለን እንድንጠይቅ ያስገድዳል፡፡ በ2011 ዓ.ም የዩኒቨርሲቲዎችቻን ጉዞ ስናየው ዩኒቨርሲቲዎች መርዶ ሲያረዱ የከረሙበት፣ ወላጆች በሰቀቀን የደከሙበት፣ የዩኒቨርሲቲ ሠራተኞችና መምህራን በሃፍረት አንገታቸውን ያቀረቀሩበት ሆኖ አልፏል፡፡ መንግስትም በሚዲያዎች በየቦታው ከገነባቸው ዩኒቨርሲቲዎች የፈጠራና የአዲስ ግኝት ዜና ሳይሆን የብጥብጥና ሁከት ዜና ሲሰማ ባጅቷል፡፡ የአገርን ችግር ይፈታል እየተባለ ተስፋ የተጣለበት፣ የነገዋ ኢትዮጵያ ተረካቢ ለማድረግ ከፍተኛ ወጭ የወጣበት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ትምህርቱን ትቶ፣ መማሩን ረስቶ በቡድን ተከፋፍሎ ብረትና ዱላ ይዞ ሲደባደብ ማየት የዩኒቨርሲቲ መሠረታዊ እሴቶች ገልብጦ ያሳየ ክስተት ነበር፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች የንድፈ ሃሳብ ትምህርት መስጫ ብቻ ሳይሆን የትግበራ ቦታዎች ሲሆኑ ለአገር ዋልታ ለወገን አለኝታ የሚሆኑ ዜጎች የማፍራያ የትምህርት ተቋም ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲዎች የሃሳብ ልዕልናን ያከበሩ ሃሳብን በሃሳብ በማጋጨት የተሻለ አማራጮች የሚገኝባቸው ተቋማት መሆን ሲገባቸው ብረትና ዱላ ተይዞ ልዕልናን በጡንቻ ለማስከበር ሲሞከር የሚታይባቸው ሲሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ከዓለም አቀፋዊ እሳቤ ጋር ያላትመዋል፣ ዘመኑንም አይዋጅም፡፡ መፅሐፍትና ወረቀት ይዞ እንደፈለገው መከራከር እና የተሻለውን ሃሳብ መደገፍም ሆነ መንቀፍ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እያለ የንግግር ባህልን ወደ ጎን በመግፋት በድንጋይና በጉልበት ልዕልና ለማግኘት የሚደረገው ትንቅንቅ አገርን ቢያስንቅ እንጂ ጠብ የሚል ነገር አያመጣም፡፡

በአገራችን ላይ የሚከሰት ማንኛውም ችግር በየዩኒቨርሲቲዎች ራሱን ሲደግም አሊያም በእጥፍ ተባዝቶ ይከሰታል፡፡ በአገራችን የምናየው ዜጎችን የማፈናቀል፣ የማሳደድና በጉልበት የማሸነፍ መክሸፍቶች በዩኒቨርሲቲዎቻችን ላይ በሠፊው ይደገማሉ፡፡ የእከሌ አካባቢ ሰዎች ተፈናቅለዋል፣ ፖለቲካዊ ሽፍጥ ተሰርቶባቸዋል፣ ፍትህ ተጓድሎባቸዋል ወይም የአካልና የህይወት ጉዳት ደርሶባቸዋል በማለት መፍትሄ ለማምጣት፣ ለሰብዓዊነት ክብር ለመቆም ወይም ለፍትህ መጓደል ለመጮህ ሳይሆን ያንን በእጥፍ በመድገም አብሮት የሚማረውን የክፍል ጓደኛ ላይ ሂሳቡን ለማወራረድ ሲተጋ ማየት እንደ አገር ያከስራል፣ እንደዜጋም ያሳፍራል፣ እንደወላጅ ያስፈራል፡፡

ስለሆነም ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ‹የተለየ› ሃሳብ ያላቸው ሰዎች ሃሳባቸውን በፅሁፍም ሆነ በፊት ለፊት ቀርበው ክርክር በማድረግ ሃሳቡን የመሞገት፣ ለሃገር የተሻለ አማራጭ መፍትሄ ይዞ መገኘት የሚያስችል ‹ሥርዓት› በመዘርጋት አይደለም ስለአገሩ ስለዓለም አቀፍ ሁኔታዎች የሚሞገትበትባ ሠፊ የሃሳብ ሜዳ መዘርጋት አለበት፡፡ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ መቀንቀን ያለበት ስለፍትህ፣ ዲሞክራሲ፣ ሰብዓዊነትና ዓለማቀፋዊ ዜግነት እንጂ ስለጎጠኝነትና በቀለኝነት ሊሆን በፍጹም አይገባም፡፡ ከዚያ ውጭ ግን መቶ በመቶ የተማረ ማህበረሰብ በሚኖሩበት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ችግሮች የሚፈቱበት መንገድ ራሱ ችግር ከሆነ ያልተማሩ ወገኖቻችን ላይ ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ‹ወደፊት› የምንለው ዕቅድም ሆነ ዕድገት መጠበቅን አስፈሪ ያደርገዋል፡፡

እናም! ዩኒቨርሲቲዎች በስማቸው እና በስሪታቸው ልክ ‹ስርዓት› ያለው ማህበረሰብ በማፍራት ለአገራችን ማህበረ-ፖለቲካ መዋቅሮች ሞዴል እንጂ በደል ላለመሆን ሊሰራ ይገባል የአብርሆት መፅሔት መልዕክት ነው፡፡

# የፕሬዝዳንቱ መልዕክት

## ‹‹ሀገራዊ ሁኔታው በተቋማችን የዕቅድ አፈፃፀም አሉታዊ ጉን እንዳይኖረው እንደ ሁሌው በታታሪነትና፣ በኃላፊነት ስሜት መደበኛ ስራችን እንስራ››

ዶ/ር ታፈረ መላኩ
የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት



ዩኒቨርስቲው በየዘመኑ የአምስት ዓመት ስትራቴጅክ እቅድ በማቀድ የተሰጡትን ሶስቱን ተልዕኮዎች በላቀ መልኩ ለማሳካት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ከሶስቱም ተልዕኮዎች አንዱ በሆነው በመማር ማስተማር ሂደቱም ምስጋና ለዩኒቨርስቲው መምህራን ይሁንና መልካም የሚባል ስም አለው። ዩኒቨርስቲው ከአጀማመሩ ጀምሮ መልካም የመማር ማስተማር ባህል ለመገንባት ጥረት አድርጓል።በ2011 በጀት ዓመትም ምንም እንኳን ሀገራዊ ሁኔታው እጅግ ፈታኝ የነበረ ቢሆንም መምህራን መደበኛ ስራቸውን በላቀ መልኩ ለመፈጸም ከመቸውም ጊዜ በላይ ጥረት አድርገዋል። በተማሪዎች ዘንድ አለመረጋጋት ሲፈጠር እንኳን ከችግሩ ተሎ በመውጣት መደበኛውን የመማር ማስተማር ሂደትን ለማስቀጠል ከሁለትና ሶስት ቀናት በላይ አልወሰደብንም። በዓመቱ መጨረሻ ካጋጠመን አሳዛኝ ገጠመኝ ማግስት መምህራን ተማሪዎቻቸውን በማረጋጋት ከሶስት ቀናት በኋላ መደበኛ የመማር-ማስተማር ስራው እንዲቀጥል መምህራን ማድረጋቸው በአርያነቱ ሊጠቀስ የሚችል ነው። በዚህ አጋጣሚ ለዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሰራተኞች፣ለተማሪዎቻችን እንዲሁም በየደረጃው ላለው አመራር ምስጋና ማቅረብ እወዳለሁ።

ዩኒቨርሲቲያችን በበቂ ወርክሾፖችና ቤተ-ሙከራዎች ገና በአግባቡ አልተደራጀም፡፡ ይህም ጉዳይ በመምህራንና በተማሪዎቻችን ዘንድ ለዓመታት ከፍተኛ ቅሬታ ፈጥሮ ቆይቷል። በበጀት አመቱም ይህን ችግር በከፍተኛ ደረጃ ለማቃለል የተለዩ ትኩረት ሰጥተን ሰርተናል። በመሆኑም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴርን 264 ሚሊዬን ተጨማሪ በጀት በመጠየቅ በመሰረታዊነት የቴክኖሎጅ ወርክሾፖችን ለማደራጀት ጥረት ተደርጓል። ችግሩም የከፋና ባለፉት ዓመታት መፈታት የነበረበት መሆኑን በመረዳት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስተር ተጨማሪ 199 ሚሊዬን ብር በመፍቀዱም ከ2 ወራት በፊት እቃዎች ገብተው ወርክሾፖች በመደራጀት ላይ ይገኛሉ። ወርክሾፖቹንም በክረምቱ በማደራጀትና ለመምህራን ተጨማሪ ስልጠና በመስጠት በ2012 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ስራ እንዲጀምሩ ይደረጋል። በበጀት ዓመቱ አዳዲስ የትም/ኘሮግራሞችን ለመክፈት ጥረት ተደርጓል። በተለይም የራዲዮሎጅ ትም/ኘሮግራም መክፈታችን የክልሉን መሰረታዊ ችግር ለማቃለል 22ተማሪዎችን ተቀብለን ማሰልጠን ጀምረናል። በተጨማሪም በየት/ም/ክፍሉ ስርዓተ-ትምህርቱን በየጊዜው ለማዳበር፣የምዘና ስርዓቱ ተከታታይነት እንዲኖረውና የትምህርቱ አቀራረቡም አሳታፊ ለማድረግ ዘርፈ ብዙ ስራዎች ተከናውነዋል።በሌላ መልኩ

በማመር ማስተማሩ ሂደት ተግዳሮቶች የሉም ማለት አይደለም። ለአብነት በየ ዓመቱ ወደ ዩኒቨርሲቲው የሚቀላቀሉ ተማሪዎች የአካዳሚክ አቅም ማነስ ከመቸውም ጊዜ በላይ ፈታኝ እየሆነ መጥቷል።ከሀገራዊ የፖለቲካ ሁኔታው ጋር በተያያዘ በተወሰኑ ተማሪዎች የስርዓት አልበኝነት ዝንባሌና የዘረኝነት መንፈስ ተጠቂ ሲሆኑ ታይተዋል። ሙሉጊዜያቸውን ለትምህርት ከማዋል ይልቁን በማህበራዊ ሚዲያዎች ተጠምደው የሚውሉት ተማሪዎች ቀላል አይደሉም። ስለሆነም እኛ መምህራንም ተማሪዎች ለዓላማቸው ተገዢ እንዲሆኑና ሙሉ ጊዜያቸውን ለትምህርት እንዲያውሉት በማድረግ፣ ስርዓተ ትምህርቱን በየጊዜው በማበልፀግ፣ አሳታፊና አነቃቂ የትምህርት አሰጣጥ በመተግበረና፣ ተከታታይ የምዘና ስርዓት በመዘርጋት የትምህርት ጥራትን ይበልጥ ለማረጋገጥ ከአሁን በፊት ከምናደርገው ጥረት በላቀ መልኩ እንድንሰራ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪ አቀርባለሁ።

ውድ መምህራንና ሰራተኞች

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ስድስቱም ስነ-ምህዳሮችና ትልቁ የምስራቅ አፍሪካ የውሃ ማማ የሆነው የጮቄ ተፋሰስ በሚገኙበት ቦታ መመስረቱ ዕድለኛ ያደርገዋል። ሁላችንም እንደምናውቀው አካባቢው በተፈጥሮ ፀጋ የታደለ ነው። በአንፃሩ የአካባቢው ማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ አሁንም እጅግ ኋላቀር የሚባል ነው። ስለሆነም ያለውን የአካባቢውን ፀጋ በመጠቀም የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎቱን በማሻሻል የአካባቢውን ማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ በማሻሻል ረገድ ተጨባጭ ስራዎችን በመስራቱ ረገድ ዩኒቨርስቲው ብዙ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ ረገድም በ2011 በጀት ዓመት የመምህራን የምርምር ባህል ከማሳደግ ጀምሮ በበጀት ዓመቱ የተሻሉ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ተሰርተዋል። በበጀት ዓመቱ 146 የምርምር ስራዎች ተከናውነዋል። የዕቅድ አፈፃፀሙም በበጀት ዓመቱ ከታቀደው እቅድ አንፃር ሲታይ እጅግ ከፍተኛ ነበር። በምርምር ስራውም 433 መምህራን የተሳተፉ ሲሆን ቁጥሩም ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀርም 36 በመቶ እድገት አሳይቷል።

በበጀት ዓመቱም መምህራን 200 የምርምር ውጤቶች በታዋቂ ጆርናሎች ማሳተም ችለዋል።የሴት ተመራማሪዎች ቁጥርም ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በ26 ከመቶ አድጓል። በባለፉት ዓመታት በዩኒቨርሲቲው ደረጃ ከሚደረገው አመታዊ የምርምር ሲምፖዚየም በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ ሁሉም ኮሌጆች የራሳቸውን ዓመታዊ የምርምር ሲምፖዚየም እንዲያዘጋጁ ተደርጓል። ሂደቱ የመጀመሪያችን ቢሆንም በየኮሌጆች የተዘጋጁት የምርምር ሲምፖዚየሞችም በዩኒቨርሲቲው ደረጃ ከተዘጋጀው ባልተናነሰ መልኩ እጅግ ደማቅና ውጤታማ ነበሩ። ለአብነት ያህልም በቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩቱን የተዘጋጀው የምርምር ሲምፖዚየም የመምህራን የሀሳብ አንድነት የታየበትና ሁሉም መምህራን ኢንስቲትዩቱ ለማሳደግ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳዩበት ነበር። በየኮሌጁና በየዲፖርትመንቱም በርካታ ሰሚናሮች ተካሂደዋል። በተመሳሳይ መልኩ ታላላቅ ሙሁራንና ተመራማሪዎች በመጋበዝ አነቃቂ ንግግሮችና ፐብሊክ ሌክቸሮች በስፋት ለዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል። የአድዋ በዓል፣የበላይ ዘለቀ የአርበኝነት ዝክረ ተጋድሎ ፣የሐዲስ አለማየሁ አመታዊ ጉባኤን ጨምሮ በርካታ ሁነቶች በበጀት አመቱ ተከናውነዋል።

በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍም የነፃ ህግ አገልግሎትን ለማስፋት በወረዳዎች ማእከላት የገነባን መሆኑ ፣የተለዬ ተሰጥኦ ያላቸውን ታደጊዎችን በክረምቱ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እንዲማሩ በማድረግ በሳይንስና በተግባር ትምህርቶች ያሉባቸውን ክፍተቶች ለመሙላት የምንሰራው የማጠናከሪያ ትምህርት፣ በጭራ ወንዝ የተቀናጀ የማህበረሰብ አቀፍ የተፋሰስ ልማት ስራዎችን በበጀት አመቱ ከተከናወኑት ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።የተለዬ ተሰጥኦ ያላቸውን ታዳጊዎች ከየ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ከ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በመመልመል በየክረምቱ በቋሚነት ለማሰልጠን STEM synergey ሙሉ እገዛና ድጋፍ በበጀት አመቱ ሁለት ዘመናዊ ወርክሾፖችም ተደራጅተዋል። በዚሁ አጋጣሚ STEM synergey

# የፕሬዝዳንቱ መልዕክት

ላደረግልን ድጋፍ በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ስም ታላቅ ምስጋና ማቅረብ እወዳለሁ፡፡ በተጨማሪም ከመቸው ጊዜ ባልተለመደ መልኩ 34 የገቢ ማመንጫ ኘሮጀክቶች በመምህራን ተቀርፀዋል፡፡ በጥቅሉ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት የነበረው እንቅስቃሴ የዩኒቨርሲቲውን የምርምር ባህል የቀየረና መምህራንም የምርምር፣ የኘሮጀክት ቀረፃና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራቸውን በላቀ መልኩና በአዲስ የስራ ተነሳሽነት የከወኑበት የበጀት ዓመት ነበር፡፡ በዚህ ረገድም የምርምር ማህበረሰብ ዘርፉን ለምትመሩና ለምታስተባብሩ አካላትና በንቃት ለተሳተፋችሁ መምህራን በሙሉ የተለየ ምስጋና ማቅረብ እወዳለሁ፡፡

ዩኒቨርስቲው በግንባታ ዘርፍም ከፍተኛ ዕድገት አምጥቷል፡፡ ዋናው ግቢ ጨምሮ በጤና ካምፓ̀ሱና በቡሬ ካምፓ̀ስ በርካታ ህንፃዎች በመገንባት ላይ ይገኛሉ፡፡ የተወሰኑትም ተጠናቀው እርክክብ ተፈጽሞ ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ የድህረ ምረቃ ህንፃ ፣ የአይሲቲ ህንፃና የዲጂታል ላይበራሪን ጨምሮ አዳዲስ ግንባታዎች በበጀት አመቱ ተጀምረዋል፡፡ የማስተማሪያ ሆስፒታሉ ዲዛይንም ተጠናቆ በ2012 በጀት ዓመት ግንባታው ይጀምራል፡፡ በሌላ መልኩ የተጀመሩ ህንፃዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ በዩኒቨርስቲው በኩል ያለው ድጋፍና ክትትል ጠንካራ ቢሆንም የግንባታ ስራን ማስተዳደር ከመቸውም ጊዜ በላይ ፈታኝ ሆኗል፡፡ በተቋራጮች በኩል ያለው የአቅም ውስንነት እንደተጠበቀ ሆኖ በያዝነው አመት የግንባታ ማቴሪያሎች ዋጋ መናር ዘርፉን ይበልጥ ውስብስብ አድርጐታል፡፡ የሆነው ሆኖ የተጀማመሩ ህንፃዎችን ለማጠናቀቅ የሚቻለው ጥረት ይደረጋል፡፡ በተቋራጮች ከፍተኛ የአቅም ውስንነት ችግር ያለባቸው ጥቂት ህንፃዎችንም በህጉ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ አማካሪዎች ተገቢውን ጥናት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ የትብብርና አጋርነትን በመለከተም በበጀት ዓመቱ ከ4 የውጭ ሀገር ተቋማትና ከ6የሀገር ውስጥ ተቋማት ጋር ትብብር ተፈጥሯል፡፡በተጨማሪም ከ25 የውጭ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በተፈጠረው ኔትወርክ ከ8 የሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎች የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አንዱ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ውድ መምህራንና ሠራተኞች

ሌላው በበጀት ዓመቱ እንሰራዋለን ብለን ያቀድነው ምቹ የስራ ከባቢ መፍጠር ነበር፡፡ በዚህ ረገድ መምህራንና ሰራተኞች አካዳሚክ ነፃነታቸው ተከብሮ በፍፁም ነፃነት መደበኛ ስራቸውን እንዲከውኑ የተዘረጋው ስርዓት አበረታች ቢሆንም በቂ የመዝናኛ ክበቦችን መፍጠር አልቻልንም፡፡ አዲሱ የመምህራንና ሰራተኞች መዝናኛ ህንፃ በመስታወት የጥራት ችግር በተፈጠረ ውዝግብ ህንፃውን ተረክቦ ስራ ማስጀመር አልተቻለም፡፡ የማህበረሰብ ት/ቤቱን ቦታ በቅርብ የተረከብንና የዲዛይኑ ስራም እየተጠናቀቀ ቢሆንም በፈለግነው መልኩ ግንባታውን ማስጀመር አልቻልንም፡፡ የሆነው ሆኖ ከረጅም ድካም በኂላም ቦታው እየተረከቡት በመሆኑ ግንባታው ይጀምራል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋራ የነበረው መስተጋብር እጅግ ደካማ ነው በሚል በተደጋጋሚ ለትችት ሲቀርብ የነበረ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው ለአካባቢው ማህበረሰብ አንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ብቻ ሳይሆን ብቸኛው ፋብሪካም መሆኑን በጽኑ በማመን ያለንን መስተጋብር ለማሻሻል በበጀት ዓመቱ አቅደን በመስራታችን እጅግ አስደሳች ውጤት አምጥተናል በእርግጥ ለዩኒቨርሲቲውማህበረሰብና ለከተማው ህዝብ መስተጋብር መሻሻል የዞንና የከንቲባ አስተዳደሩ፣ የከተማው ህዝብ የላቀ ድርሻ ነበራቸው፡፡ በዚሁ አጋጣሚ በበጐ ቀንም ሆነ በክፉ ቀን ደራሽ ለሆነው ለከተማው ነዋሪ በተለይም ለሀገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት አባቶችና ለከተማው ወጣቶች እንዲሁም ለዞንና ከንቲባ አስተዳደሩ ምስጋናየን ማቅረብ እወዳለሁ፡፡

ውድ ተማሪዎች

አሜሪካኖች ወደ ፖ̀ለቲካው ሂወት ከመቀላቀላቸው በፊት በማህበረሰብ አቀፍ ስራዎች በንቃት በመሳተፍ ያስመዘገቡትን የማህበረሰብ ለውጥ ለፖ̀ለቲካ ስራቸው መነሻ ያደርጋሉ፡፡ ለአብነትም የቀድሞው የአሜሪካ ኘሬዚዳንት ባራክ ኦባማ በመጀመሪያ ለሴናተርነት በኂላም ለኘሬዚዳንትነት ለመመረጥ የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን አጠናቀው በሞያቸው ለተወሰኑ አመታት የሰጧአቸው የማህበረሰብ አገልግሎቶችና ያስመዘገቧአቸው የማህበረሰብ ለውጦች ትልቅ ድርሻ ነበራቸው፡፡ በእኛ ሀገር ደግሞ የዩኒቨርሲቲ ትምህርታችን እንኳን ባግባቡ ሳናጠናቅቅው በ18 እና በ19 ዓመታችን ፖ̀ለቲካውን እንጀምረውና ይሄው ስካር በስካር አድርጐን ዩኒቨርሲቲዎች የሀሳብ ልእልና፣ የሳይንስ፣ የፈጠራና የአዳዲስ እውቀቶች መፍለቂያ መሆናቸው ቀርቶ በሚያሳዝንና በሚያሸማቅቅ መልኩ የዘረኝነት፣ የጥላቻና የግጭት ሁነኛ መገላጫዎች ከሆኑ ውለው አድረዋል፡፡

ውድ ተማሪዎች፡- የሀገራች ፖ̀ለቲካ በየዘመኑ ለዲሞክራሲ ሲሉ ብዙ ተስፋ ያላቸውን ወጣቶች ህይወት የቀጠፈ ቢሆንም ዛሬም ቢሆን እርስ በእርስ ከመገዳደል ባሻገር በሰለጠነ ውይይት የዳበረ ዲሞክራሲ ባህል በማስፈን ረገድ ገና አሁንም ዳዴ እያለ ነው፡፡ የእያንዳንዳችን ልብም ለሰለጠነ ውይይት ገና ደንዳና በመሆኑ ነገሮችን በሰለጠነ ውይይት ከመፍታት ይልቁን መገፋፋቱና መጠፋፋቱ ልማድ አድርገነዋል፡፡ እናም የኢትዮጵያ ፖ̀ለቲከኞች ሁሌም ወደ ስልጣን የሚመጡት በወጣቶች ደም መሆኑን አውቃችሁ፣ ሙሉ ጊዜያችሁ ለትምህርታችሁ ቅድሚያ መስጠት ብትችሉ የፖ̀ለቲካ ሁኔታውንም ለማሻሻል የራሳችሁ የሆነ አወንታዊ አስተዋጽኦ ይኖራችኂል፡፡ በዚሁ አጋጣሚም ለህግና ስርዓት ተገዢ መሆን እንደሚኖርባችሁ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡ በ2011 በጀት ዓመት አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ተደርጓ፡፡ ለዓመታት የቅሬታ ምንጭ የነበሩት የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሾችን በተለዮ መልኩ በማደስ ማራኪና ሳቢ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ የማደሪያ ህንፃዎችንም ተማሪዎች ከመግባታቸው በፊት የቀለም ቅብ ጨምሮ የጥገና ስራ ተሰርቷል፡፡ የዩኒቨርሲቲው አመራር ለተማሪዎች ቅርብ ነው፡፡ በ2011 የትም/ዘመን በየጊዜው ተማሪዎቻችን ለሚያጋጥማቸው ችግር ቀርቦ ለማዳመጥ ቀናይ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ አንዳንድ ተማሪዎች ይህን በመልካም ጐኑ ከመመልከት ይልቁን ስርዓተ ቢስ መሆንና መረን የለቀቀ ተግባር ሲፈጽሙና ውሳኔዎችን በመንጋ ሲወስኑ አይተናል፡፡ ይሄ በ2012 ፍፁም የሚደገም አይደለም፡፡ሁሉም ተማሪዎች በህግና በስርዓት ትምህርታቸውን በሰላማዊ መንገድ መከታተል ይጠበቅባቸዋል፡፡

ውድ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በሙሉ ፡-

የከፍተኛ ትምህርት ከየትኛው የፖ̀ለቲካ እምነቶች፣ ከየትኛውም ሀይማኖት ተጽኖ እንዲላቀቅና የአካዳሚክ ነፃነት እንዲሰፍን በርካታ ምሁራን ባለፉት አመታት አበክረው ጠይቀዋል፡፡ አንዳንዶችም ከስራ መሰናበት ጨምሮ ብዙ ዋጋ ከፍለዋል፡፡ በቅርቡም ይህ ሁናቴ ለመቀየር መንግስት የወሰዳቸው ማሻሻያዎች ተስፋ ሰጪ ናቸው፡፡ በአንፃሩ ትናንት በርካቶቻችን ስንቃወመው የነበረውን ዛሬ አንዳንዶቻችን በድርጊት ለመፈጸም እየዳዳን እንገኛለን፡፡ ይህ በከፍተኛ ትምህርት መርህ ፋጹም ተቀባይነት የለውም፡፡ በየትኛውም መስፈርት የራሳችን የፖ̀ለቲካ እምነት በተማሪዎቻችን ላይ የመጫን የሞራልም ሆነ የህግ መሠረት የለንም፡፡ ዩኒቨርሲቲውም በዚህ ረገድ በ2011 አልፎ አልፎ የታዩ ችግሮችን በማቻቻል ለማለማለፍ የሞከረ ቢሆንም ለዩኒቨርሲቲው ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት ሲባል ከዚህ በኂላ በቻልታ የሚያያቸው ጉዳዩች ሊሆኑ ፈጽሞ አይችሉም፡፡ ሁላችንም ለሞራላዊ ኃላፊነት ተገዥ ሆነን ተማሪዎቻችን አያቶቻችን መስዋዕትነት ከፍለው ያስረከቡን ሀገር እንዲጠብቁና ጥልቅ የሀገራዊ ፍቅር እንዲያጐለብቱ ብዙ መስራት ይጠበቅብናል፡፡፡፡

ውድ የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሰራተኞች ፡-

በ2011 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ምንም እንኳን ሀገራዊ ሁኔታው እጅግ አስቸጋሪ ቢሆንም የዩኒቨርሲቲውን የመማር ማስተማር ሂደት ሰላማዊ ለማድረግና የየዘርፉንና የክፍላችሁን ዕቅድ በላቀ መልኩ ለመፈጸምና ሁሌም ከጐናችን ሁናችሁ ስለደገፋችሁን በድጋሜ ምስጋና ማቅረብ እወዳለሁ፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው የማንኛውም የትምህርት ተቋም በተለይም የከፍተኛ ትምህርት መሻሻል ለሀገራዊ ዕድገት ሚናው ከፍተኛ በመሆኑ ተቋማዊ ራዕይን ከሀገራዊ አስተሳሰብ ጋር ማየት ይጠይቃል፡፡ የዕለት ተዕለት ስራችን ስንከውን የተቋማችን ራዕይ ከማሳካት ባሻገር የአካባቢውን ማህበረሰብ ህይወት ከመለወጥና ለሀገራዊ ዕድገት አወንታዊ ሚና ከመጫወት ጋርም ማስተሳሰር በእጅጉ ያሻል ትልቁን ምስል በአይነህሌናችን መፍጠር ከቻልን በመደበኛ ስራችን ውጤታማ ለመሆን ሌት ተቀን ለመስራት ተጨማሪ አቅም ይሆናል፤ነገሮችን በሰከነ መንገድና በተለዮ አስተውሎት ለመከወንም ዕድል ይፈጥርልናል፡፡ እናም በ2012 የትምህርት ዘመን ነገሮችን በሰከነ መንገድ ማየትና ሀገራዊ ሁኔታው በተቋማችን የዕቅድ አፈፃፀም አሉታዊ ጐን እንዳይኖረው እንደ ሁሌው በታታሪነትና፣ በኃላፊነት ስሜት መደበኛ ስራችን እንድንሰራ አደራ እላለሁ፡፡

# ‹‹ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ... በአፍሪካ ወይም በዓለም የሚጠራ ዩኒቨርሲቲ ለመሆን መልካም አጋጣሚ አለው››

ክብርት ዶ/ር ፍፁም አሰፋ

የኢትዮጵያ የፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነር

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ

ስኬታማ ሰዎች ስኬትን በአጭር ወይም በረጅም ጊዜ ይናፀፋሉ፡፡ ለስኬት የሚፈልገው ጊዜ ማጠርና መርዘምም የሚወሰነው በአስቻይ ሁኔታዎች ቢሆንም የባለቤቱ ትጋት ደግሞ መሠረታዊ ነው፡፡ በመካከለኛ የእድሜ እርከን የሚገኝ ሰው በትምህርት፣ በማህበራዊና ፖለቲካዊ ህይወት ውጤታማ ሆኖ ሲታይ የዚያን ሰው የህይወት ተሞክሮ በመቀመር ለብዙዎች የህይወት መንገድ ለማቅናት እንደሚያስችል ስለሚታሰብ የግለሰቦች ተሞክሮ በዚህ አምድ ይስተናገዳል፡፡ የአብርሆት መፅሔት በ2011 ዕትም በእንግዳችን አምድ በትምህርታቸው ከፍተኛ ደረጃ የደረሱትንና በተለያዩ የመንግስት ኃላፊነቶች ላይ የሰሩና እየሰሩ የሚገኙትን የኢትዮጵያ የፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነርንና የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢን የህይወት ተሞክሮ ትዳስሳለች፡፡ ከእንግዳችን በርካታ ቁም ነገሮችና ተሞክሮዎችን እንደምታገኙ ባለ ሙሉ ተስፋ ነን፡፡ መልካም የንባብ ቆይታ፡፡



**አብርሆት፡-** እርስዎንና የስራ ኃላፊነትዎን ቢያስተዋውቁን?

**እንግዳ፡-** ዶክተር ፍጹም አሰፋ እባላለሁ፡፡ የኢትዮጵያ ፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነርና የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ነኝ፡፡

**አብርሆት፡-** ዶክተር ፍፁም አሰፋ የት ተወለዱ?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** ደቡብ ክልል ከክልሉ መዲና ከሃዋሳ 60 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኝ አለታ ወንዶ በምትባል ከተማ ተወለድሁኝ፡፡

**አብርሆት፡-** የአንደኛ ደረጃ ትምህርትዎን እንዴት እንደተማሩ ያስታውሱታል? ትምህርትስ እንዴት ጀመሩ?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** አንደኛ ደረጃ ትምህርቴን በጣም በጥሩ ሁኔታ ነበር የተማርሁት፡፡ ማንም ሰው የሚያስታውሰው የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን ይመስለኛል፡፡አለታወንዶ ብወለድም አባቴ በስራ ምክንያት ባሌ ሄዶ ስለነበረ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን እዛ መማር ጀመርሁ፡፡ ከዚያ ታናሽ እህቴ ተወልዳ ስለነበርና እናቴ የቤት እመቤት ስለነበረች የአባቴ መስሪያ ቤትና የእኔ ትምህርት ቤት አጥር ብቻ ነበር የሚለየው፡፡ በዛ ምክንያት ቤት እናቴን የሚያርስ ስላልነበረ እኔ ነበርሁ የማግዛት ነገር ግን አባቴ ወደ ትምህርት ቤት ይዞኝ ይሄዳል ሆኖም ግን ትምህርት ቤት እንደመቆያ ነበር፡፡ በእዚህ አግባብ ትምህርቴን ተማርሁ፡፡ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያስተማሩኝ መምህራን ጉበዞች ነበሩ፤ የክህሎት ስራዎችም አሁን የሌሉ ይሰጡ ነበር፡፡ በእጅ ስራ ክፍለ ጊዜ የእጅ ስራ እንሰራለን፤ ጥጥ እንፈትላለን ሌሎችንም የተግባር ትምህርቶች እንሰራ ስለነበር የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን በጣም ነው የማስታውሰው፡

**አብርሆት፡-** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትዎን የት ተማሩ? ስለዩኒቨርሲቲ ቆይታዎም አያይዘው ቢነግሩን?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን በባሌ ከተማርሁ በኋላ አባቴ በስራ ምክንያት እንደገና ወደ ሃዋሳ በመዛወሩ ከ8ኛ ክፍል ጀምሮ ሃዋሳ መማር ቻልሁ፡፡ ኮምቦኒ በሚል ጥሩ የግል ካቶሊክ ትምህርት ቤት ተማርሁ፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴንም

አንደኛ ደረጃ በነበረኝ ጥንካሬ ማስቀጠል ችያለሁ፡፡ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናን 3.8 ውጤት በማምጣት በአካውንቲንግ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ገባሁ፡፡በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቆይታዬም ጥሩ ውጤት በማምጣት በምመረቅበት ወቅት ከክፍሉ ትልቁ ውጤት የእኔ ነበር፡፡ በ1995 ዓ/ም ስንመረቅም የክብር እንግዳ የነበሩት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኔትቴር አቶ መለስ ዜናዊ ስለነበሩ እርሳቸው መረቁን፡፡ ከተመረቅሁ በኋላ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለመምህርነት ተወዳድሬ አልፌ ስራ ልጀምር በዝግጅት ላይ እያለሁ በተመሳሳይ ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ተወዳድሬ ስለነበር ቤተሰብም እዛ ስለነበሩ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሲጠራኝ ወደ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሄድሁኝ፡፡

**አብርሆት፡-** የሁለተኛና ሶስተኛ ድግሪ ትምህርትዎንስ የት ተማሩ? የመመረቂ ፅሁፍዎስ ምን ላይ ነበሩ ስለእሱ ቢያጫውቱን?

**ዶ/ር ፍፁም:-** ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ስስራ ከቆየሁ በኋላ በመሀል ለሁለተኛ ድግሪ ትምህርት ተመልሸ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብቼ /Regional and local development studies/ ሁለተኛ ድግሪዬን ሰራሁኝ፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪየ የመመረቂያ ጥናቴ የነበረው በቡና መፈልፈያ ጣቢያዎች በአካባቢው ውሃ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖአቸው ምን ይመስላል የሚል ነበር፡፡ ያንን ሠርቼ ከተመረቅሁኝ በኋላ ወደ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሄጀ ሳገለግል ቆየሁ፡፡ በሁለተኛ ድግሪ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሳስተምር ከቆየሁ በኋላ የ3ኛ ድግሪ ትምህርት ዕድል አግኝቼ ወደ ጀርመን አገር ሄድሁኝ፡፡ ጀርመን አገር ሶስተኛ ድግሪ የተማርሁት ከሁለተኛ ድግሪ ትምህርቴ ቀየር አድርጌ ወደ ኢኮኖሚክሱ መጥቸ ስለነበር የመመረቂያ ፅሁፌ የነበረው አነስተኛ መስኖ የሚጠቀሙ ቤተሰቦች ውሃን እንዴት በጥንቃቄ ሊጠቀሙ ይችላሉ የሚል ነበር፡፡ ለምሳሌ አንድ ወንዝ የላይኛውና የታችኛውይኖረዋል፡፡ የላይኛው ተፋሰስ አገራት ወንዙን በከፍተኛ ደረጃ ይጠቀማሉ፡፡ የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ደግሞ በዝቅተኛ ደረጃ ይጠቀማሉ፡፡ ውሃን አግባብነት ባለው መልኩ ለመጠቀም ህጐች የሉም፡፡ የላይኛው ተፋሰስ አገራት ውሀን ይሸጣሉ ከዚህ ጋር ተያይዘውም ሙስና ይፈፀማል፡፡ ስለዚህም ምን አይነት ተቋማትና አደረጃጀቶች መኖር ይገባል የሚል ላይ ነበር ጥናቴ ያተኮረው፡፡

**አብርሆት፡-** ምን አልባት ይህ ጥናትዎ ከአባይ ወንዝ ጋር ግንኙት ይኖረው?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** አዎ በትክክል ጥናቱ የተሰራው በስሞል ስኬል ኢርጌሽን ቢሆንም ማንኛውም የላይኛው ተፋሰስ አገራትና የታችኛው ተፋሰስ አገራት የውሃ አጠቃቀም ጉዳዮች ያሉበት ስለሆነ ለአባይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡

**አብርሆት፡-** በትምህርት ቆይታዎ የማይረሱት ነገር ምንድን ነው?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** አገር ውስጥ በነበረኝ የትምህርት ቆይታ በጣም ጥሩ ጊዜ ነው የነበረኝ ማህበራዊ ግንኙነቴ በጣም ጥሩ ነበር፤ ከሰዎች ጋር በጥሩ እግባባለሁ ከየትም አይነት አካባቢ የመጣ ሰው ጋር አብሮ የመማር፣ የመስራትና የመኖር ችግር የለብኝም፡፡ እንዲያውም እኔ ብቻየን ማጥናት አልወድም፡፡ ጥናት የሚመቸኝ በቡድን ሆነን ነው፡፡አገር ውስጥ በነበርሁ ጊዜ ጥሩ ግንኙነት ነው የነበረኝ ነገር ግን ወደ ውጭ በሄድሁኝ ጊዜ ልጆቼን ትቼ ስለሄድሁኝ በጣም አስብ ነበር፤ ብቸኝነቱም ያስቸግረኝ ነበር፡፡ ለልጆቼም እየሄድሁ እየመጣሁ ስለነበር በጣም ከባድ ጊዜ ነበር፡፡ ሆኖም ግን የማይገል ነገር የበለጠ ያጠነክራል እንደሚባለው ጠንካራ እንድሆን ረድቶኛል፡፡ በውጭ አገር ቆይታዬም የተሻለ ልምድ፤ የተሻለ ጥናትና ምርምር አሰራር ልምድ እንዲኖረኝ የተሻለ ትምህርትና ለተሻሉ ነገሮች ዕድሉን ማግኘት ብችልም እንደ አገር ግን ሊሆን ስለማይችል ከባድ ጊዜ አሳልፌአለሁ፡፡

**አብርሆት፡-** ከ1ኛ ደረጃ አሁን እስከ ደረሱበት የትምህርት ደረጃ ሲቆዩ የገጠመዎት የተለየ ነገር የሚሉት ይኖርዎት?

**ዶ/ር ፍጹም፡-** እኔ በትምህርት ቆይታዬ የማስታውሰው ብዙ አልነበረም፡፡ ግን እኔ ሁሌም ከጭንቅላቴ የማይጠፋው በ1993 ዓ/ም ተማሪዎች አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አምፀው ነበር፡፡ እኔ በእንደዚህ አይነት ነገር ውስጥ ብዙ አልሳተፍም በሌሎች ነገሮች ለምሳሌ ስፖርት ሜዳ መጀመሪያ ነኝ፡፡ አንድ ቀን ጠዋት ተነስተን ክፍል ልንሄድ ስንል ዛሬ ትምህርት የለም ተማሪው አምጽዋል ተባለ፡፡ ወቅቱም የፋሲካ ሰሞን ስለነበረ እኔ እንዴውም ጥሩ አጋጣሚ ነው በማለት ወደ ቤተሰቦቼ እሄዳለሁ አልሁኝ፡፡ ነገር ግን ስብሰባ አለ ተባልና ሄድን፡፡ ስብሰባውን ተሳትፈን ትምህርት እንደማንገባ ተስማማን፤ ነገር ግን እሁድ ፋሲካ ነበር፡፡ ሰኞ ከትምህርት ሚኒስቴር እስከ ረዕቡ ካልተመለሳችሁ እራሳችሁ በራሳችሁ ከትምህርት እንደተገለላችሁ ይቆጠራል ተባለ፡፡ ስለሆነም ከሀዋሳ መጥቸ ለገሀር ወረድሁኝ፡፡ ትልቅ ቦርሳ ይዤ ነበር ከበዓል መልስ ስለነበር የተቆጣጠረልኝ ምሳና ሌሎች ነገሮች ነበሩ፡፡ ከአንዲት ጓደኛዬ ጋር ካሳንቺስ አራት ኪሎ ታክሲ ያዝን ልክ ቤተ መንግስት ስንደርስ ታክሲው ከዚህ አላልፍም አለ፡፡ በዚያን ጊዜ አስፋልቱ ይንቀጠቀጥ ነበር፡



ታክሲውም አወረደንና ላጥ ብሎ ሄደ፡፡የስድሰት ኪሎ ተማሪ ወደ አራት ኪሎ ይመጣል፤ ከኋላቸው ፓሊስ ያስሮጣቸዋል ፡፡ ያን ትልቅ ቦርሳ ይዘን በአራት ኪሎ ወደታች በእራ-በከንቱ እንዴት ሆነን እንደተጓዝንና አንድ ቤት ዝም ብለን ገባን፡፡ ወደ ውጭ ስንመለከተ ተማሪውም ሌላው ሰውም ይሮጣል፤ ፌዴራል ፓሊስ ወደ ፊት ነበር የሚተኩሱት ይህም በአይኔ ያየሁት እና ሁሌም የማረሳው ነው፡፡ ከዚያ ብዙ ቀን አልተኛሁም ከዚያ ቤት እንዴት ብለን እንውጣ፤ አደርን፡፡ ተማሪም መታወቂያ እየታየ ይታሰር ነበር፤ የዛኔ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መታወቂያ በጣም በብዙ ዋጋ ይሸጥ ነበር፡፡ ምክንያቱም ወደ ኬንያ መውጫ ነበር፡፡ እኛ እጅ ላይ መታወቂያው ከተገኘ ምን አልባትም የመታሰሪያ ምክንያት ነው፡፡ ያረፍንበት ቤት ሴትዬ ትልቅ የእናቶች ረዥም ቀሚስ ሰጥተውኝ እሱንን ነጠላ ለብሸ ሄድሁኝ፡፡ ስድስት ኪሎ ቢዝነስ ፋኩልቲ የጥበቃ ሰራተኞች ቁጥራችን ውስን ስለነበር ያውቁንና በጣም እንግባባ ስለነበር አስገቡኝ፡፡ የማደሪያ ክፍላችን አብረውኝ ሄደው ምንም ሌላ ነገር ሳልነካ የትምህርት ማስረጃየን ብቻ ይዥ ወጣሁና በእንግድነት ወደተጠጋሁበት ቤት ተመለስሁና እዚያው አደርሁ፡፡ ከአደርሁበት ቤት አንድ ትልቅ መነኩሴ ሰው ወደ ክብረ መንግስት የሚባል አገር ይሄዱ ነበር ፡፡ እርሳቸው የመጡት አይናቸውን ሊታከሙ ነበር፡፡ለህክምናም አይናቸው ታሽጓል እርሳቸው ይዘውኝ ወደ ለገሀር ወጡ፡፡ በመንገድም ፓሊሶች ሲጠይቋቸው አይኔን ልታሳክመኝ መጥታ ነው ብለው ለገሀር ሄድን፡፡ ከዚያ በኋላ አውቶብስ ገባሁ አውቶብስ ውስጥ የኋላ መቀመጫ የነበሩ የሀዋሳ ልጆች በሙሉ ፖሊሶች እያስወረዱ አሰሯቸው፡፡ እነሱ ሲታሰሩ እርሳቸው እኔን ልጀ ናት ስላሉና ረዥም ቀሚስ ለብሸ ስለነበር እኔ ሀዋሳ ሄድሁ፤ በመሆኑም ያንን ጊዜ በፍፁም አልረሳውም፡፡

**አብርሆት፡-** የልጅነት ህልምዎንና አሁን የደረሱበትን እንዴት ይገልፁታል?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** ያው በልጅነት ዕድሜህ ጐበዝ ተማሪ ነህ ስትባልና ሲጨበጨብልህ ያው አንድ ቦታ እንደምትደርስ ታልማለህ፡፡ ቤተሰብ ውስጥ ለትምህርት ትኩረት የሚሰጥ ካለ ደግሞ የበለጠ ትበረታታለህ፡፡ አባቴ ለትምህርት በጣም ትኩረት የሚሰጥ ሰው ነው፡፡መፅሃፍትን ይገዛልናል፤ ሁሌ ጥሩ ውጤት እንድናመጣ ይከታተለናል፡፡ አባቴ ትምህርቴን እንድከታተል ያበረታታኝ ነበር፡፡ ዩኒቨርሲቲ ሆኘ እንኳ ውጤቴን በጣም ይከታተላል፤ ያስመዘገብሁትን ውጤት ይጠይቀኛል፡፡ የዩኒቨርሲቲ መምህር ከሆንሁ በኋላ ዕቅዴ ፕሮፌሰር መሆን እንጅ እውነት ለመናገር አሁን ያለሁበትን ደረጃ በህይወቴ አስቤው አላውቅም፡፡ በፓለቲካ የነበረኝ ተሳትፎ እንደዚያ አልነበረም፡፡ ሚኒስቴር ለመሆን አስቤውም ስለማላውቅ የኢትዮጵያ ፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነር ሆኘ በሚኒስቴር ደረጃ ስመደብ እንደ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሚባል ደረጃ እኩል ነው የሰማሁት፡፡ ስለሆነም አሁን የያዝሁትን ደረጃ እሆናለሁ ብየ አላሰብም ነበር፤ ግን በያዝሁት ትምህርት ጫፍ ለመድረስ በጣም እፈልግና እሰራ ነበር:፡ እንደ ግለሰብ የራሴን ዓላማ ለማሣካት ብቻ ሳይሆን ጠብታ ያክል እንኳ ቢሆን የእራሴን አስተወፅዖ እንደ አገር ማድረግ እፈልግ ነበር፡፡ ለሴቶችም መምህር እያለሁ በቅርብ ችግራቸውን ነግረውኝ የምችለውን አግዣቸው የማልችለውንም አብሬ መክሬ ችግራቸውን እጋራቸው ነበር፡፡ ስለሆንም ከዚህ በፊት እሞክረውና እፈልገው የነበረውን ሰዎችን የመርዳት ፍላጎቴን እውን ለማድረግና ለኢትዮጵያ ህዝብ ጠብታም ያክል ቢሆን ለማድረግ ምናልባትም አሁን ያለሁበት ደረጃ ትክክለኛ ነው ማለት ነው፡፡

**አብርሆት፡-** የመጀመሪያ ድግሪዎን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ከወጡ በኋላ ስራ ሲጀምሩ የነበርዎት ስሜት ምን ይመስል ነበር?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** የመጀመሪያ ድግሪዬን ተመርቄ ስራ ስጀምር በጣም ቀጭን ነበርሁ፡፡ በመሆኑም አንዳንድ ተማሪዎች እየገቡ ያጭበረብሩ ስለነበር ተማሪዎች እኔ ስገባ ለማመን ይቸገሩ ነበር፡፡ በመሆኑም ሌሎች መምህራን ጋውን ባይለብሱም ችግር አልነበረም፡፡ እኔ ግን የግድ ጋውን መልበስ ነበረብኝ፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ብቆጣቸው ችግር ሊፈጠር እንደሚችል በመገንዘብ ከተማሪዎች ጋር የነበረኝ ግንኙነት መልካም እንዲሆን ማድረግ ነበረብኝ፡፡ ከዛም በኋላ መስራትና ማስተማር መቻሌን እያረጋገጥሁ ነው የመጣሁ ሆኖም እንደ መምህርነት የምወደው ስራ የለም፡፡ ተማሪዎችም በጣም ይወዱኝ ነበር አሁን በየቦታው ስሄድ የማገኛቸው ተማሪዎቼ አሉ፤ የመምህር ሀብቱ ተማሪ ነው፡፡ በየመስሪያ ቤቱ ስሄድ ተማሪዎቼን አላጣም፡፡ ነገር ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ማንም ሰው ወደ ስራው አለም ሲቀላቀል ይፈራል፡፡ በመሆኑም እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ ክፍል ለማስተማር ስገባ በአካል ትንሽና ወጣት ስለነበርሁኝ በጣም ነው የፈራሁት፡፡ ከዚያ ግን እየለመድሁ ሄድሁኝ፡፡

**አብርሆት፡-** በተለያዩ የስራ ኃላፊነት ሲሰሩ ስላበረከቷቸው ነገሮች ቢያጫውቱኝ?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት ስቀጠር ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲም ገና የተቋቋመበት ጊዜ ነበር፤ ግብርና ኮሌጅ ነው የነበረው ከዛም የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ የትምህርት ክፍል በማህበራዊና ስነ -ሰብዕ ኮሌጅ ስር ነው የነበረው፡፡ በስድስተኛ ወሬ ብዙ ሰው ስላልነበረ የአካውንቲንግ የትምህርት ክፍል ኃላፊ ሆንሁኝ፡፡ ከዚያም የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የብቻውን መውጣት አለበት በሚል ስራ ተሰጥቶኝ የኮሌጁን መዋቅር ሰራሁኝና ኮሌጁን በቦርድ በማፅደቅ እንዲቋቋም ያደረግሁት እኔ ነበርሁ፡፡ ከዚያ በኋላ በኮሌጅ ዲንነት፣ በተባባሪ ዲንነት ሰርቻለሁ፡፡ ስለሆነም የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ትልቅ ደረጃ እንዲደርስ ትልቅ ሚና ተጫውቻለሁ፤ ይህንን ስራየን ሰውም ይመሰክራል ብየ አስባለሁ፡፡ከዚያ በተጨማሪ በአካዳሚክስ ጉዳዮች የተለያዩ ኮሚቴዎች ላይ ሰርቻለሁ፡፡ ኃላፊዎችም ስራዎችን የሚሰጡ የለመዱትን ሰው ስለሆነ በተለያዩ ስራዎች እንድገባ ስለሚያደርጉኝ በጣም ይሰለቸኝ ነበር፡፡

**አብርሆት፡-** በስራዎ ውጤታማ ነኝ ብለው ያምናሉ?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** ስለ ውጤታማነቴ ሌላ ሰው ቢያወራ ጥሩ ነበር፡፡ ነገር ግን ከሰው ጋር ያለኝ ፍቅር፤ ቅርርብና ተግባቦት በጣም ጥሩ ነው፡፡ ከተማሪዎች፤ ከሹፌሮችና ከበላይ አመራሮች ጋር መልካም የሆነ ግንኙነት ነው የነበረኝ፡፡ ምክንያቱም መምህር ስትሆን ሌላ የመታተርፌው ነገር የለም፡፡ ስለሆነም የስኬቴን የተወሰነ ነገር ከሰዎች ጋር የነበረኝ ፍቅርና በጣም ጥሩ የሆነ ግንኙነት ይናገራል ብየ አስባለሁ፡፡

**አብርሆት፡-** ለእነዚህ ስኬት ያበቃኝ ምንድን ነው ብለው ያምናሉ?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** ይህን መግለፅ ስለ እራሴ ማውራት ባይሆንብኝ ከቤተሰብ የምትወርሰው የመለወጥ፣ የመማር፣ የተሻለ ነገር መስራትና ሰዎችን ማዳመጥ ሁልጊዜ እኔ ፈቃደኛ ነኝ፡፡ ይህ ይመስለኛል ለስኬት ያበቃኝ፡፡ ተማሪዎችን አዳምጣለሁ፤ ፀጉራቸውን ካንጨባረሩ ፀጉርህን ካልተቆረጥህ አላስተምርህም በማለት እንዲስተካከሉ፤ ጫማቸውንና ልብሳቸውን ንፅህና እንዲጠብቁ እመክራቸዋለሁ፡፡ የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች የትምህርት ክፍያ በማሰባሰብ እንዲከፈልላቸው አደርጋለሁ፡፡ ሰዎችን ለመስማት ቅርብ ነኝ፡፡ ስለሆነም እነዚህ ነገሮች ይመስሉኛል ለውጤት ያበቁኝ፡፡

**አብርሆት፡-** አሁን ባሉበት የሚኒስትር ቦታ ሆነው በኢትዮጵያ በተለያዩ ፕሮጀክቶች ታቅደው የሚጓተቱበት ሁኔታን እርስዎ እንዴት ገመገሙት?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** ፕሮጀክቶችን እኔ ወደ ኢትዮጵያ ፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነርነት ከመምጣቴ በፊትም ግምገማው ተጀምሮ ነበር፡፡ ወደ ፕላን ኮሚሽን ከመጣሁ ስድስት ወር ነው የሆነኝ፡፡ በዚህም ትልቁ ችግራችን ማቀድ አይደለም፤ መፈፀም ነው፡፡ ለዚህም የክትትልና የግምገማ ስርዓታችን ደካማ ስለነበር የክትትልና ግምገማ ስርዓታችንን ለማጠናከር በሰፊው ትልቅ ተልዕኮ ይዘን እየሰራን ነው፡፡ ትልቁ ችግር የትግበራ ነው ሲተገበርም በተጠያቂነት መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ነው እየሰራን ያለነው፡፡

**አብርሆት፡-** ይህን ለማሳካት ምን ታስቧል?

**ዶ/ር ፍፁም፡-**ይህ በአንድ ጊዜ የሚመጣ ነገር አይደለም፡፡ አንደኛ ትልቅ የአዕመሮ ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል፡፡ ሰው በስራው ልክ መመዘን አለበት፡፡ ባስመዘገበው ውጤት ልክ የሚመዘን ከሆነ ለውጤቱ ይሰራል ምክንያቱም ጥቅማጥቅም ያገኛልና፡፡ ለዚህም ስልትንና ተቋማትን መገንባት ነው፡፡በመሆኑም እንደ ፕላን ኮሚሽን እየሰራን ያለነው እነዚህን ስልቶችና ህጐችን ማርቀቅና ማፅደቅ ላይ ነው፡፡ ክትትልና ምዘና የሚደረግበትንና ሰዎች የሚመዘኑበትን መለኪያዎችና አሰራር መዘርጋት ነው፡፡አሁን ላይ በሪፖርት የሚቀርቡት ተግባራት ናቸው እንጅ ውጤቶች አይደሉም፡፡ ለምሳሌ ማዳበሪያ ተሰራጭቶ ገበሬው ተጠቅሞበት ምርትና ምርታማነቱን መጨመሩን ማረጋገጥ ላይ ነው ሪፖርት ሊቀርብ የሚገባው፡፡ ስለሆነም ትልቅ የማስተዋወቅና የማሰልጠን ስራ የሚጠይቅ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ሊሳካ የሚችል አይደለም፡፡

**አብርሆት፡-** ወደ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የስራ ቦርድ ሰብሳቢነት እንዴት መጡ? የቦርድ መዋቅሩስ ምን ይመስላል?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ ሰብሳቢ ሆኜ ስመደብ የዩኒቨርሲቲ ልምድ ስላለኝ ብዙ እንግድነት አልተሰማኝም፤ ነገር ግን የቦርድ ሰብሳቢ ሆኜ ስለማላውቅ ምንድን ነው የምሰራው ብየ አዋጁን ለማየት ሞክሬአለሁ፣ የሚመለከተው የሚኒስቴር መስሪያ ቤትም የማስተዋወቅ ስራ ሰርቷል፡፡ የቦርድ አባላት የሆኑትን ሰዎች ሳገኝ ግን በጣም ነው ደስ ያለኝ ምክንያቱም በጣም ብቃት ያላቸው በመሆናቸው ዩኒቨርሲቲውን ሊያግዙ የሚችሉና የእኔን መሪነት ብቻ የሚፈልጉ በመሆናቸው ነው፡፡ ስለሆነም ምን ምን መስራት እንደሚገባን የድርጊት መርሃ- ግብር አውጥተን ተግባራትን በባለቤትነት ተከፋፍለን እየሰራን ነው፡፡

**አብርሆት፡-** ከዩኒቨርሲቲው አመራር ጋር በምን አግባብ ልትሰሩ አስባችኋል?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** ከዩኒቨርሲቲው አመራር ጋር በጣም ቅርብ የሆነ ግንኙነት አለን፡፡ እንዴት አድርገን መስራት እንዳለብን በዕየለቱ እንነጋገራለን፣ እንግባባለን፡፡ አገሪቱም ለውጥ ላይ በመሆኗና ዩኒቨርሲቲውም ለውጥ ላይ በመሆኑ የእኛ እገዛ ምን መሆን አለበት ብለን መደበኛም ሆነ ኢ-መደበኛ በሆነ ግንኙነት ከዩኒቨርሲቲ አመራር ጋር እንነጋገራለን፡፡

**አብርሆት፡-** ዩኒቨርሲቲውንና የዩኒቨርሲቲውን መዋቅር እንዴት ገመገሙት?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** እሰራበት ከነበረው ዩኒቨርቲ ብዙ የሚለይበት ሁኔታ የለም ሁሉም የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ተግባርና የሚሰጣቸው ኃላፊነቶች መማር-ማስተማር፣ ምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት ናቸው፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ ካለበት ልዩ ባህሪ ተጨማሪ ተግባራትን ሊሰራ ይችላል፡፡ ነገር ግን ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እንደማውቀው ከፕሬዝዳንቱ ጀምሮ ለስራ ቁርጠኝነት ያላቸው መሆናቸውንና የዩኒቨርሲቲው መምህራን ፕሮፋይልም ከእሱ ተመጣጣኝ ከሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች በተሻለ ሁኔታ ነው ያለው፡፡ የአካዳሚክ ስታፉ መምህራን ጥሩ ፕሮፋይል ያላቸው፣ ሁሉም ሊባል በሚችል ደረጃ በ2ኛ ዲግሪ ያሉና ለስራ ቁርጠኝነታቸውንም ከሰማነው ሪፖርት በጣም ጥሩ እንደሆነ ለማየት ችያለሁ፡ በዚህም የመጀመሪያው ቀን የመጀመሪያው ክፍል (Day one class one) በደረሰን ሪፖርትና እኛም በራሳችን ባደረግነው ምልከታ በጣም ጥሩ ተደርጐ የሚወሰድ ዩኒቨርሲቲ እንደሆነ ነው የገመገምነው፡፡



**አብርሆት፡-** እርስዎ እንደ ዩኒቨርሲቲው የቦርድ አመራር ሰብሳቢነት በዩኒቨርሲቲው ምን እንዲመጣ አበክረው ይሰራሉ?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** እኔ እንደ ቦርድ አመራርነቴ ከሌሎቹ የቦርድ አባላት ጋር ሆነን ዕቅድ አውጥተናል፡፡ በተለመደው አሰራር ለምሳሌ በአመት፣ በየሩብ አመቱ እየተገኘንና ሪፖርት እያየን፤ ዕቅድ እየገመገመን የመሳሰሉትን ተግባራት እንሰራለን፡፡ ነገር ግን በዋናነት ዩኒቨርሲቲውን በተሻለ ልንረዳበት በምንችል አግባብ ከቦርድ አባላት ውጭ ያሉትን ሰዎች አቅም በደንብ አድርጐ ለመጠቀም በሚቻልበት ሁኔታ ዕቅድ አውጥተናል፡፡ በዚህ ውስጥ ለምሳሌ ምርምር ላይ፣ በተለያዩ ጆርናሎች የማቋቋም፣ የምርምር ስራዎች የሚታተሙበትን በተጨማም አገር ውስጥና ውጭ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች አጋርነትን በመመስረት የተሻለ ልምድ ያላቸው ስላሉ እነዚያን ለመጠቀም እንችል ዘንድ በደንብ ዕቅድ አውጥተናል፡፡ስለዚህ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በቅርብ ሆኖ ማየት የምፈልገው በምርምሩ በተለይ አካባቢውን መሠረት ባደረገና የልዕቀት ማዕከሉን ማዕከል ባደረገ መልኩ የተሻለ ደረጃ ደርሶ ጥሩ ከሆኑት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር አጋርነት መስርቶ በመማር ማስተማሩ፤ በማህበረሰብ አገልግሎትና ምርምሩ በደንብ ልቆ አሁን በአገራችን ካለው ትምህርት ግንባር ቀደም ሆኖ የተሻለ ደረጃ ላይ እንደዲሆን ነው፡፡

**አብርሆት፡-** ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አመራር ጋር በምንመልኩ ሊሰሩ አስበዋል?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** እውነት ለመናገር ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አመራር ጋር የምንገናኘው መደበኛ በሆነ ስብሰባ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ነገሮች መተጋገዝ በምንችልባቸው ነገሮች ሁሉ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡ አዲስ አበባ በፌዴራል ደረጃ መፈታት ያሉባቸው ነገሮች ሲኖሩ እየተደዋወልንና እየተገናኘን አብረ አስፈላጊ ወደ ሆኑት አካላት ጋር በመሄድ ችግሩን እንዲፈቱልን ከዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ጋር ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ችግሩን ማቅረብና ለችግሩ መፍትሔ እንዲሰጡን የማግባባት ስራ እሰራለሁ፡፡ ይህም መደበኛ በሆነ መልኩ የቦርድ አባላት መጥተው መሰብሰብ አይደለም፡፡ የዕለት ከዕለት ስራን ከማገዝ አንፃር የሚቻለውን ለማድረግ ነው፡፡ ስለዚህም ከአመራሩ ጋር ያለን ግንኙነት ከእኔ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሁሉም የቦርድ አባላት ጋር በጣም ጥሩ የሚባል ነው፡፡ ግንኙነታችንም በተሰጠን ኃላፊነትና ተግባር ብቻ አይደለም፡፡ በማንኛውም ሁኔታ መርዳት በምንችለው ሁሉ ለመርዳት ሁሉም የቦርድ አባላት ዝግጁና ፈቃኛ ናቸው፡

**አብርሆት፡-** የእርስዎ የህይዎት ፍልስፍና ምንድን ነው?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** እኔ የህይወት ፍልስፍና የሚለው ላይ ለመድረስ የሰው ልጅ የህይወት ፍልስፍና ነው ብየ ነው የማስበው ምክንያቱም በህይወትህ የሚያጋጥሙህ ነገሮች ናቸው የአንተን ማንነትን ቅርፅ የሚያስይዙ፡፡ እኔ ገና ቅርፅ አልያዝሁም፡፡ ስለሆነም በትምህርት የማገኘው፣ በስራ የማገኘው አብሬ የምሰራቸው ነገሮች አንተን ሙሉ ሰው ያደርጋሉ፡፡ የእኔ የህይወት ፍልስፍና ከእኔ ተርፌ ለሰው ማሰብ ስችል ነው፡፡ የሰውን ችግር ማዳመጥ መቻል ለሰዎች ጆሮ መስጠት ነው፡፡

**አብርሆት፡-** ስለትዳር ሁኔታዎ ቢያጫውቱኝ?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** እንግዲህ ትምህርት ትማራለህ ከዚያ በኋላ ትዳር ትመስርታለህ፡፡ ባለቤቴ ለረዥም ጊዜ በጓደኝነት አብሮኝ የቆየና የመጀመሪያ ድግሪዬን ከጨረስሁ ጀምሮ ከዚያ በፊትም ጀምሮ በጓደኝነት ለረዥም ጊዜ አብሮኝ የቆየ ሰው ነው፡፡ ከአሁኑ ባለቤቴ ጋር በጓደኝነት ቆይተን በመጀመሪያ ድግሪዬ ስራ እየሰራሁ ከዚያ ሁለተኛ ደግሪዬን ተምሬ ስጨርስ ትክክለኛ ጊዜ ነው ብየ አስብሁ፡፡ በመሆኑም ከቆየው ጓደኛዬ ጋር ለመጋባት ወሰን፡፡ ባለቤቴም የሰፈር ልጅና አብረሮኝ ያደገ ልጅ ነው፡፡ የፍቅር ጓደኝነት ከመመስረታችን በፊትም ጓደኞች ነበርን፡፡ ለረዥም ጊዜ የማውቀው ሰው ነው ከዚያም የሁለተኛ ድግሪ ትምህርቴን እንደጨረስሁኝ ተጋባን ቀጥሎ የመጀመሪያ ልጀን ወለድሁ፡፡

**አብርሆት፡-** ባለቤትዎ ማን ናቸው ?ልጅዎስ ?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** ባለቤቴ አቶ ቢኒያም ወልደ ሚካኤል ይባላል፡፡ የመጀመሪያ ልጀ ደግሞ ሄላብ ቢኒያም ትባላለች፡፡ አሁን ስምንት አመቷ ነው፡፡ ሁለተኛ ልጅም ወልጄ አምስት አመቱ ነው፡፡ የሁለተኛ ልጄ ልክ ስድስተኛ ወር ላይ ለሶስተኛ ዲግሪ ትምህርት መሄድ ስለነበረብኝ እንሱን ትቼ ለትምህርት ሄድሁኝ፡፡ ስለዚህ የእኔ ቤተሰቦች እናቴም እህቶቼም ከባለቤቴ ጋር ሆነው ልጆቼን እያሳደጉ ቆዩኝ፡፡ ከዚያ የሶስተኛ ዲግሪ የጥናት መረጃየን ሰብስቤ የጽሁፍ ስራ ስጀምር ደግሞ ሶስተኛ ልጄን ሊሊ ቢኒያም የምትባለዎን ልጅ ወልጀ አሁን ሶስት አመት ሆኗታል፡፡

**አብርሆት፡-** ሴትነትንና ኃላፊነትን እንዴት አገኙት?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** ሴትነትና አመራርነት ቀላል ሊባል የሚችል ነገር አይደለም፡፡ ልጆች የእኔን ሰዓት በጣም የሚፈለጉበት ሰዓት ነው ያሉት፣ ለባለቤቴም ቢሆን ጊዜ ልሰጥ ይገባል፡፡ ነገር ግን ኃላፊነት ከተሰጠህ የግድ ማድረግ አለብህ፡፡ ለሁሉ ነገር በትክክል ጊዜ ልትሰጥ አትችልም ይህንን እንደ መርህ ተቀብየ ነው የምሄደው፡፡ ሁሉን ነገር ልታሳካ አትችልምና ለምሳሌ ሁልቀን ልጆቼ ሳይተኙ ቤት መድረስ አልችልም፡፡ ነገር ግን ቢያንስ በሳምንት አንድ ቀን እሁድን ከስራ ነጻ አድርጌ ከእነሱ ጋር አብሬ ለመሆንና በማምንበት እምነት ቦታ ላይ ሄጀ አብሬአቸው የተወሰነ ሰዓት ለማሳለፍ እሞክራለሁ፡፡ ከዚያ ውጭ እንደ አገራችንና እንደ ባህላችን ሙሉ በሙሉ ከቤት ስራ ነፃ ለመሆን ስለማይቻል ለምሣሌ ምግብ በትክክል መሠራቱን፣ ልጆቼ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ምግብ መታሰሩን አረጋግጣለሁ፡፡ ቤት ስገባ ደግሞ ሁሉ ነገር ተሟልቶ መኖሩን አረጋግጣለሁ፡፡ ባለቤቴ ደግሞ ያግዘኛል፡፡ አሁንም በቤት ውስጥ የቤት ኃላፊነቴን ለመወጣት ልጆች የቤት ስራ መስራታቸውን በቻልሁ ጊዜ አረጋግጣለሁ፡፡ ከቻልሁም አብሬ እሰራለሁ ይህም የበለጠ መቀራረባችንን ስለሚያጠናክረ ነው፡፡ ሆኖም ግን በጊዜ መድረስ ካልቻልሁ የቤት ስራ መስራታቸውን አረጋግጣለሁ፡ ልብሳቸው ንፁህ መሆኑን፤ በአጠቃላይ ቤት ስገባ የሚስትነትና የእናትነት ሚና ይጠብቀኛል ማለት ነው፡፡ያንን በተቻለኝ መጠን ለመወጣት እሞክራለሁ፡፡ ቢሮም ልክ በእዚያው መጠን ነው ሴት ስለሆንክ የተለየ የስራ ግምገማ የለም፡፡ ስለዚህ የቢሮውንም ስራ በእዚያው መጠን ነው የምንሰራው፤ ሁሉም ሴቶች እኔም ብቻ ሳልሆን እና ቀላል አይደለም ሁሉንም ሚናዎች መጫወት ግድ ነው፡፡

**አብርሆት፡-** ማህበራዊ ህይወትዎ ምን ይመስላል?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** ማህበራዊ ህይወት የውዴታ ግዴታ ነው፡፡ ለጓደኞቼ ጊዜ መስጠት አለብኝ፣ የታመሙትን መጠየቅ አለብኝ፣ ሰው ሁሉ እኩል አይገነዘብህም ጊዜ የለኝም ብትል፡፡ በተቻለ መጠን ለቅሶ እደርሳለሁ፣ የወለደ እጠይቃለሁ፡፡ መሄድ ካልቻልሁኝ እንኳ ደውየ እጠይቃለሁ፡፡ ግን የተጠራሁበት ሠርግ ሊሆን ይችላል እዚያም ሄጀ እሳተፋለሁ፤ ለበዓል ባለችኝ ሰዓት ከዘመዶቼ፣ ከቤተሰቦቼና ከጓደኞቼ ጋር የተሻለ ጊዜ እንዲኖረኝ እሞክራለሁ እና የምፈልገውን ያክል ባይሆንም በተፈጥሮየ እኔ ብዙ ሰው በአካባቢየ እንዲኖር የምፈልግ አይነት ሰው ስለሆንሁ የብቻን መኖር የምችል አይደለሁም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ይህንን ማድረግ ቢችሉም እኔ ግን እንደዚያ አይነት ሰው አይደለሁም፡፡ ሰው በጣም እፈልጋለሁ፡፡ በተቻለኝ መጠን ሰው በአቅራቢያየ እንዲኖር ነው የማደርገው፡፡ የቢሮ ስራን ብቻ እየሰራሁ ዝም ብየ ቁጭ ብየ ማህበራዊ ኃላፊነቴን ልወጣ አልችልም፡፡ የማህበራዊ ህይወቴንም በተቻለ አግባብ ለመወጣት ጥረት አደርጋለሁ፡፡

**አብርሆት፡-** ትርፍ ጊዜዎትን እንዴት ያሳልፉታል?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** እንግዲህ ወደ እዚህ ኃላፊነት የመጣሁ ቅርብ ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ትርፍ ጊዜየን ስፖርት እሰራለሁ፣ ዋና እዋኛለሁ፣ ልክ ስራየ ብየ በሳምንት ሶስት ቀን ዋና እዋኛለሁ፣ ከዚያ ፊልም አያለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መፅሀፍ አነባለሁ፡፡ ነገር ግን አሁን ከአዲሱ ስራየ ጋራ እራሴን እያስተዋወቅሁና ጊዜየን እያመቻቸሁ ነው ያለሁ፡፡ ሰዓቴን አመቻችቼ የቱ ጋ ስፖርት መስራት እንዳለብኝ እያመቻቸሁ ነው፡፡ ነገር ግን በትልቁ የሚመቸኝና የምወደው ስፖርት መስራት ነው፡፡

**አብርሆት፡-** በህይወትዎ የገጠምዎ አሳዘኝ ወይም በጣም የተደሰቱበት ነገር ምንድን ናቸው ስለሱ ቢያጫውቱኝ?

**ዶ/ር ፍጹም፡-** እኔ አሳዛኝ ብየ የምለው እውነት ለመናገር እንግዲህ የተለየ ብየ የምጠቅሰው ነገር አሁን በአዕምሮየ የሚመጣ ነገር የለም፡፡ ግን አሳዛኝና ጥሩ ያልሆኑ አጋጣሚዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያ ልጄን የወለድሁ ጊዜ የተሰማኝ ደስታ በጣም ከፍተኛ ነበር፡፡ ሁልጊዜ እግዚያብሔርን እናመሰግናለን ነገር ግን የምናመሰንግበት ደረጃ አለው፡፡ ሁሌ የምመኘው የመጀመሪያ ልጄ ከሆዴ የወጣች ቀን ፈጣሪየን ያመሰገሁበትን አይነት ስሜት ኖሮኝ ሁሌ እግዚያብሔርን እንዳመሰግን ነው፡፡ ምክንያቱም የዚያ አይነት ደስታ የለም በእዚያ ደረጃም እግዚያብሔርን አመስግኘው አላውቅም፡፡ ስለዚህ ያን ደስታ እኔ አልረሳውም፡፡ ከዚያ ውጭ ምን አልባት የተሾምሁበትን ቀን አስቤው አይደለም የተሾምሁት፡፡ ግን የለውጥ ጊዜ ነው፡፡ አገራችን ውስጥ በነበረው ነገር እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ስከፋ ነው የነበረው ስለሆነም ሹመቴን ስሰማ በጣም ደንግጫለሁ ነገር ግን ደስ ብሎኛል ምክንያቱም አሁን ያለው ነገር ግለሰብን በመደገፍ አይነት ሳይሆን ኢትዮጵያ አሁን አዲስ ለውጥ ላይ ያለች ይመስላል፡፡ ስለሆነም ያንን የነበረውን መጥፎ አዝማሚያ ለመለወጥ የሚሰራ ቡድን ውስጥ መካተት መቻል ትልቅ ነገር ነው፡፡ ስለዚህ የእራሴን አስተዋፅኦ ጥሎ ለማለፍ እግዚአብሔር እድል የሰጠኝ ነው የሚመስለኝ፤ ከባድ ቢሆንም፡፡ በመሆኑም ሹመቴን በደንብ ሳብሰለስለው እንደሰማሁት ብደነግጥም በጣም ነው ደስ ያለኝ፡፡ ስለዚህ ለአሁኑ ላስታውሳቸው የምችል እነዚህ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ በትምህርት ብዙ ውጤታማ ብሆንም ከእኔ በላይ ወላጆቼ ናቸው ደስ የሚላቸው፡፡ ስለዚህ በህይወት ውስጥ የሽግግር ነጥቦች ማለትም ልጄን የወለድሁበት እና ወደ ኃላፊነት የመጣሁባቸው ጊዜያት የተደሰትሁባቸው ናቸው፡፡ ምክንያቱም በህይወቴ የለውጥ ምዕራፎች ናቸውና፡፡ ሌላው በህይዎቴ ብዙ አሳዛኝ ነገሮች ቢገጥሙኝም በጣም አሳዘኝ ነው ብየ የምገልፀው ግን የለኝም፡፡

**አብርሆት፡-** በመጨረሻ ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲና ለሌሎች አካላት ምን ማለት ይፈልጋሉ?

**ዶ/ር ፍፁም፡-** እኔ ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ የማስተላልፈው መልዕክት አገራችን በብዙ ፈተናዎችና ያልጠሩ መንገዶች ውስጥ ነው ያለችው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ ግለሰብ ይኽንን መንገድ ለማጥራትና የአገሩን መልካም ነገር እንዲመጣ ምን ሚና መጫዎት እንደሚገባው እንዲያስብ እፈልጋለሁ፡፡ ስለሆነም በአሁኑ ሰዓት ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ሳይሆን እያንዳንዱ ማህበረሰብ እስኪ ለተወሰነ ጊዜ ቁጭ እንበልና ወደ ውስጥ እናስብ ምክንያቱም አሁን ሰው ወደ ውስጥ የሚያስብበትን ጊዜ የተለያዩ ነገሮች የወሰዱበት ይመስለኛል፡፡ወደ ውስጥ ማሰብ አቅቶንና ተስኖን ወደ አልሆነ አቅጣጫ እየመራን ይመስለኛል፡፡ስለዚህ እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱን ሚና ካልተጫዎተ ኢትዮጵያ ያለችበት ያልጠራው መንገድ ወደ መጥፎ መንገድ ሊወስደንም ዕድሉ አለ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ያለውን ሁኔታ ሁላችን ተንከባክበን ይዘን የዚህ ጠባቂ መሆን አለብን፡፡ በዩኒቨርሲቲው ደግሞ ህፃናት ልጆች አሉ ፡፡ እነዚህ ህፃናት ሲመጡ ከኋላቸው ቤተሰቦቻቸው አሉ ስለዚህ ለእራሳችን ስናስብ እነዚህ ልጆች በምንም አይነት ሁኔታ ወደ ተሳሳተ መንገድ እንዳይገቡ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ነገር ግን ማንኛውም ሰው የራሱ የሆነ አስተሳሰብ የማራመድ፣ የራሱ ሀይማኖት ሊኖረው መብቱ ነው፡፡ ግን ዩኒቨርሲቲ ውስጥ እነዚህ ህፃናት በማያውቁት መንገድ ውስጥ ሰው በቀደደው መንገድ ውስጥ ገብተው ጥፋት ውስጥ እንዳይገቡ እንደ ልጆቻችን፣ ወንደሞቻችንና እህቶቻችን መምከር መቻል አለብን፡፡ ብዙ ያልተሟሉ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ እንደ ግለሰብ ከደመወዝ ጀምሮ ስለዚህ ያንን ሳያስብ እያንዳንዱ ሰው አገርን የመገንባት ስራ ላይ ካልተሳተፈ ወደ አላስፈላጊ አቅጣጫ የመሄድ አቅጣጫን እናሰፋዋልን ማለት ነው፡፡ስለዚህ እያንዳንዳችን በምንችለው ነገር ሁሉ እንደ ግለሰብ የየራሳችንን ሚና ልንጫወት ይገባል፡፡

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ያለበት ቦታ፣ የስታፍ ፕሮፋይል በጣም ጥሩ ነው ስለሆነም በአፍሪካ ወይም በዓለም የሚጠራ ዩኒቨርሲቲ ለመሆን መልካም አጋጣሚ አለው ስለዚህ የእኔነት ስሜት ሁሉም ኖሮት ከታች እስከ ላይ ያለው ማህበረሰብ የራሱን ሚና መጫወት ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም እንተባበር፣ አብረን እንስራ፡፡ ይሄ ብዙ ጊዜ ተሰርቶ የመጣውን ሰው የመለየያት፤ የመከፋፈል በጣም ወርዶ ወርዶ በሰፈርና በመንደር ደረጃ የመለያየት የመከፋፈሉን ነገር ሰለማይጠቅመን እንተወው፡፡ እየተጎዳን ያለነው እኛ ነን፡፡ ያንን ለአንድ ጊዜ ትተን ቁጭ ብለን ወደ አንድ መንገድ አስበን እንደ አንድ እንሁን፡፡ ሁላችንም እንደ እህት እንደ ወንድም እንሁን፤ ይህን ማድረግ ካልቻልን የሚታየው ነገር አስቸጋሪ ነውና፡፡

**አብርሆት፡-** ለጊዜዎት በጣም በአብርሆት መፅሄት አንባቢያን ስም በጣም አመሠግናለሁ!

**ዶ/ር ፍፁም፡-** እኔም አመሠግናለሁ፡፡

# የመሬት አስተዳደር ተቋም

## ዓለም አቀፍ ተሞክሮን ወደ አካባቢያዊ ፋይዳ ያሸጋገረ ተቋም



ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በውስጥ በያዛቸው ካምፓሶች ኮሌጆች፣ ትምህርት ቤቶችና ተቋማት በየጊዜው ራሱን እያሻሻለ፣ ፋይዳውን እያጎላ የመጣ ተቋም ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢና የቡሬ ሁለት ካምፓሶች፣ የሶሻል ሳይንስና ስነ-ሰብዕ፣ የተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ፣ የጤና ሳይንስ፣ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ የግብርና ተፈጥሮ ሃብት አምስት ኮሌጆች፣ የመሬት አስተዳደር ተቋም፣ የደብረ ማርቆስ የቴክኖሎጂ ኢንስትቲዩትና የሥነ-ትምህርትና ሥነ-ባህርይ ሶስት ተቋማት፣ የህግና የህክምና ሁለት ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ውስጥ በርካታ የመጀመሪያ፣ የሁለተኛና የሶስተኛ ዲግሪ ፕሮግራም የሚሰጡ ፕሮግራሞች አሏቸው፡፡ እነዚህ ፕሮግራሞች ሲከፈቱ ሥርዓት-ትምህርታቸው ዓለምአቀፍ ይዘት ጠብቆ የአካባቢውን ችግር ሊፈቱ በሚችል መልኩ መቀረፅ እና መተግበር እንዳለባቸው ይታመናል፡፡ በ2011 የአብርሆት መፅሔት ህትመትም ይህንን እና መሠል ሥራዎችን በሚገባ እየሠራ የሚገኘውን የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የመሬት አስተዳደር ተቋም እናስተዋውቃችኋለን፡፡

የኑሮና ሃብት መሰረት የሆነውን የመሬት ሃብታችንን በአግባቡና በስርዓት ማስተዳደር የምንሻውን ዘላቂ ልማት እውን ለማድረግ ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊተገበር የሚገባ ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም የምንመገበው ምግብ፣ የምንኖርበት ቤት፣ የምንተነፍሰው አየር፣ የምንለብሰው ልብስ፣ የምንጠጣው ውሃ፣ ... የሁሉም ነገር ምንጩ መሬት ነው፡፡ አብዛኛው ህዝብ በግብርና በሚተዳደርበት እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ አገራት ደግሞ መሬት ሁሉም ነገራቸው ነው፡፡

ይሁን እንጅ ይህንን የኑሮና ሃብት መሰረት የሆነውን ብቸኛ ሃብት በአግባቡ በማስተዳደር፣ በመጠቀምና በማልማት በኩል የየአገሮራቱ የመሬት አስተዳደር ስርዓትና ስሪት የተለያየ ነው፡፡ አንዳንድ አገራት በተለይም ያደጉ አገሮች መሬት የህይወትና የሃብት መሰረትነቱን ቀድሞ በመረዳት ይህንን መሰረታዊ ሃብት በአግባቡ ማስተዳደርና ማልማት በመቻላቸው ዕድገታቸውን ማፋጠንና የህዝባቸውን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ችለዋል፡፡ ሌሎቹ አገራት በተለይ ታዳጊ አገራት ደግሞ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ልማዳዊና የዘፈቀደ የመሬት አስተዳደር ስርዓት ስለሚከተሉ ትልቁን ሃብት በአግባቡ ሳይጠቀሙበት ተስተውለዋል፡፡ ለዚህም የተለያዩ ምሁራን ብዛት ያላቸው ጥናቶችን በማድረግ መሬትን በአግባቡ ማስተዳደርና ማልማት ያለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታዎች በሰፊው አትተዋል፡፡ ለምሳሌ ታዋቂው ምሁር De Soto, ‘Why Capital Triumphs in the West and Fails Everywhere’ በሚለው መፅሐፋቸው የመሬት ሃብትን በአግባቡና በስርዓት ማስተዳደር ሃብት ለመፍጠር ያለውን የጎላ ሚና አጉልቶ አሳይቷል፡፡ ተመራማሪው በፅሁፋቸው እንዳተቱትው ያደጉ አገሮች የመሬት ሃብታቸውን በአግባቡ ለክተውና መዝግበው በመያዛቸውና በዋስትና ማስያዣነት በመጠቀም ልማታቸውን የሚያሳድጉበት አሰራር በመዘርጋታቸው እድገትና ልማት ማፋጠን መቻላቸውን ሲገልፁ በአንፃሩ ደግሞ የመሬት ሃብትን ልማትና ዕድገትን ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ ስርዓት መዘርጋት ባለመቻላቸው ታዳጊ አገሮች እምቅ የሆነ የመሬት ሃብት ቢኖራቸውም በአግባቡ መጠቀም ባለመቻል የሞተ ካፒታል እንዳደረጉት ገልፀውታል፡፡

ስለዚህ ያለውን ውስን መሬት በአግባቡ ለክቶና መዝግቦ በመያዝ እና በጥናት ላይ ተመስርቶ መሬትን ሊውል ለሚገባው ተገቢ ስራ በማዋል ከመሬት የሚገኘውን አግባብ ያለው ጠቀሜታ ማግኘትና የኑሮና የዕድገት መሰረት በሚሆን መልኩ ሊያስፈፅም የሚችል የመሬት አስተዳደር ስርዓት መፍጠር የስራዎች ሁሉ ቅድሚያ ስራ፤ የልማቶች ሁሉ ቅድሚያ ልማት ነው፡፡ ምክንያቱም በገጠርም ይሁን በከተማ የምንሰራው የመሰረተ-ልማት ስራ፣ የኮንስትራክሽን ስራ፣ የተፈጥሮ ሃብት ስራ፣ የግብርና ስራ በተጣጣመ መልኩ መፈፀም የሚቻለውና መሬትና ከመሬት ጋር የተያያዙ ስራዎች ለአብነት የግብርን፣ የካሳ ክፍያን በመሬትና መሬት ላይ የተደረጉ ልማቶች የዋጋ ግምት መሰረት ያደረገ እንዲሆን ማድረግ የሚቻለው፣ ከመሬት ጋርም ተያይዞ የሚነሱ አለመግባባቶች መረጃን መሰረት ያደረገ ውሳኔ ማሳረፍ የሚቻለው በአግባቡ የተለካና የተመዘገበ የመሬት ኃብት መረጃ ሲኖርና ግልፅና አሳታፊ የሆነ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓት መዘርጋት ሲቻል ብቻ ነው፡፡

አብዛኞቹ ያደጉ አገሮች የመሬት ይዞታ ዋስትናን አንዱ የሰብአዊ መብት ጉዳይ አድርገው በህጋቸው በመቅረፅ የይዞታ ዋስትናን ማረጋገጥ ችለዋል፡፡ የመሬት ሃብታቸውንም ከሚኒስትር ደረጃ ጀምሮ ተጠያቂና ግልፅነት የተላበሰ መዋቅር በመፍጠር ማስተዳደር ከጀመሩ ብዙ መቶ ዓመታትን አስቆጥረዋል፡ ፡ የእነሱን ተሞክሮ በመውሰድም ብዙ ታዳጊ አገሮች የመሬን ጉዳይ እራሱን አስችለው በሚኒስተር ደረጃ በማዋቀር በተሻለ ሁኔታ በመምራት ላይ ይገኛሉ፡ ፡ ከጎረቤት አገራት ኬንያ፣ ሩዋንዳ፣ ዩጋንዳ፣ ታንዛንያ ወዘተ. መጥቀስ ይቻላል፡፡ በእኛም የመሬት ይዞታ ዋስትናን ማረጋገጥና ማስጠበቅ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባና መሬትን በአግባቡ ጠብቆ፣ ተንከባክቦና አልምቶ ለመያዝ የሚያስችል መሰረት በመሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአደረጃጀቱ ዙሪያ ክፍተት ቢኖርም ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል፡፡

በመሆኑም አገራችን እነዚህንና መሰል ተግባሮች በተሳለጠና በተጣጣመ መንገድ በመፈፀም ዘላቂ ልማትን ለማስፈን ምንም እንኳን ዘግይታ የጀመረች ቢሆንም ከጀመረች ጀምሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ በተለይ በገጠር የመሬት አስተዳደር ዙሪያ ጥሩ ውጤት እያስመዘገበች ትገኛለች፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ይዞታ ምዝገባና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በመስጠት የመሬት ይዞታ ዋስትና ለማረጋገጥ እየተደረገ ያለው ጅምር አበረታች ቢሆንም ዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ስላለበት በሚፈለገው ፍጥነትና ጥራት መሄድ አልተቻለም፡፡ በተለይ የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ስራው ወሳኝ የሆኑ የቅየሳና ምዝገባ እንዲሁም የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ስራዎችን ያካተተ ስለሆነ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት መቅረፍ የግድ ይላል፡፡ ገበያው የሚፈልገውን የተማረ የሰው ሃይል በብዛትና በጥራት ማምረት ደግሞ የዩኒቨርሲቲዎች ተልዕኮ በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት የተወሰኑ ዩኒቨርሲቲዎች ፕሮግራሙን ከፍተው ተማሪዎችን በማሰልጠን ላይ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርቲ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው የመሬት አስተዳደር ተቋም በ2009 በመክፈት በመደበኛው፣ በማታና በክረምት መርሃ ግብር ተማሪዎችን እየተቀበለ በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡

ፕሮግራሙን ለመክፈት ዩኒቨርሲቲው በአስፈላጊነቱ ዙሪያ ሁለት ጊዜ ያህል (2001 እና 2008) በአጋር አካላት ላይ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አድርጎ ከፍተኛ የባለሙያ እጥረት በመኖሩ መከፈቱ ጊዜ የማይሰጠው መሆኑን ያረጋገጠ ቢሆንም በተለይ የመምህራንና የቅየሳ መሳሪያዎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው በመሆኑ እነዚህ የሚሟሉበትን አማራጭ በማፈላለግ የተወሰነ ጊዜ ፈጅቷል፡፡ ለተግባሩም ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ቅድመ ዝግጅት ሲደረግ ቆይቷል፡ ፡ የሶስተኛ ዲግሪ ትምህርት ለመከታተል በሄዱበት ወቅት ዶ/ር ሣይህ ካሳው አውስትሪያ ሃገር ከሚገኙ ሁለት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠርና ይህን ክፍተት በመሙላት ፕሮግራሙ ለመጀመር በተደረሰው ስምምነት መሰረት አጋር ካላት ‘APEAR Preparatory Fund’ ላይ በመወዳደር የ15000 Euro ድጋፍ ተገኝቷል፡፡

በዚህ የገንዘብ ድጋፍም በአጋር አካላት መካከል የተጀመረውን ግንኙነት ለማጠናከር በመታሰቡ ሁለት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ አመራሮች አውስትሪያ ቬና በመሄድ እንዲሁም ሁለት ፕሮፌሰሮች ከቬና ቴክኒካል ዩኒቨርሲቲና ቦኩ ዩኒቨርሲቲ በመምጣት የእርስ በርስ ትውውቅና ፕሮጀክት በማዘጋጀት ለ3 ዓመት የሚቆይ የአውስትሪያ ልማት ፕሮጀክት ውድድር ማስታወቂያ ላይ በማመልከት መወዳደር ተችሏል፡፡ የፕሮጀክቱ ርዕስም ‘Implementation of Academic Land Administration Education in Ethiopia for supporting sustainable development’ የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጅ ምንም እንኳ በመጀመሪያው ውድድር ሳይመረጥ የቀረ ቢሆንም በቀጣይ ዓመት የፕሮጀክት ገምጋሚዎችን ሃሳቦች ታሳቢ በማድረግና ፕሮጀክቱን አሻሽሎ ቀርፆ በማቅረብ ለሁለተኛ ጊዜ በመወዳደር ለውድድር ከቀረቡ 111 ፕሮጀክቶች ውስጥ የ2ኛውን ደረጃ በመያዝ ፕሮጀክቱ የተመረጠ ሲሆን በ2016 የፈረንጆች ዓመት ጀምሮ 490000 ዩሮ ተመድቦለት ስራ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡

ከዚህ በጀት ዉስጥም 5ሺ ዩሮ በየዓመቱ ቦርዱ ለሚያካሂደው የፕሮጀክት አፈፃፀም የስራ ግምገማ የስራ ማስኬጃ፣ 67 ሺ ዩሮ ሁለት የፒኤችዲ ትምህርት ለሚከታተሉ መምህራን፣ አግልግሎት የሚውል ሲሆን 418 ሺ ዩሮ ደግሞ 4ቱ አጋር አካላት ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ላይ ለሚከናዉኑት ተግባር የተመደበ በጀት ነው፡፡

የፕሮጀክቱን አፈፃፀም በዋና ዋና ስራዎች ሲታይም በመጀመሪያ የፕሮግራሙን ካሪኩለም ከአገር ውስጥ አጋር አካል ከሆነው የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የመሬት አስተዳደር ተቋም በመውሰድና የተወሰኑ ማሻሻያዎች በማድረግ በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ፀድቆ በ2009 መደበኛ የመማር ማስተማር ስራ የተጀመረ ሲሆን ተቋሙን በማጠናከር ዙሪያ የፕሮጀክት ፈንዱ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ለአብነት ያህልም በዕቅዱ መሰረት ትኩረት ሰጥቶ በመፈፀም፡-

1. የኮምፒዩተር ቤተ-ሙከራ በሚገባ የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም 25 የተሻለ አቅም ያላቸው ዴስክቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ 25 ጠረንጴዛዎችና 25 ተሽከርካሪ ወንበሮች እንዲሁም አንድ LCD projector እንዲገጠም ተደርጓል፤

2. ለምርምር፣ ለማስተማርና ፕሮጀክት ስራ የሚያገለግሉ በአገር ውስጥ ግብይታቸው ቢፈፀም ከ7.1 ሚሊዮን ብር በላይ ሊያወጡ የሚችሉ ዘመናዊ የቅየሳ መሳሪያዎች ግዥ ከውጭ ተፈፅሞ የቀረበ ሲሆን መሳሪያዎችም 3 RTK GPS 4 total station ናቸው፤

3. ለማስተማር አገልግሎት የሚውሉ 5 handheld GPS ተገዝተው ቀርበዋል፤

4. የኢንስቲቲዩቱ ዌብሳይት በአዲስ መልኩ እንዲሰራ ተደርጓል፤



አቶ ወርቁ ነጋ
የመሬት አስተዳደር ተቋም ም/ዲን





5. ወጫቸው በፕሮጀክቱ ተሸፍኖ ሁለት መምህራን አውስትሪያ ሃገር ተልከው የ3ኛ ዲግሪያቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፤

6. በአገር ውስጥ የማይገኙ የማጣቀሻ መፅሐፍት ከውጭ ተገዝተው እንዲቀርቡ ተደርጓል፤

7. ሌላው ተግባር ከውጭ አጋር አካላትን በመጠቀም በሰው ሃብት አቅም ግንባታ ዙሪያ የተከናወነው ሲሆን ስራዎችን በሁለት ዋና ዋና የስራ ሂደቶች ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፤-

- የመጀመሪያዉ ከፌደራል እስከ ወረዳ ድረስ ያሉ የመሬት አስተዳደር ባለሙያዎችን ዩኒቨርሲቲዉ ድረስ በመጥራት GIS, Remote Sensing, Carthography, and Land consolidation ኮርሶች ላይ ከ5-6 ቀናት የፈጀ አጫጭር ስልጠና የተሰጠ ሲሆን

- ሁለተኛው ደግሞ Photogrammetry, Remote Sensing, Carthography, Land consolidation, and Gender and land rights ኮርሶችን በውጭ ፕሮፌሰሮች ለተማሪዎች ትምህርት ተሰጥቷል፤

8. 4 የምርምር ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን ሁለቱ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ፤

9. 106 ለሚሆኑ የቀበሌ መሬት አስተዳደር ኮሚቴዎችና የቀበሌ አመራሮች በአዲሱ የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ዙሪያ የሁለት ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፤

10. የፕሮጀክቱን ዕቅድ መነሻ በማድረግ ሴት ተማሪዎችን ተሳትፎም ለማሳደግ በተሰጠው ትኩረት የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎችን ለአብነት ወስደን ብናይ እንኳን የሴቶችን ቁጥር 70% ማድረስ ተችሏል፤

እነዚህ ለአብነት የቀረቡ ዋና ዋና አፈፃፀሞች ሲሆኑ በጥቅሉ ፕሮጀክቱ አዲስ የተከፈተውን የመሬት አስተዳደር ተቋም በማጠናከርና በማደራጀት በኩል ትልቅ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ ወደፊትም ግንኙነቱን በማጠናከር በዘርፉ የ2ኛ ዲግሪ ትምህርት ለመጀመር ዕቅድ ተይዟል፡፡ በመጨረሻም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የእውቀት፣ የክህሎት እና የአመለካከት ልውውጥ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ፕሮጀክት በመቅረፅ፣ ካሳይንቲስቶች ጋር ለመገናኘት፣ ምርምሮችን በጋራ ለመስራት፣ አለም አቀፍ ኮንፈረንሶችን በጋራ ለመስራት፣ የዩኒቨርሲቲውን አቅም ለማሳደግ፣ በተለይ የአካዳሚክ ስታፍ በጥንካሬ በመስራት፣ ሲኒየር መምህራን አዳዲሶችን በማማከርና የልምድ ልውውጥ ስራን በመስራት ለዋጭ እና ገንቢ ስራ ሊሠራ እንደሚገባ የዚህ ፕሮጀክት ዋና አነቃቂ በመሆን ያገለግላል፡፡

በተጨማሪም በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የመሬት አስተዳደር ተቋም ዲን አቶ ሙሉጌታ በበኩላቸዉ በኢንስቲትዩቱ ዉስጥ እየተከናዎኑ ያሉትን ተጨማሪ ተግባራት አብራርተዋል፡፡ የመሬት አስተዳደር በአሁኑ ሰዓት በሀገር ደረጃ ለከፍተኛ የሙስና መንስኤ እንዲሆን በመዳረጉ፣ በመሬት አማካይነት ለግለሠቦች የጠብ መንስኤ በመሆናቸውና መስሪያ ቤቶች በቀጥታ በማይመለከታቸው ባለሙያዎች የተያዙ በመሆን፣ ለህፃናትና ለሴቶች፣ ለአቅመ ደካማዎች ጭምርም ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መልኩ መሬቶቻቸው ያላግባብ እንዲነጠቁ እየሆነ መጥቷል፡፡ ስለሆነም ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በሀገሪቱ ያለውን የመሬት አስተዳዳር ስርዓት በዘላቂነት በመፍታት፣ የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት፣ ተማሪዎችን በመሬት አስተዳዳር ዙሪያ ትምህርት ክፍሉን ከፍቶ የተሻለ ዕውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ ሲባል ፕሮግራሙ አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተቋሙ ውስጥ ከሚተገበሩ ዋና ዋና ተግባራት መካከል ትምህርትና ስልጠና በመስጠት 3 የመደበኛ መርሃ ግብር፣ 3ኛ ዓመት በክረምትና እና በማታ 1ኛ ዙር ተማሪዎችን ተቀብሎ ከማስተማር አርሶ አደሩንና ሌላውን የማህበረሰብ ክፍል ስልጠና በመስጠት ከፍተኛ ሥራ እየሠራ ይገኛል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በተለይም ተቋሙ የተገበራቸው ስራዎች ካቀዳቸው እቅዶች ጋር ሲነፃፀር የመጀመሪያውን መነሳሳት ከፈጠረው ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ያስተማራቸውን የመጀመሪያ ድግሪ ተማሪዎችን ቀጥታ ቅጥር በመፈጸም የማስተርስና ዶክትሬት የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ በማድረግ ከፍተኛ ስራ እየሠራ ይገኛል፡፡ ስለሆነዋ ለዩኒቨርሲቲው ሰራተኞችና ሌሎች ማህበረሰቦች ስልጠና በመስጠት የእውቀትና ቴክኖሎጅ ሽግግር እንዲኖር በድረግ፣ ከውጭ ለሚመጡ አጋር አካላት የዩኒቨርቲውን ገጽታ ግንባታ በመፍጠር አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ በቀጣይም ከዩኒቨርሲቲው ስትራቴጅክ ዕቅድ ክለሳ ጋር ተያይዞ የ MSC ፕሮግራሞችና ተጨማሪ የድግሪ ፕሬግራሞችን ለመክፈት እቅድ እንደያዙ የተቋሙ ዲን አስታውቀዋል፡፡

# የህክምና ተማሪዎች የተግባር ትምህርት በሆስፒታሎች

ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣዉን የትምህረት ፍላጎትና ጥማት ለማርካት መንግስት በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች የከፍተኛ ትምህርትን ተደራሽ ለማድረግ ከፍተኛ ሥራ እየሠራ ይገኛል፡፡ ተደራሽነቱ በጥራት የተደገፈ ይሆን ዘንድም የትምህርት ሚኒስቴር ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ፓኬጆችን ቀርጾ ሃገሪቱ የምትፈልገዉን የተማረ የሰው ሃይል በማምረት በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት እንዲጐለብቱ ለማድረግ በትኩረት እየሰራ ይገኛል፡፡በተጨማሪም ተማሪዎች በተግባር የተደገፈና ሳይንሳዊ ትምህርት ይማሩ ዘንድ የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር የሚባል ተቋም በትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ ተቋቁሞ ይህን ግብ ስኬታማ ከማድረግ አንጻር ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን የንድፈ ሃሳብ ትምህርት በተለያዩ ተቋማት፣ ፋብሪካዎች እና ሆሰፒታሎች ተመድበው በተግባር መመልከት እና ልምምድ ማድረግ እንዲችሉ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡፡

ስለሆነም እኛም በዚህ አምዳችን በጤናና በህክምና ዘርፍ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን ለአንባቢዎቻችን ለማድረስ ተማሪዎች የተግባር ትምህርት ከሚሰሩበት ቦታ ተገኝተን በመመልከት፣ አስተባባሪዎችን በማናገር የተግባር ትምህርት አፈፃፀም በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ምን እንደሚመስል እናስቃኛችኋለን፡፡

የተግባር ትምህርት በተለይ ከህክምና ትምህርት አሰጣጥ ረገድ ባለሙያዎች ትክክለኛ በሽተኛውን ለመውሰድ ብሎም አስፈላጊውን ህክምና ከማግኘታቸው በፊት መለማመድ ያለባቸውን ነገሮች እንዴት ከበሽተኛው ጋር ተቀራርበው መስራት እንዳለባቸውና የታካሚ መረጃዉን ወስደው በምርምራ ከማረጋገጣቸው በፊት ይህን ዓይነት በሽታ ሊኖርበት ይችላል ብለው ሚሰሩት ተግባር ወሳኝ የህክምና ትምህርት አካል እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ እደ ዶ/ር ታለማ አይተነው ገለፃ የተግባር ትምህርት ተማሪዎች በተግባር የህክምና ስራ ከመስራታቸው ቀደም ብሎ በራሳቸውና በመምህሮቻቸው እየታገዙ እንዴት አንድን በሽታ ለይተው ማከም እንደሚችሉ ለማስረዳት የሚያስችል መንደርደሪያ ትምህርት ስለሚሆን አስፈላጊነቱ በጣም የጎላ ነው፡፡

በዚህ ረገድ አዲሱ የህክምና ስርዓት ትምህርት በተግባር የተደገፈ ትምህርት ከመስጠት አኳያ እጥረት አለበት ተብሎ በመገመቱ ምክንያት ተማሪዎች ከመጀመሪያ ዓመት ሲገቡ ጀምሮ ሙያዊ የብቃት ደረጃዎች /Professional Computational development /PCD/ በመስጠት እንዴት ደም መለካት፣ የሙቀት መጠን መለካት ሌሎች ተግባራትን መስራት እንዲችሉ ስለሚያሳይ የተግባር ትምህርት ቀደም ብለዉ የተማሩትን በተለይም 1ኛና 2ኛ ዓመት ሲሆኑ የሠው መሠረታዊ የሰውነት መዋቅሮች ከስርዓተ ተግባሩ ጋር ምን ጥቅም አለው፣ ስራውስ ምን ይመስላል፣ ጤናው ሊጓደልና መሠረታዊ አሠራርን ሊያውኩ የሚችሉ ነገሮች ምንድን ናቸው በሚሉ ፅንሰ ሃሳቦች ዙሪያ በፅንሠ ሃሳብ ደረጃ የተማሩትን በተግባር በማስደገፍ ትምህርቱ በሆስፒታል እንዲማሩትና ተግባራዊነቱን እንዲያረጋግጡ ይደረጋል፡፡

ይህ ደግሞ ለተማሪዎች በተግባር የታገዘ ትምህርት ከመስጠት ባሻገር የህክምናው ጥራት ተጠብቆ እንዲሰሠራ ያደርጋል፡፡

ለዚህ አተገባበር ያመች ዘንድ ተማሪዎች ለተግባር ትምህርት ከመውጣታቸው በፊት የሚደረግላቸው ቅድመ ዕውቅናና የሚፈጠርላቸዉ ስርዓት ይኖር ይሆን ብለን ለጠየቅናቸው ጥያቄ ዶ/ር ታለማ እንዲህ ይሉናል፡፡ ተማሪዎች ከመጀመሪያ ዓመት ጀምሮ በሽተኛውን ደም ከመለካታቸው በፊት በራሳቸው አቅም የራሳቸውን ደም በመውሠድ ያለምንም ፍርሃት እንዲሰሩ ያደረጋሉ



ዶ/ር ታለማ አይተነዉ

የህክምና ትምህርት ቤት ዲን

ለዚህ ደግሞ የተወሠነ እገዛ ይደረግላቸዋል፡፡ ይህንን ለማድረግ እንዲያግዝ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የመለማመጃ ቤተ ሙከራ መኖሩ በቀላሉ እንዲዘጋጁ ያደርጋቸዋል፡፡ ሌላዉ ተማሪዎች ለተግባር ልምምድ በሚወጡበት ወቅት ከሆስፒታል ሰራተኞች፣ ከአስተማሚ፣ ከፅዳት ሰራተኛ፣ ከበሽተኛ እና ከሌሎች የሆስፒታሉ አካላት ጋር በምን ሁኔታ መስራት እና መስተጋብር መፍጠር እንዳለባቸው እውቅና ይፈጥርላቸዋል፡፡

ድጋፍና ክትትልን በተመለከተ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ የንድፈ ሃሣብ ትምህርታቸውን ቀስመው ሲመጡ በአራት ዲፓርትመንት ማለት የማህፀንና ፅንስ፣ የህፃናት ት/ት ክፍል፣ የውስጥ ደዌ ት/ት ክፍል እና ቀዶ ህክምና ትምህርት በመክፈል እስካሁንም የተቀበልናቸውን 50 ተማሪዎች በአንድ በሽተኛ ዙሪያ 12 ተማሪዎችን እንዲመደቡ በማድረግ በቀላሉ የተግባር ትምህርቱን እንዲከታተሉ ይደረጋል፡፡ ይህ ደግሞ የትምህርቱን ጥራት ለማስጠበቅ ስለሚመች ብዙ ተማሪ ባንድ በሽተኛ ዙሪያ እንዳይኖሩ ይረዳል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አንድ ባለሙያ መረጃ መዝጋቢ አድርገው በበሽተኛዉ ዙሪያ ቆሞ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ዘወትር ከሠኞ- አርብ በሳምንት ሁለት ጊዜ/ ከ2-4 ሰዓት የትምህርት ሰዓት ወስነው ከ4-6 ሰዓት ደግሞ በበሽተኛው ዙሪያ በመቆም የሚወያዩበትና በተለዩ ክፍሎች እየተዘዋወሩ በሽተኛውን የሚከታተሉበት ፕሮግራም አላቸዉ፡፡ በሳምንቱ መጨረሻ ከሠዓት ደግሞ የሴሚናር ፕሮግራም እንደሚኖራቸው ተገንዝበናል፡፡በተጨማሪም በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል የሚመደቡት መምህራን ከ12ቱ ተማሪዎች ቢያንስ ሶስት ተማሪ እያማከሩ የተግባር ትምህርቱን ተማሪው እንዲከታተልና የያዘውን የተግባር ትምህርት እንዲሰራ ፣ በቀን የማይታዩ ሙያዊ ስራዎችን በማታ እንዲከታተሉ ተማሪዎችን መድቦ ያዩትን እንዲመዘግቡ ማን ሲሠራ እንዳዩ እንዲፈርምላቸው በማድረግ የተማሪዎችን የተጠናከረ የተግባር ትምህርት ክትትል እንደሚደረግ ዶ/ር ታለማ አብራርተዋል፡፡ ተማሪዎች መሠረታዊ የንድፈ ሃሳብ ትምህርትን 1ኛ እና 2ኛ ዓመት ሲሆኑ ተምረውት ስለሚመጡ ወደ ሆስፒታል በሚገቡበት ወቅት ዘወትር ከ2-4 ሰዓት የሚማሩት ገለጻ በማድረግ የበሽታው አይነት እና ምልክቶችን እንዴት ማወቅ እንደሚቻል፣



ምን አይነት ምርመር ማድረግ እንደሚገባቸውና እንዲያውቁ በኋላም በተግባር ትምህርታቸው በሽተኛው ላይ ተግባራዊ እንዲያደርጉት እና እንዲሰሩት ይደረጋል፡፡

በተግባር የሚሰሯቸዉ ትምህርቶች ደግሞ በብዛት በሚከሰቱ በሽታዎች እንደ ቲቪ፣ ካንሰር እና ሌሎች ትምህርቶች ላይ ትኩረት ሰጥተው በተግባር እንዲማሩ ይደረጋል፡፡ በዚህ ረገድ የተግባር ትምህርቱ ሲመረጥም በሀገር ደረጃ በስፋት የተዛመቱ እና የሚስተዋሉ በሽታዎች ምንድን ናቸው ብሎ በማጤን እና ሰፊ ትኩረት በመስጠት እንደሚሰራበት፤ ተማሪዎችም የሰሩትን ኬዝ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ በአስተማሪዎቻቸው ግምገማ ተደርጎ ይቀርባል፡፡

ተማሪዎችን በስፋት ለማገዝ እንዲያመች ሲባል የህክምና ስርዓተ ትምህርቱ ከሚፈቅድው የጊዜ ሰሌዳ ውጭም በየወሩ የሶስትና አራት ሳምንት ተጨማሪ ትምህርት ይሰጣል፡፡ ተማሪዎችም ቀደም ብለው በተለያዩ ቦታዎች የሰሩ፣ የመጀመሪያ ድግሪ የተማሩ እና ብስለት ያላቸው በመሆናቸው፣ አብዛኛው የትምህርት ይዘትም የተግባር ትምህርት የበዛበት ከመሆኑ አንፃር በቀላሉ የመያዝ፣ የመቀበልና የማገናኘት ተሰጥኦቸው የጐላ ነው፡፡ ተግባሮችንም በከፍተኛ የውስጥ ስሜት በመስራት በውስጣቸው ሃኪም ተብለው ወደሚጠሩበት የሙያ መስክ እየተጓዙ በመሆኑ ውጤታማ የስራ አፈፃፀም እንዳላቸው አስተማሪዎቻቸው ይመሰክራሉ፡፡

በቂ የሆነ የህክምና ክህሎት ለማግኘት ለተግባር ትምህርቱ ከተመደበለት ሰዓት በተጨማሪ በራሳቸው መንገድ በማመቻቸት ተማሪዎች ትምህርቱን በደንብ እንዲከታተሉ ይደረጋል፡፡ በዚህም ረገድ በመጀመሪያ ዓመት በሽታውን እንዴት መለየት /diagnose/ ማድረግ እንደሚችሉ ለ6 ሣምንታት ይሰጣሉ፡፡ በቀጣይ አመትም እንዴት ህክምና የማድረግ ማኔጅመንት በመከወን ለሶስት ወር በበቂ ጊዜ እንዲማሩና ብቁ ማድረግ ይሞከራል፡፡

ከዚህ አንጻር ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከደብረ ማርቆስ ሆስፒታል ጋር የመግባቢያ ስምምነት /memorandum of understanding / /MOU/ በመፈራረም በተለያዩ የግንኙነት ደረጃዎች በጋራ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ዩኒቨርሲቲው በትልቅ ኃላፊነት ከሆስፒታሉ ጋር የጠበቀ ግንኙነት በማድረግየራሱን ሚና እየተወጣ ይገኛል፡፡

በሆስፒታል ደረጃ እየተደረገ ያለዉን ድጋፍ ስንመለከት ዩኒቨርሲቲው ለማስተማሪያ የሚያገለግሉትን የማስተማሪያ ክፍል እና ስብሰባ አዳራሽ፣ የመምህራን ቢሮ ሶስት የመማሪያ ክፍሎች፣ የቤተ መጽሀፍት ክፍል፣ የፀሐፊ ቢሮ፣ ቦታ እንዲገነባ በማመቻች ትልቅ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎች የመሰብሰቢያ አዳራሽ ፣የጓንት፣ የፅዳት፣ የተግባር መሳሪያዎችን ጋወን፣ በማመቻቸት ሆስፒታሉ ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በበኩሉ በሆስፒታሉ ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል ከ50% በላይ ሀኪሞች የህክምና አገልግሎት በዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሀኪሞች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡የመማሪያ ክፍል ጥበት፣ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው መምህራን እጥረት፣ የባለሙያ እጥረት፣ የተማሪዎች ጥቅማ ጥቅም አለመኖር እና የመሳሰሉት ችግሮች ለተግባር ትምህርቱ ስኬታማነት እንቅፋት ቢሆኑን ችግሮችን ለመቅረፍ የህክምና ት/ቤት ዲን በሆስፒታሉ የሲኒየር ማኔጅመት ቲም አባል በመሆን፣ የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ደግሞ በዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ኮሚሽን አባል በመሆን፣ በተጨማሪም የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ደግሞ የሆስፒታል ቦርድ አባል በመሆን ሁለቱም ተቋማት በወሳኝ ስብሰባዎች በመገኘት ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ የቅርብ እድል እየፈጠርላቸው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ግንኙነታቸዉንም ወደፊት ለማስፋፋት የበለጠ ስራ ለመስራት እንደሚችሉ ወስነዋል፡፡

በመጨረሻም እንደ ዩኒቨርሲቲ የተግባር ትምህርቱን ጨምሮ በመማር ማስተማሩ ረገድ በሃገር አቀፍ ደረጃ የምዘና ፈተና የተሻለ ውጤት ያስመዘገበ የህክምና ት/ቤት ቢሆንም የማስተማሪያ ሆስፒታል በመገንባት ሥራውን በሚገባ ለማከናወን እየተጋ ስለሚገኝ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለዚህ መሳካት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ሊያበረክቱ ይገባል፡፡

ይህ ሲሳካለት ትምህርት ቤቱ የትምህርት ባለሙያዎችን ለተጨማሪ ትምህርት በመላክ፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚነትለማሣደግ፣ የአካባቢውን ሆስፒታሎች በእውቀት ለማገዝ፣ የመምህራን አቅምና ጥቅማ ጥቅም ለማሣደግ፣ በዩኒቨርሲቲው እና በሆስፒታሉ መካከል ያለውን ግንኙነት ተቋማዊ በማድረግ የበለጠ ስራ ለመስራት ፣ በመጨረሻም የድህረ ምረቃ /postgraduate / የትምህርት መርሃ ግብር ከፍቶ በተሻለ ዕዉቀት ለመምራት እድል እንዲፈጥር ሁሉም የራሱን ኃላፊነት በመወጣት እና እንዲተገበር በማድረግ ሊረባረብ ይገባል በማለት ዶ/ር ታለማ አይተነው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# ውስንነት የማይገድበው የህክምና ትምህርት ቤት



የሶስተኛ ዙር የህክምና ዶክተሬት ተመራቂዎች በከፊል

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ትምህርት ቤት የተጀመረው በ2004 ዓ/ም ሲሆን አዲስ ከተመሰረቱ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል በአገሪቱ ያለውን የህክምና ባለሙያዎች እጥረት ለመቅረፍ ታስቦ የ4 አመት ከስድስት ወር አዲስ የህክምና ዶክተሮች ትምህርት ስልጠና ለመስጠት የህክምና ትምርት ቤት ከተቋቋመባቸው ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ሲሆን በ60 ተማሪዎችማሰልጠን ጀመረ፡፡ የህክምና ትምህርት ቤቱ እስካሁን ለሶስት ዙር ያስመረቀ ሲሆን በ2011 ዓ/ም 49 የህክምና ዶክተሮችን ሲያስመርቅ ከዚህ በፊት ከ80 በላይ ሀኪሞችን አስመርቆ ወደ ስራ ማሰማራቱን የህክምና ትምህርት ዲን ዶክተር ታለማ አይተነው ገልፀዋል፡፡

የህክምና ትምህርት ቤቱ ሲጀመር የህክምና ዶክትሬት ብቻ ነበር ሰልጣኞችን በመቀበል የሚያሰለጥነው፤ ከ2010 ዓ/ም ጀምሮ የሰመመን ባለሙያዎችን ለመፍጠር የትምህርት ክፍል ከፍቷል፡፡ ይህም የሜዲካል ራዲዮሎጅ ቴክኖሎጅ ትምህርት ክፍልን በመክፈት ወደ 22 ተማሪዎችን ተቀብሎ ከጀመረበት የህክምና ትምህርት በተጨማሪ ሁለት ትምህርቶችን ከፍቷል ማለት ነው፡፡

የህክምና ትምህርት ቤት የአካባቢው ማህበረሰብን በማስተማር ብቁ የጤና ባለሙያዎችን አስመርቆ በማውጣት የተሻለ ርቀት ሄዷል፡፡ በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ህክምና ትምህርት ቤቱ ብዙ ሰርቷል ባይባልም የደብረ ማርቆስ ሪፈራል ሆስፒታልን ለማጠናከር አብዛኛው የሆስፒታሉ የህክምና ስራ እየተሸፈነ ያለው በዩኒቨርሲቲው የህክምና ትምህርት ቤት መምህራን ነው፡፡ ከሰመመን ህክምና ጀምሮ እስከ ቀዶ ህክምና ድረስ አስራ አራት የጤና ስፔሻሊስት ሀኪሞች በአሁኑ ጊዜ በቋሚነት በሆስፒታሉ ለህሙማን የህክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ ከ40 በላይ ጠቅላላ ሀኪሞችና አራት የሚደርሱ የሰመመን ሰጪ ባለሙያዎችን ይዞ የደብረ ማርቆስ ሪፈራል ሆፒታልን በማገዝ ደረጃ ጥሩ ስራዎችን እየሰራ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ በአካባቢው የሌለ የስነ-አዕምሮ ጤና ባለሙያ ያለው ከባህር ዳር ቀጥሎ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡ይህም ከሆስፒታሉ ጋር በጋራ እየተሰራ ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጀምሮ የስነ ደዌ ሀኪም ሆስፒታሉ ከጐንደር እያስመጣ ያሰራው የነበረውን ለማስቀረት ያስቻለ እና የህክምና ትምህርት ቤቱ በቀጠረው የስነ ደዌ ስፔሻሊስት ሀኪም በደብረ ማርቆስ ሪፈሪል ሆስፒታል ህሙማን በሳምንትና በአስራ አምስት ቀን የናሙና ምርምራዎችን እንዲያገኙ ለማድረግ ተችሏል፡፡ይህንን አገልግሎቱን በደብረ ማርቆስ ሪፈራል ሆስፒታል መስጠት ከመጀመር አንስቶ የችግሩን ስፋት የተረዳው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ትምህርት ቤትም በሌሎች አካባቢዎች አገልግሎቱን ለማስፋት እየሰራ ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በፍኖተ ሰላም ሆስፒታል የአይን ስፔሻሊስት በመመደብ አገልግሎቱን እየሰጠ መሆኑንና ለዩኒቨርሲቲው የህክምና ተማሪዎችም እንደሚያስተምር ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም አዋበል ወረዳ ሉማሜ ላይ የዩኒቨርሲቲው ሀኪሞችና የጤና ባለሙያዎች ጋር በጋራ የጤና አገልግሎትን በተጠናከረ አግባብ ለመቀጠል ታስቦ እየተሰራ ነው፡፡ የህክምና ትምህርት ቤቱ በህክምናው ዘርፍ መስራት የሚችለውን ያህል እንዳልሰሩ የገለፁት ዶክተር ታለማ በደብረ ማርቆስ የሚገኙ ጤና ጣቢያዎችንም የማሳደግ ስራዎች ለመስራት መታቀዱን ጠቁመዋል፡፡ ምክንያቱም ደብረ ማርቆስ ሪፈራል ሆስፒታል ብቸኛው ሆስፒታል ከመሆኑ ጋር ተያያዞ ብዛት ያላቸው በሽተኞች ስለሚመጡ ይህን ለማስተንፈስ አንድ ሞዴል ጤና ጣቢያ ህክምና ትምህርት ቤቱ ከጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና ከሆስፒታሉ ጋር በመሆን የማሳደግ ስራ ሙከራ ተጀምሯል፤ ብዙ ነገር ቢቀረውም፡፡

በዩኒቨርሲቲው የህክምና ትምህርት ቤት እየሰለጠኑ ያሉ ተማሪዎች /ምሩቃን/ አምስት ዓመት ላይ ቅድመ ጤና ህክምና ሰጪዎች እነሱ ናቸው፡፡ ጠቅላላ ሀኪሞች ከተማሪዎች ጋር በመሆን የማማከር አገልግሎት እየሰጧቸው የሆስፒታሉን አገልግሎት በከፍተኛ ደረጃ እያገዙ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለይም ብቸናና ደጀን አንዳንዴ ሞጣ ላይ የተግባር ትምህርት ሲወጡ የማህበረሰብ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በቆይታቸው በአካባቢው የሚስተዋሉ የማህበረስብ ጤና ችግሮችን በመለየት ፕሮጀክቶች እስከ መቅረፅ ድረስ ይሰራሉ፡፡ ሆኖም ግን ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ ሁሉንም ሆስፒታሎች ማዳረስ አልተቻለም፡፡ የህክምና ትምህርት ቤት በሶስት ዙር አስመርቆ ያስወጣቸው ከ130 በላይ የህክምና ዶክተሮች ለማህበረሰቡ እያበረከቱት ያለው ሚና ቢኖርም እንደ ስርዓተ ትምህርት አዲስ የህክምና ዶክተሮች ትምህርት በአገር ደረጃ አልተገመገመም፡፡ ሆኖም ግን የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ያስመረቃቸው የጤና ሀኪሞች ባደረጉት ውድድር ጥሩ ውጤት አስመዝግበዋል ይህንንም ቀጥተኛ በሆነ መልኩ ሳይሆን በተዘዋዋሪ የምናገኘው ነው፡፡ ከ2012 ጀምሮ ግን የሙያ ፈቃድ ምዘና ስለሚሰጥ ሀኪሞቻችን ያላቸውን ብቃት የበለጠ ለመሳካት ያስችለናል፡፡ ከእነዚህ በፊት በነበረው ውድድር ግን ከነባሮች የህክምና ትምህርት ማሰልጠኛ ዩኒቨርሲቲዎች ሳይቀር ተወዳድረን ሶስተኛ ደረጃ ወጥተናል፡፡

በህክምናው ዘርፍ እንደ አገር በዘርፉ የሚስተዋለውን ችግር ለመቅረፍ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ትምህርት ቤት ችግሩን ለመፍታት በማዕከላዊ ደረጃ የተቋቋመ ግብረ ኃይልን መሰረት ባደረገ አግባብ አንደኛ የስርዓተ ትምህርቱን ጥራት ማረጋገጥ፣ እንዲሁም የአምስተኛ ዓመት የህክምና ተማሪዎች ችግር የሚፈታ የተቋቋመ ኮሚቴ ላይ ዩኒቨርሲቲው ተሳታፊ እንደሆነ የመጡትን ግብዓቶች ተጠቅሞ በመገምገም የሚፈቱበትን አግባብ በመጠቆም አንድ ሰው መመደቡን ዶክተር ታለማ ተናግረዋል፡ ፡ እንዲሁም የጤና ተማሪዎች ጋር ውይይት በማድረግ በውይይቱ የተነሱ ሃሳቦችን በመቅረፍ ብቁ የህክምና ባለሙያዎችን ለመፍጠር እየተሰራ ነው፡፡ የቤተ መጽሀፍትና ቤተ ሙከራዎች የማስፋፋት ስራም ለመስራት መታቀዱን ዲኑ ገልፀዋል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2012 ዓ/ም አዲስ ገቢ የጤና ተማሪዎችን በአዲሱ የጤና ካምፓስ ተቀብሎ ለማስተማር ካምፓሱ የመማሪያ ክፍሎችን፣ የዶርሚተሪ ህንፃቻችን፣ ቤተ መፅሀፍት ተሰርተው ተጠናቀዋል፡፡ ካምፓሱ የቀሩት የመንገድ ግንባታ፣ ቤተ ሙከራዎች፣ የመብራትና የኢንተርኔት ዝርጋታ ያልተጠናቀቁ ስራዎች ናቸው፡፡ለዚህም በ2012 ዓ/ም ስራውን እንዲጀምር ለማስቻል ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰሩ ይገባል፡፡ የካምፓሱ ህንፃዎችም ጥራታቸው በጣም ጥሩ የሚባሉ ናቸው፡፡

የጤና ካምፓሱ መጠናቀቅ ካምፓሱ ብቻ ሳይሆን በዋናነት የሆስፒታሉ ግንባታ መጠናቀቅ ጠቀሜታው የጐላ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡የህክምና ትምህርት በባህሪው የተጨናነቀ በመሆኑ በዋናው ግቢ ሲማሩ ተማሪዎች የሚያነሷቸው የካፊቴሪያ ጥያቄን እና የጥራት ችግርን ይቀርፋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተቋሙ በራሱ ሲንቀሳቀስ የሚያድግበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በዋናነት ለዚሁ መሳካት ግን የሆስፒታሉ መገንባት አስፈላጊ ነው፡፡ ሆስፒታሉ ከተገነባ ለማህበረሰቡ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት ያስችላል፡ ፡ ተማሪዎችም በአግባቡ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ይረዳል በደብረ ማርቆስ ሪፈራል ሆስፒታል ዙሪያ የሚገኙ ሆስፒታሎች በሙሉ የመጀመሪያ ሆስፒታሎች በመሆናቸው ሪፈር የሚያደርጉት ወደ ደብረ ማርቆስ ሆስፒታል በመሆኑ ሆስፒታሉን የተጨናነቀ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ስለሆነም የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማስተማሪያ ሆስፒታል መከፈት ይህንን ጫና እንዲቀንስ ያደርገዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የጤና መምህራንም ያላቸውን ሙያ በአግባቡ ተጠቅመው ለማህበረሰቡ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ያስችላቸዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው የሚያስተምራቸው የስፔሻሊስት ሀኪሞች ትምህርታቸውን ጨርሰው ሲመጡ ዩኒቨርሲቲው ያወጣባቸውን ወጭ ሳይመልሱ ወደ ሌላ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሄዱ ይገደዱ የነበሩት እንዲመጡ ለማድረግ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡ ፡ የጤና ካምፓስ ሆስፒታል ግንባታ ዲዛይን በጣም ዘመናዊ በመሆኑ ረጅም የግንባታ ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል ዶ/ር ታለማ እምነታቸውን ገልጸዋል፡፡

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ በመሆኑ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ሙሉ በመሉ ተወጥቷል ባይባልም የጀመራቸውን ጅምሮች አጠናክሮ በመቀጠል ትርጉም ያለው የማህበረሰብ አገልግሎት በህክምናው ዘርፍ ማበርከት እንደሚገባው ተናግረዋል፡፡ የህክምና ት/ቤቱ  የ23 ሚሊዩን ብር ሲቲ ስካን ገዝቶ ለደብረ ማርቆስ ሪፈራል ሆስፒታል በመስጠቱ ብዙ ህሙማን ለሲቲ ስካን ምርመራ ወደ አዲስ አበባና ባህርዳር ይላኩ የነበር መሆኑን አውስተው ማሽኑ መገዛቱ ይህንን ማስቀረት እንደሚያችል ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል በኮንትራት ቅጥርና በት/ቤቱ ያሉ የጤና ሀኪሞች ከመማር ማስተማሩ ባሻገር ደብረ ማርቆስ ሪፈራል ሆስፒታል ላይ ለህሙማን እየሰጡት ያለ አገልግሎት ትልቅ ነው፡፡ ሆኖም ግን የህክምና ት/ቤቱ የማህበረሰብ አገልግሎቱን የበለጠ ማስፋትና ተደራሽነቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ የህክምና አገልግሎት በባህሪው ማህበረሰብ ተኮር በመሆኑ የተጀማመሩትን ተግባራት አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባ ዶ/ር ታለማ ተናግረዋል፡፡

የህክምና ት/ቤት በመማር ማስተማሩ የትምህርት ክፍሎችን የማስፋፋት፣ የድህረ ምረቃ ፕሮግራም መክፈት፣ በሆስፒታሉ የተጀመሩ ስራዎችን አጠናክሮ መቀጠል፣ በህክምናው ዘርፈ ብዙ ነገሮች ያልተጠኑ ስለሆነ ጥናትና ምርምሮችን ማድረግ እንዲሁም ፕሮጀክቶችን ቀርጾ ለማህበረሰቡ ሊያረክታቸው የሚችለውን ለይቶ መስራት እንደሚገባው የት/ቤቱ ዲንጠቁመዋል፡፡

የጤና ካምፓሱ የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ እውን እንዲሆን በማድረግ ሌሎች በአካባቢያችን የሚገኙ ጤና ጣቢያዎችንና ሆስፒታሉን ዩኒቨርሲቲው ኃላፊነት ወስዶ ስራው የሚስፋፋበትን፣ ለማህበረሰብ ተደራሽ የሚሆንበትን፣ ያስተማራቸውን ባለሙያዎች ከዚህ በፊት ጥረት ማድረግ አለበት ምክንያቱም አስተምረናቸው ወደ ዩኒቨርሲቲው የማይመጡ ስፔሻሊስት ሀኪሞች ስላሉ ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ልምድ በመውሰድ ዩኒቨርሲቲው ያስተማራቸው ስፔሻሊስት ሀኪሞች የሚቆዩበትን ነገር የማመቻቸት ስራ መስራት ይገባዋል፡፡ ደብረ ማርቆስ ሪፈራል ሆስፒታል የሚታከሙ ህሙማን ካለው እጥረት የተነሳ መሬት ሳይቀር ተኝተው የሚታከሙ ስላሉ ያንን ለመቅረፍ አብረን መስራት እንደሚገባ ዶ/ር ታለማ በአጽንዖት ተናግረዋል፡፡

# ምስለ ችሎት ውድድር ለመውጫ ፈተና ተማሪዎችን ብቁ ያደርጋል

የህግ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና በሃገር አቀፍ ደረጃ በ2003 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን የመውጫ ፈተና በስነ-ምግባር እና ብቃታቸው የተረጋገጠ የፍትህ ባለሙያዎችን ለማፍራት ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳለው ይታወቃል፡፡ ይህ የመውጫ ፈተና የሚሰጠው ከመጋቢት እስከ ሚያዚያ ባሉት ወራት ሲሆን በመጀመሪያው ዙር ሳያልፉ የቀሩት ተማሪዎች ደግሞ በድጋሚ በህዳር ወር በሃገር አቀፍ ፈተናዎች ኤጀንሲ ተዘጋጅቶ እንዲፈተኑ ይደረጋል፡፡ በዚህ ረገድ ሁሌም ቢሆን በትምህርታቸው ዝቅ ያሉ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ ፈተናውን አያልፉም፡፡ ነገር ግን ትምህርት ሚኒስቴር ይህን የህግ የመውጫ ፈተና እንደ ትልቅ ሞዴል ወስዶ በሌሎች የትምህርት መስኮችም ላይ ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል፡፡ እንደ ህግ ትምህርት ቤት አንድ የመውጫ ፈተና የወደቀ የህግ ተማሪ ምንም አይነት ውጤት የማይሰጠው ሲሆን የሚጠበቅበትን ክፍያ እየከፈለ ፈተናውን ከቀጣይ ተማሪዎች ጋር እንዲፈተን ይደረጋል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህግ ት/ቤት ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ሲነጻጸር በተማሪዎች የመውጫ ፈተናን የማለፍ ንጥጥር የተሻለ አፈጻጸም አለው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲገለፅ በ2008 ዓ.ም ከተፈተኑት ተማሪዎች 100%፣ በ2009 ዓ.ም 94% እንዲሁም በ2010 ዓ.ም 84% ተማሪዎች የመውጫ ፈተናውን አልፈዋል፡፡ ተማሪዎች የማለፍ መጠን ከአመት አመት እየቀነሰ መምጣቱንም ከአሃዙ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም የሃገር አቀፍ ፈተናን በመስጋት አብዛኛዎቹ የተሻለ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች የህግን የትምህርት መስክ መምረጥ መተዋቸው እንደሆነ የህግ ትምህርት ቤት ዲኑ አቶ አለሙ ታዬ ያብራራሉ፡፡ሌላው ምክንያት የተሻለ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች የትምህርት የጊዜ ቆይታ አጭር ወደ ሆነ የትምህርት ክፍሎች መግባታቸው የሚጠቀስ ነው፡፡ ለዚህም ችግር ሲባል የህግ ትምህርት ቤት ዲኖች በቅርቡ ባካሄዱት ስብሰባ ተማሪዎችን ሲመደቡ ጥሩ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች እንደሌሎች ትምህርት ቤቶች እና ትምህርት ክፍሎች ትኩረት ተሰጥቶ እንዲመደቡና በምደባው ወቅትም የህግ ትምህርት ቤት ዲኖች እና ተወካዮች ምደባው ላይ ተሳታፊ ሆነው አስተያየት እንዲሰጡበት ለትምህርት ሚኒስቴር ምክረ ሃሳቡ ቀርቧል፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ የመጣውን የተማሪዎች የመውጫ ፈተና የማለፍ መጠን ለማሻሻል ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚማሩትን ትምህርት በምስለ ችሎት ውድድርና በተግባር ትምህርት በማጠናከር ሊሰሩበት ይገባል፡፡




**አቶ ዓለሙ ታዬ**
**የህግ ትምህርት ቤት ዲን**

ምስለ ችሎት ማለት ልቦለዳዊ የሆነ ጉዳይ ተፈጥሮ ተማሪዎች እንደከሳሽ እና ተከሳሽ በመሆን ዳኞች ተብለው በተሰየሙ የህግ መምህራን ፊት ቀርበው ክርክር የሚያደርጉበት እና እውነተኛ የፍርድ ቤት ስርዓት አስመስለው የሚማሩበት ስርዓት ነው፡፡ ይህም በክፍል ውስጥ የተማሩትን የንድፈ ሃሳብ ትምህርት በተግባር እንዲማሩ የሚያስችል ነው፡፡ ምስለ ችሎት በአንድ የህግ ትምህርት ቤት በራሱ ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡ እንዲሁም ሃገራዊ፣ አህጉራዊና አለማቀፋዊ የምስለ ችሎት ውድድር ሊያካሂድ ይችላል፡፡ ይህንን ለማካሄድም ሁሉም የህግ ትምህርት ቤቶች የምስለ ችሎት አዳራሽ አስገንብተው ተማሪዎችን እንዲወዳደሩ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2011 ዓ.ም የመጀመሪያውን የምስለ ችሎት ውድድር አካሂዶል፡፡ ይህም ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ለሚካሄደው የምስለ ችሎት ውድድር ማጠናከሪያ ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲያችን የምስለ ችሎት አዳራሽ ባይኖርም ተማሪዎች በ2009 ዓ.ም በተካሄደው ሃገር አቀፍ የምስለ ችሎት ውድድር በቃል ክርክር 2ኛ ደረጃ ሲወጡ በፅሁፍ ደግሞ 1ኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቀዋል፡፡ በ2011.ዓ.ም በተካሄደው ምስለ ችሎት ውድድር በቃል ክርክር አልፈው የተሳተፉ ቢሆንም ያንን ያክል ውጤታማ አልሆኑም፡፡ በቀጣይ ለሚካሄዱ ውድድሮች ዝግጁ እንዲሆኑ አሰልጣኝ መምህር ተመድቦ እየተሰራ ይገኛል፡፡ እንደ አጠቃላይ ግን ለዚህ ውጤት መሳካት የምስለ ችሎት አዳራሽ አስፈላጊ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ይህ አዳራሽ ባለመኖሩ ተማሪዎችን ብቁ እና ተወዳዳሪ ለማድረግ ያስቸግራል፡፡ በመሆኑም ይህን አዳራሽ የሚመለከተው ሁሉ ተባብሮ መስራት እና ማዘጋጀት የከፍተኛ አመራሩ እና የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ሃላፊነት የጎላ ነው፡፡

# ሴትነትና አመራርነት



ሴት ወደ ማጀት ወንድ ወደ ችሎት የሚባለው ጊዜ እየቀረ መጥቷል፤ ሴትነት አደባባይ ከዋለ ሰንበትበት ብሏል፡፡ ችሎቶች የወንዶች ብቻ ሳይሆን የሴቶችም የመዋያ አደባባይ ሆነዋል፡፡ የፓርላማ ወንበሮች፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአገሪቱ ቁልፍ የሥልጣን ቦታዎች በሴቶች ተደፍረዋል፡፡ በሴትና በእናትነት መያዝ ጀምረዋል፡፡ ይህ እንደአገር የሚያሻግረን እንደሰው የሚያኩራራን የእናቶች፣ የሚስቶች፣ የእህቶች ወደ አደባባይ መምጣት ሊበረታታ የሚገባው እውነታ ነው፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በርካታ ሴት አመራሮች ወደፊት እየመጡ ይገኛሉ፡፡ በመሠረታዊና በከፍተኛ የአመራርነት እርከን ላይ ደግሞ የሴቶች ቁጥር እየጨመረ ነው፡፡ በዚህ ዓመት በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ አመራር እርከን ውስጥ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍን በምክትል ፕሬዝዳንትነት ስለምትመራው ጀግና ሴት ታሪክ ልናጋራችሁ ወደድን፡፡ ረዳት ፕሮፌሰር ገነት ደጉ የ2011 ዓ.ም የአብርሆት መፅሔት የሴትነትና አመራርነት ተምሳሌት አድርግን አቅርበናቸዋል፡፡

ሴትነትና አመራርነት ይደጋገፋሉም፤ ተግዳሮትም አለቸው፡፡ ተግዳሮቶች ሴቶች ባለብን ድርብርብ ኃላፊነት፣ ባህላዊ ጫናዎችና የአመለካከት ችግሮችን ሰብሮ ወደ ኃላፊነት ለመምጣት የዝግጁነት ማነስ ይታያል፡፡ ዘርዘር አድርገን ለማየት በሴትነታችን በቤት ውስጥ ለባሎቻችን፣ ለልጆቻችን በአጠቃላይ ለቤተሰብ የሚሠጥ ጊዜ አለ፡፡ በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ በሴትነታችን የሚጠበቅብን ሰፊ ተሣትፎ አለ፡፡ በመንግስት የስራ ኃላፊነትት ስንቀመጥ ደግሞ ራሱን የቻለ የሙሉ ጊዜ ከንጋት እስከ ምሽት ስራ ላይ በቢሮ ስራና በመስክ ስራ መጠመድ አለ፡፡ ስለዚህ እነዚህን ሁሉ አጣጥሞና አመዛዝኖ ስራን በውጤታማነት ማከናወን ይጠይቃል፡፡

በሌላ በኩል በሴትነታችን ተፈጠሮ በሠጠን ጥበብና አስተዋይነት፣ ታማኝነት፣ ጥንቁቅነት፣ ባካበትነው ክህሎት በተመሣሣይ መንግስታዊ ኃላፊነታችን ስንወጣም የሚያግዘን ሁኔታም ይፈጠራል፡፡ በዚህ ደግሞ ሴትነትና አመራርነት ይደጋገፋሉ ማለት ነው፡፡ ካለው ስር የሰደደ ባህላዊ አመለካከት ሴቶችን አሳንሶ የማየት ነገር በእኛ በራሳችን በሴቶች ዘንድ የሚፈጥረው አልችልም የሚል አስተሣሰብ ከሁለት መንገድ ሊመነጭ ይችላል፡፡ አንድም ከላይ በጠቀስሁት ስራም እንዳይጐዳ ቤተሰብም እንዳይጐዳ ከሚል በአንድ መልኩ ቤተሰብ ማስተዳደር ላይ ለማተኮር ሁለትም የተሰጠን የመንግስት ኃላፊነት በላቀ ውጤታማነት ሳይሸራረፍ ለመወጣት ካለ ጥቅል ስሜት ወደ አመራርነት ለመምጣት ዝግጅ ያለመሆን ከመጣንም በብዙ ጉትጉታ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ማህበረሰብ ከሴት አመራር የሚጠበቀው ውጤት ደግሞ በልክ ያለመሆን በጣም ከፍ ያለ መሆኑ ከወንዶች በበለጠ እንድንሠራ ይጠበቃል፡፡ ለምሣሌ እኔ የምመራው ዘርፍ አለ፡፡ ይህ ዘርፍ በወንድ ተይዞ በነበረ ጊዜ ውድቀት ቢያጋጥም ውድቀቱ የግለሰቡ /የመሪው / ብቻ ይሆናል፡፡ በሴት አመራር ተይዞ የተመዘገበ ውድቀት ግን በግል ለእኔ ብቻ ሳይሆን የሚሠጠው በወል ለሴቶች ይሆንና መጥፎ ምሳሌ መሆን ይመጣል፡፡ ለዚህ ሲባል ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ አቅምን አሟጦ ስራን በጥልቀትና በርቀት አስቦ ማከናወን ድርብ ጀግና / Double Good/ መሆንን ይጠይቃል፡፡

ዘርፉ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ስለሆነ ለብዙ የማህበረሰብ ችግሮች ቅርብ ሆነህ እንድታውቅ ያደርጋል፡፡ ከሙያ አንፃርም የጤና ባለሙያ እንደመሆኔ ለማህበረሰቡ ችግር ቶሎ ለመረዳትና ለመፍታት ትጋትና ስጉ /Sensitive/ መሆንን ይጠይቃል፡፡ ሌላው ውስብስብ ያሉ ዘርፈ ብዙ ስራዎች ይመጣሉ፡፡ ስለዚህ በትዕግስት ጥሩ አድማጭ በመሆን በፍፁም አገልጋይነት ስሜት ለመወጣት ሴትነት መልካም አጋጣሚ ነው፡፡ ሌላው በጀት ማስተዳደር ሴትነት ጥሩ ተሞክሮ አለው፡፡ ልክ ቤታችንን በምናስተዳድርበት ሁኔታ ነገሮች በትክክልና ስርዓት ባለው ሁኔታ እንዲሠሩ ያስችለናል፡፡ የሴት የወንድ የሚባል ስራ ባይኖርም ይህ ዘርፍ ግን ለሴት አመራር አቅምህንም ክህሎትህንም የምታወጣበት ከመሆኑ አንፃር በብዙ ዩኒቨርሲቲዎች ይህ ዘርፍ በሴት ምክትል ፕሬዝዳንቶች ይመራል፡፡

አንደኛው ጥሩ አርአያ መሆንን፣ ሰርቶ ማሳየትን፡፡ ከዓመታት በፊት ዲን መሆን እንኳን ለሴቶች ብርቅ የሆነበት ጊዜ ነበር፡፡ አሁን በርካታ ሴቶች ወደ መካከለኛ አመራር እንደመጡ ብቻየን ሳይሆን ከማኔጅመንቱ ጋር በመሆን መደላድሎችን ማመቻቸት፤ ሌላው ሴቶችን ለማብቃት በተለይም በተመራማሪ ሚናቸው የጐላ እንዲሆን ስልጠናዎችንና ተምሳሌት የሆኑ ሴት ፕሮፌሰሮችን በማምጣት ልምድ እንዲያካፍሉ ሴቶች እንዲነቃቁ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡ ነገር ግን በቂ አይደለም፡፡ ወደፊት የዩቨርሲቲውም ትኩረት አድርጐ የሚሠራባቸው የህፃናት ማቆያ፣ የልጆች የሰርቪስ አገልግሎት፣ ሴቶች ተረጋግተው ስራቸው ላይና ምርምራቸው ላይ እንድያተኩሩ ያደርጋቸዋል፡፡

የሚሰሩ ምርምሮች በአንድም በሌላ የሴቶችን የኑሮ ሁኔታ የሚያሻሽሉ እንዲሆኑ የሚቀረፁ ፕሮጀክቶች በአብዛኛው ሴቶች ላይ እንዲያተኩሩ ጥረት አደረጋለሁ፡፡ ለሴት ተማሪዎች በየመድረኩ በመገኘት ልምዴን፣ የህይወት ተሞክሮየን በማካፈል በዩኒቨርሲቲው ቆይታቸው ለያታዊ ጥቃት እንዳይጋለጡ ሳይንሳዊና ነባራዊ ሁኔታዎችን እያነሳን ምክር እንሠጣለን፡፡ የህይወት ክህሎት ስልጠናዎችን እንዲያገኙ በጀት ከመመደብ ጀምሮ በቀጥታ በመሳተፍ ጭምር በዚህ ኃላፊነት ከመምጣቴም በፊት ከመጣሁ በኋላ አትኩሬ የምሠራባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

በአሁኑ ሰዓት ሀገራችንና ህዝባችን በከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገኛል፡፡ በከፍተኛ ሁኔታ መፈናቀሎች፣ የሠላም እጦት፣ የከፋ ዘረኝነት እየተቸገርንባቸው ያሉ ሁኔታዎች ሲሆኑ በእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ከሌላው ማህበረሰብ በበለጠ ሴቶችና ህፃናት ቀዳሚ ተጠቂዎች በመሆናችን እነዚህ ሁኔታዎች ከአገራችን ከህዝባችን ጫንቃ ላይ ወርደው የተረጋጋች፣ የበለፀገች፣ ሠላሟ የሠፈነ አንድነቷ ከብረት የጠነከረ ሀገር እንድትኖረን ምኞቴ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ሁላችንም የሚጠበቅብንን እንድንሠራ አደራ ለማለት እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም እድሉ ስለተሠጠኝ እያመሰገንሁ በህይወቴ ውስጥ በህፃንነቴ እድሜየ የትልቅነትና የአሸፊነትን መንፈስ በህፃን ልቦናየና አእምሮየ ተክለህ እንዲበቅልና እንዲያድግ ለረዳኸው ለወንድሜ ለክፍሉ ደጉ አመሰግናለሁ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ለባለቤቴ ለአቶ መኮንን ስማኔና ለልጆቼ በትዕግስት ሁሉን ችላችሁ በስራዬ ውጤታማ እንድሆን ስላደረጋችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡በሦስተኛ ደረጃ በዩኒቨርሲቲው በአመራርነት፣ በዲንነት ከመጣሁበት መንገድ ጀምሮ በተለያዩ ሁኔታዎች ወደ ኋላ እንዳልደናቀፍ ድጋፍ እያደረጉ ለዚህ ደረጃ ላበቁኝ ዶ/ር ይልቃል ከፋለ እና ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ እንዲሁም አሁን ላሉት የበላይ አመራሮች ለሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ስለተረዳችሁኝና ስለረዳችሁኝ በእኔ ላይ ስላላችሁ እምነት አክብሮት አመሰግናለሁ፡፡

# የመጀመሪያው የሶስተኛ ዲግሪ ፕሮግራም



አሃዱ መንዝር (ዶ/ር
የድህረ ምረቃ ኮሌጅ ዲን

11 ዓመታትን ተማሪዎችን በማስመረቅ ለአገሪቱ የተማረ ዜጋ ማፍራት ረገድ ከፍተኛ የሆነ አበርክቶት አድርጓል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በአንድ ኮሌጅ የጀመረውን ትምህርት በአምስት ኮሌጆች፣ 3 ተቋማት፣ ሁለት ትምህርት ቤቶች እና ሁለት ካምፓሶች በማስፋፋት አቅሙን እያሳደገ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ሰዓት 54 የመጀመሪያ ዲግሪ፣ 41 የሁለተኛ ዲግሪ ፕሮግራሞች በቀን፣ በማታውና በክረምት መርሃ ግብር ተማሪዎችን ተቀብለው እያስተማሩ ይገኛል፡፡ በ2011 ዓ.ም ደግሞ የ3ኛ ዲግሪ ፕሮግራም በመክፈት ተማሪዎችን ተቀብሎ እያስተማረ ይገኛል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የፒ.ኤች.ዲ ፕሮግራም የተጀመረው በ2011 ዓ/ም ሲሆን የፕሮግራሙ መጀመር ዋና ዓላማ ማህበረሰቡንና የመምህራንን አቅም ለማሳደግ እንዳለመ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳንት አቶ ታደሰ ጤናው ይናገራሉ፡፡ በዚህ ዓመት የተጀመረው የሶስተኛ ዲግሪ ፕሮግራም በእንግሊዝኛ ቋንቋና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ውስጥ በ TEFL (Teaching English as foreign language) ነው፡፡ ይህ ፕሮግራም የተቋሙን ሁለንተናዊ አቅም ለማሳደግ እና የትብብርና አጋርነት ስራዎችን ይበልጥ አጠናክሮ ለማስቀጠል በተለይ የPHD ፕሮግራሞችን ማሳካት ወሳኝ እርምጃ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው በቀጣይ አመታት ተጨማሪ የሶስተኛ ድግሪ ፕሮግራሞችን ለመክፈት እየሰራ ይገኛል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ኤካስክቲቭ ዳይሬክተር ዶ/ር በለጠ ያዕቆብ በበኩላቸው ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሶስተኛ ድግሪ መርሃ ግብር ለመጀመሪያ ጊዜ በ2011 ዓ/ም በአንድ የትምህርት ክፍል በተለይም እንግሊዘኛ ቋንቋ ማስተማር ጀምሯል፡፡ ትምህርቱ የሚሰጠው ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ከዚያ በሚመጡ ሁለት መምህራን ነው፡፡

የሶስተኛ ድግሪ መርሃ ግብር ደረጃ ትምህርት መጀመሩ ዋናው አላማ የመምህራን አቅም በእውቀትና በክህሎት በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ በዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች የሚሰጠው የትምህርት ጥራት ከፍ እንዲል ከማድረጉም በላይ ሰልጣኞች የተለያዩ ችግር ፈች ምርምሮችን በማካሄድ በመማር ማስተምሩም ሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ ያሉትን ችግሮች በመፍታት የራሱን አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ታስቦ ነው፡፡በሦስተኛ ዲግሪ ደረጃ በዩኒቨርሲቲው ለጊዜው የሚሰጠው አንድ ብቻ ሲሆን አራት የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን በመማር ላይ ናቸው፡፡ በሚቀጥለው አመት ተጨማሪ የትምህርት ዘርፎችን ለመክፈት ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በተለይም ደግሞ በባዮሎጅ ትምህርት ክፍል በ Applied Entomology በሚባለው የትምህርት መስክ በ2012 ዓ/ም ለመጀመር ስርዓተ ትምህርቱ ፀድቆ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ ለጊዜው በ3ኛ ዲግሪ መርሀ -ግብር እንግሊዝኛ ቋንቋን በውጭ ቋንቋነት ማስተማር ላይ የሚገኙት አንድ ፕሮፌሰርና አንድ ተባባሪ ፕሮፌሰር ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የመጡ መምህራን ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በተለያዩ የትምህርት መስኮች ዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያሉ 3ኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ልዩ ልዩ ምርምሮችን በመስራት ላይ ስለሆኑ አቅማቸውን በማሳደግ የ3ኛ ዲግሪ መርሀ ግብሮች በተከታታይ በመክፈት ዩኒቨርሲቲው የሚሰጠውን ትምህርት ጥራት ለማስጠበቅ አቅዶ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ የእንግሊዝኛ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ተጠሪ አቶ አሰፋ ክንፈርግብ ሲሆኑ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የፒኤችዲ ዲግሪ ፕሮግራም የ3ኛ ዲግሪ መምህራንን ቁጥር ለማሣደግ ካለው ዓላማ የተነሳ ነው ብለዋል፡፡ በፕሮግራሙ የሦስተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን ከሚከታተሉ ተማሪዎች መካከል ተማሪ መንግስቱ አናጋው የፒኤችዲ ዲግሪ መርሃ ግብር በተቋሙ መጀመሩ ለተቋሙም ሆነ ለተማሪዎች መልካም ዕድል  መሆኑን በመናገር ለተቋሙ አማራጭ ብቻ ሳይሆን ተመራጭ ለመሆን የሚያደርገውን ጥረት ማስጀመሪያ ሲሆን ለኛ ለተማሪዎች ደግሞ ሙሉ ትኩረታችንን ከጥናታችን ላይ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮልናል ብሏል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስ ሂውማቲስ ኮሌጅ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ኢንዱስትሪ ትስስር ድህረ ምረቃ አስተባባሪ ዶክተር መኮነን እሱባለው የፕሮግራሙ መጀመር ለአገራዊዉ የሰው ሃይል እጥረት ለመቅረፍ የመምህራንን አቅም ለማሳደግ መልካም አጋጣሚና ጥሩ ሥራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የዚህ ፕሮግራም መከፈት ለመምህራንም መልካም አጋጣሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ትምህርቱ የሚሰጠው ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሚመጡ አንድ ፕሮፌሰርና አንድ ተባባሪ ፕሮፌሰር ሲሆን ለተባባሪ ፕሮፌሰሩ በሰዓት እየተከፈላቸው ነው የሚሰሩት የእኛ መምህራን ልምዱን ከእነሱ ወስደው ወደፊት አጠናክረን ለመስራት ነው፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ኮሌጅ ዲን ዶክተር አሐዱ መንዝር የድህረ ምረቃ ኮሌጅ የተጀመረ በ2005 ዓ/ም አጋማሽ ላይ በስድስት ትምህርት ክፍሎች በጤናና ቢዝነስ ኢኮኖሚክስ ትምህርት መስኮች ነው፡፡በአሁኑ ሰዓትበድህረ ምረቃ ኮሌጅ ውስጥ እየተሰጡ ያሉ የትምህርት ክፍሎች 41 /አርባ አንድ/ ትምህርት ክፍል እና አንድ የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ ፕሮግራም ሲሆን በሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ  ኮሌጅ ውስጥ በእንግሊዝኛ ቋንቋ  ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ውስጥ TEFL (Teaching English as a foreign language) ነው፡፡ በኮሌጁ እስካሁን በሁለተኛ ዲግሪ ፕሮግራም የምሩቃን ቁጥር ወ 460 ሴ 121 ድምር 581 ሲሆኑ የተማሪዎች ቁጥር ብዛት ወ 4047 ሴ 347 ድምር 4394 ይሆናል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በሦስት የትምህርት ፕሮግራሞች ማለትም በመደበኛ፣ በማታና በክረምት መርሃ ግብሮች እያስተማረ ይገኛል፡፡ መምህራን ልማት ላይም ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል እነዚህ ፕሮግራሞች በስምንት ኮሌጆች እየተሰጡ ነው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች የሚሰሯቸው የመመረቂያ ጽሁፎች ጥራት ከማስጠበቅ አኳያ ግብዓት ማሟላት ላይ በተለይም የመማሪያ ክፍልና ቤተ መፅሀፍት በማሟላት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት አለበት በዚህ ዙሪያ ትኩረት ሰጥተን እንሠራለን ብለዋል ዶ/ር አሃዱ መንዝር፡፡

# የቡሬ ካምፓስ ሁለገብ እንቅስቃሴዎች

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቡሬ ካምፓስ አካባቢው ካለው ከፍተኛ የመልማትና የትምህርት ፍላጎት በመማር ማስተማር፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ለማሰማራት ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ መርሃ ግብሮችን ከፍቶ እያሥተማረ ይገኛል፡፡ ከአዲስ አበባ በስተሰሜን ምዕራብ 400ኪ.ሜ እና ከባህር ዳር ከተማ 153 ኪ.ሜ ርቃ የምትገኘዋ ቡሬ ከተማ ላይ የተቋቋመው የቡሬ ካምፓስ ስራውን በይፋ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ባሉት አምስት ዓመታት ውስጥ በርካታ የማህበረሰብ ክፍሎች በትምህርት እድል ፈጠራና በሌሎች መስኮች ይበል የሚባሉ አስተዋጽዖዎችን እያበረከተ ይገኛል፡፡

በዚህ ካምፓስ የሰው ኃይልንና ግብዓትን ከማማላት፤ የመምህራንን አቅም ከማሳደግ፣ ምቹ የትምህርት አካባቢ ከመፍጠር እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ከመፍታት አንጻር መምህራንን በየአካዳሚክ ሴሚስተሩ እንደ አሰፈላጊነቱ በቅጥር እና ዝውውር እንዲሟላ ጥረት ይደረጋል፡፡ በዚህ ካምፓስ የመምህራን ፍልሰት በተለይም በአንዳንድ ትምህርት ክፍሎች ላይ ያሉ ልምድ ያላቸው መምህራን ወደ ሌላ ቦታ መዛወር በካምፓሱ ላይ በተደጋጋሚ የሚታይ ችግር ቢሆንምያሉትን መምህራን አቅም ለማሳደግ ዩኒቨርሲቲያችን የረጅምና አጫጭር ስልጠናዎች በመስጠት የመምህራንን አቅም ግንባታ ላይ ከፍተኛ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ለዚህም በ2011 ዓ.ም. ብቻ ከ30 በላይ የካምፓሱ መምህራን በ2ኛና በ3ኛ ድግሪ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር እየተማሩ ይገኛሉ፡፡ ከ120 በላይ መምህራን የምርምር እና የአመራር አቅማቸውን የሚያሳድግ እንዲሁም ለአስተዳደር እና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ከፋይናንስና ግዥ ጋር በተገናኘ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

መማር ማስተማር ዩኒቨርሲቲዎች ከተሠጧቸው ተልዕኮዎች አንዱ ሲሆን በመደበኛው፣ በማታው እና በርቀት መርሃ ግብር የተቀበላቸው ተማሪዎች ጥራት ያለው ትምህርት አግኝተው በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት ጐልብተው እንዲወጡና የማድረግ ተልዕኮውን ይወጣል፡፡ዩኒቨርሲቲው በማድረግ በልዩ ልዩ የትምህርት መስኮች በተለያየ ደረጃ ማለትም በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በሁለተኛ ዲግሪና በ3ኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ተቀብሎ እያስተማረ ሲሆን የቡሬ ካምፓስ ይህንን ተልዕኮ በመውሰድ በመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት መርሃ ግብሮችን ከፍቶ በመደበኛና በማታ ፕሮግራም እያስተማረ ይገኛል፡፡ ብቃት ያላቸው መምህራንንበማሟላት እንዲሁም ዘመኑ ከሚጠይቀው የቴክኖሎጂ እድገት ጋር በማጣጣም፣ ተማሪዎች በቂ ዕውቀት ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ፣ በምርምር እና በጥናት የተደገፈ ሥራ በመሥራት፣ በቂ ግብዓት ያላቸው የላብራቶሪ ክፍሎችን በማደራጀት፣ ለሥራ ምቹ የማድረግ የቤተ ሙከራ ኬሚካሎች እንዲሟሉ በማድረግ በ2011 ዓ.ም ውጤታማ የትምህርት ሥራ እንዲከናወን ስራ ተሠርቷል፡፡ የዚህን ካምፓስ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታ ስንመለከት ደግሞ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መስፋፋት በአንድ ሀገር አካባቢ የትምህርት ዕድል በመፍጠር፣ የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት፣ ችግር ፈች ምርምር በማከናወን፣ የአካባቢን ባህል፣ ወግና ታሪክ እንዲጠበቅ በማድረግ ከፍተኛ የሆነ ሚና አላቸው፡፡ ስለሆነም ወጣቶች በአቅራቢያቸው ከቤተሰብ ጋር በመሆን መማር በመቻላቸው ከአካባቢያቸው ርቀው በመሄዳቸው ይደርስባቸው ከነበሩ ከልዩ ልዩ ተግዳሮቶች መታደግ ችሏል፡፡ በርካታ የአካባቢው ማህበረሠብ በጊዜያዊ እና በቋሚ ሠራተኛነት በመቅጠርም ካምፓሱ ከፍተኛ ጠቀሜታ አስገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በግልና በጋራ በመደራጀት በአገልግሎት ዘርፉ በመሠማራት የመዝናኛ፣ የምግብና ሌሎች ሥራዎች እንዲሰሩ በማስቻል ካምፓሱ በርካቶችን ተጠቃሚ አድርጓል፡፡

ምቹ የስራ አካባቢ ከመፍጠር አንፃር በቡሬ ካምፓስ የተካሄደው የማስፋፊያ ግንባታ የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ፣ ከ480 በላይ የተማሪዎች የማደሪያ ክፍሎች፣ ከ75 በላይ የመማሪያ ክፍሎች ተጠናቀዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በማታው የትምህርት ፕሮግራም ለሚማሩ ተማሪዎች ለኪራያ የሚወጣን ወጭ ከማስቀረት በላይ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር የሚያጋጥሙ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቀነስ ተችላል፡፡

የቤተ-መፅሐፍት፣ የውስጥ ለውስጥ መንገድ፣ የውሃ መስመር ዝርጋታ እና የመፀዳጃ ቤት የመሳሰሉት ደግሞ እየተገነቡ ይገኛሉ፡፡ አሁንም ግም በካምፓሱ ውስጥ የሚያስፈልጉ የቤተ-ሙከራ ማዕከላት የአይሲቲ ፋሲሊቲዎችን እና የመሳሰሉት ተጨማሪ የመሰረተ-ልማት ግንባታዎች በዕቅድ ተይዘው ወደ ሥራ እየተገቡ ይገኛሉ፡፡ የቡሬ ካምፓስ በቡሬ ከተማ ላይ መከፈቱ በጥናትና ምርምር፣ በግንዛቤ ፈጠራና የአቅም ግንባታ በስልጠና፣ በቁሳቁስ ድጋፍ፣ በቴክኖሎጂ ድጋፍ እና በመሳሰሉት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያበረከተ እንደሆነ ነዋሪዎች ገልፀዋል፡፡

በተጨማሪም የተግባር ትምህርትን በመምራትና በመከታተል፣ የተሻለና የተሟላ የመማር ማስተማር አካባቢ ለመፍጠር መሠረተ-ልማት፣ ቤተ-መሐፍት፣ ውሃ፣ መብራት እና የመሣሠሉትን በማሟላት ላይ ይገኛል፡፡ የተግባር ትምህርቶችን በተጠናከረ መልኩ እንዲሰጥም የኢንዱስትሪ-ዩኒቨርሲቲ ትስስር በማካሄድ በእንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኙ የቡሬ ካምፓስ ዲን ዶ/ር ፀበሉ አባይነህ ተናግረዋል፡፡

የቡሬ ግቢ ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት፣ የማህበረሰቡን ችግር ያማከለና የተጠና አገልግሎት በመስጠት፣ ወቅታዊ ችግር ፈች ጥናቶችን በመስራት፣ የአካባቢውን ሃብትና ማህበረሰብ እንደሃብት/እሴት በመቁጠር የተሻለ ልማት የሚረጋገጥበት ዕውቀት የሚገበይበት ቅንነት በተሞላበት መንፈስ መፍትሔ የሚፈለግበትና ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚደረግበት ተቋም ነው፡፡

የትምህርት አሰጣጡ ውጤታማ እንዲሆን (በክፍል ውስጥና ውጭ) የተሰራበት አግባብ/ስትራቴጂ፣ ወደሌሎች ለማስፋትም የጊዜ አጠቃቀም፣ የማስተማሪያ መንገድ፣ ምዘና፣ በተግባር የተደገፈ እንዲሆን በማድረግ ይህንንም በተዋረድ በዲን፣ በምክትል ዲኖች በአካዳሚክና በትምህርት ክፍል ካውንስሎች፣ በሱፐርቪዥን ቡድን ከተማሪዎች ተወካዮች ጋር በቅንጅት ክትትል ይደረጋል፡፡ ወደፊትም አሁን በእጥረት ውስጥ ያሉንን መልካም ነገሮች በተደራጀና በተሟላ እንዲሁም ሰላማዊ ሂደቱን በጠበቀ መልኩ ማስቀጠል ይጠበቃል፡፡









## የቡሬ ካምፓስ የማህበረሰብ አገልግሎት እንቅስቃሴዎች

በመማር ማስተማር የስራ እንቅስቃሴ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ለመጡለት ዓላማ ቆመው የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ካምፓሱ እያበረከተ ያለውን ሚና ስንመለከት ከላይ እንደተገለጸው መምህራንና ተማሪዎች ጊዜያቸውን ለመጡለት አንድ አላማ ላይ እንዲያሳፉ በማድረግየካምፓሱ ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲው ኮሌጆች በተደጋጋሚ ከፍተኛ ውጤት ማስመዘገባቸው እና የዋንጫ ተሸላሚ መሆናቸው ማሳያ ነው፡፡ የቡሬ ካምፓስ በአካባቢው ካሉ ውስን ተቋማት ጋር በተግባር ትምህርት ዙሪያ በጋራ እንሰራለን ፡፡ እነዚህም ተቋማት ቡሬ ፖሊ ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ፣ ግብርና ጽ/ቤቶች፣ ሞሀ ለስላሳ መጠጦች ፋብሪካ ፣ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒየኖች፣ የግል የእርሻ እና የአትክልት ጣቢያዎች ወዘተ የካምፓሱ ዋና ዋና አጋሮች ናቸው፡፡

በአሁኑ ሰዓት በቡሬ ካምፓስ በመጀመሪያ ድግሪ በመደበኛ 10 በማታው 4 በርቀት 3 የትምህርት ፕሮግራሞች ያሉ ሲሆን በቀጣይ 6 አዳዲስ ፕሮግራሞችን ለመጀመር በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡ የትምህርት ክፍሎችን ስንመለከት በአሁኑ ሰዓት የቡሬ ግቢ በአግሪ ቢዝነስና ሰፕላይ ቼይን፣ ሆሪቲካልቸር፣ ማኔጅመንትና ፋይናንስ፣ እጽዋት ሳይንስ፣ እንስሳት ሳይንስ፣ ተፍጥሮ ሃብት አያያዝ፣ ኢክኖሚክስ፣ ጀኔራል ፎርስትሪ እና ኮምፕዩተር ሳይንስ በ10 የትምህርት ክፍሎች በመደበኛው የመጀመሪያ ድግሪ እየሠጠ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለማታው የመጀመሪያ ድግሪ አካውንቲንግና ፋይናንስ፣ ማኔጅመንት፣ ሲቪል እንጅነሪንግ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ፣ ሚድዋይፈሪ፣ ነርሲንግ፣ እና የጤና መኮንን በማስተማር ላይ ነው፡፡

በሁለተኛ ድግሪ በማታው መርሃ ግብር 11 ፕሮግራሞች ይሰጣሉ እነዚህ ፕሮግራሞች

አግሮ ኢኮኖሚክስ፣ ኢሪጌሽን፣ እንስሳት ሳይንስ፣ አካውንቲንግና ፋይናንስ፣ ማኔጅመንት፣ ሂሣብ፣ እንግሊዝኛ (TFEL) እና አማርኛ ይገኙበታል፡፡ በቀጣይም በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ሥርዓተ-ትምህርት በመቅረፅ የትምህርት ተደራሽነትን እያሳደገ ይቀጥላል፡፡

በምርምር ዘርፍ በ2011 የተከናወኑ ዋናዋና ተግባራትን ሲታዩ የምርምር ክለሳ ኮሚቴ በአዲስ መልክ እንዲዋቀር በማድረግ 12 የምርምር ትልመ ሃሳቦች በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ቀርበው አራቱ ወደ ምርምር ገብተዋል፡፡ ከዚህ መካከል አንደኛው ከመሬት አስተዳደር ጋር በጋራ እንዲሰራ ሲደረግ አንዱ ጥናት ወደ ቴክኖሎጅ ሽግግር እንዲቀረብ በማድረግ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተመራማሪዎችን አቅም ለማጎልበት ይረዳ ዘንድ ለ109 መምህራን የምርምር አቅማቸውን ለማጎልበት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ከተልዕኮዎች አንፃር የቡሬ ካምፓስ የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እየታገዘ በምርምርና ቴክኖሎጂ ዘርፍ በርካታ እንቅስቃሴዎችን አድርጓል፡፡ በዚህ ረገድ ቡሬ ካምፓስ በፍላጎት ላይ የተመሠረተና ችግር ፊች ጥናትና ምርምር በማካሄድ ከማስተማር ስራ ጎን ለጎን የምርምር ውጤቶችና ቴክኖሎጂዎች እንዲፈጥሩ በማድረግ አዳዲስ የምርምር ውጤቶችና ቴክኖሎጅዎች እንዲፈልቁ፣ የምርምር ሥራዎች ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲሰሩ እያደረገይገኛል፡

በቡሬ ካምፓስ እስካሁን በቁጥር 17 የሚደረሱ የምርምር ስራዎች እየተሰሩና በመሰራት ላይ ቢሆኑም ወደ ህብረተሰቡ የማድረስ ሥራዎች ገና በሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ በበርበሬ ዙሪያ ላለፉት ሁለት ዓመታት በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ሲሆን ከአራት ወረዳዎች ለተወጣጡ አርሶ አደሮችና ባለሙያዎች የሞላስስ ብሎክ (የተሰሻሻለ መኖ) ቴክኖሎጅ እንዲሸጋገር ተደርጓል፡፡

የምርምር ስራዎች በብዛት ተጠናክረው ጥራታቸውን ጠብቀው ችግር ፊች ሆነው እንዲዘጋጁ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በምርምር ስራዉ ለመመራመር የሚያስችሉ ሁኔታዎች በዩኒቨርሲቲውም ሆነ በካምፓሱ እየተሻሻሉ የመጡ ቢሆንም ያጋጠሙ ችግሮችም አሉ፡፡ ምርምርን እንደ መደበኛ ተልዕኮ በቂ ትኩረት አለመስጠት፣ የስታፍ ፕሮፋይል፣ ከተቋማት ጋር ያለው ትስስር አለመጠናከር፣ የተመራማሪዎች የራስ ምልከታ ችግር፣ የኢንተርኔት አገልግሎት ውስንነት፣ በተደጋጋሚ የሚታዩ ችግሮች ናቸው፡፡

በማህበረሰብ አገልግሎት የአካባቢው ነዋሪዎች ፣ የመንግስት አካላት፣ ባለሀብቱና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ለግቢው ያላቸው እይታ በጣም ጥሩ ሊባል የሚችል ነው ፡፡ ምክንያቱም ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለእነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ጥያቄ ተገቢውን መልስ እየሰጠ ይገኛል፡፡ካምፓሱ ቡሬ በመከፈቱ ለሶስት ዞኖች የትምህርት እድል የፈጠረው፣ በተለይም እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ሳይከፈት፣ በዚህም ብዙ ዜጎች የትምህርት ዕድል በአቅራቢያቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችሏል፡፡ የስራ እድል ፈጠራን በተመለከተም የቡሬ ካምፓስ ከ400 በላይ ለሆኑ ዜጎች ቋሚና ጊዜዊ የስራ ዕድል ፈጥሯል፡፡ከከተማዋ እድገት አንጻር እንደነዚህ ዓይነት ተቋማት በአንድ አካባቢ መከፈት ከተመሰረቱበት ዓላማ ና ሀገራዊ ፋይዳ በዘለለ ለአካባቢው ትልቅ መነቃቃት ይፈጥራሉ፡፡ ስለሆነውም ካምፓሱ በመደበኛወና በማታው መርሃ ግብር ከ3300 በላይ ተማሪዎችን በማስተናገድ ከፍተኛ አሰተዋጽኦ እያበረከተ ነው ፡፡

ካምፓሱ የተለያዩ ግብዓቶችንና አገልግሎቶችን ከንግዱ ማህበረሰብ የሚፈልግ ቢሆን የንግዱ ማህበረሰብ ተሳትፎ ግን ደካማ ሊባል የሚችል ነው፡፡ ለዚህ እንደትልቅ ማሳያ የሚሆነው ለተማሪዎች ስጋ አቅራቢ ጠፍቶ ለግማሽ ዓመት ከዋናው ግቢ በማመላለስ አገልግሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም የቡሬና አካባቢው የንግድ ማህበረሰብ ከካምፓሱ በርካታ የአገልግሎት ሥራዎች ላይ መሳተፍ እንዲችሉ በቅርበት ተወያይቶ በጋራ መስራት ያስፈልጋል፡፡በ2011 ዓ.ም የቡሬ ካምፓስ ከ21 በላይ የማህበረሰብ አገልግሎቶች የተሰጡ ሲሆን በዚህ ዓመት ብቻ በቢዝነስ ፕላን ዝግጅት ስልጠና፣ የኔትወርክ ዝርጋታና ኮንፊግሬሽን፣ የፒች ትሪ ”peachtree” በተግባር ተደገፈ የስልጠና ፣ በግብርና ምርት ግብይት፣ ትስስርና በማህበራት ተግባር ፣የስራ ፈጠራ ስልጠና ፣ የዶሮ እርባታ ስልጠና፣ “operating personal computer” ስልጠና ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ዙሪያ ስልጠናና የሰው ሃብት መረጃ ዳታ ቤዝ ሲስተም ለሴክተር መስሪያ ቤቶች ተሰርተዋል፡፡

## በጎ ሃሳብን ለማበልፀግ የተቋቋመው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የበጎ ሃሳብ ማዕከል

የታሪክ ሒደት ከትውልድ ወደ ትውልድ ተያያዥ እንጂ በአንድ ቦታ ወይም በአንድ ዘመን ላይ የሚቆም አይደለም፡፡ ትናንታችን ከነገ ጋር በዛሬ አማካኝነት የተገናኘ ነው፡፡ ዛሬን ያለ ትናንት፣ ነገንም ያለዛሬ ማሰብ አንችልም፡፡ የየትኛውም ሀገር ትውልድ ቢሆን ከትናንት በቀጥታ ወደ ነገ የተሸጋገረ የለም፤ ወደፊትም አይኖርም፡፡ ከትናንት በጎ ነገር አምጥቶ ዛሬን ይሠራል፤ ዛሬ ላይ ሆኖ ደግሞ ነገን ከዛሬ የተሻለ አድርጎ ለመሥራት ይጥራል፡፡ በሰዎች ዓለም ውስጥ ትናንትም ሆነ ነገ የሌሉት ዛሬ የለም፡፡

ለሰው ልጅ በተፈጥሮ የተሰጠው ማሰቢያና መመራመሪያ አእምሮ እንጂ አስቀድሞ የተወሰነ ዕጣ ፈንታ አይደለም፡፡ የማሰብ አቅሙን ተጠቅሞም ወደፊት የሚደርስበትን ግብም ሆነ ወደዚያ የሚደርስበትን መንገድ መፍጠር ይችላል፡፡ ሰው በምክንያታዊነት የሚያስብ ስለሆነ ለሚያደርገው ነገር ሁሉ አስቀድሞ ያስባል፤ ጥቅሙንና ጉዳቱን ይመዝናል፡፡ ሲጠየቅም ያስረዳና ያሳምናል ወይም ደግሞ ስሕተት ከሆነ ያምናል፡፡ በየጊዜው የምንሰማቸውና የምናያቸው የፈጠራ ግኝቶች የሰው ልጅ የሐሳቡ በረከቶች ናቸው፡፡

ራሽያዊው የሥነ ልቡና ሊቅ ቪጎትስኪም የሰዎችን የዕውቀት ደረጃዎች በሦስት ይከፍለዋል፡፡ የመጀመሪያውን እውናዊ ዞን (Actual Zone) ይለዋል፡፡ ይህ ማለት ማንኛውም ሰው አሁን ያለበት የዕውቀት፣ የአመለካከትና የክህሎት ደረጃ ማለት ነው፡፡ እንስሳት ምንጊዜም የሚኖሩት በዚህ ዞን ውስጥ ነው፤ እስከጊዜ ሞታቸው ድረስ በዚሁ ዞን ተወስነው ይኖራሉ፤ እድገት ወደሚያሳዩበት ወደ ሁለተኛውና መካከለኛው ዞን (Proximal Zone) አይሄዱም፡፡ ለዚህ ነው ቪጎትስኪ "እንስሳት ከሰው በተለየ መካከለኛ የሚባል ዞን የላቸውም" የሚለን፡፡ የሰው ልጅ ግን እንዲህ አይደለም፡፡ ከቀን በቀን ውሎው፣ ከሰዎች ጋር በሚያደርጋቸው መስተጋብሮች፣ በሚያነባቸው መጻሕፍት፣ በሚያደርጋቸው ክርክሮች፣ በትምህርት፣ ወዘተ የተነሣ ዛሬ ካለው ዕውቀት፣ አመለካከትና ክህሎት ወደተሻለ የመሔድ ብቃት አለው፡፡ ይህን የሚያደርገውም ከእንስሳት በተሻለ መልኩ ማሰብ በመቻሉ የተነሣ ነው፡፡ የሰው ልጅ ዛሬ ካለበት ደረጃ የመሻት እጁን እየዘረጋ ነገ ላይ ሲደርስ ነገን ዛሬ ያደርገውና ሌላ ነገ ይፈጥራል፡፡ የሰው ልጅ ሁልጊዜም ሊደርስበት የሚሻውን ቦታ ነው ቪጎትስኪ እምቅ ዞን (Potential Zone) የሚለው፡፡ ይህ ሦስተኛውና የመጨረሻው ዞን ለሚያስቡና ለሚመራመሩ የሰው ልጆች ብቻ የተሰጠ ልዩ ሀብት ነው፡፡ ይህ ዞን ዕቅድ ለሚያወጡና ርእይ ላላቸው ፍጡራን ብቻ የተሰጠ ነው፡፡ በመንፈሳዊው ዓለም ይህ ዕውቀት ለመላዕክት የተሰጠ ዕውቀት ነው፤ ሁልጊዜም እውናዊ፡፡ የመላእክት ዕውቀት አንድ ጊዜ የተሰጠ የማይጎድል ስለሆነ ትምህርት ቤት መግባት፣ መማር፣ መጽሐፍ ማንበብ፣ መከራከር፣ መወያየት፣ ወዘተ የለባቸውም፡፡

የስኬት መለኪያው መድረሻው ራሱ አይደለም፤ ደስ የሚያሰኘው ወደዚያ የመሔጃ መንገዱ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የሰው ልጅ ሐሳቡን የሚያንጸባርቅባቸውና የሚያሳድግባቸው የተለዩ የሐሳብ መፈተኛ ቤተ ሙከራዎች (Thought Experiment Laboratories) ያስፈልጉታል፡፡ እነዚህ መካናት በመደበኛም ሆነ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ለሰው ልጆች የተሻለ ሐሳብ ማበልጸጊያነት ይውላሉ፡፡ ነገር ግን በሀገራችን እንደ ትምህርት ቤቶች ብዛትና እንደ ባህላችን እምቅነት በሚገባ የሚያስቡ ዜጎች አሉን ለማለት አያስደፍርም፡፡

ከዚህ አንጻር ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በሃዲስ ዓለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም ስር "ሰው መሆን የበጎ ሐሳብ ማዕከል" የሚል ጽህፈት ቤት "የበጎ ሐሳብ ጽ/ቤት" (Office for Good Ideas) ጥር 04/2011 ዓ.ም አቋቁሞ የቀደምቶቻችንን ታሪክ፣ ትውፊት፣ ፍልስፍና፣ አጠቃላይ አኗኗርና ባህል አሁን ላይ ሆነን ለመዘከርና ነገን ከዛሬ የተሻለ አድርገን ለመፍጠር እየሰራ ይገኛል ፡፡



አቶ ይኩኖአምላክ መስፍን
የበጎ ሃሳብ ማዕከል ኦፊሰር

በጎ ሐሳብ የጋራ ጥረት ውጤት ነው፡፡ ማንኛችንም ብንሆን አንድን ነገር ብቻዬን ሠራሁት ልንል አንችልም፡፡ የዚህን ማዕከል አመሰራረት በተመለከተ የማዕከሉ መስራች እና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህር ከሆኑት ከአቶ ምንዋጋዉ ተመስገን ጋር አብርሆት መፅሔት ቆይታ አድርጋለች፡፡ ማእከሉ "ሰው መሆን የበጎ ሐሳብ ማእከል (BEING Center of Good Ideas)" የሚል ስያሜ ይዞ የተቋቋመ ነው ፡፡ ይህም ማለት በማእከሉ ውስጥ በተለያዩ መድረኮች እየተነሡ ውይይትና ክርክር የሚደረግባቸው ጉዳዮች ዘመንና ቦታ የማይገድባቸው ስለሆኑ ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ የትናንት፣ የዛሬና የነገ ተብለው ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡ ከቦታ አንጻርም የዚህና የዚያ ሆነው ከሀገር ውስጥ አንሥቶ በውጭ ሀገር እንዲሁም ከሚታየው ግዙፍ ዓለም እስከ ረቂቁ ዓለም ድረስ ይሆናል፡፡

በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ለአንድ ነገር እውን መሆን የብዙ አካላት አስተዋጽዖ ያስፈልጋል፡፡ ብቻዬን ሠራሁት የምንለው አንዳች ነገር ካለ ያ ነገር ያልተሠራ መሆን አለበት፡፡ ሐሳብም እንዲሁ ነው፡፡ ሐሳብ ያለ ሰው ሰውም ያለ ሐሳብ አይኖርም፤ ማእከሉም "ሰው መሆን የበጎ ሐሳብ ማእከል" መባሉ ለዚህ ነው፡፡ ሰው ከቁሳዊ ሀብትና ከሚታይ ክብር ተለይቶ በማንነቱ ላይ ከሠራ ነገን የተሻለ ያደርጋል፡፡

ማሰብ ማለት ከዕለት ጉርስና ከዓመት ልብስ በዘለለ ለትውልድ የሚተርፍ አኩሪ ታሪክ ሠርቶ ለማለፍ የሚደረግ ልዩ ጥረትን የሚጨምር ነው፡፡ ሰው ጥሩ አሳቢ ነው የሚባለው ከራሱ አልፎ ለሌሎች መኖር ሲጀምር እንደሆነ የዓለማችን ታላላቅ ሰዎች ከምንላቸው ሕይወት መማር እንችላለን፡፡ በመሆኑም ይህን ከራስ በላይ የማሰብ ክሂሎት የሚያበለጽጉ ተቋማት ማቋቋም አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ግዴታም የሆነበት ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡

የስያሜው ሐሳብ የተወሰደው ያዕቆብ ራንድና አብርሃም ጄ. ታንንባውም (Yaacob Rand and Abraham J. Tannenbaum) እንዲሁም ራስል ኤች. ህቮልቤክ (Russell H. Hvolbek) ከገለጹት የሰው ልጅ ሦስት ባሕርያት ውስጥ ነው፡፡ እነዚህም መሆን፣ ማግኘትና መሥራት የሚሉ ናቸው፡፡ መሆን (Being) ስንል ውስጣዊ ሰላም የሰፈነበት፣ በጸጋ የተትረፈረፈ ሕይወትን ገንዘብ ማድረግ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ይህም በጎ ከማሰብ ይመነጫል፡፡ ማግኘት (Having) ደግሞ ቁሳዊ ሀብትን፣ ግለሰባዊና ማኅበራዊ ዕውቅና ማግኘትን ዓላማ ደረገ ነው፡፡ ዲግሪ ያላቸው ነገር ግን ካላቸው ዲግሪ በታች የሚያስቡ ዜጎች የሚፈጠሩትም በዚህ ታዋቂ መሆንን ብቻ ትኩረት ከማድረግ የሚመጣ ነው፡፡ መሥራት (Doing) ግን ከሁለቱም ይለያል፡፡ በአካባቢና ማኅበረሰብ ውስጥ ንቁ ሚና እየተጫወቱ ራስን፣ ቡድንንና ጠቅላላ ማኅበረሰብን ብሎም ሀገርን ወደላቀ ደረጃ ማድረስን ግብ ያደረገ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ግን ማሰብ አስፈላጊ ነው፡፡ ማሰብ ብቻ አይደለም፤ በጎ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ በጎ ሐሳብ ደግሞ በጎ ተግባርን ያስገኛል፡፡ እንዲህ እያለ በጎው ሐሳብ የሚወልደው በጎ ተግባር (Doing) ግለሰብን፣ ቡድንን፣ ማኅበረሰብን፣ ሀገርን ብሎም ዓለምን በጎ የማድረግ ዐቅም ይኖረዋል፡፡ መሆን (Being) የሚለው ለማእከሉ መጠሪያ የሆነውም ለዚህ ነው፡፡

የማእከሉ መመሥረት ዓላማ በአብዛኛው በሀገር ደረጃ ብዙ ማሰብና ሀገር መገንባት የሚጠበቅበት ወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል የጥፋት ሰለባ ሲሆን ይታያል፡፡ እንደሚገባ ማሰብ ባለመቻሉም ጥፋት ያሰቡ ሁሉ እንደፈለጉ የሚልኩት እስከመሆን ደርሷል፡፡ ሰው ማሰብ ሲችል "እንዴት? ማን? ምን? ለምን? የት? ወዴት? መቼ?" የሚሉ ወሳኝ ጥያቄዎችን ይጠይቃል፡፡

ማእከሉ በሐሳብ የበላይነት የሚያምንና በሥነ ምግባር የተገነባ ዜጋ ለመፍጠር ከመጣር ውጭ በየትኛውም ሃይማኖታዊም ሆነ መንግሥታዊ አሠራር ውስጥ ጣልቃ አይገባም፡፡ የሚነሡት ሐሳቦች ሁሉ እያንዳንዳችንን በበጎ መንገድ እንዲነኩን ማድረግ ፤ሰላምና መረጋጋት ለመፍጠር፣ ዲሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ እንዲኖረን ለማድረግ፣ ሀገር በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና በማኅበራዊ ጉዳዮች የላቀች እንድትሆን በምክንያት የሚያስቡ ዜጎች ያስፈልጓታል፡፡ መልካም ዜጎች ደግሞ በሒደት የሚፈጠሩ እንጂ በአንድ ሌሊት እንደመና ከሰማይ የሚወርዱ አይደሉም፡፡ የበጎ ሐሳብ ማእከላትን መመሥረት ዋና ዓላማውም ይኼው ነው፡፡

በመሆኑም ማእከሉን ማቋቋም በዋናነት መልካም ዜጋን ለመፍጠር የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች የማስፈጸሚያ መንገዶች ተቀምጠዉለታል፡፡

- ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ የተማሪዎችን ሥነ ጥበባዊና ሌሎች ልዩ ልዩ የፈጠራ ዐቅምና ችሎታ ያላቸውን ዜጎች ተሰጥያዋቸውን አውጥተው እንዲጠቀሙበት የሚያስችሉ መድረኮችን መፍጠር

- የትምህርት ተቋማት የውይይትና የክርክር መድረኮች እንዲዘጋጁ ለማድረግ የበጎ ሐሳብ ክበባትን ማቋቋም

- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን በማሰባሰብ በየአካባቢያቸው ያሉትን በጎ የሕይወት ተሞክሮዎች አውጥተው እንዲጠቀሙ በማድረግ ከግጭት መንሥኤነት ይልቅ የሰላም ምንጮች እንዲሆኑ ማስቻል

- የትምህርት ሂደቶችና የመሳሰሉት ለትውልዱ የሐሳብ ማሳደጊያነትና የመልካም ምግባር መገንቢያነት እንዴት እንደሚጠቅሙ ማሳየት ሁሉን አቀፍ ጠቃሚ እሴታቸውን ብቻ መውሰድ ::

- ምርቃቶች፣ ቀረርቶዎች፣ ፉከራዎች፣ ምሾዎችና ዘፈኖች ለትውልድ ቅብብሎሽ ያላቸውን ሚና ማስተዋወቅና እምቅ እሴታቸውን አውጥቶ መጠቀም

- የአደባባይ ንግግሮች (Public Speeches) እንዲካሔዱ በማድረግ እንዴት በሐሳብ አሸንፎ መሪ መሆን እንደሚቻል ዴሞክራሲያዊ ባህልን ለወጣቱን ትውልድ ማለማመድ

- በአንድ ነገር ላይ ሰፋ ያለ ዕውቀት አላቸው የሚባሉ ባለሙያዎችን ጋብዞ ውይይት እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት

- በየዘመኑ የሚፈጠሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን (ፌስቡክ፣ ትዊትር፣ ኢንስታግራም፣ ቴሌግራም፤ የቪድዮና ፊልም ቴክኖሎጂ፤ አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ፤ ወዘተ) ከማኅበረሰቡ የኑሮ ሁኔታ ጋር እንዴት ሊገናኙ እንደሚችሉ መላ የሚፈጥሩ መድረኮችን ማመቻቸት

- በሐሳብ አሸንፎ መሪ መሆን ባይቻል በሥርዓት መመራትም ሌላው የሐሳብ ልዕልና ውጤት ስለሆነ ይህን የእርስ በርስ መስተጋብርና መገናዘብ ጠብቆ መዝለቅ እንዴት እንደሚቻል ትውልዱን ማስተማር



የማዕከሉ ምስረታ የምክክር መድረክ በከፊል





- ዜጎች መጻሕፍትንና ተፈጥሮን የማንበብ ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የመጻሕፍት ንባብ ዳሰሳዎችን ማካሔድ

- በሀገር በቀል ፍልስፍናዎችና ፈላስፎች ላይ ያተኮሩ ጥናትና ምርምሮች እንዲካሔዱ ማድረግ

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያስተምሩ መምህራን ያላቸው የትምህርት ደረጃና የሙያ ስብጥር (Multidisciplinarity) ከአስተሳሰብ ዕድገት ጋር ተያይዞ እንዲቀርብ፣ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ወደከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመጡ ተማሪዎች ይዘውት የሚመጡትን ወግና ባህል ለሌሎች እንዲያካፍሉ:: ማእከሉ የተቋቋመው በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞችና ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ውስጥ የተለያዩ የእምነት፣ የትምህርትና የማኅበራዊ አገልግሎት ስላሉ ለእነርሱ እንዲሆን ታስቦ ነው፡፡

በዚህም መሠረት ክርክሮች፣ ሕዝባዊ ንግግሮች፣ ሥነ ጽሑፎች፣ ትችቶች፣ የውሎ ዘገባዎች፣ የሕይወት ተሞክሮዎችና ገጠመኞች፣ ወዘተ እየቀረቡ ባህል እንዲሆኑ ቢደረግ በሒደት በምክንያት የሚያምንና በምክንያት የሚያሳምን መልካም ዜጋ እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ ለዚህም ሀገር በቀሉ ባህላችን ያለው ያልተነካ ሀብትን መጠቀም መልካም አጋጣሚ ነው፡፡

የበጎ ሐሳብ ማእከሉ ያስቀመጣቸው ዓላማዎች የሚፈጸሙት በዋናነት በበጎ ፈቃድኝነት ስለሆነ ሥራውን በኃላፊነት የሚያስተባብሩ የተወሰኑ የሥራ አስፈጻሚ አባላት ያስፈልጉታል፡፡ ይህም ማለት የማእከሉን ዓላማ ለማስፈጸም ከገንዘብ ነጻ ሆነው የሚያስቡና በተለይም ጊዜያቸውን ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑ አካላት ማለት ነው፡፡ በአስተባባሪነት የሚቀመጡት ሰዎች ጊዜያቸውን ለትውልድ መልካምነት የተከፈለ ዐሥራት አድርገው እንዲያስቡ ይጠበቃል፡፡

ማእከሉ በበጎ ፈቃድ በማኅበረሰብ የአስተሳሰብ ለውጥ ላይ የሚሠራ በመሆኑና ዓላማውንም ስለሚጋራ ሥራዎቹን ሁሉ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ርእይና ተልእኮ አንጻር የተቃኘ ነው፡፡ በተጨማሪም የበጐ ሃሳብ ማዕከል ኦፊሰር አቶ ይኩኖአምላክ መስፍን የማዕከሉን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በተመለከተ ሃሳባቸውን አጋርተውናል፡፡

ማእከሉ በሁለት በጎ አሳቢ ግለሰቦች /መምህር ምንዋጋዉ ተመድገን እና ተማሪ ዋሴ ደሴ ሃሳብ አማካይነት የተቋቋመ ማእከል እንደሆነ አስረድተዋል፡ ፡ በበጐ ሃሳብ ማዕከሉ የዩኒቨርሲቲዉ አመራሮች እና ሰራተኞች በትምህርት በምግባር፣ በጥበብ፣ በዉይይት፣ በንባብ ባህል፣ በምክንያታዊነት አንድነት እና ሰላም ግንባታ ላይ ሊያበረክቱት የሚችለዉን ገንቢ ሚና በመገንዘብ ማእከሉ ተቋቋሟል፡፡

ማእከሉ ሲከፈት የያዘዉ አላማም እንደ ማህበረሰብ ያለብንን ሃገራዊ እና ተቋማዊ ክፍተቶች ለመሙላት በሚል ነዉ፡፡ ብዙ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ክፍተቶች መነሻ ምንጩ ተቀራርበን ካለመነጋገር፣ ካለመወያየት በሃሳብ የበላይነት ካለማመን፣ በራስ ወዳድነት እና ካለማወቅ የሚመጣ ነዉ፡፡

ለዚህ ነዉ የጥንቱ የግሪክ ፈላስፋ የክፋትና የተንኮል ምንጩ አለማወቅ ነዉ የሚሉት፡፡ የሰዉ ልጅ ብዙ ባወቀና በተማረ ቁጥር የበለጠ ትሁትና በጎ አሳቢ ይሆናል፡፡

ዩኒቨርሲቲው የእውቀት፣ የጥበብ፣ እና የሳይንስ ማዕከል እንደመሆኑ መጠን እና በዉስጡ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ዜጎች (መምህራን፣ ተማሪዎችና ሰራተኞች) የሚገኙበት ተቋም ከመሆኑ አንጻር የማእከሉ መከፈት በጎ ሚና እንዳለዉ ገልጸዋል፡፡

ማእከሉ ዩኒቨርሲቲዉ ማስተማር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ክዋኔ ሊያሳልጥ በሚችል መልኩ የሚከተሉትን አንኳር የትኩረት አቅጣጫዎች ለይቷል፡፡ ተማሪዎችና መምህራን በትምህርታዊ፣ ሃገራዊ፣ ታሪካዊና ስነ-ምግባራዊ እና ጥበባዊ ጉዳዮች ላይ ነጻ እና ምሁራዊ ዉይይት እያደረገ፣ ተጋባዥ እንግዶችን እየጠራ፣ ጠያቂ፣ ምክንያታዊ እና አንባቢ ትውልድ ለመፍጠር ጥረት ያደርጋል፡፡

በጐነትን ምሁራዊና ሞራላዊ እሴቶቻችን አድርጎ ማዕከሉ ሲቋቋም ተማሪዎችን በሃገራዊ ትምህርታዊ እና ስነ-ምግባራዊ ጉዳዮች ላይ ነፃና ምክንያታዊ ውይይት ክርክር እንዲሁም ፅሁፍ እንዲቀርቡ መጋበዝና መድረክ ማመቻቸት የማዕከሉ አንዱ ተልዕኮ ነው ብለዋል፡፡ ፊደል በቆጠሩ አንደበቶች ሁሉ ተደጋግመው ስሙ የማይጠፋው ወይም የሚጠራው ሶቅራጦስ እንዲህ ይላል (No one does evil knowingly evil or wrong did originated from ignorance) ማንም እያወቀ ክፉ አይሰራም የክፋት ምንጩ ሁሉ ድንቁርና ነው ይላል፡፡ (The more you are intellectual the more you become innocent or kind) እንደ ሚለው በማለት ተናግረዋል፡፡

ዕውቀት በሳይንስና ጥበብ ክዋኔያችን ብቻ አይሳካም፡፡ ዕውቀት ራስን ከመሆን አካባቢንና ተፈጥሮን ከማወቅ እና ሌሎችን ከመገንዘብ ይጀምራልና ለተፈጥሮና ለፍጥረታት ባመጣው በጐነት ልክ ይለካል፡፡ የክፋት ምንጩ አለማወቅ ነው ካልን እና ዩኒቨርሲቲ የዕውቀትና ጥበብ ማዕከል ነው ካልን ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ለሚወጡ ሁሉ ለእውነት፣ ለበጐነት የወገኑ ናቸው ብለዋል፡፡

ስለሆነም ተማሪዎች በሙሉ ኢትዮጵያ ከእነሱ የጠራ ዕውቀት፣ የጠነከረ እምነት፣ ጥልቅ እሳቤ፣ ምክንያታዊ ውሳኔ፣ የተስተካከለ አስተውሎት፣ የጐላ ሰባዊነትና ግብረገብነት በጥበብ፣ በዕውቀት፣ በምግባራዊነት የሚወጣ ወጣት ታሪክ ሊያስቀጥል ይችላል፤ አሊያም ሊፈጥር ይችላል፡፡ ወይም ሊሽር ይችላል ፍርጃውና ውሳኔው ሁሉ በምክንያትና በዕውቀት መሠረት ላይ ይሆናል ፡፡

አቶ ይኩኖአምላክ መስፍን በመልዕክታቸው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ኢትዮጵያ ምሁራንን ትፈልጋለች ስለሆነም ድንጋይ ለሚወረውር ድንጋይ አቀባይ ሳይሆን ድንጋይ የሚያስጥል ሃሳብ አቅራቢ፤ ጥላቻ ለሚዘሩ ሰላም ፈጣሪ በጨለማ ለሚጓዙ ብርሃን ሰጪ፣ በስሜት ለሚነዱ በአስተውሎት፣ ገነዉ ባለማወቅ የሚኖሩ ሚስጥር ገላጭ እነዚህና መሰል ምሁራዊና ሰብአዊ በእያንዳንዳችን ጐልተው ይወጡ ዘንድ የበጐ ሃሳብ ማዕከሉ ተቀዳሚ ሥራ ስለሆነ ማዕከሉን በመደገፍ ልናሳድገው ይገባል፡፡

# አገራዊ ቅርፅ እየያዘ ያለው በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተጀመረው የልዩ ተሰጥኦ ማበልፀጊያ ማዕከል

በአካባቢው የሚገኙ ልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች ወደ አንድ ማእከል በማምጣትና ተገቢውን ድጋፍና እገዛ በማድረግ የልጆችን አቅም በማጎልበት ለነገ የተሻለ ህይወት እንዲኖራቸው ለማስቻልና ለአገራቸውም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማስቻል በ2008 ዓ/ም በደብረ ማረቆስ ዩኒቨርሲቲ በረዳት ፕሮፌሰር አቶ ገበየሁ ሽፈራው የልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ማበልጸጊያ ማዕከል በራሳቸው የግል ተነሳሽነት ተጀመረ፡፡



ገበየሁ ሽፈራው (ረዳት ፕሮፌሰር
የልዩ ተሰጥዖ ማበልፀጊያ ማዕከል ኦፊሰር

አቶ ገበየሁ ስለ አጀማመራቸው ሲናገሩ አንድ ቀን በእርሳቸው የመኖሪያ ቤት አንድ ህፃን ልጅ ዲሽ ሲሰራ ይመለከቱና በስራው ተደንቀው ያንን ህጻን እንዴት ተማርህው ብለው ይጠይቁታል፡፡ ልጁም ስራውን የአስተማረው ሰው እንደሌለና በራሱ ሙከራ እና ጥረት እንደተማረው ይገልፅላቸዋል፡፡ አቶ ገበየሁ አያይዘው ምን መሆን ትፈልጋለህ ይሉታል፡፡ ህፃኑም የሰጣቸው ምላሽ የነበረው በፈጠራ ስራ ላይ መሰማራት ነበር፡፡ ይህ ነገር ልባቸውን ነካው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መምህርነት እያሉ ይህን ሁኔታ ይታዘቡት የነበሩት አቶ ገበየሁ አጋጣሚ ይህን ልጅ ማየታቸው ካልሆነ በስተቀር ሌሎችም ምን አልባትም የበለጠ ችሎታ ያላቸው ሊኖሩ እንደሚችሉ ዝንባሌው አደረባቸው፡፡ አቶ ገበየሁ ይህንን ዲሽ ሰራተኛ ህፃን መጠየቃቸውን ቀጠሉ "አሁን የሰራኸው ነገር አለህ ወይ አሉት" ፡፡

ልጁም በዚህ በፈጠራ ስራ በትምህርት ቤት ይሳተፍ እንደነበረና ሶስት እግር ያለው የመኪና ሞዴል ሰርቶ በአቀራቢያ ወደ ሚገኝ ጋራዥ ቤት ያቀናል የሰራውን ሞዴልም ለጋራዥ ሰራተኞች ሲያሳያቸው ስድሳ ሺህ (60000) ብር እንደሚያወጣ ይነግሩታል፡፡ ሞዴሉም አሽከርካሪው እንቅልፍ ሲይዘው እራሱ ተሽከርካሪው ዳር ይዞ የሚቆም እንደነበር ለአቶ ገበየሁ ይነግራቸዋል፡፡ በዚህም በጣም ይገረማሉ ይህም እንግዲህ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ማበልፀጊያ ማዕከል ለማቋቋም የመነሻ ንድፈ ሀሳብ ሆናቸው፡፡ ሁኔታው ያላስተኛቸውና ረፍት የነሳቸው አቶ ገበየሁ የትልመ ሀሳብ ወረቀት በማዘጋጀት በወቅቱ ለነበሩት የደብረ ማርቀስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶክተር ጥላየ ጌቴ ያቀርቡላቸዋል፡፡ ፕሬዝዳንቱም ሌሎች መምህራንን በመመደብ ከአቶ ገበየሁ ጋር አብረው እንዲሰሩና በስራው እንዲቀጥሉበት ውሳኔ ይሰጧቸዋል፡፡ በመጨረሻም አቶ ገበየሁ ማዕከሉን ለማቋቋም ፕሮጀክት ቀረጹ፡፡

የልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ማበለፀጊያ ማዕከሉ ሲቋቋም ልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎችና ሰዎች ችሎታቸውን የሚጠቁሙባቸውን ምቹ ሁኔታ መፍጠር አላማው አድርጎ ተነሳ፡፡ ልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎችን በእሱ ደረጃና እድሜ ክልል ውስጥ ለየት ያለ ችሎታ ያላቸውን የሚመለከትና ብዙ የፅንሰ ሀሳቡን ስራ ወደ ተግባር መቀየር የሚችሉትን ሰዎች ነው፡፡ እነዚህ ደግሞ በየቦታው እንደሚገኙ ገልጸው ከአርሶ አደሮች፣ ነጋዴዎችና ሌሎችም ውስጥ እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ የሚያድጉበትን ምቹ ሁኔታ፣ ግብዓት የሚያስፈልጋቸው ከሆነ እያሟላን ለማሣዳግ፣ የማማከርና የትምህርት አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ በመፍጠር ለማሣደግ እንደሆነ አቶ ገበየሁ ተናግረዋል፡፡

የልዩ ችሎታና ተፈጥሮ ማበልፀጊያ ማዕከል የተጀመረው በሳይንስና ቴክኖሎጅ 30 ተማሪዎችን፣ በስነ- ጽሁፍ 13 ተማሪዎችን ተቀብሎ በአጠቃላይ በ43 ተማሪዎች ነበር፡፡ በተማሪዎች ተከታታይ ለውጥ ካልታየ በወላጆች ምክንያት ወደ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ሲገቡ እየወጡ አሁን በልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ማበልጸጊያ ማዕከሉ ያሉት 24 ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡

ለተማሪዎች የሚደረግላቸው ድጋፍ የማጠናከሪያ ትምህርት በተለይም በሣይንስ ትምህርቶች፣ ሂሳብ እና እንግሊዝኛ ትምህርትን ጨምሮ ሁል ጊዜ ቅዳሜና እሁድ ከ8፡00 ሰዓት ጀምሮ በየክፍል ደረጃቸው የማጠናከሪያ ትምህርት በዩኒቨርሲቲው እውቅ ምሁራን እንዲማሩ እየተደረገ ነው፡፡ የልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎችን ለሚያስተምሩ መምህራንም ዩኒቨርሲቲው በአወጣው መመሪያ መሠረት የተመረጡ መምህራን የትራንስፖርት ክፍያ እንዲያገኙና የተሳትፎ የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ እየተደረገ ነው፡፡ ይህም ለመምህራን ዕውቅና ለመፍጠርና የድካማቸውን ያህል እንኳን ባይሆን ስራውን ወደውት እንዲሰሩ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች ባላቸው ችሎታና ፍላጎት መሠረት የተለያዩ የፈጠራ ስራዎች እንዲሰሩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ለዚህም ለሚሰሯቸው የፈጠራ ስራዎች የሚያስፈልጓቸውን ግብዓቶች ዩኒቨርሲቲው ያሟላላቸዋል፡፡ በአብዛኛው ልጆች የፈጠራ ስራቸውን የሚሰሯቸው አገልግሎታቸውን ከጨረሱና ከወዳደቁ ነገሮች ነው፡፡ የልዩ ችሎታ ፈጠራ ተማሪዎች በዕድሜያቸው ህፃን በመሆናቸው አሁን እየሰሯቸው ያሉት የፈጠራ ስራዎች ከኤሌክትሪክ ንክኪ የፀዱ ናቸው፡፡በዚህ ፈንታ ዲናሞ እንዲጠቀሙ እየተደረገ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ተማሪዎች በፈጠራ ስራዎቻቸው እያደጉ ሲሆን በቀለም ትምህርታቸውም ወደ ዩኒቨርሲቲው በልዩ ችሎታና ፈጠራ ማዕከል ከመምጣታቸው በፊት ከነበራቸው ውጤት በእጅጉ ተሻሽሏል፡፡ የልጆችን ውጤት ለመከታተልም በቅድሚያ ልጆች ወደ ልዩ ችሎታና ማበልፀጊ ማዕከል ሲመጡ ካርዳቸውን እንዲያመጡ በማድረግ ኮፒውን ሰንዶ በማስቀመጥ ክትትል እንደሚያደርጉና በአመቱ መጨረሻም ውጤታቸውን እንዲያመጡ በማድረግ የንጽጽር ስራ እንደሚሰራ አቶ ገበየሁ ገልጸዋል፡፡

ወደ ማዕከሉ ለመቀላቀል የሚፈልጉ ተማሪዎችም በዩኒቨርሲቲው መምህራን በተዘጋጀ የመመልመያ መስፈርት መሰረት ተማሪዎች የራሳቸውን የፈጠራ ስራ ይዘው እንዲመጡ በማድረግ በዳኞች የመረጣና የምልመላ ስራ ይሰራል፡፡ ተማሪዎች ለውድድር ይዘዋቸው የሚመጡት የፈጠራ ስራ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ እና በስነ-ፅሁፍ ነው፡፡ ስነ-ፅሁፍ ብዙ የህይወት ተሞክሮ የሚጠይቅ፣ ብዙ ማንበብን የሚጠይቅ እና አካባቢን መረዳት የሚጠይቅ በመሆኑ ከእድሜያቸው አንፃር ለእነዚህ ተማሪዎች በሙያው የ2ኛና የ3ኛ ድግሪ ያላቸውን መምህራን በመመደብ እገዛ እንዲያደርጉላቸው ተደርጎ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ሊቀበሉ ስላልቻሉ አሁን በማዕከሉ ያሉት ተማሪዎች የቴክኖሎጂ ፈጠራ ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡ በልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ማዕከል ሲሳተፉ የነበሩ ተማሪዎች በአሁኑ ሰዓት የመሰናዶ ተማሪዎች የደረሱ እንዳሉና ተማሪዎችም የተለያዩ ሶፍትዌሮችን ማበልፀግ መቻላቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በአብዛኛው የልዩ ችሎታና ፈጠራ ተማሪዎች የሚሰሯቸው ሞዴሎችን ነው፡፡

የልዩ ችልታና ፈጠራ ማበልጸጊያ ማዕከል በአሁኑ ሰዓት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ሆኖም ግን ግብዓቱ ሲሟላ የማስፋፋት ስራ ይሰራል፡፡ ይህንን የልዩ ችሎታና ፈጠራ ማበልፀጊያ ማዕከል የጀመረው ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቢሆንም በርካታ ዩኒቨርቲዎች ማለትም ወሎ ዩኒቨርሲቲ፣ ጐንደር ዩኒቨርሲቲ፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲና አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ዩኒቨርሲቲ ሃሳቡን ወስደው ትልቅ ደረጃ አድርሰውታል፡፡ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የልዩ ችሎታና ፈጠራ ማዕከልን ሲያቋቁም አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ አስር ኮምፒውተሮችን የሰጠን



ሲሆን፣ ማዕከሉን ለማደራጀትም አንድ አይሱዙ መኪና ቁሳቁሶችን ሰጥቶን ነበር፡ ፡ ሆኖም ግን ልምዱን ወስዶ ሳይንስና ቴክኖሎጂ በቢሾፍቱ ትልቅ ማዕከል እየገነባ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ይህም በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተጀመረው የልዩ ችሎታና ፈጠራ ማበልፀጊያ ማዕከል አገራዊ እየሆነ መምጣቱን ያመላክታል፡፡ ሆኖም ግን ዩኒቨርሲቲው እንደ አጀማመሩ እያደገ እንድሄድ አላደረገም፡፡ እስካሁን ያለው አንድ የማዕከሉ መኮንን ብቻ ነው፡፡ ዘርፍ አድጐ ይቀይራል የሚለው አስተሳሰብ ችግር አለ፡፡ የሰው ሀይልና በጀት ሊሟላለት ይገባል፡፡

የልዩ ችሎታና ተሰጠኦ ማበልፀጊያ ማዕከሉ በመንግስት፣ በትምህርት ቤትና ወላጆች ያለው ትኩረት አነስተኛ ነው፡፡ ትምህርት ማለት የቀለም ትምህርት ብቻ ተደርጐ መቆጠሩ አግባብነት የለውም፡፡ በትምህርት ቤት የፈጠራ ስራ ያላቸው እንዲያመጡ ከተደረገ በኋላ እዛው ወዳድቆና ተሰባስሮ ነው የሚቀረው፡፡ ስለሆነም በዚህ አግባብ የአዕምሮ ፈጠራ ሳያድግ ይቀራል፡፡ ለዚህም ነው በዩኒቨርሲቲው የማጠናከሪያ ትምህርት እንደያገኙ የተደረገው ምክንያቱም ተማሪዎች የፈጠራ ስራ ሊሰሩ ሲመጡ ወላጆቻቸው ስለማይልኳቸው ነው ጐን ለጐን እንዲሰጥ የተደረገው፡፡ ከዚህ ጋር ተያያዞ ብዙ ተማሪዎች ሊመጡ ቻሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አንድ ጊዜ ብልጭ ያለን የፈጠራ ስራን ወደያው ካልሰሩት ይረሳል፡፡ ስለሆነም ይህን እንዲሰሩትና የፈጠራ ስራቸውም ከየትኛው የንድፈ ሀሳብ ጋር ተያያዥነት እንዳለው ለመገንዘብ ያስችላቸዋል፡፡ ለዚህም መምህራን ድጋፍ ያደረጉላቸዋል፡፡ ተማሪዎችም ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ምላሽ ሲሰጡ ችሎታቸውንና እውቀታቸውን እያዳበሩ መሄድ ይችላሉ፡፡

በአሁኑ ሰዓት በመንግስት በኩልም የልዩ ችሎታና ፈጠራ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ነው፡፡ የፈጠራ ሰዎችን የማበረታቻ ሽልማትና ሌሎች ድጋፎች እየተሰጡ መሆኑ ይበል የሚያስብልና በቢሾፍቱ የልዩ ችሎታና ፈጠራ ማዕከል መገንባቱም ተማሪዎች ከከፍተኛ ትምህርት ሲወጡ ሊያመሩበት የሚችል ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ልዩ ችሎታና ፈጠራ ማበልፀጊያ ማዕከል የአካባቢውን ማህበረሰብ በአሁኑ ሰዓት ተጠቃሚነቱን ያረጋገጠ ነው ባይባልም ዋናው ነገር ግን መጀመሩ በራሱ ትልቅ ነገር ነው፡፡ በመመስረቱም በአሁኑ ስዓት ሁለት የልዩ ችሎታና ፈጠራ ማበልፀጊያ የማዕከል የኮምፒዩተርና ቨርችዋል ቤተ ሙከራዎች እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ የማዕከሉ ተማሪዎችም በማዕከሉ መሳተፋቸው ለቀለም ትምህርታቸው ማጠናከሪያ እንዲያገኙ መደረጉ እንዲሁም ያላቸው የፈጠራ ስራ ለመስራት የሚያስፈልጓቸው ግብዓቶች እንዲሟሉላቸው መደረጉ የአካባቢውን ማህበረሰብ በዩኒቨርሲቲው ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ያስቻለ ነው ብለዋል ረዳት ፕሮፌሰር ገበየሁ፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ማበልፀጊያ ማዕከል ልጆች የተለያዩ የፈጠራ ውጤቶችን የሚሰሩባቸውን ዕቃዎች ተሟልተው፣ የተማሪዎች ንድፈ ሀሳባዊ ዕውቀት የሚጐለብትበትንና የንድፈ ሃሳብ ዕውቀት ወደ ፈጠራ የሚቀይሩበትን ማየትና ሞዴሎችን መስራት ብቻ ሳይሆን የተሰሩ የፈጠራ ሰራዎች ወደ ማህበረሰቡ ገብተው ማህበረሰቡ የሚጠቀምበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንደሚሰሩም አክለው ተናግረዋል፡፡ በማዕከሉ ተማሪዎች አሁን ላይ የተሰሩ በርካታ የፈጠራ ስራዎች ማለትም መፀዳጃ ቤት ውስጥ ሰው መኖሩንና አለመኖሩን የሚገልፅ ሴንሰርና የውሃ ማጣሪያ የተሰሩ ሰለሆነ እነዚህ ወደ ማህበረሰቡ እንዲገቡና ሌሎችም ወደ እዚህ እንዲመጡ በማድረግ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል ብለዋል፡፡

የልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ማበልፀጊያ ማዕከል የሚያድግበትን ሁኔታ በማመቻቸት የዩኒቨርሲቲው አመራሮች በአገር አቀፍ ደረጃ የሚገኙባቸው መድረኮች በርካታ ስለሆኑ ልዩ ችሎታና ተሰጥኦንጉዳይን አንስተው ሊነጋገሩበት እንደሚገባና በየዩኒቨርሲቲዎች የተጀማመሩ ነገሮች ተቋማዊና አገራዊ እንዲሆኑ ብሎም በኤጀንሲ ደረጃ የሚቋቋምበትን መንገድ በመነጋገር የልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ያላቸውን ልጆች ከያሉበት ፈልጐ በማምጣት ያላቸውን አቅም ለመጠቀም መስራት ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ጉዳይ እስካሁን ያጣነው ትልቅ ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡

የሰው ልጅ አዕምሮ የተለያየ በመሆኑ የቀለም ትምህርት ችሎታ የሌላቸው የልዩ ችሎታና ፈጠራ ባለቤት ሊሆኑ ስለሚችሉና አገር ሊቀይሩ ስለሚችሉ መንግስት ይህን ኃላፊነት ወስዶ መስመር ቢዘረጋለትና ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሲጨርሱ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡትንና ከዩኒቨርሲቲ ወጥተው ወደ ስራ የሚሰማሩበትን ትስስር መፍጠር ወሳኝ ነው፡፡ ይህን ስናደርግ በተለያዩ ፋብሪካዎች ይደራጃሉ፣ የስነ-ፅሁፍ ዘርፍ ተማሪዎችም ያላቸውን ችሎታ እንዲያዳብሩ ለማድረግ መምህራን፣ ወላጆች የልጆችን ችሎታ መለየትና ወደሚፈልጉት እንዲያተኩሩ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም ሁላችንም የሚጠበቅብንን ድርሻ መወጣት እንዳለብን የማዕከሉ አስተባባሪ አሳስበዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲው የቴክኖሎጂ ፈጠራ ያላቸው ተማሪዎችም ያላቸው የፈጠራ ስራ የሚያቀርቡት ሁኔታ ተመቻችቶ በመምህራን እንዲገመገሙ ተደርጐ የተሻሉትን በደረጃ በመለየት የቴክኖሎጂና ፈጠራ ትዕይንት ቀን በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ አካላትን በመጋበዝ እንዲከበር ተደርጓል፡፡ በዚህም የኢንኩቤሽን ማዕከል እንዲቋቋም ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ በቀረበው የቴክኖሎጅ ፈጠራም ለአስረጅነት ያክል ከወዳደቁ ወረቀቶች እንዴት ሃይል ማመንጨት እንደሚቻል፣ የሂሳብ ቀመርና ሰብልን የሚያጭድና የሚወቃ ሌሎችንም የፈጠራ ስራዎችን ሞዴሎች አቅርበዋል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ማበልፀጊያ ማዕከል ተጠቃሚ ልጆች ወላጅ የሆኑት አቶ ሀብታሙ ቢያልፌ በደብረ ማርቆስ ከተማ ነዋሪና የተማሪ ዘላለም ሀብታሙ እና ዘለቀ ሀብታሙ ወላጅ ሲሆኑ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የልዩ ችሎታና ተሰጥአ ያላቸው ተማሪዎችን ሲመለምል በምልመላው አልፈው ወደ ማበልፀጊያ ማዕከሉ የተቀላቀሉ ልጆች ናቸው፡፡ ልጆች ወደ ማዕከሉ ከተቀላቀሉ በኋላ በተሰጣቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እየመጡ ሲከታተሉ የሚስተወሉ ለውጦችን ፈጥረዋል፡፡ልጆች በበጋም ሆነ በክረምት በዩኒቨርሲቲው የልዩ ችሎታና ፈጠራ ማበልፀጊያ ማዕከል እየተሳተፉ ሲሆን ዩኒቨርሲው ባደረገላቸው ድጋፍና ክትትል አንደኛው ልጃቸው በባህር ዳር ባደረገው ውድድር የሜዳሊያ ተሸላሚ መሆን መቻሉን ተናግረዋል፡፡ ልጆቻቸው ወደ ማዕከሉ ከመጡ ጀመሮ እውቀታቸው እየጐለበተ የመጣ ሲሆን ይህም ሊሆን የቻለው የኢንተርኔት አጠቃቀማቸው፣ የንባብ ልምዳቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመመጣቱ ነው ብለዋል፡፡

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተደራሽ የሆነው ለደብረ ማርቆስ ከተማ ተማሪዎች ብቻ በመሆኑ ለሌሎችም ተደራሽ መሆን እንዲችል የማስፋፍያ ስራዎችን ቢሰራ ጥሩ ነው ብለዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው የጀመረውን በማጠንከር ልጆች ለትልቅ ደረጃ እንዲደርሱ መስራትም ይገባዋል ብለዋል አቶ ሀብታሙ፡፡ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ልዩ ችሎታና ፈጠራ ላላቸው ተማሪዎች እያደረጉት ያለው ድጋፍን በማጠናከር የተሻለ ደረጃ እንዲደርሱ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ሹፌሮችንም ለልጆች በፈቃደኝነት የሰርቨሲ አገልግሎት መስጠታቸው በጣም ሊመሰገን የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ መምህራንም በእረፍት ጊዜአቸው ለተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠታቸው ሊመሰገኑ ይገባል፡፡ ስለሆነም  ይህን ነገር ዩኒቨርሲቲው በስፋት አጠናክሮ ሊቀጥልበት እንደሚገባ  አቶ ሀብታሙ ቢያልፌ አሳስበዋል፡፡

በክረምት ደግሞ በየክፍል ደረጃቸው ከየወረዳው ተመርጠው የሚመጡ ተማሪዎች ጋር በSTEM Outreach ፕሮግራም ተጠቃሚ እንደሆኑ የማዕከሉ ተጠቃሚዎች ተናግረዋል፡፡ በማዕከሉ ቆይታቸው ለፈጠራ ስራቸው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን እየተሟሉላቸው መሆኑን ጠቅሰው ወደ ማዕከሉ ከመምጣታቸው በፊት ከነበረው የፈጠራ ስራ የተሻለ መስራት እንዳስቻላቸውና በትምህርት ቤታቻው የኮምፒውተር አቅርቦት ካለመኖር ጋር ተያይዞ ምንም ዓይነት የኢንተርኔት ተጠቃሚ እንዳልነበሩ አስታውሰው ኢንተርኔት መጠቀም  በመቻላቸው  የኮምፒውተር አጠቃቀም ችሎታቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ገልፀዋል፡፡

ወደ ልዩ ችሎታና ፈጠራ ማበልፀጊያ ማዕከል እንዲመጡ የቤተሰቦቻቸው ሚና ትልቅ እንደነበር ያወሱት ተማሪዎች በውድድሩ ከተሳተፉ በኋላ አልፈው የነበሩ ሌሎች ሲቀሩ የእኛ ቤተሰቦች እንድንቀጥን አድርገዋል ብለዋል፡፡ በልዩ ችሎታና ፈጠራ ማዕከል ውሰጥ ዘወትር ቅዳሜና ዕሁድ የማጠንናከሪያ ትምህርት እንደሚማሩና ከማጠናከሪያ ትምህርት በኋላም የፈጠራ ስራዎቻቸውን በማዕከሉ እንደሚሰሩ ተናግረዋል፡፡ ለሚሰሯቸው የፈጠራ ስራዎቻቸውም የኢንተርኔት አገልግሎት እንደሚጠቀሙ ተማሪዎች ገልፀዋል፡፡  በማዕከሉ መካተታቸው ከዚህ በተጨማሪ በመደበኛው ትምህርታቸው ያልተሸፈኑ ምዕራፎችን በማጠናከሪያው ትምህርት ፕሮግራም ስለሚሰጡ ያልተማሩትን እንዲማሩ ያስቻላቸውና በክፍል ውስጥ ተምረዋቸው በደንብ ሳይረዷቸው የቀሩትንም ለመምህራን እንዲያስተምሯቸው በመንገር መገንዘብ እንደቻሉ ተናግረዋል፡፡ በክረምት የ STEM Outreach ፕሮግራምም የሚማሩት በቅድሚያ የሚገቡበትን የክፍል ደረጃ ትምህርት በመሆኑ ቅድመ ዝግጅት ስለሆነ በመደበኛው ክፍላቸው ሲማሩ ትምህርቱን የበለጠ እንዲገነዘቡ ያስቻለን ነው ብለዋል፡፡ ይህም በክፍል ውስጥ የነበረኝን የትምህርት ደረጃ በማሻሻል ወደ አንደኛ ደረጃ እንድመጣ አስችሎኛል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ማበልጸጊያ ማዕከል መሳተፍ መቻላችን አንደኛ  የዩኒቨርሲቲ ህይወት ምን እንደሚመስል ዕውቅና ስለፈጠረልን ወደ ዩኒቨርሲቲ ስንገባ ለዩኒቨርሲቲው እንግዳ አንሆንም፣ የዩኒቨርሲቲ ህይወትም እንግዳ ስለማይሆንብን የተለያዩ ነገሮችን በቀላሉ በማየት ትምህርታችንን ቀላል ያደርግልናል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ለእኛ ዕድሉን መስጠቱ ጥሩ ቢሆንም ወረዳ ያሉ ተማሪዎች በልዩ ችሎታና ፈጠራ ማበልፀጊያ ማዕከሉ ተጠቃሚ መሆን ስላልቻሉ የእነርሱን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በክረምት ወቅት አምጥቶ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ቢያደርግ ጥሩ ነው፡፡ ወደ ፊትም የተለያዩ የልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች አቅማቸውን እንዲያጐለብቱ ለማስቻል አቅም በፈቀደ መልኩ በየአካባቢው ለማቋቋም የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማበርከት እንደሚሰራ ተማሪ ዘለቀ ሀብታሙ ገልጿል፡፡ ዩኒቨርሲቲውም የልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ተማሪዎችን ስራ ከሌሎች ተቋማት ተማሪዎች ጋር ውድድር እንዲያደርጉ ቢደረግ የተሻለ መሆኑን ጠቁሟል፡፡

## ማስብ አስተምሩኝ

ዓሣ በሞላባት በዚህች ባሕር ዓለም፣
ማስገር እንደማወቅ የሚያዋጣ የለም፤
ቢሆንም ግን ቅሉ፣
የዞረበት ዕቅሉ፤
ብዙ ነው መዘዙ ሲያዩት አስተውሎ፣
ትውልድ የሚያደንዝ የሚያነቃ መስሎ፤
ሀገር የሚጎዳ አያሌ እኩይ አለ፣
የተጠመደ ዓሣ እንኩ ብሉ እያለ፤
ከእንስሳት ልዩ ነው ያለው ስሜት መግቻ፣
ለመኖር አይችልም ሰው በሆዱ ብቻ፤
ስለዚህ ጠቢባን፣
እናንተም ምሁራን፤
ተሟጋች፣ ‘አክቲቪስት’፣ አዋቆች ሁላችሁ፣
ጎረቤት ወይ ተቋም ቤተ እምነት ያላችሁ፤
ከዛሬና ከዚህ፣
ለነገና ለዚያ በርእይ አሸጋግሩኝ፣
እንስሳ አይደለሁም ማሰብ አስተምሩኝ!
ይኼ ሁሉ ምሁር ይህ ሁሉ ተማሪ፣
ይህ ሁሉ ተከታይ ይኼ ሁላ መሪ፤
ለአንድ አካል ጎላዌ አንዱ ራስ አንዱ እግር፣
ዜጋ ሆኖ ሳለ ለዚህች ታላቅ ሀገር፤
“እኔ እለብስ እኔ እለብስ” እየተባባለ ይውላል ሲሳሳብ፣
መጨመር ተስኖት በወሬ ላይ ሐሳብ፡፡

(በምንዋጋው ተመስገን)

# ሃገር በቀል ዕውቀትን የማዘመን ፕሮጀክት



ወ/ሮ ደጅይጥኑ አለነ

የፕሮጀክቱ ዋና ተመራማሪ

ዕውቀት ሳይንሳዊ ሲሆን የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑ ነባራዊ ሀቅ ቢሆንም የሀገር በቀል ዕውቀት የአካባቢን ችግር ስር ነቀል በሆነ መልኩ መፍትሔዎችን ለመሻት አይነተኛ መሳሪያ እንደሆነ ይነገርለታል፡፡ዛሬ ላይ በሉላዊነት ተፅዕኖ ምክንያት የሰው ልጅ ከሀገር በቀልና ከአካባቢያዊ ዕውቀት ይልቅ ሳይንሳዊ ዕውቀትን በመፈለጉ ሀገር በቀል ዕውቀት እየተተወና እየተረሳ በመምጣቱ የነበሩት ትላልቅ ሚስጥሮች እየተዳፈኑና እየጠፉ መጥተዋል፡፡ ሳይንሳዊ ዕውቀት ያለው ሚና የሚናቅ ባይሆንም ለሳይንሱ መነሻ የሆነውን የሀገር በቀል ዕውቀት ማወቅና ማሳደግ መቻል ደግሞ ጠቀሜታው እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተሰጡትን ተልዕኮዎች መካከል አንዱ የማህበረሰብ አገልግሎትን በምርምር በታገዘ አሰራር በላቀ ደረጀ ለመፈጸምና ውጤታማ ለማድረግ ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል በአካባቢው የሚስተዋሉ ችግሮችን መፍታት ነው፡፡ ለዚህም የሀገር በቀል ዕውቀትን በአግባቡ ማጥናት፣ ማደራጀትና ሳይንሳዊ የሆነ ፈርጅ እንዲይዝ ማድረግ ለነገ የማይባል ተግባር ነው፡፡

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ነገን ዛሬ ሊሰራ ትልቅ ራዕይ ሰንቆ ዩኒቨርሲቲው የሃገር በቀል ዕውቀትን ለአካባቢያዊ ችግር መፍቻ ያለውን አዎንታዊ ሚና በውል በመገንዘብ በዩኒቨርሲቲው የሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም ስር የሀገር በቀል ዕውቀት ጽ/ቤትን በማቋቋም ወደ ስራ ገብቷል፡፡ የሀገር በቀል ዕውቀት ፅ/ቤት ስራውን ለመጀመር ፕሮጀክት ቀርፆ ወደ ሰራ ተሰማርቷል፡፡ ስለፅ/ቤቱና ስለሚሰራቸው ፕሮጀክቶች በሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም ከ2005-2010 ዓ/ም የባህል ጉዳዮች ጥናትና ምርምር አስተባባሪና የባህል ጥናት ባለሙያ በመሆን ከ2010 እና 2011 ዓ/ም ደግሞ የስነ-ፅሁፍ ባለሙያና በሀገር በቀል ዕውቀት ፕሮጀክት ላይ ዋና “PI” በመሆን እየሰሩ ያሉትን ወ/ሮ ደጅይጥኑ አለነን አነጋግረናል፡፡

የሐገር በቀል እውቀት ብያኔው “ትርጉሙ” በጣም ብዙና ሰፊ ነው የሚሉት ባለሙያዋ፡፡ የሐገር በቀል እውቀት ማለት የአንድ ማህበረሰብ ወይም የተለያዩ ህዝቦች “የተለየ” ተፈጥሯዊና አካባቢያዊ የእውቀት ስልት ክምችት ነው፡፡ የሀገር በቀል እውቀት በአንድ በተወሰነ ጆግራፊያዊ አካባቢ የሚገኝ “የተለየ”፣ ባህላዊ አካባቢያዊ እውቀቶችን የሚያጠቃልል ሆኖ የተወሰኑ የወንዶችና ሴቶች ጥበብ ነው /Grenier 1997/፡፡ የአለም አቀፍ የጤና ድርጅት /2002/ እንዳስቀመጠው የሀገር በቀል እውቀት አካባቢያዊ ሆኖ እውቀቱም ባህላዊና ማህበራዊ ነው፡፡ አገር በቀል እውቀት ውስጥ አንዱ ሀገረሰባዊ መድኃኒት ነው፡፡ እነዚህ ሃገረሰባዊ መድኃኒቶች ከቀድሞው ጊዜ ጀምሮ የነበሩ ሲሆን ባህላዊ ዳራዉ ግን ይለያያል፡፡ በዚህም የተለያዩ መድኃኒትነት ያላቸው እፅዋቶች (የእፅዋት ቀንበጥ፣ ቅጠል፣ ቅርፊት፣ ግንድ ስር) የእንስሳት ተዋፅኦ እና ማእድናትን በመጠቀም የሰውን፣ የእንስሳትና የሰብልን በሽታዎች ለመፈወስ እንደሚቻል የአለም አቀፍ የሳይንስ ጥናት 2011 የምሁራንን ሃሳብ በመጥቀስ አስቀምጦታል፡፡ “ሀገረሰባዊ መድሀኒት” ማለት የአጠቃላይ እውቀትና ተግባር ድምር ውጤት የሆነ፣ አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ማህበራዊ ጠንቆችንና ተውሳኮችን ለመከላከል፣ ለማስወገድና ለመመራመር የሚተገበር ሙያ ነው፡፡ ሆኖም ግን የሀገር በቀል እውቀትን በአሁኑ ሰዓት እየተጠቀምንበት አይደለም ምክንያቱም ወይ ረስተነዋል ወይም ወደ ጐን እያወቅን ትተነዋል ማለት ይቻላል፡፡

የሀገር በቀል እውቀታችን እየተጠቀምንበት ያለው በዘልማድና ባህላዊ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ሳይንስና ቴክኖሎጂውን ዘመናዊ እውቀት ያለው ሰው ወደ ሀገር በቀል እውቀት ይዞት አልገባም፡፡ ይህም ማለት ሀገር በቀል እውቀቱ በሳይንስ አልተፈተሸም ወይም እውቀና አልተሰጠውም፡፡

የሀገር በቀል እውቀት ላይ ምሁራን ከተለያዩ የእውቀት ዘርፍ በተቀናጀ መልኩ በመስራት ማህበረሰቡ ላይ ሊዳሰስና ሊጨበጥ የሚችል ለውጥ ማምጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲው አመራርም የአገር በቀል እውቀት ያለበትን ደረጃ በመገንዘቡ ፕሮጀክት ቀርጾ ላቀረበ ሰው በጣም አወንታዊ ፈቃድና ጥሩ ምላሽ አለው፡፡ ለዚህም ማስረጃ በሀገር በቀል እውቀት “መድኃኒታማ ዕፅዋት ላይ መምህራንና አጥኝዋ በጋራ በተቀናጀ መልኩ ደረጃ በደረጃ የሚሰራውን ፕሮጀክት ቀርፀው ሲያቀርቡ በጣም በደስታና አበረታች በሆነ መልኩ ዩኒቨርሲቲው አፅድቆት ወደ ሥራ ግብቷል፡፡

የሀገር በቀል ዕውቀትን ለመጠቀም በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚገኙ ምሁራን ላይ ያለ አመለካከት ትክክል አይደለም፡፡ ምክንያቱም “የሐገራችን ምሁራን” አመለካከትና አስተሳሰብ ከኔነት ያለፈ ባለመሆኑ እኔ ከማጠናው ጥናት ምን እጠቀማለሁ እንጅ የምሰራው ስራ ውጤት ለማህበረሰቡም ሆነ ለአገር ያለውን ጥቅም ምን ሊሆን ይችላል ወይም ማህበረሰቡ ላይ ምን ሊፈይድ ይችላል ብሎ የሚሰራ ዜጋ አልተፈጠረም ይላሉ ወይዘሮ ደጅይጥሁ፡፡ የምሁራን አመለካከት መሆን ያለበት ሐገሬ አስተምራኛለች፣ ኃላፊነት አለብኝ ስለዚህ እኔ የተሻልሁ ስለሆንሁና የሀገር አደራ ስላለብኝ ለማህበረሰቤ ምን ልስራለት? ማህበረሰቡ ምን ሀገር በቀል እውቀት አለው? የሚያስፈልገው ዘመናዊና ሳይንሳዊ እውቀትና ቴክኖሎጅ ምንድን ነው የሚለው አስተሳሰብ እንዲመጣ ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ስልጠናዎችና ውይይቶችን በማዘጋጀት መስጠት የሚያስፈልገው ይሆናል፡፡

የአገር በቀል እውቀትን ከመጠቀም አኳያ እስካሁን መሬት ላይ የወረደ፣ የሚታይና የሚዳሰስ የለም፡፡ የማህበረሰቡን የአገር በቀል እውቀት ለመጠቀምም በፕሮጀክት የተደገፈ ስራ አልነበረም፡፡ ነገር ግን የተለያዩ የምርምር ስራዎች ግን ይሰራሉ ሆኖም ግን በሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም ዩኒቨርሲቲው የሚገኝበት አካባቢ በባህላዊ መድሀኒት የታወቀ ስለሆነና ጥበቡ ስላለ ወይዘሮ ደጅይጥኑ ባደረጉት ጥናት መነሻነት ከተለያዩ የሙያ ዘርፍ የተውጣጡ 40 ምሁራንን የሚያሳትፍ 108 ሚሊዮን ብር የተበጀተለት የ10 ዓመት ፕሮጀክት በሀገር በቀል እውቀት ላይ በመድኃኒታማ እፅዋት ላይ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ፕሮጀክቱን ለመቅረጽ አንድ ድፍን ዓመት የወሰደ ሲሆን ፕሮጀክቱም ከተቀረፀ በኋላ ሙያውና ልምዱ ባላቸው ፕሮፌሰሮችና ዶክተሮች ወደ አዲስ አበባና ጐንደር በመላክ ግምገማ ተደርገበታል፡፡ ከዚያም ፕሮጀክቱ የተሰጠውን አስተያየት በመቀበልና እንዲሻሻል በማድረግ ፕሮጀክቱ እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡

ፕሮጀክቱ የተነሳው ከምርምር ስራ ነው የፕሮጀክቱ ርዕስም “Mega Project Proposal On Indigenous Knowledge Documentation, Medicinal Plant Conservation and validation towards Standardization In East And West Gojjam, Awi And Metekel Zones, Ethiopia የሚል ሲሆን ይህ ፕሮጀክት አምስት ትልልቅ ክፍሎች አሉት እነሱም

ወደ ገፅ 30 ዞሯል

# የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ግብርና ፕሮጀክት





መንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ሲያስፋፋበዋናነት በጥናት ላይ ተመርኩዞ ለችግሮች የመፍትሄ ሃሳቦችንና መንገዶችን ማምጣት ነው፡፡ ይህም የማህበረሰቡን ችግሮች በመፍታት ህዝቡን ተጠቃሚነት ብሎም የሃገሪቱን እድገት ለማረጋገጥ ዋነኛ አቅም እንደሚሆኑ በማመን ነው፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተልዕኮዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡ እነዚህ ተልዕኮዎች መማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት ናቸው፡፡ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከተልዕኮዎች አንጻር በዋናነት የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት ያስችለው ዘንድ በምርምር እና ማህበረሰብ አገልገሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ጽህፈት ቤት በስሩ የተለያዩ ዳይሬክቶሬቶችን በማቋቋም የምርምር፣ የማማከር እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡ ከእነዚህ ዳይሬክቶሬቶች ውስጥም አንዱ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት አንዱ ነው፡፡ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከተቋቋመ ጀምሮ በዙሪያው ያሉ ወረዳዎች እና ከተሞችን ሲያማክር፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ሲሰጥ እና የምርምር ስራዎች እያካሄደ ይገኛል፡፡ ምርምሮችንም ወደ ፕሮጀክት በመቀየር የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ እየተጋ ይገኛል፡፡

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በምርምር ሥራዎች ላይ በመመርኮዝ ወደ ፕሮጀክት ማደግ የሚችሉትን የሚለይበት የራሱ አሰራር አለው፡፡ የርምር ሥራዎች በተጨባጭ የማህበረሰቡን ችግር የሚፈቱ ሆነው ሲገኝ ወደ ፕሮጅት አድገው የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማምጣት ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ፕሮጀክቶች አንዱ ደግሞ በደብረ ማርቆስ ከተማ ውስጥ በሚኖሩ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚተገበረው የአረንጓዴ ልማት የከተማ ግብርና ፕሮጅት ነው፡፡ በ2010 ዓ.ም በተጀመረው የአረንጓዴ ልማት የከተማ ግብርና ፕሮጀክት በከተማው ውስጥ ያሉ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የከተማው ነዋሪዎች ባላቸው ውስን ቦታ ላይ ራሳቸውን መመገብና ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኙ የሚያስችል ዓላማ አንግቦ የተቀረፀ ፕሮጀክት ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት ከደብረ ማርቆስ ከተማ ግብርናፅ/ቤት ጋር በመተባበር በዝቅተኛ ደረጃ የሚኖሩ የከተማው ነዋሪዎችን በቀበሌ አመራሮች አማካኝነት በመለየት በአትክልት እና ፍራፍሬ እንዲሁም በዶሮ እርባታ የከተማ ግብርና ሥራዎች እንዲሰማሩ በማድረግ ራሳቸውን የሚመግቡበትንና ተጨማሪ ገቢ የሚያገኙበትን አሰራር ለመዘርጋት ያለመ ፕሮጅክት ነው፡፡ የከተማ አረንጓዴ ልማት ከግብርና ጋር በማስተሳሰር (Urban Greening through Urban agriculture in the case of Debre Markos City Adiminstration) የሚል ፕሮጀክት ለ5 አመት የሚቆይ ነው፡፡ የዚህ ፕሮጀክት ዋና አላማ እና ንውሳን አላማዎች አሉት፡፡ የፕሮጀክቱ ዋና አላማ የማህበረሰቡን የተመጣጠነ ምግብ አቅርቦት ማሻሻል እንዲሁም ንጹህ እና ውብ የሆነች ከተማን መፍጠር ሲሆን የሚከተሉት ንዑስ ዓላማዎች አሉት፡፡

- የማህበረሰቡን የተመጣጠነ የምግብ አቅርቦት ማሻሻል፣
- አረንጓዴ ከተማን መፍጠር፣
- ለተማሪዎች የተግባር ማስተማሪያ ማድረግ ፣
- የዕውቀት እና የቴክኖሎጅ ሽግግር በማህበረሰቡ ዘንድ እንዲፈጠር ማድረግ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ከሆኑት ግለሰቦች መካከል ወ/ሮ በየኑ አማኑ አንዷ ናቸው፡፡ ወ/ሮ በየኑ በፕሮጀክቱ በመታቀፍ የጓሮ አትክልት እና ፍራፍሬ በማልማት ላይ የተሰማሩ ናቸው፡፡ ወ/ሮ በየኑ በዚህ የአትክልት ልማት መሳተፋቸው ራሳቸውን በምግብ ከመቻል አልፎ ለአካባቢው ማህበረሰብ በመሸጥ በሳምንት ከመቶ እስከ ሶስት መቶ ብር ገቢ ያገኛሉ፡፡ በዚህም ራሳቸውም ሆነ ጎረቤቶቻቸው ተጠቃሚ ሆኖል፡፡

ለዚህ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል 2,786,786.00 ብር በዩኒቨርሲቲው ተመድቧል፡፡ በዚህ ስራ የከተማ አሰተዳደር ግብርና ፅ/ቤት፣ ማዘጋጃ ቤት እንዲሁም የቀበሌ 07 አስተዳደር የሚመለከታቸው አመራሮች እና ባለሙዎች በከፍተኛ ደረጃ ፕሮጀክቱን በማገዝ የድጋፍና ክትትል ሥራዎችን ይሠራሉ፡፡

በአጠቃላይ በፕሮጀክቱ የቆይታ ጊዜ 210 (ሁለት መቶ አስር) ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች ሲኖሩት በተጨማሪም ከመዘጋጃ እና ከጥቃቅን እና አነስተኛ ጋር በመሆን በስፋት ለመስራት ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ጀምሮ በእቅዱ መሰረት ለ30 የተመረጡ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ላሉ የከተማው ነዋሪዎች የተሻሻሉ እና ለአካባቢው ተስማሚ የሆኑ የአፕል እና የአቮካዶ ዝርያዎች ተሰራጭተዋል፡፡ እንዲሁም 100 ለሚሆኑ ተጠቃሚዎች የዶሮ ቤት ተሰርቶላቸው የተጠናቀቁ ሲሆን ቀሪ የዶሮ መኖ እንዲሁም የኬሚካል ግዥ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በዶሮ እርባታም ለእያንዳንዱ ተጠቃሚ 25 ዶሮ እንዲሁም ለአንድ ዶሮ የመጀመሪያ ዙር እንቁላል እስኪጥሉ ድረስ ለዘጠና ቀን የሚሆን ምግብ ለእያንዳንዱ ተጠቃሚ ይሰጣቸዋል፡፡

አገር በቀል....ከ ገፅ 28 የዞረ

1. የማህበራዊና ባህላዊ ቡድን
2. የብዝሃ ህይወትና ነርሰሪ ቡድን
3. የጤና ቡድን በውስጡም የሰው ጤና፣ የእንስሳት ጤናና ምርምሩ የሚካሄድበት የሰብል ጤና
4. የልየታና ማጣራት ቡድን
5. የአእምሮ ባለቤት ጥበቃ /ፓተንት / ቲም የሚባሉ ሲሆን የእነዚህ የእያንዳንዳቸው /PI/ ቡድን አስተባባሪ አላቸው፡፡ የእነዚህ የሁሉም አስተባባሪ ደግሞ ሌላ አንድ /PI/ ሲኖረው በአጠቃላይ ፕሮጀክቱ ስድስት PI እና 36 የቲም አባላት ያሉት ሆኖ የመጀመሪያ ስራዎችን ካስኬድ በማድረግ ለመስራት ታስቦ በበጀት እጥረት ምክንያት ወደ አዲስ ዓመት ተሸጋግሯል፡፡

በሌላ በኩል የሀገር በቀል ዕውቀት ፕሮጀክት ወደ ስራ እንዳይገባ በጣም ችግር አለ፡፡ ይኸውም ምሁራኑ መደበኛ ስራቸው ማስተማር ስለሆነ እነርሱን በተፈለገውና በታሰበው ሰዓት ለማግኘት አለመቻሉና እንዲሁም ፕሮጀክቱን ቶሎ ያለማፅደቅ፣ ከፀደቀ በኋላም መረጃዎችን አደራጅቶ አለመያዝ ለስራው መጓተት ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የሀገር በቀል ዕውቀት ፕሮጀክት ሊያከናውን ያሰባቸው ተግባራት ስራውና በተለያዩ ክፍሎች የሚከናወኑ ተግባራት በቅደም ተከተል ተለይተው የተቀመጡ ሲሆን እስከ 10 ዓመት ሊቆይ የሚችል ፕሮጀክት ነው፡ ፡በመጀመሪያ የሚሰራው “Flock knowledge” የማህበረሰቡን እውቀትና ጥበብ አሰባስቦ በመተንተን የመሰነድ ተግባር ነው፡፡ በ2ኛ ደረጃ ደግሞ እውቀትና እፅዋቱ እየጠፉ ስለሆነ ቦታኒካል ጋርደን በማቋቋም የሚጠፉ መድሃኒታማ እፅዋቶችን ማልማትና መንከባከብ፣ ማብዛትና ለማህበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ ሲሆን ይህም የሚሰራው በብዝሀ ህይወትና ነርሰሪ ቡድን አማካኝነት ነው፡፡ የሁለተኛው ተግባር ከተሰራ በኋላ የእፅዋቱ መርዛማነትንና የማዳን አቅምን የማጣራት ስራን ደግሞ የልየታ ቡድን እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በመቀጠልም የቤተ-ሙከራ ስራዎችና ምርምሩ የሚካሄድ ሲሆን ይህን የሚካሂዱትም የጥናት ቡድን ነው፡፡ በመጨረሻም የእውቀቱ ባለቤት የሆነው ማህበረሰቡና ዩኒቨርሲቲው በምን ስምምነት መስራት እንዳለባቸው የአጥኝዎች ባለመብትነትና የዩኒቨርሲቲው ተጠቃሚነትን በተመለከተ መስራት የሚጠበቅባቸው ደግሞ የአዕምሮ ባለቤትነት ጥበቃ ቡድን ነው፡፡ በዚህ ላይ የተለያዩ የቅድመ ግንኙነት ውይይቶች፣ ወርክ ሾፕችና ስልጠናዎች እንዳስፈላጊነቱ በየስራ ጣልቃውና የስራው ሁኔታ የሚሄዱ ይሆናል፡፡

በሀገር በቀል ዕውቀት ፕሮጀክት የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስና ማህበረሰቡ ላይ ጠብ የሚል ስራ ለመስራት ማሰባቸውን የገለጹት ባለሙያዋ ለስራው ውጤታማነትና ስኬታማነት ከእነርሱ በተጨማሪ በዋናነት የፈጣሪ እገዛ ትልቅ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ይህ ፕሮጀክት ሰፊ የሰው ኃይልና ሰፊ ስራ ስለሚከናወንበት ራሱን ችሎ በዳይሬክተር ደረጃ የሚመራ መሆን ቢችል አሁን እየተጓተተ ያለው ስራ ምክንያቱ ቢሮክራሲዎች ስለበዙ ነው ፡፡ ነገር ግን ራሱን ችሎ ዳይሬክተር ቢኖረው የማስፈፀም አቅሙ ስለሚጎለብት ስራዎችን በፍጥነት መስራት እንደሚችሉ ወይዘሮ ደጅይጥኑ እምነታቸውን ገልጠውልናል፡፡ እኛም የሀገር በቀል እውቀት ፕሮጀክት ወደ ስራ ገብቶ ማህበረሰቡ በራሱ እውቀት የሚጠቀምበትን ጊዜ ተመኘን፡፡ መልካም እድል፡፡

አገራዊ እሴቶች....ከ ገፅ 31 የዞረ




ይህ የባህል ጥናት ተቋሙ የማህበረሠቡን ፍላጐት መሠረት ያደረገ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ዘጠኝ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በዩኒቨርሲቲው 28 ምሁራንን በማሳተፍ 1,279,551 ብር በመመደብ ጥናቶች እያሰራ ይገኛል፡፡ እነዚህ ጥናትና ምርመሮችም

- → በጐጃም የቅኔ ትምህርት አጀማማርና እድገት፣ የቅኔ ሊቃውንትና ቅኔዎቻቸው ከየት ወዴት፣
- → Indigenous knowledge and values system in Gojjam its role for social cohesion and contemporary challenges
- → The culture of cooperation trust and respect Continuity, Change, and impacts in East Gojjam Zone.
- → The impact of modernization on the practices of indigenous knowledge in Ethiopian orthodox Church: The case of in fluent 21 east Gojjam Abinet Schools
- → The Role of Ethiopian orthodox Tewahido church in Safeguarding three selected cultural values Amhara Region in focus.
- → ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በምስራቅ ጐጃም ዞን ማህበረሠብ ውስጥ
- → የዘመናዊ ኪነ- ጥበብ አጀማመር፣ እድገት እና የወደፊት ጉዞ በምስራቅ ጐጃም
- → የእንግጫ ነቀላ በዓል በምስራቅ ጐጃም ዞን አሁን ያለበት ሁኔታ፣ የክብረ በዓሉ ስርዓት- ክዋኔ፣ ተግዳሮትና መልካም አጋጣሚዎች በሚሉ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ጥናቶች እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ በዚህ የባህል ተቋም ፕሮጀክቶችን በመደገፍ ሲሚናሮችና ወርክሾፖች በማካሄድ የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ማለትም ሙያዊ እገዛ፣ የገንዘብ እገዛ፣ ስልጠናዎችን በመስጠት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ያለ የባህል ጥናት ተቋም እንደሆነ አቶ ግዛቸው በሪፖርታቸው አትተዋል፡፡

# አገራዊ እሴቶቻችን የተንፀባረቁበት የሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም ሰባተኛ የምርምር ጉባኤ ቅኝት




ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም ሰባተኛው ሀገራዊ አውደ ጥናት ‹‹የጋራ ባህላዊ እሴት ለጠንካራ አገራዊ አንድነት›› በሚል መሪ ቃል ከግንቦት 10-11/2011 ዓ/ም በልዩ ዝግጅቶች በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በድምቀት ተካሂዷል፡፡ በዚህ ዓውደ ጥናት የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ፕሬዝዳንት ደራሲ አበረ አዳሙ እና ታላላቅ የሀገሪቱ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ ምሁራንና ተመራማሪዎች፣ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባላት፣ ተማሪዎች፣ አርቲስቶች በተገኙበት በድምቀት ተካሂዷል፡፡

በአውደ ጥናቱ መክፈቻ ላይ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዝዳንት ረዳት ፕሮፌሠር ገነት ደጉ ባስተላለፉት የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በክቡር ሀዲስ አለማየሁ ስም የባህል ጥናት ተቋም ሲያቋቁም ተቀዳሚ አላማው የአካባቢውን ፀጋዎች ተጠቅሞ የአካባቢውን ባህል፣ ወግ፣ ቋንቋ፣ ስነ ጥበብ እና ስነ-ፅሁፍ፣ እንዲሁም አገረሠባዊ እውቀትን ሳይንሳዊ በሆነ ጥናትና ምርምር ተደግፈው እንዲታወቁ፣ እንዲለሙ፣ በአግባቡ እንዲጠበቁ እና ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ ነው ብለዋል፡፡ ረዳት ፕሮፌሰር ገነት የጥናት ተቋሙ በታላቁ የስነ ጽሁፍ አባት፣ ዲፕሎማት እና አርበኛ ክቡር ሀዲስ አለማየሁ ስም ሲሰየም ፈለጋቸውን ተከትለው በርካታ ሀዲሶች፣ በርካታ ቴዎድሮሶች እንዲሁም ሀገር ወዳድ ዜጎችን በማፍራት የሀገር ግንባታ ሂደቱ የበኩላችንን አስተዋጽኦ ለማበርከት እንደሆነ አያይዘው ገልጸዋል፡፡ ይህ ለ7ኛ ጊዜ የሚካሄደው “የጋራ ባህላዊ እሴት ለጠንካራ አገራዊ አንድነት” በሚል መሪ ቃል የተዘጋጀው ዓውደ ጥናት ወቅታዊ የሀገራችን ሁኔታ እንደሚነግረን በአራቱ ማዕዘናት አንድነቷና የህዝቦች ደህንነት ፈተና ውስጥ የወደቀች ሀገራችንን፣ የሠላም እጦት፣ መፈናቀል የዕለት ከዕለት መገለጫዎች ከሆኑ ከዚህ አረንቋ ለመውጣት ወሳኝ ምዕራፍ ላይ በመገኘታችን ጭምር በመሆኑ ልዩ እንደሚያደረገው ረዳት ፕሮፌሰር ገነት ደጉ አብራርተዋል፡፡

በዚህ አውደ ጥናት ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት ደግሞ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ታፈረ መላኩ ናቸው፡፡ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በመክፈቻ ንግግራቸው ‹‹የጋራ ባህላዊ እሴት ለጠንካራ አገራዊ አንድነት›› በሚል መሪ ቃል የተዘጋጀው አውደ ጥናት ሀገራችን ኢትዮጵያ በየዘመኑ ብዙ ፈተና እየገጠማት ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በተለይ በዚህ አንድ ዓመት ውስጥ የሚታዩ ሁኔታዎች ግን በይዘትም ሆነ በባህሪው ፍጹም የተለየ እንደሆነ ገልጸው አጠቃላይ ሁኔታው ከኢትዮጵያ ባህል፣ ስነ ምግባርና ሞራላዊ ኃላፊነት ፍጹም ያፈነገጠ በመሆኑ ሊስተካከል እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡ ዶ/ር ታፈረ አያይዘውም የጥቁር አፍሪካዊያን ኩራት፣ ለአለም ህዝቦች ተምሳሌት የነበረን ዜጎች፣ የስልጣኔ ቀደምት የሰው ልጆች መፈጠሪያ የነበረን፣ ባህላዊ እሴት ባለቤት የነበረች ሀገር በእርስ በርስ ግጭት እና መፈናቀል ከአለም ተጠቃሽ እየሆነች ስለመጣች፣ አሁን ካለንበት ቀውስ ለመውጣት የሀይማኖት እና የትምህርት ተቋማት ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ለነገ የሚባል እንዳልሆነ በአፅንዖት ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም ይህን አውደ ጥናት በየዓመቱ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ሲያዘጋጅ ኢዲሱ ትውልድ የትናንት የአባቶችን ሀገራዊ ማንነት መለስ ብሎ እንዲያይ እና ኢትዮጵያ ትናንትም ሆነ ዛሬ ወርቃማ ማህበራዊ እና ሀገራዊ እሴቶች ያላት ሃገር መሆኗን በኪነ ጥበብ እያወዙ ለማስተማር ታስቦ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር ግዛቸው አንዳርጌ የተቋሙን 7ኛ ዓመታዊ አገር አቀፍ ዓውደ ጥናት አስመልክተው እና የተቋሙን የስራ እንቀሰቃሴ ዙሪያ የሰጡንን መረጃዎች እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በታላቁ ደራሲ፣ መምህር፣ አርበኛና ዲፕሎማት በሆኑት በክቡር ዶ/ር ሐዲስ አለማየሁ ስም “የሐዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም” በሚል ስያሜ ታህሣስ 17 ቀን 2004 ዓ/ም ተቋቋመ፡፡ ተቋሙ ሲመሰረት የተለያዩ ተልዕኮዎች ያሉት ሲሆን እነዚህ ተልዕኮዎች በባህል ዘርፍ ጥናትና ምርምር በማድረግ ለባህል ጥበቃ፣ እድገት እና ልማት ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከት፣ አማተር ከያንያን እና ፀሐፊያንን በማበረታታት ለኪነ-ጥበቡ እድገት የበኩሉን ሚና መጫወት ሲሆን ተቋሙም እነዚህን ተልዕኮዎች በአግባቡ ለማሳካት በክፍሉ ባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃ ዘርፍ፣ ትያትር ዘርፍ፣ ግዕዝ ጥናት ዘርፍ፣ ስነ-ጽሁፍ ዘርፍ፣ ባህል ጉዳዮች ጥናት ዘርፍ እና በቤተ መዛግብት ማዕከላት በስሩ በማደራጀት ሰራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡

ወደ ገፅ 30 ዞሯል

# ውጤታማ የልዕቅና ማዕከላት



አቶ አብዮት ሞላ

የጮቄ ተፋሰስ ፕሮጀክት የምርምርና ልማት ዳይሬክተር

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጮቄን የዩኒቨርሲቲው መለያ ብራንድ ለማድረግ እየሠራ ይገኛል፡፡ ይህንን ለማድረግም በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዘርፍ የጮቄ ተፋሰስ ምርምር እና ልማት ፕሮጀክት ዳይሬክቶሬት አቋቁሟል፡፡ የዚህ የሥራ ክፍል ዳይሬክተር አቶ አብዮት ሞላ ስለ ጮቴ ፕሮጀክት የሠጡንን መረጃ እንደሚከተለው አሰናድተን አቅርበናል፡፡

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የጮቄ ተፋሰስ ስርዓተ- ምህዳርን ለመመለስ እና ለመጠበቅ እንዲሁም ህብረተሰቡ ከተፈጥሮ ሃብቱ እና ከግብርና ተግባራት በዘላቂነት መጠቀም እንደሚችል በማሰብ እና ልዩ ትኩረት በመስጠት ራሱን የቻለ የስራ ክፍልየጮቄ ተፋሰስ የምርምርና ልማት ፕሮጀክት ዳይሬክቶሬት በጥቅምት 2006 ዓ/ም በማቋቋም የተለያዩ የምርምር እና የልማት ስራዎችን ለማከናወን በምስራቅ ጐጃም ዞን በሰባት ወረዳዎች ማለትም ጐዛምን፣ ስናን፣ ባሶሊበን፣ አነደድ፣ አዋበል፣ ደጀን እና ማቻከል ላይ 13 የልዕቅና ማዕከላት ተመስርተዋል፡፡ እነዚህ የልዕቅና ማዕከላትም ለምርምር እና ልማት ተግባራት ያመች ዘንድ ስነ-ምህዳርን መሰረት በማድረግ በመገንባት እና በምርምር በመታገዝ በአዳዲስ የሰብል፣ የእንስሳት፣ የአትክልት እና ፍራፍሬ ዝርያዎች እና በተፈጥሮ ሃብት እና ኢነርጅ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና ሌሎች የአካባቢ አርሶ አደሮችን ከእነሱ ተሞክሮ በመውሰድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማሰብ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ በ2010/2011 ምርት ዘመን በተከናወኑ አዳዲስ የምርምር እና የልማት ስራዎች ከ195 በላይ የሚሆኑ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከዩኒቨርሲቲው ተልዕኮዎች አንዱ ችግር ፈች የምርምር እና ልማት ስራዎችን ማከናወን ስለሆነ ዳይሬክቶሬቱ የሚያከናውናቸው ተግባራት ከዩኒቨርሲቲው የምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር በቀጥታ ተዛማጅነት አላቸው፡፡ ስለሆነም በእነዚህ የልዕቅና ማዕከላት የሚከናወኑ የምርምር እና ልማት ስራዎች ከተለያዩ ኮሌጆች በተለይ ከግብርና ኮሌጅ ከተውጣጡ ባለሙያዎች እና ተመራማሪዎች ጋር በመሆን ዳይሬክቶሬቱ ከኮሌጆች ጋር ከፍተኛ የሆነ ትስስር እንዳለው ማሳያዎች ናቸው፡፡ ዩኒቨርሲቲው እነዚህን የልዕቅና ማዕከላት እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም እና ጮቄን የተቋሙ መለያ በማድረግ ቢሮውን ወደ ምርምር ማዕከል በማሣደግ የምርምር ስራዎችን በተደራጀ እና በተቀናጀ መልኩ ቢሰሩ ዩኒቨርሲቲውን በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት ወደፊት አንድ እርምጃ የሚያራምዱ እንዲሁም በተጨባጭ የሚታዩ ችግር ፈች የምርምር ውጤቶችን ያፈልቃል የሚል እምነት አለኝ፡፡

የጮቄ ተፋሰስ የምርምርና ልማት ፕሮጀክት ዳይሬክቶሬት የልቅና ማዕከላት አንዱ የሆነው በስናን ወረዳ የገዳማዊት ቀበሌ ሲሆን በቀበሌው አርሶ አደሮች በደጋ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ሰብል ዝርያ፣ ማዳቀል ኑሯቸውን ማሻሻል እንደቻሉ ይናገራሉ፡፡ ዩኒቨርሲቲው በሚሰጣቸው የሙያ ድጋፍ፣ የተሻለ ዘር እና ሌሎች ክትትሎች አርሶ አደሮች ከሥነ-ምህዳሩ ጋር የሚስማሙ የአትክልትና ዕፅዋት ዝርያዎችን በማልማት ጥሩ ገቢ እያገኙ እንደሆነ ከተጠቃሚዎች አንዱ የሆኑ አቶ ተስፋየ ይታየው ይናገራሉ፡፡

እንደ አቶ ተስፋዬ በአካባቢ የሚፈለጉ ጌራ፣ ሸኮላ፣ ጓሳ፣ የሚባሉትን ምርጥ የድንች ዘሮች፣ የስንዴ ዘር፣ የባቄላ ምርጥ ዘር ዩኒቨርሲቲው በማቅረብ አርሶ አደሮች በሽታን መቋቋም የሚችሉና ምርታቸው የተሻለ ዘሮችን ለአርሶ አደሮች መስጠቱን ተናግረዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው የእኛን ጥቅምና ዋስትና ያስጠብቃል የሚሉት አርሶ አደሮች የድንች ማቆያ ተብሎ እየተዘጋጀ ያለው የፕሮጀክቱ ሥራ ብዙ በጀት ተመድቦለት እየተሰራ ይገኛል፡፡ ፕሮጀክቱ የሰጠን ድንች፣ ስንዴ፣ አገር በቀል ዛፎች፣ ቢራ ገብስ፣ የሚታዩና የሚጐበኙ እፅዋቶች ውጤታማ ስለሆኑ ለቀጣይም ለሚመጡ እፅዋት የችግኝ መትከያ ቦታ የግብርና ባለሙያዎችድጋፍና ክትትል እየሠራን ይገኛልበማለት አርሶ አደሮች ይናገራሉ፡፡ ይህ ፕሮጀክት የአርሶ አደሩን ህይወት እየቀየረ ይገኛል፡፡ በደጋማው የአየር ንብረት አብዛኛውን ጊዜ በጋማና ዳልጋ ከብት እርባታ ብቻ ይተዳደር የነበረ ቢሆንም የደጋ ዕፅዋትን በማላመድ አርሶ አደሮቹ አካባቢያቸው ሳይራቆት ከፍተኛ ገቢ እያስገኘ ነው፡፡ በገዳማዊት ቀበሌ ያለው የገበሬዎች ማሳ ላይ የሚሰሩ ሥራዎች አርሶ አደሮች የአፕል ችግኝ እና የአፕል ምርት በመሸጥ ገቢ እያገኙበት ነው፡፡ ለዚህም አንድ የአፕል ችግኝ ከ30-40 ብር በመሸጥ አፕልን ለገቢ ማግኛ አድርገውታል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሮጀክት ለየት እንደሚል ያሳውቃል የሚሉት የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች ከዚህ በፊት እነሱ ጋ ይሰሩ የነበሩ ፕሮጀክቶች ጋር እያነፃፀሩ ውጤታማ ሥራ እያከናወነ እንደሆነ ይመሰክራሉ፡፡ አንዳንድ ፕሮጀክቶች ይመጡና ውጤቱን ሳያዩት በዓመት እና ሁለት ዓመት የሚሄዱበት ሁኔታ አለ ይህ ግን የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት ከ2005 ዓ/ም እስከ አሁን ድረስ በጥሩ ሁኔታ እየረዳን የተለያዩ የእንስሳት ዝርያዎችን የዋሸራ በግ እየሰጠን ነው በማለት ነዋሪዎቹ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ፡፡ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት በሰጠን ስልጠና መሰረት ህብረተሰቡ ድንች፣ ቢራ ገብስ ላይ ውጤት አምጥተናል አፕል አምና ለ30 ሰዎች ተሰራጭቶ ነበር እናም ለወደፊቱ ውጤት እንደምናመጣ ነው፡፡

በስናን ወረዳ ረዕቡ ገበያ ከተማ ገደማይት ቀበሌ ኗሪ አርሶ አደር ይርጋ መኩሪያው ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በፕሮጀክቱ አምና ቢራ ገብስ ዘር ወስደው በመጠቀም ጥሩ ምርት ማግኘታቸውን ገልጸዋል፡፡ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት የበግ ዝርያ፣ ማጭድ፣ ዘመናዊ ማረሻ እኛ ይህን ምርጥ ዘር በመስጠት በቡሮአቸው ላይ ውጤት መምጣቱንም አቶ ይርጋ መስክረዋል፡፡

እንደዚህ የአየር ንብረት ለውጥ ፈተና በሆነባቸው አገራት ላይ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበረገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ በመገንባት ሥነ-ምህዳሩ ተጠብቆ የአርሶ አደሩን ህይወት የሚሻሻልበት ሃገር በቀል ፕሮጀክት ውጤቱ በአርሶ አደሩ ቤት በቀላሉ የሚታይ ነው፡፡ አርሶ አደሩ ከምንም ነገር በፊት አካባቢውን በመጠበቅ የተመረጠ ዘር በመውሰድ ውጤታማ የሚያደርግ ስለሆነ የጮቄ ተፋሰስ የምርምርና የልማት ፕሮጀክት የልዕቅና ማዕከላት ሥራዎች በየደረጃው ባሉ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚተገበሩበትን አሰራር በመዘርጋት ሁለንተናዊ ድጋፍ ሊደረግ እንደሚገባ የአካባቢው ነዋሪዎች መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ፡፡

# ዝክረ አድዋ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ





ምኒሊክ ተወልዶ ባያነሣ ጋሻ

ግብሩ እንቀላል ነበር ይሄን ጊዜ አበሻ፤

***

ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ

መድፍ አገላባጭ ብቻ ለብቻ፤

***

የአድዋ ሥላሴን ጠላት አረከሰው

ገበየሁ በሞቱ ግባና ቀድሰው፤

የካቲት ወር የአፍሪካውያን ወር ይባላል፡፡ ይህን ወር የአፍሪካውያን ወር ያሰኘው ብቸኛ ምክንያት የዓድዋ ድል ነው፡፡ ነጮች አፍሪካውያንን በግፍ በሚረግጡበት፣ በባርነት በሚገዙበት፣ ያሻቸውን ያለከልካይ በሚፈፅሙበት በዚያን ወቅት ‹‹እምቢኝ! ሀገሬን በቅኝ አላስገዛም›› ብሎ በጀግንነት የተነሳ፣ ተነስቶም የቅኝ ገዢዎችን በትር በሀይል መስበር የተቻለበት ወር ይህ የካቲት ወር ነው፡፡

123ኛዉ የአድዋ በዓል ‹‹የአድዋ ድል ለሀገራዊ አንድነት›› በሚል መሪ ቃል በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተከብሯል፡፡

የበዓሉ የመክፈቻ ላይ  የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ፕሬዘዳንት ዶ/ር ታፈረ መላኩ ‹‹የአድዋ በዓል ሀገራዊ አንድነትን ያሳየን ለመላዉ ጥቁር ህዝቦች  የነጻነት ጮራ እንዲፈነጥቅ ያደረገ ትልቅ የድል በዓል በመሆኑ ክብር መስጠት የሚገባንን ሰዎች ክብር ባለመስጠታችን በትዉልድ መካከል የሚታይ ሰፊ ክፍተት እንደሆነና አሁን ያለዉ ትዉልድ አያቶቻችንና ቅድመ አያቶቻችን አጥንታቸዉን ከስክሰዉ ደማቸዉን አፍሰዉ ከቀኝ ግዛት ባርነት ስላወጡን ተገቢዉን ክብር ልንሰጣቸዉ እንደሚገባ፤ እኛም እንደ ትዉልድ በብዙ መስዋትነት በመክፈል ያቆዩልንን ሀገራችንን ለሚመጣዉ ትዉልድ የማቆየት ሃላፊነት በአግባቡ ልንወጣ ይገባል›› በማለት መልክታቸዉን አስተላልፈዋል፡፡

በፓናል ውይይቱ ላይ ጥናታዊ ፅሁፍ ያቀረቡት የታሪክ ተመራማሪዉ ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ   ‹‹የአድዋ ድል ሚስጥር››  በሚል ርዕስ ጥናታቸውን አቅርበዋል፡ ፡ ይህ ድል የኛ ድል ስለሆነ እያጋነነዉ እንዳልሆነ ምክንያቱም በድሉ ሃያ አራት ሰዓት ዉስጥ በአለም ዉስጥ ያሉ የመገናኛ ብዝሃን ሁሉ የመጀመርያ ገጽ አድርገዉ የዘገቡት የታሪክ ክስተት ሁኖ ነበር ፡፡

ፕሮፌሰር ሹመት  ጣሊያን ለኢትያየጵያ ያላትን የተሳሳተ አመለካከት ሲገልጹ ‹‹ኢትጵያዉያን ለየት ያለ ባህል እንዳላቸዉ አልተገነዘቡም ኢትዮጵያኖች ለተለየ ባህልና ታሪክ ስለነበራቸዉ ጣሊያን በሌሎች ሀገሮች የሰራዉ ዘዴ በኢትየጵያኖች ላይ ከሸፈ›› ይህ ደግሞ የምስራቅ አፍሪካን ቀጠና የመግዛት ህልም የነበራትን ጣሊያን የዉርደት ካባ ሊያከናንባት ችሏል፡፡

 ጣሊያኖች ከዛሬ ነገ ይገባል እያሉ የሚጠብቋቸዉ ራስ መንገሻ ዮሃንስ የጣልያን ሰራዊት ገፍቶ ገና ምኒሊክ ትግራይ ሳይደረሱ መረብ ሲሻገር እንዲህ አሉ ‹‹ህይወቴን እንደ ጀግናዉ ቴዋድሮስ እዚህ እጨርሳለሁ እንጅ አልሸሽም›› ብለዉ በብዙ ልመና ነዉ የንጉሰ ነገስቱ ጦር እዚህ እስኪደርስ ድረስ አፈግፍገዉ እንዲቆዩ የተደረገዉ፡፡ እንዲሁም ደጃዝማች ጓንጉል ዘገየ የተባሉ ሰዉ ከአጼ ምኒሊክ ጋር የተጣሉ ሸፍተዉ በርሃ እያሉ የጣልያን ጦር መግፋትና የምኒሊክን የጦርነት አዋጅ ሲሰሙ ወደ አጼ ምኒሊክ አማላጅ ልከዉ ‹‹ጃንሆይ ከርሰዎ ጋር ተጣልቼ በርሃ ገብቼአለሁ፤ አሁን ግን በሀገሬ ላይ የዉጭ ጠላት ስለመጣ የእርስዎና የኔን ጉዳይ ወደ ጎን በመተዉ ይማሩኝና መጥቼ ከእርስዎ ጎን ከጌታየ ሁኜ  የሀገሬን ጠላት ልዉጋ››  ብለዉ በዘመቻዉ እንደተካፈሉ ፕ/ሩ ያብራራሉ፡፡

ጸኃፌ ትዕዛዝ ገ/ስላሴ እንደገለጹት ይላሉ ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ ‹‹ሰራዊቱም ስለ ሀገሩ ስለ መንግስቱ ተናዶ ነበርና መድፉ ይመታኛል፣ ነፍጡም ይጥለኛል እሞታለሁ ብሎ ልቡ አልፈራም ጀግኖ ነበር ጌታዉ ቢወድቅ ሎሌዉ አያነሳዉ ወንድሙ ቢሞት ወንድሙ አያነሳዉም የቆሰለዉም ሰዉ አልጋዉ ይቁም እንጅ ኋላ ስትመለስ ታነሳኛለህ በማህይም ቃሌ ገዝቸሃለዉ ይለዉ ነበር ››  ዳግማዊ ምኒሊክ ለሩስያዊዉ ንጉሰ ነገስት በጻፉት ደብዳቤ ለዛር ኒኮላስ ይህንን የጣሊያን ግፍና የኢትዮጵያን መብት በጻፉት ደብዳቤ የሚከተለዉን ብለዋል ‹‹ጣሊያን ገንዘብ በላያችን ላይ የለብን ሀገራቸዉም ሩቅ ነዉ አለም ከተፈጠረ ጀምሮ ነጻነቱና እራሱን የቻለ መንግስት የሆነዉን በተንኮል ሊወስዱት እንዴት ይቻላቸዋል፤ ይህንን የግፍ ግፍ በሙሉ ልቦናዎ በዉል እንዲመለከቱት ተስፋ አለኝ>>  በማለት ምኒሊክ ደብዳቤ ጽፈዉ ነበር፡፡ይህ ወደ ዉስጥ ሰርጾ የገባ የሀገር ስሜትና ምርኩዙ አድርጎ የተቀነባበረዉ የምኒሊክ በሳል አዕምሮ ለአድዋ ድል አይነተኛ ዋስትና ሰጦታል፡፡

ፕሮፌሰር ሹመት በጹሁፋቸዉ እንደጠቀሱት በዘመናችን እንደተነሱት የጎሳ መሪዎች እንደሚያራምዱት የሀገሪቱ ህዝቦች ለማዕከሉ መንግስት ያላቸዉን ታመኝነትና ለኢትዮጵያነት የሚሰጡትን ከበሬታ ነፍገዉ አሁን እንደሚታየዉ የግል ጎሳና ለክልል ጉዳያቸዉ ላይ ቢጠመዱ ኑሮ! ያ በአለም ዙርያ የተጎናጸፈነዉ ድልና ግርማ ሞገስ ቀርቶ የተገዥነትና የተዋራጅነት ካባ እንደርብ ነበር መጭዉ ትዉልድ ለተመሳሳይ ከፍተኛ አላማ ግብ መሰለፍ አለበት በማለት መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ጠላትማ ጠላት ምንጊዜም ጠላት ነው፣

አስቀድሞ መግደል አሾክሿኪውን ነው።

 ቀጥለዉ ሰዓሊ እሸቱ ጥሩነህ  ‹‹አድዋ ላይ ማንነትን  ላይ አነቃቂ ንግግራቸዉ አሁን ባለዉ ማንነታችን መሰረቱ  ‹‹አድዋ›› በአተረፈልን የማንነት የጉዳይ ነዉ፡ ፡ ዛሬ የአደዋ ድል በማንነቱና በኢትዮጵያነቱ የማይደራደር ዜጋን ለመፍጠር

ያለዉን አስተዋጾ የወገኖቻችን መስዕዋትነት ኢትዮጵያዊነትን ከፍ ባለ ማማ ላይ ያሰቀመጠ ብሔራዊ ኩራታችን መሆኑ ልንዘነጋዉ የማይገባን ስለሆነ ሁላችንም በተሰራማነበት የሰራ ዘርፍ ሃላፊነት በመዉሰድ የተሻለ ታሪክ በመስራት ለመጭዉ ትዉልድ የሀገራችንን ገጽታ በመገንባት ለዜጎቿ ምቹ የሆነች ሃገር በመፈጠር እኛ ዉጭ ሀገር ሂደን ለመኖርን እንደምንመኘዉ ሁሉ የሌሎች ሀገር ዜጎች ሀገራችን ወደዋት ለመኖር ምርጫቸዉ እንዲያደርጓት በቀናነት መስራት ይጠበቅብናል ብለዋል፡፡በዕለቱ ከቀረበዉ መነባንብ ወስጥ ፡፡

ልጅህ አንኳን አድጎ በአምሳልህ እስከምትቃኘዉ

ላሊበላ እንዴት ተሰራ አክሱም እንዴት ቆመ ብሎ፡፡

ቢጠይቅህ በቅሎ ነዉ በል አዎ መሬት ሰንጥቆ ወጦ

እሱም ታምር ነዉ ይበል በታምራት ተቃኝቶ፡፡

ተረት አድረገዉ ሮሃ በሚባል ሀገር አንድ ንጉስ ነበር

ገና ከመወለዱ በኔዎች የተተለመ የወደፊት መንገዱ፡፡

እግዚሄር እጁን ይጫንበት መንፈስ ቅዱስ እፍ አለበት ከዚያ ምኑ ቅጡ በረከቱን ተቀባና የወደፊት ህይወቱን እንዲያቀና፡፡

እመነትን በእዉነት እንዲመራ ገና መላዕክቶች እጁን ሲነሳ ተረባረዉ

አክሱም ላሊበላ ፋሲልን ገነቡ እያልክ ተረተዉ ትንግርት አድረገዉ፡
፡

ያኔ አዕምሮህ ቆስሎ ተጃጅሎ ቆስሎ አይፈነዳ መግል ይዞ እንዳይጠነባህ

ትንግርት አድረገዉ እስኪ አንተን ልጠይቅህ ማንይሙት አንተን ማን ወለደህ፡፡

ያ የላሊበላ ቤተ መቅደስ ፊልፋይ ወይስ የአክሱም ሃዉልት የጠራበ

የፋሲልን  ግንብ ገንቢ ያ ስልጣኔን ቀድሞ የማለደ እዉን አንተን ወለደ እዉን እሱ አንተን ወለደ እዉን አንችን ወለደ እዉን እናንተን ወለደ፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ የታሪክ መምህር ዶክተር አየነዉ ማሞ ‹‹የአድዋ ድልና የታሪክ አሻራዉ ›› በሚለዉ ፅሁፋቸዉ የአድዋ ድል ታሪክ ምን መማር እንዳለብን በተለይ የአሁኑ ትዉልድ ኢትጵያ ክብሯን እንደጠበቀች ለመጭዉ ትዉልድ ለማሰተላለፍ አሁን ያለዉ ትዉልድ ያለፈበትን ትዉልዶች ታሪክ ማወቅ እንደሚጠበቅብን  በስፋት ተንትነዉ አቅርበዋል፡፡

ጀግናው ጊድን ገብሬ የሜዳው ዝሆን

ፈረሱን ጫኑለት ይነሳ እንደሆን

ወፍጮ ቢወቅሩት አይለሰልስም

በጊድን ግንባር ማንም አይደርሥም

የጊድን እኅት ምጥን ወይዘሮ

ጥይት አቀባይ እንዳመልማሎ

አቶ እያሱ በካፋ የተባሉ የታሪክ ነጋሪ ‹‹ቅደመ አደዋ ፣ ድህረ አደዋ›› የአድዋ ጦርነት ከመካሄዱ በፊትና ያለዉን የነጮች በጥቁሮች ላይ ያላቸዉን አመለካከት ጦርነቱ ከተካሄደ በኋላ ደግሞ ነጮች በጥቁሮች ላይ ያላቸዉን አመለካከት የቀየረ እና የጦርነቱ መነሻ መንስኤዎች ጦርነቱ ያስከተለዉን ወጤት በመጨረሻም ለጥቁር ህዝቦች የነጻነት ካባ ያጎናጸፈ ታሪካችን መሆኑን የታሪክ መጽሀፍትን መነሻ በማድረግ የአድዋ ጦርነት የታሪክ ሁነቶች በስፋት ዳሰሳ አድረገዋል፡፡




በዓሉ ዕለት ከቀረቡት ግጥም ወስጥ

ይድረስ ለባለዉለታዬ ለምዬ ምኒሊክ እንደምን ባጅተሃል

እኛስ ደህና አይድለም ዘረኝነት የሚሉት በሽታ ተጠናዉቶናል፡፡

የምን ዘረኝነት አልከኝ እሱስ እኔንም አልገባኝ ትዉለዱ ተረቷል

ለህገሩ ትቶ ለኔ ብቻ አድልቷል፡፡

ያኔ ደምህን ያፈሰስክላት

አጥንተህን የከሰከስክላት

ስጋህን የቆረስክላት

ዛሬ እናትነቷን እረስተዉ ቆራርጠዉ በሏት

ባይታወር ሁናለች ለሷ የሚያሰብ ልጅም የላት ፡፡

እና እንዳለችህ ልጄን ጠባቂየን

ከወራሪ ጠባቂዬን በ

ጸሎት አሳቢዬን

አምጡልኝ ብላለች

የቅፉ ቀን ደራሽዋን አንተን ትሻለች፡፡

አዎ አባታለም ናላት ያላንተ ምስኪን እናት ማንም የላት

ከመብረቅ ፍጠንና እንባዋን ጥረግላት ስቃይዋን በቃሽ በላት፡፡

አርበኝነት ለኢትዮጵያ አንድነት ያበረከተዉን ሚና በተመለከተ ፅሁፍ ያቀረቡት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ መምህሩ ዶክተር ሀይማኖት ዋሴ ‹‹የአበሻ ጀብዱ›› የሚል  መፅሀፍ ላይ መሰረት ያደረገ አቡቹ ሰለሚባል ወጣት የሰራዉን ጀብድ ወጣት አርበኞች በአድዋ ጦርነት ያደረጉትን አስተዋጾ በተመለከተ ሰፊ ሙሁራዊ ትንታኔ አቅርቧል፡፡

# ብዙዎችን ነፃ ያወጣው ነፃ የህግ አገልግሎት

በኢትዮጵያ በየአካባቢው የሚስተዋሉ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች የአገሪቱን ወጣቶች በበጎ ፍቃድ ስራዎች ላይ የመሳተፍ ልምዳቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ስለመምጣቱ አመላካች ተደርገው ሊጠቀሱ ይችላሉ። በተለይም ቀደም ባሉት ዓመታት በክረምት ወራት ብቻ ይከናወኑ የነበሩ የወጣት ተማሪዎች የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች አሁን አሁን በትምህርት መስጫ ወራቶችም ጭምር ሲከናወኑ ማየት እየተለመደ መጥቷል። ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ ተቋማትም በማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች ያላቸው አሻራ ትልቅ ነው፡፡ ከተቋማት መካከል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከማሰልጠንና ከጥናትና ምርምር ጎን ለጎን የማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው ይታወቃል፡፡ ለደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ ነፃ የህግ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው የደበረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከሚሰጣቸው የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች በቀዳሚነት ይጠቀሳል።




አቶ ዓለሙ ታየ
የህግ ትምህርት ቤት ዲን

ወይዘሮ ጤና መላክ የቸር-ተከል ቀበሌ  ነዋሪ የሆኑት የነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ተጠቃሚ ከሆኑትና በማዕከሉ ቅጥር ግቢ ካገኘኋቸው ተጠቃሚዎች መካከል አንዷ ናቸው። ወይዘሮዋ በሚች የትዳር አጋራቸዉ ቤተሰቦች መሬታቸዉን በጉልበት በመቀማታቸዉ በደል ቢደርስባቸዉም መሬታቸዉ መልሰዉ ማግኘታቸዉና የሚገባችውን ጥቅሞች ለማስጠበቅ በማዕከሉ የበጎ ፍቃድ አገልጋዮች ነፃ የህግ አገልገሎት ፡፡ስላገኙ ንብረታቸው እንዲመለስላቸው ተደርጓል፡፡ ይህንን የሚያደርገው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የነፃ የህግ አገልግሎት ማዕከል እንደሆነም ተጠቃሚዋ ይናገራሉ፡፡ የወ/ሮ ጤናን አናሳን እንጂ በዩኒቨርሲቲው የነፃ የህግ አገልግሎት ብዙዎቹ ነፃ ወጥተዋል በተለይም ሴቶች፣ ድሆች፣ ህፃናትና አረጋውያን፡፡

የነፃ የህግ አገልግሎቱ ለህብረተሰቡ እያበረከተ ከሚገኘው ፋይዳ በተጓዳኝ ከንድፈ-ሀሳባዊ ይልቅ በተግባር የመማር ወይም በፈረንጆቹ አባባል (Learning by doing) የሚባለውን የትምህርት ስነ ዘዴ እንዲከተል በተለይም በአገልግሎቱ እየተሳተፉ የሚገኙ መምህራን የመረጃዎች አቀራረብና የችሎት ክርክሮችን ጨምሮ ዘርፉ የሚጠይቀውን እውቀትና ልምድ እንዲያገኙ በማድረግ በኩል የጎላ ጠቀሜታ እያበረከተ እንደሚገኝ የአገልግሎቱ አስተባባሪ የሆኑት የህግ ትምህርት ቤት ዲን አቶ አለሙ ይናገራሉ።

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ቤት በየዓመቱ በሚያቅደው እቅድ እንደ ህግ ተቋም ከተሰጡት ተልዕኮዎች ውስጥ የማህበረሰብ አገልግሎት አንዱ ተግባሩ አድረጎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ ከዚህ ዉስጥ ቅድሚያ ሰጥቶ እየሰራ ያለዉ የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች መካከል ትምህርት ቤቱ የሚታወቀው በህግ ት/ቤቶች የሚሰጠዉ ነፃ የህግ አገልግሎት ነው፡፡



ወ/ሮ ጤና መላክ
ነጻ ህግ አገልገሎት ተጠቃሚ

ትምህርት ቤቱ ከነፃ የህግ ድጋፍ በተጨማሪ ለተለያዩ የፍትህ አካላት ማለትም አቃብያነ ህጎች፣ ዳኞች፣ ፓሊሶች፣ ማረሚያ ቤት አስተዳደርና ጠበቆች የተለያየ ስልጠና በማዘጋጀት ባለሙያዎች ከአዳዲስ የህገራችና አለም አቀፍ ህጎች እዉቅና የትርጉም ግንዛቤ እንዲኖራቸው እያደረገ ይገኛል፡፡ ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች የህግ ድጋፍ ሲፈለጉ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ጋርበመቀናጀት  ትምህርት ቤቱ የህግ ጉዳዮች ላይ አበክሮ እየሠራ ይገኛል፡፡ ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የፋይናንስ ጉዳይ የሚያመቻች ሲሆን ህግ ት/ቤት ደግሞ በተጠየቀው የስልጠና መስክ ላይ ተገቢ የሆነ የተሻለ ልምድና እውቀት ያላቸዉን መምህራን በመመደብ ስልጠና ይሰጣል፡፡

ትምህርት ቤቱ በእርግጠኝነት ውጤታማ የሆነበትና በኩራት ሰርተነዋል ብለው የሚያምኑት የማማበረሰብ አገልግሎት  አቅም ለሌላቸዉ  ሰዎች የነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት በመስጠታችን ነው፡፡ ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት የሚያገኙት በገንዘብ በኩል አቅም የሌላቸዉን የማህበረሰብ ክፍሎችን በችግር ምክንያት እነዚህ ማህበረሰቦች ፍትህ ማጣት የለባቸዉም ብለው የህግ ድጋፍ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡

ይህንን አገልግሎት ለማግኘት የድህነት ማስረጃ ከቀበሌ ማቅረብ የመጀመሪያ ቅድመ ሁኔታ ሆኖ በተለይም ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለአካል  ጉዳተኞች እና ለአረጋውያን አገልግሎቱ ይሰጣል፡፡ ነገር ግን ይህ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ብዙ ተግዳሮቶች የሚያጋጥሙ ሲሆን ተግዳሮቶቹ ከህግ ት/ቤት ውስጥም ከህግ ት/ቤት ውጭም የሚመነጩ ናቸው፡፡ ከት/ቤቱ የሚመነጬት ተግዳሮቶች መምህራን ሙሉ በሙሉ በነፃ አገልግሎቱን ለመስጠት ሙሉ ቁርጠኛ ያለመሆን አንዱ ነው፡፡ ይህ አገልግሎት በተፈጥሮ በጐ የመስራት ሰብአዊነት ያለው ባለሙያን ይጠይቃል፡፡  እንደ አቶ ዓለሙ ታዬ ገለፃ ‹‹አብዛኛዎቻችን መምህራን እኔን ጨምሮ አስተዳደጋችን ሰውን በነፃ ለመርዳት ፈቃደኛ ያለመሆን ችግር አለ፡፡ ይህ ችግር የብዙ ኢትዮጵያዊያን ችግር ነው ብየ አስባለሁ፡፡ የተቸገሩትን መርዳት ከምንም ገንዘብ ክፍያ በላይ እንደሚያረካ ስለማንገነዘብ ብዙ መምህራን ጉዳይ ለመያዝ ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ ቢይዙ እንኳን በትክክል የመከታተል ችግር ይታይባቸዋል፡፡››

ውጫዊ ተግዳሮቶች ደግሞ የዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አግልግሎት ዳይሬክቶሬት የሚጠበቅበትን አለመወጣት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አገልግሎቱን ለመስጠት በቂ በጀት ስለማይመደብላቸው መምህራን ከኪሣቸው ገንዘብ

አውጥተተው አገልግሎቱን ይሰጣሉ፡፡ እንዲሰራበትየተፈቀደን 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ ፕሮጀክት በጀት እንኳን አለቀቁልንም በዚህ ዓመት በዚህ ጉዳይ ላይ መምህራን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሰላቹ እንዲሄዱ በማድረጉ ብዙም አበረታች ሥራዎች አይታዩም፡፡ የራሳችን ቢሮ በየወረዳዎች አለመኖርና የፀሃፊ እና ጉዳይ የሚቀበል አለመኖር ሌላው ችግር ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ብዙ ጊዜ ኮንቲነር ቢሮ እገነባለሁ፣ ፀሃፊና የህግ ባለሙያ አሟላለሁ ቢልም እስከአሁን የገባውን ቃል በተለያየ ምክንያት ሊፈፅም አልተቻለም፡፡ ሌላው ዋናው ጉዳይደግሞ ከተጠቃሚዎች ጋር ይያያዛል፡፡ ይኸውም ድሃ ያልሆኑት ሁሉ በየቀበሌው ከሚገኙ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የድህነት ማስረጃ በማምጣት ጉዳያቸውን እንድንይዝ በማድረግ ስራ ጫና እንዲኖር አድርገውብናል፡፡ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ማስረጃን ለሚገባው ሰው እየሰጡ አይደለም፡፡

ቢሆንም በጥሩ ሁኔታ ለማህበረሰቡ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችል እንዲሟላለን ምንፈልገው ብዙ ነገር በመሆኑ እንዲሟሉልን የምንፈልገውን ለዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራር አቅርበናል፡፡ ት/ቤቱ በአጭር ጊዜ እንዲሆን የሚያስፈልገው ነገር  ነፃ የህግ ድጋፍን በበላይነት የሚመራ ህግ ት/ቤት ውስጥ ዳይሬክተር ያስፈልጋል፡፡ ይህን መዋቅር መፍቀድና ሰው እንዲመድብ ተጠይቋል፡፡ ይህ ከተሳካ አሁን ከሚሰራበት አሰራር የተሻለ ጥራት ያለዉ አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ ያምናሉ፡፡

ዩኒቨርሲቲው አሁን ባሉት ስምንት የነፃ የህግ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ላይ ፍርድ ቤቶች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ዩኒቨርሲቲው ቦታ በማስፈቀድ ኮንቴነር ማስቀመጥ ሙሉ ዕቃዎችን ለማሟላት በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ተሞክሮ በመውሰድ ቢሮ ውስጥ ባለጉዳይ የምትቀበል ፀሃፊ፣ እንዲሁም የህግ ባለሙያ መምህራን የሚያግዝ ለማሟላት ጥረት እየተደረገ ነው

ይህንን ዩኒቨርሲቲው አምኖበት የግንባታ ጨረታ ያወጣ ቢሆንም ብዙ መጓተት እየታየ ስለሆነ የሚመለከታቸው ትኩረት ሰጥተው እንዲያስጨርሱ የህግ ት/ቤት ይጠይቃል፡፡

የትምህርት ቤቱ ዲን አቶ ዓለሙ እንደተናገሩት የህግ ትምህርት ቤቱ ብዙዎችን ነፃ ማውጣት የሚችል የህግ አገልግሎት እንዲሰጥ በረጅም ጊዜ እንዲሟላላቸው የሚፈልጉትን  ነገር ት፣ምህርት ቤቱን በሰው ሃይል ማሟላት ነው፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ የሚያስተምሩት ህግና ስርዓትን በመሆኑ መምህራን ተደራራቢ ኮርሶችና የስራ ጫና እንዲኖራቸው በማድረግ የምንፈልገዉን ግብ ማሳካት አይቻልም፡፡ሙሉ የሰው ሃይል ካለን ግን መምህራን ለነፃ የህግ ድጋፍ የሚያግዝ ፕሮጀክት በመቅረፅ፣ ነፃ የህግ ድጋፎችን በመስጠት እንዲሁም ተማሪዎችን መምህራንን በሚሰሩት ችሎት ታዳሚ በማድረግ ሙሉ የሆነ የተግባርና የንድፈ ሃሳብ እውቀት እንዲኖራቸው ያግዝናል፡፡ መምህራን ለፕሮጀክት ቀረፃ፣ የችሎት ክርክር ልምድ ያላቸውን መምህራን በመምረጥ ትላላቅ ጉዳዮችን እንዲይዙና ተማሪዎች ሆነ አዳዲስ መምህራንም ዕውቀት እንዲያገኙ የሚያስችል ስራ በመስራት ጫና የማናደርግበት መምህር በመፍጠር የመምህራን ቁጥር እንዲጨምርእየተሰራ እንገኛል፡፡

ሙሉ መዋቅር ህግ ት/ቤት ተብሎ 2 እና 3 የPHD ተማሪዎችን ብቻ የሚስተምሩ ዩኒቨርሲቲዎች በአለም ላይ አሉ፡፡ በአጠቃላይ የዩኒቨርሲቲያችንን ራዕይ ለማሳካት ነፃ የህግ ድጋፍ የበላይ አመራሩ የሚደርስበት ስራ መሆኑን እናውቃለን፡፡ ህግ ት/ቤት ማህበረሰቡን ማገልገል “መነሻና መድረሻችን” ነው፡፡ ጉድለቶቻችንን በማረም ከምንም ነገር በላይ ደግሞ የማህበረሰቡን የፍትህ ጥማት ለማርካት የምንሰራቸውን ሥራዎች አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡

የግንባታ ሥራ....ከገፅ 41 የዞረ

በሌሊት ተቆርጦ መሰረቁ በስራው ላይ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ተገልጿል፡፡

በቡሬ ካምፓስ ያለዉን የግንባታ እንቅስቃሴ ስንመለከት ደግሞ 11 ህንፃዎች ተጠናቀዉ ርክክብ ተደርጓል፡፡ አንድ ጥልቅ የውሃ መስመር በማስቆፈርም እንደዚሁ አስተማማኝ ውሃ የተገኘ ሲሆን የመስመር ዝርጋታ ስራውም ተጠናቋል፡፡ ይሁን እንጅ የቡሬ ማዘጋጃ ቤት የመስመር ቦታውን ፈቅዶ ካስረከበ በኋላ የተወሰነውን ቦታ መንገድ በሚያሰሩበት ጊዜ ስላበላሹት (ስላቋረጡት) ለጊዜው አገልግሎት መስጠት አልቻለም፡፡ የምድረ ግቢዉን ስራ ውል ተሰጥቶ መጀመሩ ተገልጿል፡፡ የአጥርና የጠበቃ ማማ ስራዎችን  በጥሩ ሁኔታ እየተሰሩ እንደሚገኙ ዶ/ር ሳይህ ካሳው ገልፀዋል፡፡

የግንባታ ስራዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ የሚኖራቸውን ሚና ለመግለፅ በሁለተኛዉ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን መጨረሻ የተማሪዎችን የቅበላ አቅማም 17ሺ በማድረስ፣ ምቹ የመማሪያ ክፍሎች እንዲኖሩ በጥራት እየተሰሩ ያሉ እንደሆነ፣ በምርምር ዘርፉ ደግሞ መምህራን ተረጋግተዉ በመቀመጥ ለተማሪዎች ተገቢ ቦታ በመስጠት እንዲሁም ለአካባቢዉ ማህበረሰብ የስራ ዕድል በመፍጠር፣ በሆቴልና ቱሪዝም ስልጠናዎችንና የስራ ፈጠራ ክህሎት ስልጠና በመፍጠር አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡ በከተማ እየተገነቡ ያሉት ግንባታዎች ለማህበረሰቡ ከሚሰጡት አገልግሎት በተጨማሪ  ለከተማው ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንደሚያበረክቱ ተብራርቷል፡፡

የግንባታ ጥራት ክትትልን በተመለከተ በእያንዳንዱ ሂደት ላይ የሚከታተል ተቆጣጣሪ መሃንዲስ ስላለው በየቀኑ የቁሳቁሶችን ጥራት በተፈለገው መንገድና የጥራት ደረጃ መሄዳቸውን፣ የሚቀርቡ ቁሳቁሶችን በመፈተሽና መከታተል በመቻል፣ በግንባታ ፕሮጀክት ፅህፈት ቤቱም ጥብቅ ክትትል በማድረግ ጥራትን ለማስጠበቅ የተጠናከረ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ የአሸዋ ጥራት ችግርን ለመቅረፍ ከቡለን ድረስ ጥራት ያለው አሸዋ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ነገር ግን ውድድሩ በግልፅ ጫረታ ስለሚወጣ አቅም ያለውም የሌለውም ተወዳድረው ከገባ በኋላ በሚከሰተው የተቋራጮች የፕሮጀክት ማኔጅመንት፣ የማቴሪያሎች የዋጋ ንረት ፣ የምንዛሬ ችግርና መሠል ችግሮች ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያለመፈፀም ችግር እየታየ ይገኛል፡፡ ይህን ችግር ለመፍታትም ተከታታይ የሆነ የስራ ክትትልና ድጋፍ ለአቅራቢዎች ዋስትና እስከመውሰድ ድረስ እየተደረገ ግንባታዎችን ለማስጨረስ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

በመጨረሻም በተለይ በኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በኩል ህጐችን በመከለስ፣ ተቋራጮችን በመገምገም፣ የአፈፃፀም ሪፖርት ተቀብሎ ድክመት ያለባቸውን የያዘውን ፕሮጀክት ሳያጠናቅቅ ሌላ ላይ እንዳይሳተፍ በማድረግ፣ የሶስትዮሽ የግምገማ መድረክ በማዘጋጀት (አማካሪ፣ ተቋራጭና አሰሪ) የአማካሪ ድርጅቶችንም አሠራርና መመሪያን በመፈተሽ በኮንስትራክሽን ዘርፉ የተሻለ አፈፃፀም ማስመዝገብ እንደሚገባ ዶ/ር ሳይህ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

# ‹‹ዩኒቨርሲቲውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ሰራተኛ በባለቤትነት ስሜት መስራት አለበት››

**አቶ መላኩ ጥላሁን**

**የለውጥና መልካም አስተዳደር ዳይሬክተር**




አቶ መላኩ ጥላሁን
የለውጥና መልካም አስተዳደር ዳይሬክተር

በሀገራችን የሚታየውን የመልካም አስተዳደር፣ የሙስና፣ የፍትሕ እጦት፣ የኪራይ ሰብሳቢነትና ተዛማጅነት ያላቸውን ችግሮች ለማስወገድ በብሔራዊ ደረጃ የተጀመረው ትግል የተጠበቀውን ያህል ባይራመድም የተወሰኑ ለውጦችን ማሳየት ግን ችሏል፡፡ የመልካም አስተዳደር ችግርን በመፍታት በመንግስታዊ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና አስተዳደሮች ውስጥ ሕዝብን በማገልገል ረገድ የታየው ሰፊ ችግር ከብልሹ አሰራርጋር በሰፊው የተቆራኘ በመሆኑ ይህን ትግል በስፋት በማካሄድ ውጤት ማምጣት የሚቻለው በዋነኛነት ሰፊውን የሕብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ ነው፡፡

ወጣቶችን ከትምህርት ቤት ጀምሮ በማስተማር፣ በየደረጃው ኮትኩቶ አስተሳሰባቸውን መቅረጽን ይጠይቃል፡፡ በተለያየ የኃላፊነት ደረጃ ከታች እስከ ላይ የሚገኙትን አስቀድሞ የሚጠልፈው የኪራይ ሰብሳቢነት ተግባር የሚረማመደው መልካም አስተዳደርን በመደፍጠጥ ነው፡፡ የመልካም አስተዳደር ችግር ለበርካታ ማሕበራዊ ችግሮችም መንስኤ ነው፡፡ ሰላምና መረጋጋትን ያደፈርሳል፤ የሕብረተሰሰቡን ማሕበራዊ ሕይወትና መስተጋብር ያስተጓጉላል፡፡ የመልካም አስተዳደር ችግር በሕብረተሰቡ ውስጥ ገኖ ሲሰፍን ለሁከት፣ ለብጥብጥና ለትርምስ መነሻ ይሆናል፡፡ በሀገራችን በመልካም አስተዳደር ችግር መንስኤነት የተፈጠሩት ችግሮች ሌሎች ብዙ ችግሮችን ሲወልዱ የተመለከትነውም ለዚሁ ነው፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተቋማዊ ለዉጥና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ መላኩ ጥላሁን በ2011 ዓ.ም በመልካም አስተዳደር የተሰሩ ሰራዎችን በተመለከተ አነጋግረን የሰጡንን መልስ እንደሚከተለዉ አቅርበነዋል፡፡

2011 ዓ.ም ክፍሉ በዋናነት ካከናወናቸው ተግባራት መካከል ነባርና የአገልግሎት ዘመናቸውን የጨረሱ አመራሮች በአዲስ የመተካት ስራ ተሰርቷል፡፡ ይህንን ለማድረግም በዩኒቨርሲቲው የማኔጅመንት አባላት መመሪያ አዘጋጅቶ በማፅደቅ በፊት ይነሱ የነበሩ ችግሮችን ማለት በፊት በነበረዉ አሰራር ሁሉም የኃላፊነት ቦታዎች በሹመት ይሰጥ የነበረ ሲሆን አሁን ግን ይህንን አሰራር በመቀየር በ2010 ዓ.ም ዓመት ከ90% በላይ የኃላፊነት ቦታዎች በምርጫ እንዲያዙ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል እያንዳንዱ የዩኒቨርሲቲ ሰራተኛ በክፍሉ እቅድ መሰረት መመራት መቻሉን ለማረጋጥና ድጋፍ ለማድረግ የሱፐርቪዥርን ቡድን በማቋቋም ከሌሎች ክፍሎች ጋር በመሆን ክትትል አድርገናል፡፡ የሱፐርቪዥሮኑ ዋና አላማ ሁሉም ሰራተኛ ስራውንና ኃላፊነቱ አዉቆ ቀልጣፋና ውጤታማ ስራ እንዲሰራ ለማድረግ ሲሆን በዚህም መሰረት ግብረ መልስ እና ችግሮች በታየባቸዉ ክፍሎች የማስተካከያ እርምጃ ተወስዷል፡፡

ከላይ እንደገለጽኩት በ2011 ዓ.ም አዳዲስ አመራሮች ወደ ኃላፊነት ከመምጣታቸው ጋር ተያይዞ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በትጋትና በብርታት እንዲወጡ ብሎም ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ስልጠናዎችና የማነቃቂያ ንግግሮች በተጋባዥ እንግዶች እንዲሰጥ አድርገናል፡፡ በተለይም በአመራርነትና የስራ አመራር ክህሎት ዙሪያ ታዋቂ ምሁራንን በመጋበዝ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ በዚህም ሁሉም የተሰጠውን ኃላፊነት በተቋም ደረጃ በተገቢው መንገድ እንዲወጣ ከማድረግ አንፃር ትልቅ ውጤት አስገኝቷል ማለት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ለዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ሰራተኞች አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በካይዘን ጽንሰ ሀሳብና አተገባበር ዙሪያ ተከታታይ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍንና ምቹ የስራ ሁኔታ እዲፈጠር ከማድረግ አንጻር የተለያዩ ስራዎችን የሥራ ክፍሉ እያከናወነ ይገኛል፡፡ በተለይም በዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ሰራተኛ ዘንድ ተግባራዊ የሆነውን የሥራ ነጥብ ምዘና ጋር ተያይዞ የተነሱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በአስቸኳይ እንዲቀረፉ ተሰርቷል፡፡ እንደአቶ መላኩ አነጋገር ‹‹ከአስተዳደር ሰራተኞች የተነሱት ሁሉም ጥያቄዎች ተገቢነት አላቸው ብለን ባንወስድም ተገቢ የሆኑትን ግን ከሚመለከተው አካል በመነጋገር ፈጣን ምላሽ እንዲሰጥ አድርገናል፡፡››

የዩኒቨርሲቲው ያስቀመጣቸውን ተልዕኮዎች እንዲሳኩና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ለማድረግ ክፍላችን የተለያዩ ስራዎችን ሲሰራ የቆየ ሲሆን ሁሉም በሃላፊነት ቦታ ያሉትን አመራሮችና ሰራተኞችን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የወጡ መመሪያዎችን መሰረት አድርገው ስራቸውን እንዲሰሩ ለማድረግ በትኩረት ስንሰራ ቆይተናል፡፡ ይህን በማድረግ የመልካም አስተዳደር መርሆች በተለይም ግልጸኝነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ለማድረግ መሰረታዊ የሆኑ ስራዎችን በመስራት ውጤት አስገኝቷል፡፡

ተቋማዊ ለውጥ ጽ/ቤት በዋናነት ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል ዩኒቨርሲቲውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚያስችሉ አሰራሮችን በመዘርጋትና ያሉትንም አሰራሮች በመከለስ ምቹ የስራ ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ ላይ ያተኮረ ስራ ነው፡፡ በተጨማሪም ከተለያዩ የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች የሚነሱ ቅሬታዎችንና የመልካም አስተዳደር ክፍተቶች ሲከሰቱ የማጣራት ስራ በማድረግ የህግ የበላይነት እንዲረጋጥ ማድረግ ትልቁና ዋነኛው የምንሰጠው አገልግሎት ነው፡፡

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በተለያዩ ክፍሎች የሚሰሩ ሰራተኞች አቅም ለማጎልበት የድጋፍና ክትትል ሥርዓት መዘርጋት ከምንሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ሌላው ዩኒቨርሲቲውን ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የተለያዩ የስራ ክፍሎችን በአዲስ መልኩ እንዲፈተሹ በማድረግ አዲስ የመዋቅር ለውጥ ማድረግ ክፍሉ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚከሰቱ የመልካም አስተዳደርና የህግ ጥሰቶችን ለመከላከል ያከናወነው ነገር በመጀመሪያ የተላለፉት ውሳኔዎች ከተቀመጠው መመሪያ አንጻር በደንብ የመፈተሽ ስራ ሲሆን በቀጣይም እነዚህን ውሳኔዎች ከመመሪያው አንጻር የሚጣረሱ ሆነው ከተገኙ በክፍላችን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል በጽሁፍም ሆነ በአካል እናሳውቃለን፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ጊዜ የተከሰቱ ችግሮች በቀጣይ እንደይደገሙ እና አሰራሮች ህግንና ህግን ብቻ መሰረት አድርገው እንዲሰሩ ክፍሉ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ክትትልና ድጋፍ እናደርጋለን፡፡

በዚህ የበጀት አመት ከተለያዩ የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ጥቆማዎችን አብዛኛዎቹ ከተደረገው የስራ ነጥብ ምዘና ምደባ ጋር የተገናኙ ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ከስራ ክፍሎች የደረሱ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ አግኝተዋል ማለት ይቻላል፡፡ ባደረግነው የማጣራት ስራ መሰረት ችግሮች የመነጬት ከምደባ ጋርና ሰራተኞች የሚፈልጓቸውን ክፍሎች በደንብ ጠንቅቀው በማወቅ አገናዝቦ ካለመሙላትና እንዲሁም የምደባ ኮሚቴ ሁነው ሲያገለግሉ የነበሩ ባለሙያዎች ኃላፊነታቸውን በደንብ ካለመወጣት ጋር የሚያያዙ ችግሮች ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡

በመጨረሻም ዩኒቨርሲቲውን ወደ ምንፈልገውና ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ሰራተኛ በባለቤትነት ስሜት መስራት አለበት፡፡ በተለይም መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ከተፈለገ የሁሉም ተሳተፎ ትልቁን ድርሻ ሊይዝ እንደሚችል መረዳትና አብሮ ተባብሮ መስራትን ባህል ማድረግ አለብን ብየ አስባለሁ፡፡ ከምንም በላይ በአሁኑ ሰዓት ግቢያችንም ሆነ ሀገራችን የሚያስፈልጋት ሰላም ስለሆነ ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ ሁላችንም የበኩላችን ንኃላፊነት እንድንወጣ መልክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡

# የፋይናንስ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ

መንግስት ከፍተኛ የሰው ሃይል ከሚያፈራባቸው ተቋማት መካከል አንዱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት የራሳቸው የሆነ ተልዕኮ እና ራዕይ ያላቸው ሲሆን ይህን ለማስፈጸም የሚያግዙ ከገንዘብ እስከ ተለያዩ ድጋፎች በመንግስት በኩል ይደረጋል፡፡ ይህ ድጋፍ ደግሞ የመማር ማስተማሩን ስራ ለማሳለጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አንዱ ሲሆን የፋይናንስና በጀት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ለዩኒቨርሲቲው በ2011 ዓ.ም ዕቅድ ማስፈጸሚያ ከመንግስት ግምጃ ቤት ከተመደበለት እና ከውስጥ ገቢ ከሚያመነጨው ዓመታዊ በጀት አጠቃቀም ምን እንደሚመስ እናስቃኛችኋለን፡፡

| ተ.ቁ | ፕሮግራሞች | ለዓመቱ ከገ/ሚ/ር ጸድቆ የተመደበ በጀት | ዝውውር | | የተስተካከለ | ወጭ | ግዴታ የተገባበት | ከወጭ ቀሪ | አፈፃፀም በመቶኛ (%) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የተጨመረ | የተቀነሰ | | | | | |
| 1 | መደበኛ ድምር | 499,700,000.00 | 67,725,992.46 | 38,286,021.74 | 529,139,970.72 | 527,274,369.92 | | 1,865,600.80 | 99.65 |
| 1.1 | ሥራ አመራርና አስተዳደር (381/01/01) | 127,901,300.00 | | | 127,901,300.00 | 127,601,359.06 | | 299,940.94 | 99.77 |
| 1.2 | መማር ማስተማር/ አገልግሎት መስጠት (381/02/01/) | 147,826,400.00 | 43,478,918.72 | 13,238,948.00 | 178,066,370.72 | 177,224,379.43 | | 841,991.29 | 99.53 |
| 1.3 | መማር ማስተማር /ተማሪ አገልግሎት መስጠት (381/02/02) | 193,742,300.00 | 8,907,217.00 | 9,957,217.00 | 192,692,300.00 | 192,129,564.98 | | 562,735.02 | 99.71 |
| 1.4 | የውስጥ ገቢ | | | | | | | | |
| | መማር ማስተማር/ አገልግሎት መስጠት (381/02/01/) | 4,495,000.00 | | | 4,495,000.00 | 4,461,075.98 | | 33,924.02 | 99.25 |
| | መማር ማስተማር አገልግሎት መስጠት (381/02/02) | 4,305,000.00 | | | 4,305,000.00 | 4,268,848.59 | | 36,151.41 | 99.16 |
| 1.5 | ጥናትና ምርምር ማካሄድ | 17,555,000.00 | 2,350,000.00 | 810,000.00 | 19,095,000.00 | 19,040,418.65 | | 54,581.33 | 99.71 |
| 1.6 | የምርመር ውጤቶችን ማሰራጨትና ማሳተም | 1,095,000.00 | 303,829.74 | 693,829.74 | 705,000 | 704,931.20 | | 68.80 | 99.99 |
| 1.7 | ማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት | 2,780,000.00 | 431,896.00 | 1,331,896.00 | 1,800,000.00 | 1,843,792.01 | | 36,207.99 | 98.07 |
| 2 | የካፒታል በጀት | 460,000,000.00 | 129,333,549.00 | 49,333,549.00 | 540,000,000.00 | 539,129,246.98 | 91,918,934.52* | 870,753.02 | 99.84 |
| | ጠቅላላ መደበኛ እና የካፒታል በጀት | **959,700,000.00** | **197,059,541.50** | **87,619,570.74** | **1,069,139,970.72** | **1,066,403,617.90** | 91,918,934.54 | **2,736,353.82** | **99.74** |

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የ2011 በጀት ዓመት የበጀት ምደባና አጠቃቀም ሪፖርት

# የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ አስተዳደር ሰራተኞችን የጄኤጂ ምደባ አካሄደ



አቶ መንግስቴ ቢተው
የሰው ሃብት ሥራ አመራር ዳይሬክተር

JEG ወይም የነጥብ ስራ ምዘናና ደረጃ አፈፃፀም ማለት JEG (Job Evaluation and Grading) ማለት ስራን መመዘንና ደረጃ ማውጣት ማለት ነው፡፡ የነጥብ ስራ ምዘናና ደረጃ ማውጣት ማለት ስራውን በተገቢው መንገድ በመመዘን የሚሠጠውን ነጥብ መሰረት በማድረግ እንደ ስራው ክብደትና በሚሠጠው ነጥብ አማካኝነት ደረጃ ማውጣት ማለት ነው፡፡ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2010 ዓ.ም ጀምሮ ባስጠናው ጥናት መሠረት በ2011 ዓ.ም የአስተዳደር ሠራተኞችን ጅኤጂ መድቧል፡፡ ይህን አስመልክቶ የሰው ሃብት ልማት አስተዳደር ዳይሬክተር አቶ መንግስቴ ቢተውን አነጋግረን የሚከተለውን መጣጥፍ አዘጋጅተናል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሠራተኛውን የJEG ምደባ ሲቪል ሰርቨስና የሠው ኃብት ልማትሚኒስቴር ባወጣው በነጥብ ስራ ምዘናና ዘዴ የመንግሰት ሠራተኞች የድልድል መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ሆኗል፡፡ በዚህ መሰረት የዩኒቨርሲቲያችን የአስተዳደር ሠራተኛ በምደባ መመሪያው ላይ ግልጽ በማድረግ መግባባት ላይ በመድረስ

- በሠራተኞች በተመረጡ 2 አባላት፣
- በከፍተኛ አመራሩ በተመረጡ 3 አባላት፣ እና
- ከሠው ሃብት ስራ አመራር በተወከለ 1 ድምጽ አልባ ፀሐፊ አማካኝነት ነው ምደባ የተከናወነው፡፡ ወደ ምደባው ከመገባቱ በፊት ሠራተኞች በቀጥታ የመረጧቸው ሠራተኞችና መዳቢ ኮሚቴው ቀድመው የJEG ምደባ ያከናወኑ ዩኒቨርሲቲዎችና የፌደራል ተቋማት ተሞክሮ በማምጣት ተሞክሮውን በመቀመር ወደ ስራ ገብተናል፡፡ በሂደቱም ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮች ሲገጥሙ የሲቪል ሰርቪሲና የሠው ሃብት ልማት ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለሙያዎች በስልክና በአካል በመገኘት በሚሠጡን ማብራሪያዎች ላይ በመመርኮዝ የተፈፀመ ምደባ ነው፡፡ ምንም እንኳ JEG የምደባ መመሪያ በራሱ ክፍተቶች ያሉበት ቢሆንም ክፍተቶችን በተቻለ መጠን በመሙላት አብዛኛውን ሠራተኛ ተጠቃሚ ሊያደርግ በሚችል መልኩ እና ተገቢውን ሠራተኛው በተገቢው ቦታ በመመደብ ስራንና ሠራተኛን ለማገናኘት ተችሏል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አሠራር መመሪያውንና መመሪያን ብቻ መሰረት አድርገን በመስራታችን ሠራተኛው ረክቷል ብለን ነው የምናምን፡፡ ነገር ግን መመሪያው በፈጠረው ክፍተት አማካኝነት ያልረኩ ሠራተኞች ይኖራሉ፡፡ ይህ ደግሞ ሊስተካከል የሚችለው ይህን የJEG ምደባ ሠርቶ በማጠናቀቅ በሂደቱ የተፈጠሩ ክፍተቶችን ሲቪል ሰርቪስ በቀጣዩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የማረም (የማስተካከል) ስራ ይሠራል፡፡ ይህ ክፍተት ከተሞላ በኋላ ጠቀሜታውን በመመዘን ቀጣይነቱ የማረጋገጥ ስራ ይሠራል፡፡ ይህ ማለት ይህ ምደባ የመጨረሻ ነው ማለት ሣይሆን ቀጣይነት ያለውና ችግሮች እርማት እየተደረገባቸው አገሪቱ ከምትደርስበት የዕድገት ደረጃ ጋር እየተገናዘበ የሚፈፀም ሲሆን በምደባው ቅር የተሠኑ ሠራተኞች ቅሬታቸው በሂደት መልስ ያገኛል ብለን እናምናለን፡፡

በምደባው ቅር የተሰኙ ሠራተኞች የቅሬታ ስርዓቱን ተከትለው እስከ ሲቪል ሰርቪስ ፍ/ቤት ድረስ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ አንዳንዶች ያቀረቡት ቅሬታ ተገቢነት ያለው በመሆኑ አስተዳደር ፍ/ቤቱ እንዲወዳደሩ ወስኖላቸው በውሣኔው መሠረት እያወዳዳርን በመመደብ ላይ እንገኛለን፡፡ ለአንዳንድ ሠራተኞች የወሰነላቸው ደግሞ እጅግ ከመመሪያው ውጭ በማፈንገጥ ያልተገባ ስራ ልምድ እንዲያዝላቸው እና እንዲወዳደሩ አስተዳደር ፍ/ቤቱ ወስኗል፡፡ ይህም ቢሆን በፍ/ቤቱ ውሣኔ መገዛት ስላለብን ባናምንበትም የተወሰነላቸው እንዲወዳደሩ አድርገናል፡፡ በውድድሩ መሰረት ከዚህ በፊት መዳቢ ኮሚቴው መድቧቸዉ ከአሁን ቀድመው የያዙትን ቦታ እንዲለቁ ሲደረግ በሚገኘው ክፍት ቦታ መመሪያውን ተከትለን የምንመድባቸው ሲሆን በምደባው ቅር ከተሰኑ ዩኒቨርሲቲው አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ቅሬታቸውን ለሚመለከተው አካል ስርዓቱን ተከትለው እንዲያቀርቡ ያደርጋል፡፡ የዩኒቨርሲቲያችን የአስተዳደር ሠራተኞች ለመማር ማስተማሩ ስራ አጋዥ እንደ መሆናቸው መጠን መንግስት የጣለባቸውን ኃላፊነት በተገቢው በመውጣት የትምህረት ጥራት እንዲያረጋግጥ እርስ በዕርስ በመቻቻልና



አቶ ተስፋ በዛ
የህግ አገልግሎት ዳይሬክተር

በመመካከር ዜግነታቸውን እንዲያበረክቱ አቶ መንግስቴ ቢተው አሳስበዋል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህግ አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ተስፋ በዛ ሲሆኑ የነጥብ የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ድልድል አፈፃፀም /Job Evaluation and Grading /JEG/ ማለት የሲቪል ሰርቪሱን ስራዎች ለመመዘን የሚያስችሉ መስፈርቶችን በመጠቀም ስራዎችን መዝኖ በሚያገኙት አጠቃላይ ነጥብ መሠረት ደረጃ የማስቀመጥና በዚህ መሠረት ሰራተኞችን በውጤት መዝኖ በመመደብ ሥራንና ሰራተኛን በማገናኛት ተወዳዳሪነት ያለው ውጤታማ ስራ በመፈፀም የሃገርን ኢኮኖሚ በማሳደግ የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ሲሆን ለእኩል ስራ እኩል ክፍያን ወደ ፊት ሊያስፍን ይችላል በሚል እሳቤ ላይ የተመሰረተ የሰው ሀይል /ሃብት/ ሪፎርም ሂደት ነው፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲም ያሉትን የአስተዳዳር ሠራተኞች የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በኢ.ፌዲሪ አዋጅ ቁጥር 16/2008 አንቀጽ 17 መሠረት በተሰጠው ስልጣንና ተግባር የሰው ሀብት ሪፎርሙን ለመተግበር ያመች ዘንድ ባዘጋጀው

ግንቦት 2008 ዓ/ም  የአፈፃፀም መመሪያንና ይህንን ለማብራራት ባወጣቸው ተከታታይ አግባብነት ካለው የሰራተኛው ስራ ልምድ ጋር በማነፃፀር በኮሚቴው ከተፈረጅና አግባብ የስራ ልምድ ያላቸው እንዲለዩ  ከተደረገ በኋላ ቀደም ሲል በተሰጣቸው የስራ አፈፃፀምና ማህደር ጥራት፣ ይዘውት የነበረው የስራ ደረጃ የፓሊሲ አፈፃፀም እና በዳይሬክተር ደረጃ ላሉት መደቦች በበላይ የተቋሙ አመራሮች የሚሰጥን ውጤት ጨምሮ የሚሰጡ ነጥቦች በመመሪያው መሠረት በአግባቡና በጥንቃቄ ተደምረው ሰራተኞች መርጠው ከተወዳዳሩበት ሁለት የስራ መደቦች ውስጥ ከትልቁ የስራ ደረጃ ጀምሮ ወደ ታች በማወዳደር አብላጫ ውጤት ያመጡትን በቅደም ተከተል ቀደም ሲል በፀደቁት የስራ መደቦች ላይ በመደልደል /መመደብ/ የተፈጸመ ነበር፡፡ በዚህ  ሂደት  ዋናው ካምፓስና የቡሬ ካምፓስን ጨምሮ 1376 ሰራተኞች ውስጥ 1100 /80 %/ የሚሆኑትን በምርጫቸው ተመድበዋል 275 /20%/ የሚሆኑት ሰራተኞች ደግሞ ምርጫቸውን አላገኙም፡፡ ይሁን እንጅ በተቻለ መጠን መመሪያውና የዚሁ ማብራሪያ በሚፈቅደው መሠረት ቀደም ሲል ይዘውት ከነበረው የስራ መደብና የትምህርት ዝግጅት አቻ ደረጃ ላይ ባለ ክፍት የስራ መደብ ላይ እንዲመደቡ የተደረገ ሲሆን ጥቂቶችም ዝቅ ባለ መደብ ላይ በJEG ኮሚቴው እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡

ያልተመደበ ሰራተኛም የለም፡፡ 35 የሚሆኑ ሠራተኞች በተደረገው ምደባ ላይ አስተዳደራዊ በደል ደርሶብናል በሚል ለአብክመ እንባ ጠባቂ ተቋም አቤቱታ አቅርበው ዩኒቨርሲቲውም መልስ እንዲሰጥ ተጠይቆ ያቀረቡት ቅሬታ በማስረጃም ሆነ በህግ ያልተደገፈ በመሆኑ ባለው JEG ምደባ ማስረጃ መመሪያን በማስደገፍ መግለጫ እንድያቀርቡ በተጠየቀው ጊዜ በጽሁፍ መግለጫ አቅርቧል፡፡ ከዚህም ባሻገር የኮሚሽኑ ባለሙያ ቡድን በአካል ከተቋሙ ድረስ በመምጣት የምደባ ዶክመንትና ማስረጃዎችን አቤቱታ አቅራቢዎች ባሉበት በመመልከትና በመማማር ምንም አይነት የመብት ጥሰትም ሆነ የአስተዳዳር በደል እንዳልተፈፀመባቸው በማረጋገጥ ተመልሷል፡፡ ቢሆንም እነዚህን ጨምሮ 184 ሰራተኞች ለተቋሙ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይህንኑ ቅሬታቸውን አቅርበው ታይቶላቸው ለፕሬዝዳንቱ ከቀረበው የውሳኔ ሃሳቦች ውስጥ የ1 ሠራተኛ ብቻ ተቀባይነት ሲያገኝ ሌሎች ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ይህን የፕሬዝዳንት ውሳኔ በመቃወም 35 የሚሆኑት ቅሬታ አቅራቢዎች ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍ/ቤት ይግባኝ ጠይቀው ዩኒቨርሲቲውም ጥያቄያቸውን በፍትህ አደባባይ እስከ መጨረሻው ለማረጋገጥ ቀደም ሲል በገባው ቃል መሠረት የተጠየቀውን ማስረጃ ሁሉ በቅንነት በማቅረብ ጉዳዮች ከታዩ በኋላ የ30 ሰዎች ጉዳይ ተቀባይነት የላቸውም፤ ምደባው የተፈፀመው በህጉ በተቀመጠው JEG መመሪያና ማብራሪያዎች መሠረት ነው ተብሎ ውሳኔ ሲሰጣቸው 5- ባለጉዳዎች ግን የስራ ልምዳቸው ለመደቡ አግባብነት የላቸውም በሚል በ JEG ኮሚቴው ተፈርጆ በዚህ መደብ ላይ በውጤት እንዳይወዳደሩ መደረጉ አግባብነት የለውምና ቀደም ሲል ለውድድር ለመረጡት መደብና አሁን ቅሬታ ላቀረቡት የስራ መደብ ከሌሎች ቀደም ሲል በምርጫቸው ለውድድር ከሞሉት ሠራተኞች ጋር እንደገና እንዲወዳደሩ ካሸነፉም እንዲመደቡ በሚል ውሳኔ ሰጥቷል፤ ዩኒቨርሲቲውም ሁሉንም የአስተዳደር ፍ/ቤት ውሳኔዎች በቅንነት ተቀብሎ አስተናግዷል፡፡ ከመነሻ እስከ መጨረሻው የቅሬታ ክርክሩ ውጤት ሲመዘን 0.36% የሚሆነው ወይም በቁጥር -5 የሚሆኑ ሰራተኞች በአስተዳደር ፍ/ቤቱ ውሳኔ መሠረት እንዲስተካከልላቸው ተደርጎ ተመድበዋል፡፡ ይህም ቢሆን በሌሎች ተመዳቢዎች ላይ በማፈናቀል ሌላ የቅሬታ ምንጭ መሆኑ ግን አልቀረም፡፡ ስለሆነም የገጠሙት ችግሮች መመሪያው ራሱ ካሉበት ክፍተቶች  መነሻነት ነው፡፡ ለክፍተቶችም የሚመለከተው የደንቡ አውጭ አካል እንዲስተካከሉ ሃሳብ ቢቀርብም በፍጥነት ለማስተካከል ባለመፈለጉ የተፈጠሩ ናቸው፡፡

በጥቅሉ ሲታይ እንደ ተቋም ጥሩ አፈፃፀም ነበረው፤ ከመመሪያው አንፃር ሲታይ ሰራተኞችንም ያረካ ይመስለኛል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለውም ኮሚቴው ስራ ከመጀመሩ በፊት በመመሪያዎቹ ላይ የግልፅኝነት ግንዛቤ መያዙ በተደጋጋሚ መመሪያውን እንዴት በጥንቃቄ ምርጫቸውን መምረጥና መወዳዳር እንደሚገባቸው ለሠራተኞች ስብሰባዎችንና ውይይቶች መደረጋቸው ከውድድር በፊት ከ100% ያላቸውን ውጤትና የስራ ልምድ በማስታወቂያ ለሁሉም ግልጽ መደረጉ ይመስለኛል፡፡

እንደ አቶ ተስፋ እምነት በምደባው አብዛኛው ሰራተኛ ረክቷል፤ እጅግ ጥቂት ከሆኑት በስተቀር፡፡ ይህም ቢሆን ሪፎርሙ ባንዴ ተሰርቶ የሚበቃ አይደለም ስላልሆነ በትግበራው ላይ የታዩ የመመሪያና የአፈፃፀም ችግሮች እንደግባት ተይዘው በሀገር ደረጃ እንደገና ሪፎርም ይደረግባቸዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ቀጣይነት ባለው ሂደት ቀሪ ችግሮች ይስተካከላሉ ብየ አምናለሁ፡፡ ቅሬታ ያቀረቡ ሰራተኞች ቅሬታ ስንመለከት አብዛኛዎቹ የስራ ልምድ መስፈርቱ "አግባብነት" ያለው የስራ ልምድ ብቻ መጠየቅ አልነበረበትም ወይም በሌላ አገላለፅ ማንኛውም የስራ ልምድ ለማንኛውም የስራ መደብ ውድድር ሊያዝ ይገባል የሚሉ ናቸው፡፡ ጥቂቶች ደግሞ የሚፈለገውን የትምህርት ዝግጅት እስኳሟላን ድረስ የስራ ልምድ መጠየቁ አስፈላጊ አይደለም የሚሉ ናቸው ይላሉ የህግ አገልግሎት ዳይሬክተሩ፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ የሰው ሀብት ልማት ባለሙያ አቶ ግርማ አበበ እንኳሆነ  በነጥብ የስራ ምዘና ዘዴ የተመዘኑና ደረጃ በወጣላቸው የስራ መደቦች ላይ ተገቢውን ሠራተኛ በተገቢው ቦታ የመመደብ ሂደት ነው፡፡ ሆኖም የሠራተኛው የጅኤጅ ምደባ ሠራተኞችን በግልፀኝነት፣ በፍትሃዊነትና በተጠያቂነት የተደረገ ምደባ መሆኑንና በአብዛኛው ሠራተኛ በምርጫው መሠረት የተመደበበት እንደሆነ አቶ ግርማ ያምናል፡፡ በተጨማሪም 75% የሚሆነው ሠራተኛ የረካበትና አንዳንድ ሰራተኞች ግን ጥናቱ ላይ በተቀመጠው መሠረት ማለትም የትምህርት ዝግጅቱን አሟልተው የስራ ልምዱን ሳያሟሉ የቀሩ የስራ ልምድን አሟልተው ደግሞ የተቀመጠውን የትምህርት ዝግጅት ባለማሟላታቸው ምክንያት ቅሬታ የቀረቡበት በመሆኑ ጥቂቶች ያረኩበት ሁኔታ መኖሩን ይናገራሉ፡፡ የሠራተኛው ቅሬታ በአብዛኛው በዚህ የትምህርት መስክ ዲግሪ ስላለኝ እዚህ መደብ ላይ መመደብ አለብኝ የሚል ከመሆኑ ጋር በተያያዘና የድልድል አፈፃፀም መመሪያው ላይ የተቀመጠው ደግሞ የትምህርት ዝግጅትም ቢኖራቸው ተፈላጊውን የስራ ልምድ ሳያሟሉ ቀርተው በምርጫቸው ያልተመደቡ እና አንዳንዶች ደግሞ በተመሳሳይ የስራ ልምድ አልተያዘልንም የሚል ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ባቀረቡት ቅሬታ መሠረት በመመሪያው መሠረት እያንዳንዱ ቅሬታ አቅራቢ ሠራተኛ ምላሽ አግኝቷል፡፡

የዩኒቨርሲቲውን ራዕይ ለማሳካት የሠራተኞች የነጥብ የስራ ምዘና ዘዴን በሚገባ እንዲጠና በማድረግ የዩኒቨርሲቲውን የአስተዳዳር ሠራተኞችን በምደባ ሂደቱ ላይ በተለያየ ጊዜ ስልጠናዎችን በመስጠት ሠራተኞች ግልፅ ሆነው ባላቸው የትምህርት ዝግጅትና በአካበቱት የስራ ልምድ መሠረት አሟልተው ሲገኙ ብቻ በምርጫቸው መሠረት እንዲመደብ ለማድረግ የድልድል ኮሚቴ በማዋቀር በነጥብ የስራ ምዘና ዘዴ የተመዘኑና ደረጃ በወጣላቸው የስራ መደቦች ላይ ተገቢውን ሠራተኛ በተገቢው ቦታ እንዲመደብ በማድረግ ዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ ስራ ሰርቷል፡፡ በአብዛኛው ሠራተኛም በተመደበበት የስራ ክፍል የቻለውን ያክል በመስራት ዩኒቨርሲቲያችን ከሌሎች ዩኒቨርሲዎች ተወዳዳሪ እንዲሆን ሁሉም ርብርብ ማድረግ አለበት ብለዋል አቶ ግርማ፡፡

በለላ በኩል በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መፅሀፍትና ዶክመንቴሽን ዳይሬክቶሬት ሠራተኛ አቶ አንሙት ጤናው እዚህ ተቋም ብዙ ተስፋ ነበረኝ ማኔጅመንት ዲግሪ አለኝ ይሁን እንጅ የጅኤጅ ምደባ የነጥብ ስራ ምዘና ዘዴ መሠረት ተደርጎ የሚሠራበት የስራ ድልድል መመሪያ ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን መሠረት ያደረገ አይደለም ከፊሎቹ በትክክለኛ ችሎታቸው፣ ትምህርት ዝግጅታቸውና በስራ ልምዳቸው ተመድበዋል፡፡ አብዛኛዎቹ ግን የተመደቡበት መደብ የማይገናኝ የትምህርት ዝግጅት የስራ ልምድ ይዘው ችሎታ በሌለው ሰው የስራ መደብ ተመድበው እየተቸገሩና ስራ እየተጉዳ ነው፡፡ በሌላ በኩል በዘመድ በመተዋወቅ ማነው ተናጋሪ ማን ነው ዝምተኛ የሚሉትን መሠረት ተደርጎ የተመደበ መሆኑና ለምን ተብሎ ለመዳቢ ኮሚቴዎች ጥያቄ ሲነሳ ከላይ ታዝዘን ደብዳቤ ተፅፎልን ነው የማኔጅመንት ኮሚቴ ነው የመደበው መድቡን ተብለን ነው በሚል ሰበብ ሠራተኛው ሳይረካ ቀርቷል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መፅሀፍትና ዶክመንቴሽን ዳይሬክቶሬት ሰርኩሌሽን ሠራተኛ አቶ ሽጋው ደባስ ጄኤጂ ስራችንን ለመመዘን የሚያስችሉ መስፈርቶችን በመጠቀም የሰራተኞችን የስራ እንቅስቅሴ እና አተገባበር መዝኖ በሚያገኙት አጠቃላይ ነጥብ መሰረት የአፈፃፀም ደረጃ የማስቀመጥ ዘዴ ማለት ነው፡፡ የሠራተኛው የጂኤጅ ምደባ አፈፃፀም የመንግስት ሠራተኞችን ድልድል አፈፃፀም መሰረት ባደረገ መልኩ ነው ለማለት ይከብዳል ምክንያቱም የተካሄደው ምደባ መመሪያውን የጣሰ ወይም ከመመሪያው ውጭ ነበር ይላል አቶ ሽጋው፡፡ አቶ ሽጋው አያይዘውም የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ሠራተኞች ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሪፖርት በማድረግ ሙሉ ስድስት ወር ነው የፈጀው ምክንያቱም ራሱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የሠራተኛውን ቅሬታ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ለማስተናገድ ፈቃደኛ አይደሉም፡፡

# ‹‹የግንባታ ሥራ ፈታኝና ዉስብስብ ዘርፍ በመሆኑ የሁሉን አጋር አካላት ትኩረት ይሻል››



ሳይህ ካሳዉ (ዶ/ር)
የቢዝነስና ልማት ም/ፕሬዝዳንት

ዛሬ ዛሬ መንግስት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሰጠዉ ልዩ ትኩረት ዩኒቨርሲቲዎችን በማህበረሰቡ ከፍተኛ ፍላጎትና ባለዉ የትምህርት ተደራሽነት ፖሊሲ በተለያዩ አካባቢዎች በመገንባት ላይ ይገኛሉ፡፡ አንድ አገር ባላት የሃብት ብዛት፣ የመልክዓምድር አቀማመጥ፣ የህዝብ ብዛት እና የመንግስት አስተዳደር ብቻ አታድግም፡፡ ይልቁንም ለትምህርት በከፈሉት ዋጋ እና በሚተገብሩት የትምህርት ፖሊሲና መልካም የመንግስት አስተዳደር ጭምርም እንጅ፡፡

ስለሆነም የተማረ የሰዉ ሃይል ለአገር እድገት ከማበርከት አንጻር ዩኒቨርሲቲዎች በተለያዩ ጊዜያት እየተገነቡ እና እየተስፋፉ አገሪቷ የምትፈልገዉን የሰው ሃይል በዕዉቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት እየታነጹ ሲወጡ ይታያል፡፡ ይህን ሚና በመወጣት ረገድ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከሁለተኛ ትዉልድ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል አንዱ ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲዉ ላለፉት 11 ዓመታት ከ39 ሺ በላይ ተማሪዎችን በማስመረቅ ለአገር ሁለንተናዊ ዕድገት የበኩሉን አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል፡ ፡ ዩኒቨርሲቲው በአሁኑ ሰዓት በመደበኛ፣ በተከታታይ እና በኤክስቴንሽን የትምህርት ዘርፍ በዋናዉ ግቢ፣ በቡሬ ግቢና በበላይ ዘለቀ የርቀት ትምህርት ማሰተባበሪያ ካምፓሶች በድምሩ ከ33 ሺ.ተማሪዎች በላይ በማሰልጠን ላይ ይገኛል፡፡

ከትምህርት ፕሮግራሞች መስፋፋት እና ከተማሪዎች ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ ለመማሪያና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ግንባታዎች እየተገነቡ ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም እየተገነቡ ያሉ ግንባታዎችን ዓይነት፣ ሂደት፣ ክትትልና ሌሎች ግልጋሎቶች በተመለከተ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ሳይህ ካሳዉ (ዶ/ር) አነጋግረን ተከታዩን ማብራርያ ሰጥተውናል፡፡

ሳይህ ካሳዉ (ዶ/ር)
የቢዝነስና ልማት ም/ፕሬዝዳንት

ዩኒቨርሲቲው ከ2008 በኋላ ከፍተኛ በጀት በመመደብ የማስፊፋያ የግንባታ ፕሮጀክቶች በሶስት ካምፓሶች እያስገነባ የሚገኝ ሲሆን በዋናው ግቢ ሁለት የመማሪያ ህንፃዎች G+4 የሆኑ እያንዳንዳቸው 25 በድምሩ 50 ክፍሎች ያሏቸው ተጠናቀው ለአገልግሎትክፍት ሆነዋል፡፡ የመምህራንና ሰራተኞች መዝናኛ ህንፃም አብዛኛው ስራ ተጠናቆ የርክክብ ሂደት ተጀምሯል፡፡ በተጨማሪም 3000 ሠው የሚያስተናግድ የኦዲቴሪየም አዳራሽ ግንባታው ተጠናቆ ስራ ጀምሯል፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብለው ተጀምረው ስራቸው ቆመው የነበሩ 4 የቴክኖሎጅ ወርክሾፕ ህንጻዎች ተጠናቀው ስራ እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ባሻገር 1 የነባር መምህራን ለምርምር ምቹ የሆነ ቢሮ በማሰራት ያለውን የመምህራን ቢሮ እጥረት በተወሰነ መልኩም ቢሆን ለማቃለል ጥረት ተደርጓል፡፡

ከትላልቅ ግንባታዎች በተጨማሪም ትናንሽ ግንባታዎችም ስራ እየተሰራ ሲሆን ለአብነትም የመጸዳጃ ቤት ችግርን ለመቅረፍ በየህንፃዎች ላይ ካሉ መጸዳጃ ቤቶች በተጨማሪ አራት ደረጃቸውን የጠበቁ የመምህራንና ሰራተኞች ግንባታዎች ፣ ዘጠኝ የተማሪዎች መጠባበቂያ ሽንት ቤት ከነ ሻወሩ በመገንባት አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ በያዝነዉ ወር ተጠናቆ ርክክብ የሚደረግ አንድ የተማሪዎች ላውንች እና አንድ የጅምናዚየም ክፍል ስራ እንደሚጀምሩ ዶ/ር ሳይህ አብራርተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የጥበቃ ስርዓቱን ተደራሽ ለማድረግ በዋናው ካምፓስ ሰባት የጥበቃ ማማዎች ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት የጀመሩ መሆኑ ገልፀውልናል፡፡እነዚህን እና መሰል ግንባታዎችን በዋናው ግቢ የሚከናወኑ ሲሆን በዩኒቨርሲቲዉ ዋና በር ላይ በፍሊንስቶን ተቋራጭ የሚገነባው የአስተዳደር ህንፃ የአፈጻጸም ስራው በጣም የዘገየ ሲሆን አፈፃፀሙን ለማሻሻል የተደረጉ ተደጋጋሚ ጥረቶች ለውጥ ማምጣት ባለመቻላቸው በውሉ መሰረት ወደ ቀጣይ እርምጃ ሊገባ እንደሚችል ምክትል ፕሬዝዳንቱ ገልፀዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከዋናው ካምፓስ በተጨማሪ በደብረ ማርቆስ ከተማና በሌሎች ካምፓሶች ላይ የማስፋፊያ ግንባታዎችን እየሰራ የሚገኝ ሲሆን በደብረ ማርቆስ ከተማ እያስገነባቸው ያሉ ሁለት ህንፃዎች የስራ ፈጠራ ማሰልጠኛ የሚሆን G+6 ህንፃ እና የሆቴልና ቱሪዝም ማስልጠኛ ተግባር የሚያገለግል G+6 እያስገነባ ሲሆን በተለያዩ ችግሮች ምክንያት አፈፃፀሙ በውሉ መሰረት ባይሆንም ግንባታዎችን በያዘው ተቋራጭ በቅርብ ጊዜ ተሰርተው ይጠናቀቃሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ዩኒቨርሲቲው የመቃ ላይ የጤና ሳይንስ ካምፓስ በአዲስ መልኩ ከፍቶ በሁለት ተቋራጮች እያንዳንዳቸው አስር አስር ህንፃ እየሰሩ ሲሆን በአፍሮ ፅዮን የሚሰሩ ህንፃዎች በአብዛኛው ተጠናቀው የርክክብ ሂደት የተጀመረ ሲሆን በስሪኤም ኢንጅነሪንግ የሚሰራው ግን ወደ 70% የፊዚካል አፈፃፀሙ ቢደርስም ተቋራጩ እያሳየ ባለው የአፈፃፀም ድክመት ምክንያት ወደ መቋረጥ ደረጃ ሊደርሱ እንደሚችሉ ገልፀዋልናል፡፡ ለዚህ ካምፓስ ውትርን መስክ ላይ ዩኒቨርሲቲው ሁለት ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ በማስቆፈር አስተማማኝ ውሃ የተገኘ ሲሆን ወደ ካምፓሱ የሚደረገው የውሃ መስመር ዝርጋታም በጥሩ ሁኔታ እየተሰራ መሆኑን ዶ/ር ሳይህ ሲገልፁ የአስፓልት መንገድ ስራው ትንሽ የተቀዛቀዘ ስለሆነ በፍጥነት እንዲሠሩ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ብለዉናል፡፡ ይሁን እንጅ በአሳፋሪ ሁኔታ የተዘረጋው የመብራት መስመር

ወደ ገጽ 36 ዞሯል

# የአይሲቲ አውቶሜሽን ሥራዎች በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ

የቢዝነስ እና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት በስሩ ካሉ ዳይሬክቶሬቶች ወስጥ አንዱ የሆነው (የኢንፎርሜሽንና ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (አይሲቲ) ዳይሬክቶሬት ነው፡፡ ዳይሬክቶሬቱ የዩኒቨርሲቲውን ስራዎችን በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጅ በመታገዝ ጥራት እና ቅልጥፍና ያለው አሰራር እንዲኖር የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ያለ የስራ ክፍል ነው፡፡ የስራ ክፍሉ የተለያዩ የስራ በቴክኖሎጂ በማደራጀት ፈጣን እና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት፣ የአውቶሜሽን ስራዎችን መስራት፣ የኔትዎርክ አገልግሎትን ማስፋት፣ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚገኙት የተለያዩ የአይሲቲ እቃዎች ጥገና መስጠት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህን ስራዎች በአግባቡ በመስራት፣ በማደራጀት ደንበኞችን አገልግሎት ቀልጣፍ እንዲሆን እና የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እንዲጠቀሙ ማድረግ የዳይሬክቶሬቱ ስራ ነው፡፡ የአይሲቲ ዳይሬክቶሬት በ2011 የበጀት ዓመት የተለያዩ የሶፍትቄር ፕሮግራሞችን የሰራ ሲሆን ከነዚህ ሶፍትዌሮች መካከል የሬጅስትራር ሲስተም፣ ፔሮል ማኔጅመንት ሲስተም፣ ሪሶርስ ማኔጅመንት ሲስተም፣ ናጊወስ የኔትዎርክ መቆጣጠሪያ ሲስተም፣ ዋን ካርድ ሲስተም አውቶሜሽን የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ዳይሬክቶሬቱ ለተማሪዎች አገልግሎት የሚውል በር፣ ቤተ-መፅሀፍት እና ምግብ ቤት መግቢያ አውቶሜሽን ተሰርተው ያለቁ እና ወደስራ ለመግባት በዝግጅት ላይ ያሉትን ጨምሮ በመስራት ከፍተኛ እምርታ እያመጣ ያለ የሥራ ክፍል ነው፡፡ እነዚህ ሥራዎች ከፍተኛ የስራ ጫናን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አላቸው፡፡

የአይሲቲ ማዕከሉን የበለጠ ለማዘመን እና ለማሻሻልም ትምህርት ሚኒስቴር የአራት ዩኒቨርሲቲዎችን ዳታ ሴንተር ለማሰራት ውል በገባው መሰረት እቃዎቹ ተገዝተው የገቡ እና በቀጣይ ወራት



አቶ ጌታቸው ቁሜ
የአይሲቲ ዳይሬክተር

የማደራጀት እና የፋይበር ዝርጋታዎች የሚከናወኑ ሲሆን በአጠቃላይ በግቢው 200 መቶ ዳብል የኔትወርክ ኖድ ይዘረጋል፡፡ ይህ ደግሞ ከ 90 እስከ 100 የሚደርሱ በግቢው ውስጥ ባሉ ህንጻዎች የገመድ ኢንተርኔት አገልግሎት ያገኛሉ፡፡ አይሲቲ ዳይሬክቶሬቱ ከዚህ የበለጠ ብዙ ስራዎች ቢኖሩም በቀጣይ ለስራ እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮችን እንደ ግዥ መጓተት፣ የመለዋወጫ እቃዎች ገብያ ላይ ያለመገኘት፣ የመብራት መቆራረጥ፣ የስልጠናና የጥገና ማዕከል አለመኖር የሚጠቀሡ ተግዳሮቶች ቢሆኑም የሚመለከታቸው አመራር እና ባለድርሻ አካላት ይህን ችግር በመቅረፍ በቀጣይ የተሻለ ስራ መስራት ተገቢ ነው፡፡







የአይሲቲ የመሠረተ ልማት ሥራዎች

# ተማሪዎቻችን

## ‹‹ትምህርት የቅድሚያ ቅድሚያ የምሰጠው ዓላማዬ ነው››

**መውደድ ይሁኔ**

*የ2011 ዓ.ም የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሴት ተማሪዎች ዋንጫ ተሸላሚ*



ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2011 ዓ/ም ለ11ኛ ጊዜ ተማሪዎችን ሲያስመርቅ በቡሬ ካምፓስ ደግሞ በካምፓሱ ውስጥ ለ2ኛ ጊዜ ተማሪዎችን አስመርቋል፡፡ በዚህ የ11ኛ ዙር የተማሪዎች ምረቃ ላይ ከዩኒቨርሲቲው አጠቃላይ ሴት ተማሪዎች ከኮምፒውተር ሳይንስ ትምህርት ክፍል 3.8 አጠቃላይ ውጤት በማስመዝገብ የሜዳሊያና የዋንጫ ተሸላሚ ስለሆነች ሴት ተማሪ የህይወት ተሞክሮ እናካፍላችኋለን፡፡ መልካም ንባብ፡፡

ተማሪ መውደድ ይሁኔ ትባላለች፡፡ በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን ማቻከል ወረዳ የነጭ ቀበሌ ልዩ ስሟ የቋንጣ በምትባል ቦታ  በ1987 ዓ.ም ከአባቷ ከአቶ ይሁኔ ወርቁና ከእናቷ ከወ/ሮ በላይነሽ መህሪ ተወለደች፡፡ እንደማንኛውም የአርሶ አደር ልጅ እድሜዋ ለአደንኛ ደረጃ ትምህርት እስኪደርስ ድረስ በከብት ጥበቃና ቤተሰብን በመርዳት አደገች፡፡ቤተሰቦቿ ከእሷ በፊት የነበሩትን ትልልቅ ወንድምና እህቶቿን ወደ ትምህርት ቤት አይልኩም ነበር፡፡ ይልቁን ትዳር መስርተው ልጆች ወልደው እንዲኖሩ ነበር የሚያደርጉት፡፡ነገር ግን እሷ እድሜዋ ለትምህርት ሲደርስ አጋጣሚ ሆኖ መንግስት ቤተሰቦቻቸውን ለትምህርት የደረሱ ልጆቻቸውን ለትምህርት እንዲልኩ ይገደዱ ነበር፡፡መምህራንም በአካባቢያችን እየመጡ ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወላጆች ወደ ትምህርት እንዲልኳቸው ይቀሰቅሱ ነበር፡፡ ስለዚህ ቤተሰቦቿም መውደድን ከትምህርት ቤት ለማስቀረት የሚችሉበት ምክንያት አልነበራቸውም፡፡  የሚገርመው ነገር ቤተሰቦቿ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት መላክ የለመዱ ባይሆንም የተፈጠረው ሁኔታ ስለሚያስገድዳቸው በሰባት ዓመቷ በ1995 ዓ/ም በቀበሌውበሚገኘው የነጭ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመግባት ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ትምህርቷን ተከታትላለች፡፡

በአንደኛ ደረጃ የነበራት የትምህርት አቀባበል ጥሩ የሚባል ነበር፡፡ ነገር ግን 1ኛ ክፍል የገባችው ቅድመ መደበኛ ትምህርት ሳትማር በመሆኑ በአንደኛው መንፈቅ ዓመት ላይ 34ኛ ደረጃ ወጣች፡፡ ነገር ግን ከሁለተኛው መንፈቅ ዓመት ጀምሮ ከትምህርት ቤቱም ከትምህርቱም ጋር ራሷን በማላመድ ውጤቷን ማሻሻል ጀመረች በመሆኑም በሁለተኛው መንፈቅ ዓመት 1ኛ ክፍል  በአንደኛው መንፈቅ አመት ላይ የነበራትን ውጤት በማሻሻል ደረጃዋን ወደ  አንደኛነት ከፍ ለማድረግ ችላለች፡፡ በሁለተኛ ክፍልም የአንደኛ ክፍል የሁለተኛውን መንፈቅ አመት የትምህርት አቀባበሏን በማስቀጠል 1ኛ ደረጃ ወጥታ ተሸላሚ ለመሆን በቅታለች፡፡ በዚሁ መልክ የ1ኛ ደረጃ ትምህርቷን ከ1ኛ-3ኛ ደረጃ በመያዝ ጨረሰች፡፡ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ያለውን ትምህርቷን በአማኑኤል ከተማ በሚገኘው አማኑኤል ቁጥር ሁለት ትምህርት ቤት ተከታትላለች፡፡ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ደግሞ አማኑኤል 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማረች፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በአማኑኤል ቁጥር ሁለት ትምህርት ቤት የተከታታለች ሲሆን ትምህርቱም አብዛኛው የትምህርት አይነቶች በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጡ በመሆናቸው ከደረጃዋ በመጠኑ ቀነሰች፡፡ ነገር ግን ራሷን ከቋንቋውና ከየትምህርት አይነቶች ጋር ለማስተዋወቅ ያደርገችው ጥረት ከፍተኛ ስለነበረ በአጭር ጊዜ ውጤታማ ለማድረግ ችላለች፡፡

የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ስትከታተል ትምህርት ቤቱ ከምትኖርበት አካባቢ ርቀት  ስለነበረው ቢያንስ 45 ደቂቃ እየሮጠች ስትሄድ የሚወስድባት ስትራመድ ደግሞ አንድ ሰዓት እና ከዚያ በላይ ይወስድባት ነበር፡፡ የ2ኛ ደረጃ ትምህርቷን ግን ስትከታተል ትማርበት የነበረው ትምህርት ቤት ከመኖሪያ አካባቢዋ ርቀቱ በጣም ፈጠን ካለች 1 ሰዓት ይወስድባት ነበር፡፡ ይህ ማለት ከቤት ወደ ትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ለመሄድ መማሪያ ደብተሮችን፣ መፅሀፎችንና ሌሎችን ቁሳቁሶችን ተሸክማ በቀን የ2 ሰዓት የእግር ጉዞ እንድትጓዝ ትገደድ ነበር፡፡

ሆኖም ግን 12ኛ ክፍል ስትደርስ ታማ ስለነበር ይህንን ርቀት በእግሯ እየተመላለሰች መማር ስለማትችል ከቤተሰቦቿ ተነጥላ በአማኑኤል ከተማ ቤት ተከራይታ ትምህርቷን መማር ጀመረች፡፡ ከቤተሰቦቿ ተነጥላ  መኖሩ ቢከብዳትም በመመላለስ ታጠፋው የነበረውን ጊዜና ጉልበት ስለቀረ ትምህርቷን በአግባቡ ለመከታተልና በደንብ እንድታነብ ረድቷታል፡፡ ስለሆነም የ12ኛ ክፍል ውጤተዋ 445 በማምጣት ወደ ደብረ ማርቆሰ ዩኒቨርሲቲ በኮምፒዩተር ሳይንስ ትምህርትክፍል ለመማር በቃች፡፡

ወደ ዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት ካመጣሁ በማለት የነበሯት ምርጫዎች በመጀመሪያ ደረጃ የማህበረሰብ ጤና ነበር ሆኖም ግን የሁለተኛ ምርጫዋ የኮምፒዩተር ሳይንስ ደርሷት  ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተመደበች፡፡ የመጀመሪያ ምርጫዋ የማህበረሰብ ጤና እንዲሆን የፈለገችውሁ  የጤና ባለሙያዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን አክብሮትና ትልቅ ቦታ ታይ ስለነበረ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ጓደኛዋ እንድትማር ይገፋፋት እና ይመርጥላት የነበረው ኮምፒዩተር ሳይንስ ነበር፡፡ ይህንም የመረጠበት ምክንያት በመሰናዶ የትምህርት ቆይታ ጊዜ በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ትምህርት

ላይ የነበራትን አቀባበልና እንቅስቃሴ በማየት አንቺ ኮምፒዩተር ሳይንስ ብትማሪ ጥሩ ነው ይለላት ስለነበር ነው፡፡በመሆኑም የሁለተኛ ምርጫዋ በነበረው የኮምፒዩተር ሳይንስ ትምህርት መመደቧን ስታውቅ የጓደኛዋ ፍላጐት ስለተሳካለት ደስ አላት፤ እሱም ደስተኛ ነበር፡፡ በመሆኑም ወደ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አቀናች ማለት ነው፡፡ ጓደኛዋም የተመደበው ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ አካውንቲንግ ትምህርት ክፍል ስለነበረ በሁለተኛና መሰናዶ ትምህርት ቤት የነበረንን የእርስ በርስ ድጋፍና እገዛ ለማስቀጠል ያስቻለ ስለነበር ደስታቸው በጣም የላቀ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ሁለታቸውም ወደ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርቲ ከመጡ በኋላ የገጠማቸው ነገር በጣም ከባድ ነበር፡፡ ይኸውም ሁለታቸውም ከቤታቸው ሲመጡ አብረው እንደሚማሩ ቢሆንም የመውደድ የትምህርት ክፍል የሚሰጠው በቡሬ ካምፖ`ስ ስለሆነ ወደ ቡሬ መሄድ አለብሽ ስትባል ትልቅ ፈተና ገጥሟት ነበር፡፡ይህንን ችግር ለመቅረፍም ጓደኛዋ ከተመደበበት የትምህርት ክፍል ወደ ሌላ ክፍል ለመቀየር ጥረት ቢያደርግም የትምህርት ክፍሉን ለመቀየር ቢስማሙም ከደብረ ማርቆስ ዋናው ግቢ ወደ ቡሬ ሄደው ለመማር ግን የተስማማ አልነበረም፡፡



ስለሆነም ምን ቢቃጠሩ ደረሰ ቀኑ እንዲሉ የመወደድ ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ ወደ ቡሬ ግቢ መሄድ እርግጥ መሆኑን ሲታወቅ ሁለታቸውንም የሀዘን ድባብ ዋጣቸው፡፡ ከብዙ የእርስ በእርስ ምክክርና መፅናናት በኋላ ወደ ቡሬ ካምፖ`ስ አቀናች፡፡ በቡሬ ካምፖ`ስ ቆይታዬ ጓደኛዬ ከደብረ ማርቆስ እሁድና ቅዳሜ እየሄደ ዘወትር በስልክ ከሚያደርጉት ግንኙነት በተጨማሪ ያበረታታትና ይደግፋት ጀመር፡፡

የጓደኛዋ የዘወትር ምክሩም ትምህርቷን በአግባቡ ተከታትላ የተሻለ ውጤት እንድታስመዘግብና ለወደፊት የተሳካ ህይወት እንዲኖረራቸው ነበር፡፡ ስለሆነም ለዚህ ከፍተኛ ውጤት እንድትበቃ ያስቻላት ጓደኛዋ ነው፡፡ ምክንያቱም እርሱ በየሴሚስተሩ ልታስመዘግብ የሚገባትን ውጤት በማቀድ፤ ለእዚያ ውጤት ስትበቃ አቅም በፈቀደ ደግሞ የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣት ነበር፡፡ ይህም የበለጠ ለትምህርቷ ትኩረት እንድትሰጥ አድርጓታል፡፡



ቤተሰብ ጠንካራ ተማሪ እንድትሆን ቢፈልጉም እንደ ጓደኛዋ የእያንዳንዱን ትምህርት ተግባርና እንቅስቃሴ አይከታተሏትም፡፡ የቤተሰቦቿ ድጋፍ በዋናነት ለመማር የሚያስፈልጋትን የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ነበር፡፡ ትምህርቷን እንድትከታተል የቤተሰቦቿ ምክር ዘወትር አለ ሆኖም ግን በአጠገቧ ተገኝቶ ትምህርቷን እንድታጠና ያደርግ የነበረ ጓደኛዋ ነው፡፡

በትምህርታቸውም ሆን በህይዎታቸው ውጤታማ ለመሆን ሁለቱም ዒላማ አስቀምጠዋል፡፡ ከትምህርት ውጭ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ አልነበራቸውም፡፡ ይህንን ግብ ለመምታትም የሚገጥማቸውን ማንኛውም ነገር ለመወጣት ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ዓላማቸውን ለማሳካት ደግሞ የሚከተሏቸው መንገዶች፤ ጓደኛን ከመምረጥ ጀምሮ በአግባቡ ያዩአቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ በህይዎት ጉዞ የሰው ልጅ ምንም አይነት ፈተና ሳይገጥመው ስኬታማ መሆን ስለማይችል ፈተናዎችን መቋቋም የህይወታቸው መርህ አድርገው ተግብረውታል፡፡

ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው በተለይም ሴት ተማሪዎች ጓደኛ መረጣ ላይ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡ ለመውደድ ውጤታማነት ምስጥሩ ጓደኛዋ ነው፡፡ ማንኛውንም የሚገጥሙአትን ፈተናዎች በተለያየ አግባብ መፍትሔዎችን በማፈላለግ ለዚህ ውጤት እንድትበቃ አድርጓታል፡ ለዚህም ምስጋናዋ የላቀ ነው፡፡ውጤታማ እንድትሆን ሁሉም መምህራን የአደረጉላት ድጋፍ ዕውቅና ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ መምህራን ተማሪዎችን ሲያሰተምሩ ኛ ትምህርታቸውን አጠናቀው ነገ ለእራሳቸው፡ ለቤተሰቦቻቸው ብሎም ለአገራቸው የሚጠበቅባቸውን አስተዎፅኦ እንድያበረክቱ ለማስቻል ነው፡፡ስለሆነም መምህራን ተማሪዎችን ውጤታማ ለማድረግ ብዙ ይደክማሉ፡፡ ተማሪዎች ውጤታማ ሲሆኑ የሚደሰቱትን ያህል ውጤታማ ሳይሆኑ ሲቀር ደግሞ መከፋታቸው አይቀርም፡፡ በትምህርት ውጤታማ ለመሆን ያሰበ ሰው በመጀመሪያ ደረጃ መምህራንን መውደድ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም መምህራንን ሳይወዱ እነርሱ የሚያስተምሩትን ትምህርት ሊወዱት አይችሉም፡፡ መውደድም ሁሉም መምህራኖቿን ስለምትወድና ስለምታከብር የሚያስተምሯትን ትምህርት ወድዳ ትማራለች፤ ይህም ውጤታማ ለመሆን ካበቋት ነገሮች መካከል አንዱ ነው ስትል መውደድ ለመምህሮቿ ዕውቅና ሰጥታለች፡፡



ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ሲመጡ ከቤተሰቦቻቸውና ከአካባቢያቸው ርቀው በመሆኑ የቤተሰብ ፍቅር እንደሚያስቸግራቸው ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የቤተሰብ ፍቅር ቢኖርም ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው እንዲነጠሉ ያስገደዳቸው ነገር የነገ ህይወታቸው ስለሆነ የቤተሰብ ፍቅርን ተቋቁመዉ፣ ራሳቸውን ካላስፈላጊ ግንኙነቶችና ተግባሮች ቆጥበው ቤተሰቦቻቸው የጣሉባቸውን ኃላፊነቶች፣ ለአገር የሚጠብቅባቸውን አስተዋፅኦ ለማድረግ በባለ ሙሉ ተስፋነት ለትምህርታቸው የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥተው ሊሰሩ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ሁላችንም ከቅርብም ይሁን ከርቀት የመጣነው ከቤተሰብ ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ  ውጭ ስለሆነ እራሳችን የማንቆጣጠር ከሆነ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ለጓደኛ ምርጫ ተጠንቅቀን ለመጣንለት አላማ ተገቢውን ጊዜና ትኩረት ሰጥተን ልንሰራ ይገባል የ2011 ዓ.ም የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የዋንጫ ተሸላሚ አስተያየቷን ሰጥታለች፡፡

በመውደድ ህይወት ውስጥ የምታስታውሰው ከ1ኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቆይታዋ ከቤት ወደ ትምህርት ቤት ለመድረስ የ40 ደቂቃ ሩጫ ማድረግ የሚጠበቅብን ስለነበረ ያንኑ ያህል ደቂቃ ከጓደኞቿ ጋር ስትሮጥ ሄዳ ትምህርት ቤት ስትደርስ ስለሚረፍድ የትምህርት ቤቱ የፈረቃ አስተባባሪ በመዘግየታቸው ምክንያት እንደገና እንዲሮጡና እንዲንበረከኩ ካደረጉ በኋላ ይገርፉአቸው እንደነበር ስታውሳለች፡፡ ምክንያቱም እሷና ጓደኞቿ ሩጫ የሚጀምሩት ትምህርት ቤት ከመድረሳቸው ከ40 ደቂቃ በፊት ስለነበረና ደክሞአቸው እሰይ ደረስን ሲሉ እንደገና እንዲሮጡና እንዲንበረከኩ መደረጉ አግባብነት የሌለውና የሚነሱበትን ቦታ ካለማወቅ ወይም የዘገዩበትን ምክንያት ባለመገንዘብ  ነበር፡፡

ከወንድ ጓደኛዋ ጋር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስትከታተል ጀምሮ የተዋወቅን ሲሆን በመጀመሪያ የተዋወቁት አብረው የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ስለነበሩ ሲሆን ትውውቃቸውም የፍቅር ሳይሆን የትምህርት ቤት ጓደኛሞች ነበር፡፡ በትምህርት ቤት ጓደኛነትም እርስ በራሳቸው እየተማማሩና እየተረዳዱ ለብዙ ጊዜ ቆዩ፡፡ ይህ የትምህርት ቤት ጓደኝነት ቆይታቸውም የበለጠ እንዲተዋወቁ ስላደረጋቸው ሁለታቸውም በትምህርታችቸው ወደፊት ለትልቅ ዓላማ መስራት እንደሚገባ በመነጋገር የትምህርት ቤት ጓደኛነታቸው አድጎ ወደ ፍቅር ተሻገገረ፡፡ ይህ የፍቅር ግንኙነታቸው ደረጃ በደረጃ የመጣ በመሆኑ በትምህርቷ ላይ ምንም አይነት ተፅዕኖ አላመጣባትም፡፡ የፍቅር ጓደኛዋም ለትምህርት የሚያስፈለጉ መፅሀፍትንና ሌሎችን እየገዛ ድጋፍ ያደርግላት ነበር፡፡

አንዳንድ ሰዎች ሴትነት ለትምህርት ተፅዕኖ አለው ቢሉም ለመውደድ ግን ሴትነት ከትምህርት ይገድባል የሚለው ሃሣብ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሴት በመሆናቸው በህይወት የተለያዩ ችግሮች እንደሚገጥሙን ይታወቃል፡ ፡ ስለሆነም በቅድሚያ  ዓላማ ሊኖረን ይገባል፣ ለዓላማችን መሳካትም ከፈጣሪ ቀጥሎ የእራሳችን ጥረት ወሳኝነት አለው፡፡ ስለሆነም በሴትነት የሚገጥሙን ፈተናዎች ቢኖሩም የራስ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ እና ከጣርን ፈጣሪም ይደግፈናል ታላለች መውደድ ይሁኔ፡፡ሴት ተማሪዎች ከመውደድ ሊጋሩት የሚገባው ቁም ነገር  የራሳቸውን ዓላማ ሊኖራቸው ይገባል፣ ዓላማቸውን ለማሳካትም የሚያጋጥሙ ማንኛውንም ተግዳሮቶች ለመወጣት ቁርጠኝነት ሊኖረን ይገባል፡፡ እንዲሁም ጓደኛ ምርጫ ላይ ተገቢ የሆነ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡ ለሴት ጓደኛዎቿም ‹‹ሴት ጓደኞቸ ሴትነት ውጤታማ ከመሆን ስለማያግድ ለትምህርታችሁ ተገቢውን ትኩረት ሰጥታችሁ በመማር ውጤታ በመሆን ያለውን የተሳሳተ አመለካከት ልትቀይሩ ይገባል›› የመውደድ መልዕክት ነው፡፡

# ከሜዳሊያ ጀርባ... የስኬታማ ተማሪዎች ወግ

የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ካሰበው ደረጃ ይደርስ ዘንድ በሚያደርገው ጥረት አንዱ በምቹ ሁኔታ ውስጥ አልፎ ስኬትን ሲያስመዘግብ ሌላው በከፍተኛ ችግር ውስጥ ያልፋል፡፡ በዚህ ውጣ ውረድ ውስጥ የሚፈጠሩ ተፈጥሮአዊ ግብግቦች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ተፈጥሮዊ ግብግቦች የሚደረጉት ያለምነውን ነገር ሁሉ ለማሳካት ነው፡፡ በዚህ ውጣ ውረድ ውስጥ አንዳንዱ ለውጤት ሲበቃ ሌላው ተሰናክሎ በመንገድ ላይ ካሰበው ሳይደርስ ይቀራል፡፡ አብርሆት መጽሔትም በ2011 ዓ/ም እትሟ በዩኒቨርሲቲችን የተለያዩ ፈተናዎችን በመቋቋም ለውጤት ከበቁ እና በያዝነው የትምህርት ዘመን ከተመረቁ ተማሪዎች ውስጥ ትምህርት እናገኝበት ዘንድ የተወሰኑ ተማሪዎችን የህይወት ተሞክሮ ይዛ ቀርባለች፡፡

## ‹‹ተማሪነት ማለት ሁለንታናዬ የህይወቴ ፋና እና የመንገዴ ቀያሽ ማለት ነው››

ተማሪ መላኩ ላዕከማሪያም ጌራ(የ Midwifery ትምህርት ክፍል ተማሪ)



ተማሪ መላኩ ላዕከማርያም  ይባላል ተወልዶ ያደገው በአዊ ዞን ጓንጓ ወረዳ ልዩ ስሙ ዋይከላ በምትባል  ቀበሌ ነው፡፡ ተማሪ መላኩ ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ በአካባቢው ወደ አለው በዋይከላ አጠቃላይ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት የትምህርት ዓለምን ተቀላቀለ፡፡ በዚሁ ት/ቤት ከ1-6ኛ ክፍል ትምህርቱን ተከታተለ፡፡ በመቀጠል ወደ 7ኛ ክፍል ሲዘዋወር በመሰለ አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት 7-8 ክፍል ተማረ፡፡ በ2003 ዓ/ም የ8ኛ ክፍል መልቀቂ ፈተና ተፈትኖ ክረምቱን በጉጉት ሲጠባበቅ ጥሩ ውጤት በማምጣት ቻግኒ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተቀላቀለ ከዚያ በኋላ ያለው ት/ቤት ቤቱ ብዙ የእግር ጉዞ ስለነበረው ስቃይ የበዛበት እና በጣም ከባድ ነበር፡፡ ምክንያቱም ቻግኒ እነሱ ከሚኖሩበት የአምስት ሰዓት የእግር  መንገድ ስለሆነ በወቅቱ የተሽከርካሪ አገልግሎት ስለሌለ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ከ 9-12ኛ ክፍል ያለውን ትምህርቱን ስንቅ በመሸከም የተማረው  መላኩ በፈተናዎቹ ሳይበገር በ 2007 ዓ/ም  የዩኒቨርሲቲ የመግቢያ ፈተና ወስዶ ለዩኒቨርሲቲ መግቢያ የሚሆን ጥሩ ውጤት  አመጣ፡፡ ከዚያ በኋላ ዩኒቨርሲቲ ሙሉ ሲባል ስለዩኒቨርሲቲዎች እውቅና ስለሌለው በግምት ሞላው፡፡ መቼም ሁንያለው አይቀርም እና ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተመደበ፡፡ በ2008 ዓ/ም የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ መሆኑን ያረጋገጠው ተማሪዎች ተጠርተው ወደ ግቢ ሲገቡ ነበር፡፡ በወቅቱ ለአካባቢውም ይሁን ለዩኒቨርሲቲው አዲስ የሆነበት መላኩ ግራ ሲገባው አማረጮችን ከመፈለግ አልተቆጠበም፡፡ አማራጭ የቅርብ ጓደኛው ጋር እስከሚለምደው ከሱ ጋር ለሁለት ሣምንት ድረስ ቆየ፡፡ ከጓደኛው ጋር ብዙ ነገሮችን ካየና ከተለማመደ በኋላ ወደራሱ መጠለያ እና ወደ ማህበራዊ ኑሮ በፍቅር ወደሚኖሩባት ዶርሚታሪ ከ አምስት ጓደኞቹ ጋር ኑሮውን ‹ሀ› ብሎ ጀመረ፡፡ ከዚህ በኋላ የሚቀረው ዋናው ትምህርቱን መጀመር ነበር እና  ተማሪዎቹ ጤና ትምህርት ከባድ እንደሆነ ይነግሩት ስለነበር በፈራቻ ተውጦል፡፡መጀመሪያ ዓመት ላይ እባረራለሁ ብሎ ሁሌ ይጨነቃል፡፡ እሱም ከመባረር ለመዳን ሌት ከቀን ከደብተሩ ጋር በመሆን ቤቱንላይበራሪ አደረገ ፡፡ ምንም እንኳን ከባድ ቢባልም ለሱ በዚያ አስተሳሰብ አልቆየም ፈተናውን እንደተፈተነ ማንነቱን አረጋገጠ፤ ጥሩ ውጤት አመጣ፡፡ ሁለተኛ ዓመትከሆነ በኋላ ትምህርቱ በይዘትም እየከበደ ሲመጣ  ምን ማድረግ እንዳለበት ወሰነ እሱም የተለያዩ የማንበቢያ ስልቶችን ቀየሰ፤  የቀየሳቸውንም ለመተግበር ብዙ መሰናክሎች ቢገጥሙትም ያሰበውን ለማሳካት ግን አላቃተውም፡፡ ይህም ከ ከመጀመሪያ ዓመት በተለየ መልኩ አንብቦ ስለነበር 2 4 ነጥብ በማምጣት ከዲፓርትመንቱ ሰቃይ ሆነ፡፡ አሁንም ይህንን ድካሙን እና ጥንካሬውን በማስቀጠል 3.98 በማምጣት ከጤና ሳይንስ ኮሌጅ አንደኛ በመውጣት የሚዳሊያ ተሸላሚ ሆኗል፡፡ ተማሪ መላኩን በግቢ ውስጥ ካሳለፍኩቸው ገጠመኞች  ትንሽ ላካፍላችሁ ይለናል፡፡

‹‹ፍረሽነትና ተማሪነት ለእኔ እንዲህ ነው ብየ ከምገልፀው በላይ ሁሉ ነገሬ ነው፡፡ ፍረሽነት ማለት ንፁህ ከሱስ እና ከመጥፎ ነገር የፀዳ ማለት ነው፡፡ ለእኔም  ፍረሽነት የሁሉ ነገር መጀመሪያ እና ነገሮችን አሀዱ ብዬ የጀመርኩበት ሰዓት ነው፡፡ ፍረሽነት በጣም ደስ የሚል እና አዝናኝ ጊዜ ነበር አንድ ነገር የማስታውሰው ነገር ቢኖር ተማሪዎች ትባረራላችሁ እያሉ ሲያስፈራሩኝ ነበር እና ይህን ለማለፍ ደሞ ቀን ከሌት በጣም ሳነብበት የነበርኩት ጊዜ በተለይ Anatomy የሚባል ትምህርት ነበር፡፡ እስከ 10 ሰዓት ያነበብኩበት ጊዜ መቼም አይረሳኝም ተማሪዎች ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄዱ ከላይበራሪ ቆይቼ ወደ ዶርም ሲሄዱ ፍረሽነት እንዲህ እንደሆነ እና በጣም ደስ የሚል ጊዜ ቢኖር ለእኔ ፍረሽነት ነው፡፡ ከአንደኛ ዓመት እስከ አራተኛ አመት  ድረስ በጣም ደስ በሚል ሁኔታ ተማሪነትን አሳልፌ ወደ መጨረሻው የዩኒቨርሲቱ ጊዜ ላይ እገኛለሁኝ ለእኔ ተማሪነት ማለት ሁለንታናዬ የህይወቴ ፋና እና የመንገዴ ቀያሽ ማለት ነው›› ይለናል

## ‹‹ዩኒቨርሲቲ ማለት ራስክን የምትገነባበት ወይም እብድ ሆነህ የምትወጣበት ነው››

ተማሪ አክሊሉ መንበር(የባዩ ቴክኖሎጅ ትምህረት ክፍል ተማሪ)



ተማሪ አክሊሉ መንበር ይባላል፡፡ተወልዶ ያደገው በአዊ ዞን ጥንጥ ወረዳ ቻግኒ ከተማ ሲሆን እድሜው ለአቅመ ትምህርት ሲደርስ አምቢቂ አጠቃላይ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታተሏል፡፡ በዚያው ትምህርት ቤት ከ1ኛ-8ኛ ትምህርቱ ተምሯል፡፡ የክልል አቀፍ ፈተናውንም ጥሩ ውጤት በማምጣት ቻግኒ 2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት ለ4 ተከታታይ አመት ትምህርቱን ሲከታተል ቆይቷል፡፡ 9ኛና 10ኛ ክፍል ትምህርቱን ከተከታተለ በኋላ የ10ኛ ክፍል ማትሪክ 3.88 በማምጣት ወደ 11ኛ ክፍል ተዛወረ፡፡ 11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ትምህርቱንም  በዚህ ትምህርት ቤት አጠናቋል፡፡ በትምህርት ቆይታውም ጥሩ ውጤት ነበረው፡፡ ነገር ግን 12ኛ ክፍል እያለ  በወባ በሽታ ታመመ፡፡ ከዚያ በፊት ህመም የማያውቅ ስለነበር አስቸጋሪ ሆነበት ምክንያቱም የ12ኛ ክፍል ፈተና እየደረሰ ስለነበር አይደለም ማንበብ ቀርቶ ትምህርት ቤት መሄድ አልቻለም፡፡ ከደብተር ጋርና ከመጽሀፍ ጋር የነበረው ጓደኝነት እየቀነሰ ሄደ፡፡ ሁሌ

ወደ ገፅ 48 ዞሯል

# ከራሳችን ጋር የተዋወቅንበት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የባህል ፌስቲቫል





በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በፀደቀው አዋጅ መሰረት በመላው ኢትዮጵያ ሁልጊዜ ህዳር 29 በየአመቱ የብሄሮች፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች በዓል በመላው ኢትዮጵያ ይከበራል፡፡ በዚህ በዓል ላይ ሰዎች የራሳቸውን ባህልና ወግ ይዘው ያቀርባሊ፤ ያስተዋውቃሉ፡፡ ዩኒቨርሲቲ ማለት ደግሞ ትንሿ ኢትዮጵያ ሲሆን በሀገሪቱ የሚገኙ ብሄሮች ብሄረሰቦች እና ህዝቦች አማራው፣ ትግሬው፣ አፋሩ ፣ ሶማሌው ፣ ቢንሻንጉሉ ፣ ሲዳማው፣ ሀረሬው፣ ኦሮሞው፣ እና ሌሎችም በመቻቻል በመፈቃቀድ በመተሳሰብ የሚኖሩበትና ባህልና ወጋቸውን የሚያስተዋውቁበት፤ መከባበር የሠፈነበት የብዝሃነትን ስፍራ ነው፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት "ትምህርት ብሄራችን ዕውቀት ዜግነታችን" በሚል መሪ ቃል የመጀመሪያውን የባህል ፌስቲቫል አዘጋጅቷል፡፡ በዚህ የባህል ፌስቲቫል ላይ ተማሪዎች ከመጡበት አካባቢ ውጭ ያለውን ባህል ወይም የራሳቸውን ባህል እንዴት ማስተዋወቅ እንደቻሉ ሲታይ ደግሞ ብዝሃነትን የሚያወድስ ፕሮግራም ነበር፡፡ በዚህ ፕሮግራም ላይ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ዘረኝነትን አውግዘዋል፤ ህብረ ብሔርነትን አወድሰዋል፡፡

በፕሮግራሙ ላይ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ታፈረ መላኩ ጨምሮ ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣ መምህራን ፣ የአስተዳደር ሠራተኞች እና ተማሪዎች ተገኝተዋል፡፡ በዚህ ፐሮግራም ላይ መልዕክት ያስተላለፉት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ/ር ታፈረ መላኩ የአገራችን ኢትዮጵያ ህዝቦች በመተሳሰብ እና በመዋደድ ተቻችለው የሚኖሩባት ሀገር ብትሆንም በአሁኑ ሰዓት አላስፈላጊ ብጥብጥና ትርምስ ውስጥ ስለምትገኝ ሁላችንም ለሰላም ዘብ ልንቆም ይገባል ብለዋል፡፡

ዶ/ር ታፈረ አያይዘውም የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች መደበኛ ስራችሁን በመውደድ፤ በመተሳሰብ ትምህርታችሁን ትኩረት ሰጥታችሁ መከታተል እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

በፕሮግራሙ ላይ የክብር እንግዳ በመሆን የተገኙት የምስራቅ ጐጃም ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ሀላፊ ወ/ሮ ውዳላት አልማው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከአራቱም የሀገሪቱ ማዕዘናት በመምጣት ባህላቸውን፣ ማንነታቸውን፣ እሴቶቻቸዉን በመግለጽ በባህላቸዉ የሚኮሩበትና የሌሎችን በዓል የሚያከብሩበት ዝግጅት በመዘጋጀቱ ተማሪዎች እድለኛ መሆናቸው ነው፡፡

በፕሮግራሙ አንዱ የሌላኛውን ባህል ማወቅ በረከት እንጅ መረገምት አለመሆኑንና አፅንኦት ተሰጥቶ የተሰራበት ሲሆን የባህል ትርኢትና ውድድር የሙዚቃ ዝግጅትና የጠቅላላ ዕውቀት ጥያቄና መልስ ዝግጅት ተከናውኗል፡፡

ስለዚህ በዚህ ፕሮግራም ላይ በተካሄደው የባህል አምባሳደር ውድድር በሴቶችና በወንዶች የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የ2011 ዓ.ም የባህል አምባሳደሮች ምርጫ ተካሂዷል፡፡

በውድድሩም አሸናፊ ለነበሩ የዕለቱ ተወዳዳሪዎች የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ታፈረ መላኩ እና በምስራቅ ጐጃም ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ሀላፊ ወ/ሮ ውዳላት አልማው በተገኙበት ሽልማት አበርክተዋል፡፡

ከሚዳሊያው.... ከገፅ 46 የዞረ

በየሁለት ሳምንቱ ያመው ጀመር እንኳን ማንበብ ይቅርና የሚወደውን ትምህርት ቤት መሄድ ራሱ በጣም እየከበደው መጣ፡፡ ብዙ ሰዎች ካለው አቅም አንጻር ጥሩ ውጤት እንደሚያመጣ ይጠብቁ ስለነበር ይህን ሲያስብ ብዙ ይጨነቅ ነበር፡፡ ነገር ግን የጠበቀውን ውጤት ማምጣት ባይችልም የዩኒቨርሲቲ መግቢያ የሚሆን ውጤት በማምጣት ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲን ተቀለቀለ፡፡ በዚህ ጊዜ አሁንም በሽታው ስላለቀቀው ምን ማድረግ እንዳለበት ሰዎችን ማማከር ጀመረ፡፡ ሰዎቹም የባህል መድሃኒት እንዲወስድ መከሩት፡፡ ከዚያም መድሃኒቱን እንድወስድ ወሰንኩ፤ ምክንያቱም ሀኪም ቤት ቢሔድም ማስቆም አልቻሉም፡፡ ስለመድሃኒቱ አወሳስድ እንዲህ ይለናል ‹‹መድሐኒቱን አምጥቼ ቤተሰቦችን ከአሳመንኩ በኋላ ወሰድኩኝ ግን ያልጠበኩት ነገር ሆነ፡፡ ሰውየው ሲሰጠኝ መድህኒቱን ከመውሰድህ በፊትም ሆነ በኋላ ጠላ፣ ምግብ መውሰድ አይቻልም ብሎኝ ነበር፡፡ መድሃኒቱን ከወሰድኩ በኋላ ማርከሻ የጠራ ጠላ እንድወስድ ታዘዝኩኝ፣ ጠላውንም ወሰድኩት፣ ከወሰድኩት በኋላ ግን ማንነቴን ሳትኩኝ፡፡ ይህም ለሁለት ተከታታይ ቀናት ዘለቀ ከዚያ በኋላ እንቅልፍ የጣለኝ ይመስል መንቃት ጀመርኩ፡፡ ቀስ እያልኩም ማንነቴን ማወቅ ጀመርኩ ፈጣሪ ይመስገን ከዚያ ወዲህ ወባ የምትባል በሽታ ከነአካቴው ጠፋች፡፡›› ከዚያ የደረሰው ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ነበር እና ዩኒቨርሲቲው ሲጠራ በ2008 ዓ/ም ወደ ዩኒቨርሲቲ ገባ፡፡ የደረሰው የተፈጥሮ እና የቀመር ሳይንስ ኮሌጅ ስለነበረ ኮሌጁ ደግሞ ሰባት የተለያዩ የትምህርት ክፍሎች ስላሉት እሱ ለሀገራችን አዲስ እና ብዙ ምርምር ሊሰራበት ይችላል ብሎ በማሰብ ባዮቴክኖሎጅ ትምህርት ክፍል አንደኛ አድርጎ በመምረጥ ገባ፡፡በዚህ ዲፖርትመንት ሲገባ ግን ምን ይታወቃል ተመራማሪ በመሆን የልጅነት ህልሙን እውን ላደርገው እችላለሁ እያለ ነበር፡፡ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ በአሰለፋቸው በትምህርት ሕይወቴም በጣም ጥሩ የሚባል ውጤት ማስመዝገብ በመቻሉ 3.87 በማምጣት ከተፈጥሮና ቀመር ሳይነስ ኮሌጅ ቀዳሚ ሆኖ አጠናቋል፡፡ ይህም ተማሪዎች ሳይሰለቹ ለመጡበት አላማ ተግተው ከሰሩ የማይሆን ነገር እንደሌለ መገንዘብ ይቻላል ማለት ነው፡፡

ተማሪ አክሊሉ በዩኒቨርሲቲ የነበረውን ቆይታ በራሱ አንደበት እንዲህ ይተርከዋል፡፡ አንደኛ አመት እያለሁ በጣም ትንሽ ነበርኩኝ ነገር ግን አንድ የአጐቴ ልጅ ሴኔየር ነበር እና እሱ ነበር ስለ ግቢ የነገረኝ፡፡ ስለ ግቢ ህይወት ግቢ ህይወት፣ መደረግ ስላለባቸው ነገሮች ግቢ ውስጥ አሪፍ ውጤት መስራት እንደምችልና በጠቅላላ ስለ ግቢው ምንነት በደንብ አስረዳኝ፡፡ ምክንያቱም እሱ ነባር ስለሆነ 1ኛ አመት ሁኜ እሱ የማታ 2ኛ ዓመት የባዮሎጅ ተማሪ ነበር፤ አካዳሚካል በጣም ጐበዝ ስለነበር ብዙ የሕይወት ትምህርቶችን ነግሮኝ ነበር፡፡ በወቅቱ ልጁ ጥሩ ውጤት ስለነበረው እንዴት አድርጐ እንዳመጣው እና እንዴት አድርጌ ማንበብ እንዳለብኝ መክሮኛል፡፡ ሌላኛው ደግሞ እንደ እኔ አስተሳሰብ ተማሪነት ደስ የሚል ሕይወት ነው ብየ አስባለሁ፡፡ ምክንያቱም ከምንም ሃሳብ ነፃ ሁኘ ዕውቀትን ብቻ ቦታ ሰጠህ ራስክን የምትገነባበት ስለሆነ ነው፤ አንድ ነገር አሳስብሽኝ... ዩኒቨርሲቲ ማለት ራስክን የምትገነባበት ወይም እብድ ሆነህ የምትወጣበት ነው ብየ አስባለሁ፡፡ ምክንያቱም አልባሌ ቦታ የምትውል ከሆነ ጫት ቤት፣ ሺሻ ቤት የምትውል ከሆነ መቼም ጥሩ ሕይወት አይኖርህም፡፡ በተጨማሪም ደግሞ ከቤተሰቦች ቁጥጥር ውጭ ሁነህ ራስክን መምራት የምትጀምርበት ስለሆነ ባልተስተካከለ መንገድ ከሄድክ ራስክን ልታጠፋ ትችላለህ፡፡ እዚህ ግቢ ላይ ጥሩ ሰው ሁነህ ለመውጣት የመጀመሪያውና መነሻው ነገር ቢኖር ጥሩ ጓደኛ መምረጥ ነው፤ ይሄም አንድን ሰው በመልካም የሚገነባ ነው፡፡ ግን ይህም ሆኖ ግቢ ውስጥ ስኖር አንድ ፎርሙላ ነበረኝ፡፡ ፎርሙላው ሒሳብ ወይም ፊዚክስ አይደለም፡፡ በተለይ 1ኛ ዓመትና 2ኛ ዓመት እያለሁ ተጠቅሜበታለሁ፡፡ ይህም “CCLC” የሚል ምርጥ ቀመር ነበረኝ፡፡ “CCLC” ማለት Café, Church Library, & class በማለት የተጠቀመሁበት ምህፃረ ቃል ነበር፡፡ ጥዋት ወደ ቤተ-ክርሲያን፣ ከዛ ወደ ክፍል፣ ከዛ ከክላስ ወጥቸ ምሳ ወይም ካፌ፣ ከዚያ ወደ ላይብራሪ እሄዳለሁ ከዛ ወደ አመሻሽ አካባቢ ወደ ቤተክርሲቲያን፣ ተመልሼ ራት ከበላሁ በኋላ ወደ ቤተ-መፅሀፍት እገባለሁ እስከሚበቃኝ አንብቤ ወደ ዶርሜ እገባለሁ፡፡ በቀላሉ ግቢ ውስጥ የነበረኝ ሕይወት በዚህ ነበር ያለፈ፡፡ በዩኒቨርሲቲ ቆይታየ ጥሩ የሚባል ጊዜ ያሳለፍኩበት ነው ማለት እችላለሁ፡፡ሌሎች ጓደኞቼ ላስተላልፈው የምፈልገው ነገር አንድ ሰው በሕይወት እያለ ብዙ ፈተናዎች ይገጥሙታል፣ ፈተናውን በትዕግስት ማለፍ ግን የመጨረሻ መፍትሔ መሆን አለበት አንዳንድ ጊዜ ችግርን በችግር ለመፍታት መሞከር የባሰ ችግር ይዞ እንደሚመጣ በዚች ትንሽ ጊዜ ዘርዝሬ የምጨርሰው ነገር አይደለም፡፡ በቀላሉ የነበረኝ የ16 ዓመት የትምህርት ቆይታየ ይሄን ይመስል ነበር፡፡ በአሳለፍኳቸው ነገሮች ብዙ ነገር ተምሬበታለሁ፡፡

# “መመረቅ የመጨረሻ ሳይሆን ለአስተማረችኝ ሀገሬና ወገኔ አገልግሎት መስጠት የምጀመርበት ነው”

ዘላለም ሉሌ




ከአርሶ አደር ቤተሰቦቹ አምስት ልጆች ዉስጥ የመጨረሻ ልጅ ሲሆን ኦሮሚያ ክልል ወለጋ ዞን ጉደሩ ወረዳ ተወለደ፡፡ ዕድገቱም እንደ አንድ አርሶ አደር ልጅ እንደሚያደረግዉ ወላጆችን በስራ በማገዝ አደገ፡፡ እድሜዉ ለትምህርት ሲደርስ በአቅርቢያዉ በሚገኝ ት/ቤት ትምህርቱን አንድ ብሎ ጀመረ እስከ ሶስተኛ ክፍል ከተማረ በኂላ በወቅቱ በነበረበት ትምህርት ቤት ከሶስተኛ ክፍል በላይ መቀጠል ስለማይችል ቀለም የነፍስ ጥሪ የሆነበት ዘላለም ከትዉለድ ሀገሩ ወጣ ብላ የምትገኘዉን ከተማ አሻግሮ ማየት ጀመረ፡፡ በከተማዉ እንደ ዕድል ሆኖ ከአራተኛ ክፍል እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚያስተምር ትምህርት ቤት በመኖሩ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በዚህ ሁኔታ አጠናቀቀ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እያለ ለትምህርቱ ብዙም ትኩረት የማሰይጥ ተማሪ እንደነበር ይናገራል፡፡ ይሁን እንጅ በክፍል ከአንድ አስከ አስረኛ ደረጃ ቢወጣም ለእሱ ግን ይህ ደረጃ በቂ ስላልነበረ የዛሬ ስኬት መነሻዉን ወደ ኂላ ሲያስታዉሰዉ አምስተኛ ክፍል አንድ የወንድ አንድ የሴት የክፍል ጓደኞች ነበሩት፡፡ ዘላለም በወቅቱ ጓደኞቹ የደረጃ ተማሪ በመሆናቸዉ በአመቱ መጨረሻ ሲሸለሙ ሲያይ ‹‹እኔስ ከነሱ በምን አንሸ ነዉ›› የሚል የቁጭት ስሜት ይሰማዉ ጀመረ ይህን ቁጭት ወደ ተግባር ቀይሮ ስድስተኛ ክፍል ጀምሮ የደረጃ ተማሪ ሆነ፡፡ በ2008 ዓ.ም በአገራችን ብሎም ዘላለም በሚኖርበት ኦሮሚያ ክልል በነበረዉ ረብሻ ምክንያት የመጨረሻ አመት የመሰናዶ ትምህርቱን በትክክል ባይማርም የዩኒቨርስቲ የመግቢያ ፈተና ተፈተኖ ዉጤት አመጣ፡፡ ግን እሱ በሚጠብቀዉ ደረጃ ወጤት ስላልመጣለት የሚፈለገዉን ዲፓርትመንት ማግኘት ባለመቻሉ ተስፋ ቆረጠ፡፡ ዘላለም ሌላ ያልጠበቀዉ ክስተት ተፈጠረ ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ዋናዉ ካምፓስ ወደ ቡሬ ካምፓስ ሲመደብ በወቅቱ ቡሬ ከተማን በደንብ ስለማያዉቃት ተስፋዉ ይበልጥ ጨለመበት ትምህርቱን ለማቋረጥ ወስኖ ዉሳኔዉን ለወንድሞቹና ጓደኞቹ ሲያማክራቸዉ በደረሰዉ በግብርና ተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ ተረጋግቶ እንዲማር መከሩት፡፡ ይህን ምክር ምንም አማራጭ ስላልነበረዉ የወደፊት ህልሙን ለማሳካት እጣ ፋንታዉን አምኖ መቀበል እንዳለበት ዉሳኔ ላይ ደረሰ፡፡ ‹ሁሉ ነገር ለበጎ ነዉ› እንደሚባለዉ የሀገራችን ብሂል በዚህ መነሻ በዩኒቨርሲቲ ህይወቱ ዉስጥ የሚገጥሙትን ፈተናዎች ሁሉ በመጋፈጥ የተሻለ ስኬታማ ተማሪ ለመሆን ለራሱ ቃል የገባዉ ዘላለም ሙሉ ጊዜዉን ለትምህርቱ ብቻ በመስጠት ስኬታማ በመሆን በ agribusiness & value management ትምህርት ክፍል 3.98 ነጥብ በማምጣት በ2011 ዓ.ም ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አንደኛ በመሆን ሊመረቅ ቻለ፡፡ ለዚህ ሁሉ ስኬቱ የአንበሳዉን ድርሻ ቤተሰቦቹ እንደሚወስዱ በተለይ ለታላቅ ወንድሙ ዶክተር ዳኛቸዉ ሉሌ በትምህርት ህይወቱ ላደረገለትን አስተዋጾ የተለየ ፍቅርና አክብሮት እንዳለዉ ይናገራል፡፡ ዘላለም ለዚህ ስኬት የበቃበት ሚስጥር ለሌሎች ተማሪዎች ሲመክር ማድረግ የሚጠበቅባቸዉ ነገሮች ብሎ ያስቀመጣቸዉ በመጀመሪያ በደረሳቸዉ ዲፓርትመንት ደስተኛ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ቀጥለዉ ጊዜቸዉን በአግባቡ መጠቀም አለባቸዉ እንዲሁም ወላጅ ልጆቻቸዉን ወደ ዩኒቨርስቲ የሚልኩት ተምረው እራሳቸውን፣ ወላጆቻቸውንና ሀገራቸውን እንዲጠቅሙ ብለዉ አስበዉ ስለሆነ ተማሪዎች ከአልባሌ ቦታዎች ራሳቸዉን ጠብቀዉ ስኬታማ እንዲሆኑ ስለሆነ ማሰብ ያለባቸዉ ሁሌም እራሳቸዉ ለፈተና ዝግጁ መሆን፤ተስፋን ስንቃቸዉ በማደረግ ነገ ለማየት የሚገጥመማቸዉን ፈተናበብቃት ከተወጡ ምኞታቸዉን ያሳካሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡ በሌላ በኩል ዩኒቨርስቲዎች የረበሻ ማዕከል የፖለቲካ ማስፈጸሚያ ሳይሆኑ ተልዕኮአቸዉ ትምህርት ላይ ብቻ ትኩረት አድረገዉ መስራት ከቻሉ የዘሩት ዘር አፍረቶ ለሀገር ለወገን የሚሆኑ ዜጎችን መፍጠር ይችላሉ ይላል፡፡ አሁን ሀገራችን ኢትዮጵያ ችግር ላይ ብትሆንም በብሄር ሳንከፋፈል በኢትዮጵያነታችን ኮርተን አንድ በመሆን አባቶቻችንና አያቶቻችን ዳር ድንበረዋን አስከበረዉ ለእኛ እንዳስረከቡን እኛም ሀገራችንን ከዚህ ችግር በማዉጣት ለመጭዉ ትዉልድ የማስተላለፍ ሃላፊነት አለብን ሲል መዕክቱን አስተላልፏል፡፡

# የተማሪ ፓሊስ የግቢያችን የሠላም ዘብ



ተማሪ ግርማ ጸጋዬ



ተማሪ ጌታነህ አንዱአለም

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአስተዳደርና ተማሪዎች ጉዳይ ምክትል ፕሬዝዳንት ስር የተቋቋመው የግቢ ፀጥታና ደህንነት ዳይሬክቶሬት በዩኒቨርሲቲው የሠላምና ፀጥታ ጉዳይ በቅርበት ከተማሪዎች ጋር ለመስራት ተማሪዎች በማደራጀት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለሰላም ዘብ በመቆም በርካታ ሰራዎችን እየሰሩ ይገኛሉ፡ ፡ ለዚህ ደግሞ በተማሪዎች አደረጃጀት ውስጥ ያሉትን የብሎክ ማስተር፣ የፍሎር ማስተር ጨምሮ የተማሪ ፖሊሶችን በመጠቀም ነው፡፡

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሁለተኛ ዓመት የሶሺዮሎጅ ትምህርት ክፍል ተማሪ ጌታነህ አንዱአለም የተማሪ ፖሊስ ክበብ ተጠሪ ነው፡፡ እንደጌታነህ ገለፃ ይህ ዘርፍ በዋናነት የተቋቋመው በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ሰላማዊ መማር ማስተማር እንዲኖር ለማድረግ እና በተማሪዎች መካከል በግቢው ውስጥ አላስፈላጊ የሆኑ የዲሲፕሊን ግድፈቶችን ለመከላከልና ለመቆጠር ሲሆን በዚህ ዓመት በርካታ ስራዎችን አከናውነዋል፡፡

የተማሪዎች ህብረት ፖሊስ ዘርፍ ከሞላ ጐደል ለመጥቀስ ያህል በግቢው ውስጥ በዶርምና በየብሎኮች የሞባይል፣ የላፕቶፕ እና የልብስ ዝርፊያዎችን ከመቆጣጠር አንፃር ማለትም አጥፊዎችን በመከታተልና በመያዝ የማስተማርና በእጅጉ የመቀነስ ስራ ሰርተዋል፡፡ በተለምዶ በግ ተራ የሚባለው ቦታ ላይ ከሰዓት እላፊ በኋላ የሚንቀሳቀሱ ተማሪዎችን በማስተማር ወደ ትምህርታቸው እንዲያተኩሩና በግብረ ስጋ ግንኙነት ከሚመጡ በሽታዎች እንደ ኤች አይ ቪ ኤድስ፣ የተለያዩ አባላዘር በሽታዎች እና አላስፈላጊ እርግዝና እንዳይከሰት ሰፊ ስራ በመስራት ግቢውን እያገለገለ ያለ ህብረት ነው፡፡

እንደሚታወቀው በ2011 ዓ/ም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የስጋት አመት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ እንደ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ምንም እንኳን ችግር ውስጥ ያለን ቢሆንም እንደ ህብረቱ የፓሊስ ዘርፍ በርካታ ስራ ባንሰራ ኖሮ ከዚህ የከፋ ችግር ሊኖር እንደሚችል እንገምታለን ይላል የክበቡ ተጠሪ ተማሪ ጌታነህ፡፡

የተማሪ ፖሊሶች አላስፈላጊ ያታዊ ትንኮሳን በመከላከል ረገድም ከፍተኛ ሥራ ሰርተዋል፡፡ በላይበራሪ፣ በምግብ ቤት፣ በብሎኮችና በተመረጡ የስጋት ቦታዎች በመንቀሳቀስ የፀጥታ ስራውን ያግዛሉ፡፡ ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ተማሪዎች የግቢውን ብሎም የሀገራችንን ሰላም ከማስጠበቅና እርስ በርሳችን ከአላስፈላጊ የጐሰኝነትና የዘረኝነት አስተሳሰብ ወጥተን ለሀገራችንና ለራሳችን የበኩላችንን አስተዋፅኦ እናድናበረክት ይህ ክበብ አበክሮ ይሰራል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሶስተኛ ዓመት ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል ተማሪ ዘላለም ጌታነህ እንደተናገረው በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሲማር በአጋጣሚ በወቅቱ እውነት ባልሆነ ነገር ላይ ተከስሼ ወደ ተማሪ ፓሊስ ቢሮ ሄዶ ነበር፡፡ ሆኖም አንዳንድ ተማሪዎች በጥሞና ቃሌን እንዲሰጥ ሲጠየቅ በተጠየቀው መሠረት በሚገባ ካስረዳ በኋላ የተማሪ ፓሊስ ጉዳዩን አጣርቶ ጥፋተኛ እንዳልሆነ ነግሮታል፡፡ ‹‹ከዚህ በኋላ በውሸት ልትከሰስ ትችላለህ ነገር ግን እውነት ይዘህ እስከተጓዝህ ድረስ ሁሌም ነፃ ነህ ምንም አትሆንም በርታ እኛንም በአንዳንድ ነገሮች ላይ እንድታግዘን ብሎ ጠየቀኝ፡፡ እኔም በሰጡኝ አገልግሎት ተደስቼ ከዛን ቀን ጀምሮ በተማሪዎች በኩል በሚከበሩ በዓላት ላይ ለምሳሌ በ100ኛ ቀን እና በ50ኛ ቀን የ G.C በዓል ላይ እኔም የሚጠበቅብኝን አስተዋፅኦ እያገዝኳቸው፤ እነሱም ለአደረግሁላቸው ትብብር ምስጋና ተቀብየአለሁ የሚለው ተማሪ በዚህ አጋጣሚ የተማሪ ፓሊሶች ሰላማዊ መማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እያደረጉ እንደሆነ መታዘቡን ይናገራል፡፡፡፡

ሌላኛው ጠማሪ የሁለተኛ ዓመት የሶሾሎጅ ትምህርት ክፍል ተማሪ ግርማ ፀጋዬ ሲሆን የተማሪ ፖሊስ ስራ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል በአጋጣሚ ብዙዎች የተማሪ ፖሊስ ጓደኞቹ ስለሆኑ ብዙ እንደተማሩበት ይነግሩኛል ብሏል፡፡ እንደተማሪ ግርማ አስተያየትከሆነ ሁሉም ነገር ግልፅ ሆኖ የሚታየውና የሚታወቀው የክበቡ አባል ስትሆን ነው፡፡ ከአባልነቱ ሳይቀላቀል በፊት የሚወራውን ማመን ስራው ነበር፤ ተማሪ ግርማ በግልፅ ሲያብራራውም ‹‹ብዙ ነገር ይወራል፤ በዘረኝነት ይሰራል፤ በዘመድ አዝማድና በጉርብትና ምን ታደርገዋለህ ብዙ ይባላል ግን በጣም ከእነዚህ ሁሉ የፀዳ ስራ ነው፤ በመሆኑም የሚሰራው አባል ስትሆን እና አባል ሳትሆን ብዙ ነገሮችን አስተውለህ እንድታይ ያደርግሃል፡፡ አባል በመግባቴ በጣም ደስተኛ እንድሆን አድርጎኛል ምክንያቱም ግልፅ የሆነ ነገር እየተሰራ እንደሆነ ሳውቅ የአዕምሮ እረፍት አግኝቼለሁ፡፡››

# ማንን እናስታውስ?

## ዝክረ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ





ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም የደጃዝማች በላይ ዘለቀ 75ኛ ዓመት የአርበኘነት ተጋድሎ ለመዘከር ‹‹ዝክረ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ የአርበኘነት ተጋድሎ ለጠንካራ አገራዊ አንድነት እና አስተማማኝ ሰላም›› በሚል መሪ ቃልe በጥንታዊት የበላይ ዘለቀ የተጋድሎ እንብርትና መዲና በሆነችው ቢቸና በተለይም በለምጨን አካሄደ፡፡

በምስራቅ ጎጃም ዞን የሚገኘዉ እነማይ ወረዳ፣ እናርጅ እናዉጋ፣ የሸበል በረንታ ህዝብ በቢቸና ከተማ የደጅአዝማች በላይ ዘለቀ ሃዉልት በሚገኘበት ቦታ በመሰብሰብና በአማራ ክልል ፖሊስ ማርሽ ባንድ በመታጀብ ዝክረ በላይ ዘለቀ በዓል በሚከበርበት ቦታ ወደ ቢቸና ከተማ ስታዲየም በመሄድ በደመቀ ሁኔታ እንዲከበር ተደርጓል፡፡

በፕሮግራሙ ላይ ንግግር ያደረጉት በምስራቅ ጐጃም ዞን የእነማይ ወረዳ አስተደደሪ አቶ ምንያህል አዳነ የዝግጅቱ ዋና ዓላማ የደጃዝማች በላይ ዘለቀን ታሪካቸውን፣ ተጋድሎአቸውን ማሰብ ወይም መዘከር ለአሁን የሀገር አንድነት ወሳኝ መሰረት ስላለው ነው ብለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት አገራችን ያለችበት ሁኔታ ጥሩ ስላልሆነ ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት፣ ለአማራ ህዝብ አንድነት፣ አመራር ሰጭነት፣ ጀግንነታቸውን፣ አስተዋይነታቸውን የአሁኑ ወጣት መገንዘብ ይኖርበታል፤ እሳቸው በሀገር ፍቅር ስሜት የሀገራቸውን ዳር ድንበር አስከብረዋል፤ ይህንንምትውልዱ በሰከነ መልኩ ሊጠብቅ ይገባል ሲሉ አቶ ምንያህል ተናግረዋል፡፡ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዕውቀቱን፣ ጊዜውን፣ ጉልበቱንና አንዳንድ ቁሳቁሶችን በመስጠት ከቢቸና ከተማ አስተዳደር ጋር በመተባበር ለተዘጋጀው ዝግጅት አቶ ምንያምር ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

በፕሮግራሙ ላይ ጉብኝት የተካሄደባቸው ቦከና ማርያም የባሻ ላቀ ዋጌ መኖሪያ ቤት ፍርስራሽ የሚገኝበት ሲሆን ስለ ዋርካየም ከህዝቡ ጋር ውይይት ተደርጓል፡፡ በዚህም ከቀበሌ ማዕከሉ እስከ ወርካየ ድረስ 3 ኪሎ ሜትር መንገድ ስላለ ለማሰራትና የዋርካውን ዙሪያ ግንብ አጥር ለማድረግ እና የተጋድሎ ቦታውን ለህዝብ ማስተዋወቅና ለትውልዱ እንዲተላለፍ ለማድረግ እየተሰራበት ነው፡፡

በምስራቅ ጐጃም ዞን የቢቸና ከተማ አስተዳደር አቶ ውባለ ሙሄ ሲሆኑ የተከበሩ የምስራቅ ጐጀም ዞን አስተዳዳሪ አቶ አብርሃም አለኸኝ፣ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶክተር ታፈረ መላኩ፣ ምሁራን፣ የአመራር አካላት፣ የሀይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የጀግኖች አርበኞች ማህበር አባላት፣ የእነማይና ቢቸና አስተዳደር ኗሪዎች ሙስሊም ክርስቲያኑ ተግባብቶ የሚኖርባት ጐጃም እነማይ ቢቸና ናት፡፡ የፍቅር እስከ መቃብር መነሻ ሃሳብ መፍለቂያ ዲማ ጊዮርጊስን አካቶ የጥበብና የጠቢባን የታላቁ ጀግና አባ ኮስትር በላይ ዘለቀ የደራሲ ክቡር ዶ/ር ሀዲስ አለማየሁ፣ ዮፍታሄ ንጉሴ፣ አውጋቸው ተፈራ፣ አያልነህ ሙላቱ፣ ውዳላት ገዳሙ፣ በውቀቱ ስዩም፣ ጌትነት እንየው እና የመሳሰሉት ከመምህር እስከ ኘሮፌሰር የሊቀ ሊቃውንት የእነ አለቃ አያሌው ሀገር የደጋግ ሰዎች መፍለቂያ ጐጃም እነማይ ቢቸና ነው፡፡

በዕለቱ በነበረው የፓናል ውይይት ላይ የጥናት ፅሁፍ ያቀረቡት የታሪክ ተመራማሪው ዶ/ር ስልጠነ ስዩም የኢትዮጵያ ክብርና ሞገስ የሆነውን የጀግናው ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ተጋድሎ ታሪክ ጎላ ብሎ መነገር ያለበት እንደሆነ ታሪክ እያጣቀሱ ተናግረዋል፡፡ እንደዶ/ር ሰልጠነ ጣሊያኖች አድዋ ላይ ከተሸነፉ በኋላ ከአርባ አመት ዝግጅት በኋላ የቀድሞ ክብርና ሃያልነታቸውን ለመመለስ በሚል ኢትዮጵያን ለመበቀል መጡ እንጅ ጣሊያኖችን ኢትዮጵያን መውረር ሲጀምሩ የዓለም ሰላም ፀጥታ ለማስጠበቅ የተቋቋመው ሊግ ኦፍኔሽን እንኳን በጣሊያኖች ላይ እርምጃ መውሰድ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም አርባ ዓመት ተዘጋጅተው የመጡ ስለሆነ ከጠረፍ ተነስተው በተለያዩ አቅጣጫዎች ከፍተኛ ጥፋት እያደረሱ መሀል ሀገር አዲስ አበባ ገነት ልዑል ቤተመንግስት በመግባት በቁጥጥር ስር አደረጉ ተባለ፡፡ቢቸና አውራጃ አካባቢ ጣሊያኖች የጦር ካምፕ ነበራቸው በየአካባቢው የነበሩ አርበኞች እንደዚህ ብለው ተቀኝተዋል፡-

አባ ኮስትር በላይ የዘለቀ ልጅ

ከዳሞት ይምጡልን መጣብን ፈረንጅ

አባ ኮስትር በላይ ቶሎና ቶሎና

ቢቸና አገርህን ጅብ አጠቃውና

አባ ኮስትር በላይ የጦር ሜዳው ሳንቃ

ዳቦ እንጀራ ሰራ በትልልቅ ዕቃ

ይህ ነጭ እንደሆነ ለቁርስም አይበቃ ተብሏል፡፡

ወደ ገፅ 52 ዞሯል

# አራት ዐይና ጎሹ ካልዕ

## በምንዋጋው ተመስገን ንጋቱ

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2011 ዓ.ም በግቢው ውስጥ ያሉትን የተለያዩ የሥብሰባ አዳራሾች በባለደማቅ አሻራ ሰዎች ስም ሰይሞ መጠቀም ጀምሯል፡፡ በቁጥር ይጠሩ የነበሩትን አዳራሾች በክቡር ዶ/ር ሃዲስ ዓለማየሁ፣ በቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሴ፣ በደራሲ አቤ ጎበኛ፣ በአራት አይና ጎሹና በአለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ ስም በመሠየም መገልገል ጀምሯል፡፡ እነዚህ አዳራሾች ውስጥ በተሰበሰብን ቁጥር ምን ያደረጉ ሰዎች ናቸው የሚለውን ሠዎች እንዲጠይቁና ከእነሱ የተወሰነ ትምህርት እንዲወስዱ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ተብሎ ስለታመነበት ማስተታወሻነቱ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በአብርሆት መፅሔት የ2009 ዓ.ም እትም ክቡር ዶ/ር ሃዲስ ዓለማየሁ፣ የ2010 ዓ.ም እትም ደግሞ የቀኝ ጌታ ዮፍታሄ ንጉሴን ህይወትና ሥራዎችን ይዘው ወጥተዋል፡፡ በዚህ የ2011 ዓ.ም የአብርሆት መፅሔት ደግሞ በተጋባዥ ፀሐፊ አቶ ምንዋጋው ተመስገን የአራት ዓይና ጎሹ ታሪክን እንደሚከተለው እናስዳስሳችኋለን

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ትምህርት መሠረት አንድ ተማሪ የሚያልፍባቸው የተለያዩ የአብነት ትምህርት ደረጃዎች (Levels) አሉ፡፡ እነርሱም ንባብ ቤት (4 ዓመታት የሚወስድ)፣ ዜማ ቤት (11 ዓመታት የሚወስድ)፣ ቅኔ ቤት (5 ዓመታት የሚወስድ) እና መጻሕፍት ቤት (10 ዓመታት የሚወስድ) ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ሁሉንም የትምህርት ደረጃዎች ለማጠናቀቅ ከሃያ ዓመታት እንደሚወስድ ተስፋዬ ሽብሩ (2010) ተናግረዋል፡፡ ዜማ የሚያስተምሩ መምህራን መጋቤ ስብሐት የሚል ማዕረግ ይሰጣቸዋል፡፡ መጋቤ ምሥጢር የሚለው ደግሞ ለቅኔ መምህራን የሚሰጥ ማዕረግ ነው፡፡ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ከመጻሕፍት ትርጓሜ ጋር የተያያዘ ስለሆነ የእያንዳንዳቸውን ዝርዝር ወደማየት አንገባም፡፡ በሥርዓተ ትምህርቱ መሠረት "አራት ዐይና" የሚለው ማዕረግ የሚሰጣቸው ደግሞ አራቱን ዓይነት መጻሕፍት በአንድምታ ትርጓሜ ለማስተማር ብቁ ለሆኑ የቤተ ክርስቲያኒቱ መምህራን ነው፡፡ አራቱ ዓይነት መጻሕፍት የትኞቹ እንደሆኑና የአራት ዓይናነት ማዕረግ እንዴት እንደሚሰጥ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

በመጻሕፍት ቤት የሚሰጡት የትርጓሜ መጻሕፍት በአራት ይከፈላሉ፡- መጻሕፍተ ብሉያት፣ መጻሕፍተ ሐዲሳት፣ መጻሕፍተ ሊቃውንት እና መጻሕፍተ መነኮሳት ተብለው፡፡ መጻሕፍተ ብሉያት የሚባሉት ከክርስቶስ ልደት በፊት የተጻፉና ስለቀደመው ዘመን የሚናገሩ ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው፡፡ መጻሕፍተ ሐዲሳት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ተጽፈው ስለእግዚአብሔር ቃል ሰው መሆን የሚናገሩ ሲሆኑ፣ መጻሕፍተ ሊቃውንት ግን በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን በነቢያትና በሐዋርያት የተገለጸውን የእግዚአብሔር ቃል እያብራሩ የሚተረጉሙ በተለያዩ ጊዜያት በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የተደረሱ ናቸው፡፡

ሊቁ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ(1989) ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ዓይነት መጻሕፍት "እግዚአብሔር አድሮ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያጻፋቸው[ና] የሚያጽፋቸው ቅዱሳን ሰዎች ፫ [ሦስት] ክፍል ናቸው፣ በ፫ ይከፈላሉ፡፡ ይኸውም ጸሐፍተ ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሊቃውንት ናቸው፡፡ ዓላማቸውም የነቢያት ትንቢት፣ የሐዋርያት ስብከት፣ የሊቃውንት ትርጓሜ ነው፡፡" በማለት ገልጸዋቸዋል፡፡ ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ እንደገለጹት ደግሞ "ብሉይ ኪዳን ንባብ፣ ሐዲስ ኪዳን ምሥጢር፣ መጻሕፍተ ሊቃውንት ትርጓሜ ናቸው፡፡ ደግሞም የብሉይ ኪዳን ንባብ ምሳሌ፣ የሐዲስ ኪዳን ንባብ ትርጓሜ፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንት ንባብ ምሥጢር፣ መፍቻና ማብራሪያ ናቸው"(ማህበረቅዱሳን፣ 2010) በማለት ያብራራሉ፡፡ ይህ ዐሥራውንም (ሰማኒያ አንዱ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጻሕፍት) ሆነ አዋልዱን መጻሕፍት (ዐሥራው መጻሕፍትን መሠረት አድርገው በሊቃውንት የሚደረሱት) በሙሉ እርስ በርሳቸው ያላቸውን ግንኙነት የገለጹበት መንገድ ነው፡፡

አራተኛው የትርጓሜ መጻሕፍት ምድብ መጻሕፍተ መነኮሳት ይባላል፡፡ ይኸውም በውስጡ ሦስት የተለያዩ መጻሐፍትን ያካትታል፡፡ የመጀመሪያው ማር ይስሐቅ፣ ሁለተኛው ፊልክስዩስ፣ ሦስተኛው ደግሞ አረጋዊ መንፈሳዊ ይባላል፡፡ በማር ይስሐቅ መቅድም ላይ እንደተጠቀሰው ሁሉም ስለመነኮሳት የሚናገሩ ሆነው "ማር ይስሐቅ (መቅድም) ያራቸውን(ፈተና፣ ሽክም፣ መከራ ማለት ነው፡፡) ግብራቸውን፣ ፊልክስዩስ ታሪካቸውን፣ አረጋዊ መንፈሳዊ ደግሞ ጸጋቸውን መዓርጋቸውን ይናገራሉ፡፡"

ከላይ የተዘረዘሩትን አራት ዓይነት መጻሕፍት በሚገባ የተማሩና ያስመሰከሩ መምህራን በቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርዓት መሰረት ዐራት ዐይና በመባል ይታወቃሉ፡፡ አራት ዐይና ለመሰኘት አራቱን የመጻሕፍት ክፍሎች 46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት (ምድብ አንድ)፣ 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (ምድብ ሁለት)፣ ሦስቱን መጻሕፍተ መነኮሳት ማለትም ማር ይስሐቅ፣ ፊልክስዩስና አረጋዊ መንፈሳዊ (ምድብ ሦስት) እንዲሁም ከመጻሕፍተ ሊቃውንት መካከል ውዳሴ ማርያም፣ ቅዳሴ ማርያም፣ ትምህርተ ኅቡዓት፣ ሃይማኖተ አበው፣ ተግሣፅ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ተረፈ ቄርሎስ፣ ፍትሐ ነገሥት፣ ወዘተ (ምድብ አራት) በአንድምታ ትርጓሜ ማስተማር መቻል የግድ ነው፡፡

በዚህ መንገድ ከሚታወቁት መካከል አራት ዐይና ጎሹ ካልዕ አንዱ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አራት ዐይና ጎሹ በሚል ስም የሚታወቁ ሁለት የትርጓሜ መምህራን አሉ (ከፍያው መራሒ፣ 2003)፡፡ የመጀመሪያው (አራት ዐይና ጎሹ ቀዳማይ) በጎንደር ደንቢያ ተወልደው መጻሕፍትን ያስተማሩና የአራት ዐይናነት ማዕረግ የተሰጣቸው ሊቅ ሲሆኑ፣ ሁለተኛው አራት ዐይና ጎሹ (ጎሹ ካልዕ) ደግሞ ጎጃም የተወለዱና እንደ መጀመሪያው ጎሹ ሁሉ አራት ዐይና በመባል መጻሕፍትን በአንድምታ ትርጓሜ ያስተማሩ ናቸው፡፡ በሚያስደንቅ ሁኔታ ሁለቱም አራት ዐይና ጎሹዎች በሥጋ ዐይነ ስውራን ነበሩ፡፡ የሥጋ ዐይናቸው ቢጠፋም ግን አእምሯቸው የሰላና ብሩህ ስለነበረ መጻሕፍትን ከመማርና ለትልቅ ማዕረግ ከመድረስ አላገዷቸውም፡፡ በተለይም አራት ዐይና ጎሹ ካልዕ ከመጻሕፍት ትርጓሜ በተጨማሪ በቅኔ ሊቅነታቸውም የታወቁ እንደነበሩ ይነገራል፡፡

# ማንን እናስታውስ?

በላይ....ከገጽ 50 የዞረ



በዚህ ፕሮግራም ላይ የምስራቅ ጐጃም ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ አብረሃም አለኸኝ በላይ ዘለቀ የረገጠውን መሬት የረገጣችሁ ለሀገራችሁ ልዕልና ለህዝባችሁ ደህንነት ሌት ተቀን ለምትሠሩ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ የምስራቅ ጐጃም ዞን የቢቸና ከተማ አስተዳደር፣ የእናርጅ እናውጋ ወረዳ አስተዳዳር፣ የእነማይ ወረዳ አስተዳደር፣ የሸበል በረንታ ወረዳ አስተዳደር የፀጥታ አካላት፣ አባት አርበኞች ለጀግናው በላይ ዘለቀ 75ኛ ዓመት መታሰቢያ በዓል ያደረጉትን ዝግጅት አመስግነዋል፡፡

አቶ አብሃም በንግግራቸው ‹‹ጀግናው በላይ ዘለቀን ስናስታውስ በርካታ ነገሮች አሉ፤ ህዝብ ለህዝብ ትልቅ ነበርን፤ የትልቅ ታሪክ ባለቤቶች፣ የታላላቅ ልጆች ነን፤ የእነ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ፍሬዎች ታላላቅ ነገስታት፣ ታላላቅ የሃይማኖት አባቶች፣ የታላላቅ የታሪክ ሊቃውንት፣ ታላላቅ ፀሀፍት እና ከያንያን የተገኙበት፣ ፀሀፍት፣ አክቲቪስቶች፣ ፖለቲከኞች፣ ምሁራን፣ መምህራን፣ ተማሪዎች አርሶ አደሮች፣ በአጠቃላይ የጐጃምና የአማራ ህዝብ ዛሬ በላይን የምንሆንበት ጊዜ ላይ እንገኛለን፤ ኢትዮጵያ በላይን ትፈልጋለች፤ የአማራ ህዝብ በላይን ይፈልጋል፡፡ ምክንያቱም በላይ ከሰውነት ከፍታ በላይ መብረር የሚችል ነበር›› ብለው ለሃገራዊ አንድነት አዲሱ ትውልድ የበላይን ዱካ ሊከተል እንደሚገባ ተናግሯል፡፡

አቶ አብርሃም አያይዘውም የአማራ ህዝብ የኢትዮጵያ ህዝብ ሰላም እንዲያድር እድል እንሰጣለን ሆኖም በዛ ዘመን ባንዳና ሰላቶ ነበር ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ለአማራ ህዝብ አጠቃላይ ጥቅም የማይጨነቅ፤ ዛሬም ባንዳ አለ ስለሆነም የታላቁ አርበኞችንን ባህል ስናከብር እንደ እሱ በመሆን ታላቋን ኢትዮጵያ የአማራ ህዝብን ለመታደግ እጅና ጓንት መሆን ይኖርብናል በማለት ንግግራቸውን ቋጭተዋል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ታፈረ መላኩ ጀግናው በላይ ዘለቀ ቤተሰቦቹ ላይ ለምጨን ቀበሌ አካባቢ ያለው ስሜት አብሮ የተዋሀደ ዘላለማዊ በደማቸው ውስጥ ያለ ነገር ነው ብለዋል፡፡ ታሪካችንን የመዘገብ፣ የማውሳት ነገር የተረሳ ነው ብዬ ስለምገምት በማህበረሰቡ እንደዚህ ዓይነት ስሜት ይኖራል ብዬ አላስብም ነበር፡፡ ስለዚህ ፕሮግራሙ ከጠበቅሁት በላይ ነው እጅግ አስደሳች፣ ደማቅ፣ አድርጎ ማህበረሰቡ ያከበረበት መንገድ ይገርማል፡፡

በላይ ዘለቀ እንደ ሀገር ያጣነው ብሄራዊ ጀግኖችን የመዘከር ነገር ነበር ዝግጅቱ ሁሉ በራሳቸው ተነሳሽነት ሆኖም ትውልድ መማር አለበት፡፡ በላይ ዘለቀ ለኢትዮጵያ ብሎ ልጅን አሳልፎ የሰጠ ብሄራዊ ጀግና ነው፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዝዳንት ረዳት ፕሮፌሰር ገነት ደጉ ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመለት ሶስት አላማዎች ውስጥ አንዱ የአካባቢው ታሪካዊ፣ ተፈጥሮአዊና ቁሳዊ፣ መንፈሳዊ ሃብቶች ማልማት፣ ማስተዋወቅ፣ ማበልፀግ፣ ለሚቀጥለው ትውልድ ሳይከለሱ ሳይበረዙ ማስተዋወቅ መሆኑን አፅንዖጽ ሰጥተው በመግለፅ ዩኒቨርሲቲው በቀጣይም እንደነዚህ ዓይነት መሰል ተግባራትን እንደሚያከናውን ተናግረዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ 77ኛውን የጀግኖች የኢትዮጵያ አርበኞች በዓል በዩኒቨርሲቲያችን ግቢ ውስጥ ጥናታዊ ፅሁፍ በማቅረብ በጉባኤ መልክ አዘጋጅቶ በርካታ መነቃቃቶችን ፈጥሯል፡፡ በዚህ ዓመት የደጃዝማች በላይ ዘለቀ 75ኛ ዓመት ዝክረ ሰማዕትነት ለማክበር የተጋድሎ ስፍራው ድረስ በመምጣት ዩኒቨርሲቲው መስራቱ ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚገባ አስተያየት ሰጭዎች ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም የተጋድሎ ቦታዎች ለምተው ለቱሪዝም መዳረሻ መሆን ይኖርባቸዋል፡ ፡ የተለያዩ የጦር መሳሪያዎች በቤተ ክርስትያንና በአንዳንድ ተቆርቋሪ ግለሰቦች ተሰብስበው የሚገኙት በሙዚየም መቀመጥ አለባቸው፡፡ ቅርሶች እንዳይጠፉና እንዳንዶች ደግሞ የተጐዱ ስለሆነ ሙዚየሙን በመገንባት ሂደት ውስጥ ዩኒቨርሲቲው እንደ አንድ አጋር አካል መሆን ይኖርበታል ሲሉም አስተያየት ሰጭዎች አክለው ተናግረዋል፡፡

## ስለ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መረጃ ለማግኘት

ሊቀ-ማርቆስ ሳምንታዊ የቴሌቪዥን ፕሮግራም

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እና የአካባቢው ማህበረሰብ ሬዲዮ ኤፍ ኤም 97.7

ሳምንታዊ ዩኒቨርሲቲያችን ፕሮግራም

በወርሃዊ ዜና መፅሔት

በፌስ ቡክ አድራሻችን facebook/Debre Markos University

በዌብሳይታችን www.dmu.edu.et

## Urban Greening Project of Debre Markos University Benefits Low Income Households in the town





DMU: Debre Markos University urban greening project, which has launched with 1.7 Million ETB, benefits low income households of Debre Markos town. The progress of the project has visited with the presence of Debre Markos University and Debre Markos town administration teams in the site, kebele 07.

The Director of Debre Markos University Community Service Directorate Dr. Mihret Alemayehu states that the Urban Greening Project aims to feed low income households in improving their nutrition and getting income through small-scale urban farming.

In addition to this, Dr. Mihret explains that the Project enables beneficiaries to engage in poultry and vegetables production to compensate their life with the collaboration of the town's agricultural office and Debre Markos University. According to Dr. Mihret the Project has shown a remarkable change that has to be strengthened in order to assure improvement on the life of members of the project. .

The project has launched having an ultimate objective to improve the life of needy people in the town by producing vegetables and other small scale urban farming within their limited area.

Debre Markos University Agriculture and Natural Resource college Instructor and Coordinator of the project Mr. Mengest Belay,, on his part says that about 30 households are participating on the project and producing different kinds of vegetables.

According to Mr. Mengest, the urban greening project helps people who are low income to improve their diet, to engage on one's own work and to enhance the town beautification. One of the beneficiaries of the project Mrs. Beyenu Amanu says that after being a member of the project she is delivering fresh vegetables to the community and earning about 500 birr per a week by selling vegetables that have been producing on a free space at home. Thus, it helps to strengthen her work.

Debre Markos Town Administration Agricultural and Environmental Conservation Land Administration Office Extension Agriculture Team Leader Mr. Belachew Moges, appreciates Debre Markos University for improving the lives of needy households and making them role models for others living in the town.

It is noted that Debre Markos University is working with the town's agriculture Office to address vegetable seedlings for those who will be members of the project.

## Debre Markos University Library and Documentation Directorate Trains Librarians

DMU: Debre Markos University Library and Documentation Directorate offers a three days capacity building training under the theme "Basic Library knowledge for all library workers" for library workers.

The training is designed to enable new comers of the directorate with the basic knowledge and skill of library service in order to give effective and proper service to the customers.

Mrs. Betelhem Tamene, Debre Markos University Library 2 Officer, says that the objective of the training is to equip newly assigned workers by the JEG (Job evaluation and grading) with basic knowledge and skills of library services. It is noted that the training enables them to serve students of the university with diverse language and culture appropriately. Thus, Mrs. Simret Kumlachew, Shift Coordinator of Library 2, on her part says that the training content focuses on basic library services, property administration, customer handing, services delivery and ethics of the worker.

Furthermore, the training would enable to fulfill library facilities to deliver appropriate library service followed by rules and regulation.

The Library and Documentation Team Leader Mr. Azmeraw Endalew says that the training is designed to familiarize newly placed workers to enable them serve the students appropriately and ethically.

Finally, Participants of the training promised to deliver quality service properly and ethically as per the training consequently their service has an impact on the students' academic achievement.

